
# ሐመር

## ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ


ሐመር ፲፪ኛ ዓመት ቁጥር ፩ ኅዳር/ታኅሣሥ ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.



ምዕ. ጎጃም ፍዳ ማርያም ገዳም-መስኖ ልማት




ደብረ ወገግ አስቦት ገዳም-የሽመና ፕሮጀክት



ባሌ መካነ ሕይወት አቡነ ተክለሃይማኖት ገዳም የወተት-ላም ርባታ ፕሮጀክት



ደቡብ ጎንደር አምስቲያ የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም - መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት



በማዕ. ትግራይ ሀገረ ስብከት- የአባ ሃደራ ገዳም መነኮሳት በፕሮጀክት ጥናት ውይይት ወቅት

# ገዳማውያን ዛሬም በልማት...

© ማኅበረ ቅዱሳን 

# ከአንባብያን ለአንባብያን

## የማወቅ መብታችን

በየደረጃው ያለው የቤተ ክርስቲያናችን አስተዳደር ለቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ የኾነውን ድጋፍና ትብብር ሁሉ በየወቅቱ ከምእመናን እንደሚጠይቅ ይታወቃል:: ምእመናንም የቤተ ክርስቲያን ልጆች እንደ መሆናቸው መጠን ለዚሁ ዕቅድ ተፈጻሚነት ባላቸው ዐቅም ሁሉ የድርሻቸውን ይወጣሉ:: ብዙውን ጊዜ በአንድ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አስተ ዳደር ከሚቀርቡት ጥያቄዎች መካከል የሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ማሠሪያ፣ የሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ማስጠገኛ፣ የስብከተ ወንጌል አዳራሽ፣ የመንፈሳዊና የቀለም ትምህርት ቤት መገንቢያ... የሚሉት ይገኙበታል:: እነ.ህ ሁሉ በራሳቸው በጎ እንደ ሆኑ እናምናለን:: በአንጻሩ ግን ከእነዚህ ተግባራት ጋር በተገናኘ ስለ በዓላት አከባበር፣ ስለ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አጠባበቅ፣ ስለ ንስሓ አባትና ልጅ ግንኙነት፣ የተቀረጹ ምስሎችን መሥራት እንደማይገባ አስመልክቶ በልዩ ልዩ የአገልግሎት መዋቅሮች የምንገኝ አባላት ለምናቀርበው ጥያቄና አቤቱታ ምላሽ የሚሰጠን የለም:: በመሆኑም በዓላት ይሻራሉ፤ በቅዳሴ ሰዓት ሬብሻዎች አሉ፤ አንዳንድ ካህናት በሥርዓተ ኖሎት አይመሩም፤ ሳይገባቸው ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን የሚሳተፉ ሰዎች ይታያሉ፤ በክርስቲያናዊ ትውፊታችን የሌለው የቅርጽ /ሐውልት/ ሥራ ተስፋፍቷል:: ይህም ሁሉ ሆኖ ግን ከላይ የተዘረዘሩት በርካታ የግንባታ እንቅስቃሴዎች በታቀዱላቸው የጊዜ ክልል አይከናወኑም:: ስለዚህም ምእመኑ ቤተ ክርስቲያንን በዐቅሙ የማገልገል መንፈሳዊ ግዴታ ያለበትን ያህል ስለሚከናወኑት ተግባራት መረጃ የማግኘትና ለሚያቀርባቸው ጥያቄዎችና አቤቱታዎች ተገቢውን ምላሽ የማወቅ መብት እንዳለው የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ሊረዱት ይገባል::

*ቦሌ ደብረ ሣህል መድኃኔ ዓለም*
*ቤተ ክርስቲያን ምእመናንና*
*ምእመናት*
*አዲስ አበባ*

## በትምህርትና ሥልጠና ቢታቀፉ

በአብዛኛው የቤተ ክርስቲያናችን ቅጽሮች ዙሪያ የሚገኙት ነዳያን ሰው መሆናቸው እስከሚያጠራጥር ድረስ ተጎሳቁለው እንደሚታዩ ሁላችንም የምንመለከተው ነው:: እነ.ህ ወገኖች ከየት እንደ መጡ፣ በምን ምክንያት እንደዚህ እንደ ሆኑ፣ ችግራቸው ምን እንደ ሆነ ሳይታወቅ እንደ ጉድፍ ተጥለው፥ ከጊዜ ወደ ጊዜም ብዛታቸው እየጨመረ ይገኛል:: ምጽዋት ለመስጠት እንኳን በእጅጉ እያዳገተ ነው:: ለአካል ጉዳተኛው ሲሰጥ ባለ ሙሉ አካሉ ይበሳጫል:: ከሕፃን እስከ አረጋዊ የዕድሜ ክልል ድረስ ያሉት ነዳያን ተቀምጠው ያገኙትን እየበሉ ሲሰዳደቡና ሲደባደቡ ይውላሉ:: ይህ የእውነተኛ ድህነት ይሁን

የስንፍና በውል የተጠና ነገር የለም:: እነ.ህ ወገኖቻችን እኮ እንደ እኛ በአርአያ ሥላሴ የተፈጠሩ፣ ማሰብና መሥራት የሚችሉ ናቸው:: ከችግራቸው ተላቀው ተገቢ በኾነ ክርስቲያናዊ ሕይወት ታንጸው፣ በተለያዩ የዕውቀትና የሥራ መስክ ይሰማሩ ዘንድ መታገዝ ይገባቸዋል:: ስለዚህም በየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያን የሰበካ ጉባኤያት፣ ሰንበት ት/ቤቶች፣ መንፈሳውያት ማኅበራትና በጎ አድራጊዎች ትብብር ከሥርዓተ ትምህርት ጀምሮ መሠረታዊ ፍላጎታቸው ሊሟላላቸው ያስፈልጋል:: በዚህ ረገድ ሲከናወኑ የቆዩት ጥረቶች ወቅታዊነት የሚታይባቸው ናቸው:: በርግጥ በጊዜያዊነትም ቢሆን መረዳት የሚገባቸው ዐቅመ ደካሞች የሉም ማለቴ አይደለም:: በአጠቃላይ ግን ቅንጅትና ዘላቂነት ባለው መልኩ ለችግሮቻችን ተገቢውን ቅድም ተከተል በመስጠት መፍታት ይኖርብናል እላለሁ::

*ወ/ሮ ይመናሹ ዘውዱ*
*አዲስ አበባ*

## የህገራቸውንና የቤተ ክርስቲያናቸውን ባዕም እንዲያውቁ

በ12ኛ ዓመት ቁጥር አንድ 1996 ዓ.ም ሐመር መጽሔት እትም ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ ዓምድ የቀረበው የአቶ አክሊሉ አረጋ እና የወ/ሮ እማዋይሽ ወልዴ ቃለ ምልልስ በእጅጉ አስደስቶኛል:: አርአያነታቸውን በባሕር ማዶ የሚኖሩ ሌሎች ዜጎቻችን ቢከተሉት መልካም ነው:: እነርሱና እነርሱን የመሰሉ ኢትዮጵያውያን ወላጆች በአንድነት ተቀናጅተው በአሜሪካ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሕፃናትና አዳጊዎች ማንነታቸውን ጠንቅቀው የሚያውቁበት ዐጸደ ሕፃናትና ልዩ ልዩ የትምህርት ተቋማት የሚመሠርቱበትን መንገድ ጠንክረው ማመቻቸት ይገባቸዋል:: ይህንን አስመልክቶ በእናንተ በኩል የመወያያ መድረክ መከፈት ይኖርበታል እላለሁ::

*ከንፈ ገብርኤል*
*ደብረ ዘይት*

## ጫትና ሲጋራ...

መልእክቱ አግባብነት የሌለውንና እርምት የሚያሻውን ድርጊት ይመለከታል:: ለጽሑፌ መነሻ የኾነኝ ወንድም ባለሁበት አጥቢያ የሚጠቀስ መንፈሳዊ አገልግሎት ያለው ወጣት ነው:: ትዳር ሊመሠርት ያስብና ወደ እጮኛው ቤተሰቦች ሽማግሌ ይልካል:: በመጨረሻም በሥርዓተ ተክሊል በቅዱስ ቁርባን ጋብቻውን ይፈጽማል:: ታድያ ያሳዘነህ ነገር ምንድን ነው? ብትሉኝ፥ ወጣቱ ሽማግሌዎቹን ወደ ልጅቱ ቤት ሲልክ ያሲያዛቸው ጫት፣ ሲጋራና ሌሎችም ተከታይ ነገሮችን መሆኑ ነው:: ወንድማችን ይህን ሲያደርግ ያሰበው እንዲሳካለት እንጂ ክፋቱን ሳያውቅ ቀርቶ አይመስለኝም:: ዳሩ ግን የህዋቂ አጥፊ በመሆን ሰዎችን ለስሕተት የሚዳርግ ተግባር መፈጸም አግባብ አይደለም፤ ይህን መሰል ጥፋቶች መታረም ይኖርባቸዋል::

*ኃይለ ሚካኤል*
*ምዕ. ሐረርጌ*

## «ለቡራኬ ወይስ ...»


እኔ የምኖረው በቡርጂ ልዩ ወረዳ በሶያማ ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን አጥቢያ ሲሆን በሰንበት ትምህርት ቤታችንም በተሰጠኝ ሓላፊነት አገለግላለሁ:: ልጠቁማችሁ የወደድኩት ችግር በአንዳንድ አበው ካህናት ላይ የምመለከተው አሳዛኝ ነገር ነው:: ይኸውም የተሳሳቱ ነገሮችን ለማረም ምክርና ተግሣጽ መቅደም ሲገባው በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ለሚፈጸሙ ስሕተቶች ሁሉ «እንዳናወግዛችሁ፤ አውግዤአለሁ» በማለት ማስፈራራታቸው ነው:: በመሠረቱ፣ አባቶቻችን በእጃቸው የጨበጡት ቅዱስ መስቀልም ይሁን የተቀበሉት ሥልጣነ ክህነት የምንቀደስበትና የምንባረክበት እንጂ ማስፈራሪያ ሊሆን አይገባም:: በመሆኑም ሥርዓተ ኖሎቱና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያናችን ክርስቲያናዊ ትውፊት በሚያዝዘው መሠረት እየተጠ ስተዋለ በአግባቡ ቢፈጸም መልካም ነው እላለሁ::

*ኃይለ ኢየሱስ ጌታሁን*
*ሶያማ ቅድስት ሥላሴ ቤተ*
*ክርስቲያን*


የሐመር መጽሔትና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ደንበኛ ይሁኑ

| | ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ | | ሐመር መጽሔት | |
|---|---|---|---|---|
| | የ6 እትም | 12 እትም | የ6 እትም | 12 እትም |
| ለአዲስ አበባ | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| ለክፍለ ሀገር | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| አፍሪካ | 9 ዶላር | 18 ዶላር | 12 ዶላር | 24 ዶላር |
| አውሮፓና መካከለኛው ምሥራቅ | 12 ዶላር | 24 ዶላር | 15 ዶላር | 30 ዶላር |
| አሜሪካና ሩቅ ምሥራቅ | 15 ዶላር | 30 ዶላር | 18 ዶላር | 36 ዶላር |

ለባለው ታደለ እና/ወይም መስፍን ጥላሁን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራዳ ቅርንጫፍ
Balew Tadelle and/or Mesfin Tilahun
የባንክ ሒሳብ ቁጥር 68608 አዲስ አበባ ከፍለው
አድራሻዎንና የከፈሉበትን ደረሰኝ ኮፒ



ከጥቅምት 18-21 ቀን 1997 ዓ.ም የተደረገው ሐዋርያዊ ጉዞ መልካም ነበር። እኔ የደረስኹ ምሥራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት ናዝሬት ነበር። ሕዝቡ በተመስጦ ትምህርቱን ይከታተል ነበር። በእርግጥ አንዳንዱ ስለ በሽታው መነሣት ቀርቶ ትምህርት ብቻ ለመማር ፍላጐት ነበረው። ሆኖም ግን ቃለ እግዚአብሔር ሰዎች ከዝሙት እንዲሸሹ የውስጥ ንጽሕናቸውን እንዲጠበቁ የሚያዝ በመሆኑ እኛም መንፈሳዊ ይዘቱን ያለቀቀ በሽታውን የተመለከተ ትምህርት አስተላልፈናል። እንዲህ ዓይነቱ ጉባኤ ብዙ የድኅነት ምርት የሚያስገኝ ስለሆነ ተጠናክሮ ቢቀጥል መልካም ነው።

ሌላው፦ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ በቤተ ክርስቲያን አባቶች፥ በአበው ካህናት መሐል እጅ እንደ ሆነ ከሀገር ተርፎ መላው ዓለም የሚያምንበት ጉዳይ ነው። በዚህ መሠረት ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ የዋለችውን ውለታ ያህል ኢትዮጵያ ለራሷ አልዋለችም። በቀድሞ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የሀገር፥ የሕዝብ ጠባቂ በመሆኗ ሕዝብን እንድትጠብቅ የእግዚአብሔርን ቃል እንድታስተላልፍ የሬድዮ ጣቢያ ነበረች። በትምህርት ቤት ተማሪው ክፍል ከመግባቱ በፊት የግብረ ገብ ትምህርት ታስተምር ነበር። በየሆስፒታሉ ሕሙማንን የሚባርኩና የሚያጽናኑ አባቶችን መድባ ታስተምር ነበር። ለሚሞቱትም የኑዛዜ ሥርዓት ትፈጽም ነበር። በማረሚያ ቤትም እንደዚሁ፤ ዛሬ ይህ ሁሉ መንፈሳዊ የአገልግሎት ድርሻዋን መንግሥት መልሶ ቢፈቅድላት ቤተ ክርስቲያኒቱ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከልና የችግሩ ተጠቂዎችንም መኖር እንደሚቻል ተስፋ እየሰጠች በመከባከብ መልካም ውጤት ልታስመዘግብ ትችላለች። ምክንያቱም ክርስቲያኑ ሕዝብ ለቤተ ክርስቲያን ድምፅ ታዛዥ ነውና።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር


| | |
|---|---|
| ዋና አዘጋጅ | - ዲ.ን መርሻ አለኸኝ |
| ም/ዋና አዘጋጅ | - አሉላ ጥላሁን |
| ከፍተኛ ሪፖርተር | - መ/ር ኃይለ ማርያም ላቀው |
| መ/ ሪፖርተር | - ዲ.ን ፋሲል አስረስ |
| ኮምፒዩተር ዲዛይን | - ወይንሸት ወጉ |
| ኮምፒዩተር ጸሐፊዎች | - ፍቅርተ ኃይሌ |
| | - ጸዳሉ ሁንዴሳ |

ስልክ 556328
ፖስታ 80078
አዲስ አበባ
E -mail:Hamer@EOTC-Mkidusan.org
Website: – www.EOTC-Mkidusan.org


«ማኅበረ ቅዱሳን»

እግዚአብሔር ያከበራቸው
የነቢያት፣የሐዋርያት፣የጻድቃን፣ የሰማዕታት
በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ትሩፋትና አማላጅነት
የሚዘከርበት በመሆኑ ይህን ስያሜውን አግኝቷል።


ሐመር
፲፪ኛ ዓመት ቁጥር ፬
ኅዳር/ታኅሣሥ ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.


## ይዘት


የማኅበሩ መልእክት
- ለውሳኔዎቹ ተግባራዊነት........................................፪

ደብዳቤዎች ........................................................፬

ከሰሞኑ በረከት
- ከሥርዓቱ ፈቀቅ ብላችኋል........................................፯

ትምህርተ ሃይማኖት
- ምሥጢረ ሥጋዌ በውዳሴ ማርያም..............................፲
- የቃና ዘገሊላ ተአምር በመጽሐፈ ምሥጢር...................፲፪

የጥያቄዎቻችሁ መልስ
- ሥርዓቱን ከልማዱ ለይታችሁ አሳውቁን.......................፲፭

ኪነ ጥበብ
- ዘማዊቷ ...............................................................፲፯

እናስተዋውቃችሁ
- በማኅበረ ቅዱሳን የተጠኑ፥ የተተገበሩና በመተግበር ላይ የሚገኙ የልማት ፕሮጀክቶች .....................፲፱
- ቅዱስ ሐርቤ ........................................................፳፪
- ዓምደ ወራዙት
- የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሞያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ግቢ ጉባኤ ..............................................፳፬

ሐመረ ሕይወት
- መፍትሔው ከዚህ አለ..............................................፳፮

ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ
- ፈተና የሚመጣው ከየት ነው?...................................፳፯

ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ
- ድህነት እንዲቀንስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሚና ምን መሆን አለበት?.......................፴፪
- በአንዳንድ አህጉር እየተከሰተ ያለው የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ችግርና መንሥኤው ...............................፴፭

አቡጊዳ - የግእዝ ቋንቋ ትምህርት
- ተውሳከ ግስ............................................................፴፯

ወቅታዊ ጉዳዮች
- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰሜንና ደቡብ አሜሪካ ...........................................፴፱


በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የኅትመት ዝግጅት ማስተባበሪያ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ።


© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የማኅበሩ መልእክት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ::

## ለውሳኔዎቹ ተግባራዊነት...

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰጠቻቸው አገልግሎቶች ዙሪያ የምትመክርባቸው፣ መከራ ስታበቃም ለደከሙት ብርታትን፣ ለዘገዩት ፍጥነትን የሚሰጡ የመፍትሔ ሐሳቦችን አስቀምጣ አገልግሎቷን የምታጠናክርባቸው ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤያት አሏት:: ከእነዚህም ውስጥ አንዱ በየዓመቱ ጥቅምት ወር ላይ የሚካሄደውና በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ርዕሰ መንበርነት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ በጠቅላይ ቤተ ክህነት የየመምሪያውና የየድርጅቱ ሓላፊዎች፣ የየአህጉረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጆች፣ የካህናት፥ የሰንበት ት/ቤቶች፣ የስብከተ ወንጌልና የምእመናን ተወካዮች፣ የአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎችና ምክትል ሊቃነ መናብርት እንዲሁም በውጭ ሀገር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተወካዮች የሚሳተፉበት የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ነው::

ይህ የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ዘንድሮ ለ23ኛ ጊዜ ከጥቅምት 6-11 ቀን 1997 ዓ.ም በመንበረ ፓትርያርክ የስብከተ ወንጌል አዳራሽ ተካሂዷል::

ጉባኤው ለአራት ተከታታይ ቀናት ከተሰበሰበ በኋላ ወደ 27 የሚደርሱ የጋራ መግለጫዎችንና የውሳኔ ሐሳቦችን አሳልፏል:: በየደረጃው ያለን የቤተ ክርስቲያን አካላትና አባላት ውሳኔዎቹን ዐውቀን ለተግባራዊነታቸው የድርሻችንን ለመወጣት እንድንችል በአርዕስት ከፋፍለን በአጭር በአጭሩ እንደሚከተለው ለማቅረብ እንሞክራለን::

1. **ልማትን በተመለከተ፡-** በአንዳንድ አካላት ቤተ ክርስቲያናችን የልማት እንቅፋት እንደ ሆነች ተደርጐ መነገሩን ጉባኤው ተቃውሞታል:: ለዚህ ወቀሳና ክሰሳ ተግባራዊ ምላሽ ለመስጠትም በየደረጃው ያሉ የቤተ ክርስቲያናችን አካላት «ሊሠራ የማይወድ አይብላ» የሚለውን መርሕ በማንገብ ራሳቸው በሥራ እየተጉ ሕዝቡን እንዲያተጉ አሳስቧል:: እንደ ክርስቲያናዊ ተራድኦና ልማት ኮሚሽን፣ ሕፃናትና ቤተሰብ ጉዳይ ድርጅት፣ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት እና ሌሎች የቤተ ክርስቲያኗ የልማት አካላትም ቤተ ክርስቲያኗ በምትፈልገው አቅጣጫ በመንቀሳቀስ የተሰጣቸውን ተልእኮ በተግባር ሊያሳዩ ይገባል ብሏል::

2. **አህጉረ ስብከትን ማጠናከር በተመለከተ፡-** የቤተ ክርስቲያናችን ጥንካሬ የሚገለጸው በአህጉረ ስብከት መጠናከር እንደ መሆኑ ጉባኤው አህጉረ ስብከቱ በሰው ኃይልም ሆነ በፋይናንስ እንዲጠናከሩ አሳስቧል:: ለዚህም «ሕግ ይወጽእ እምጽዮን፥ ሕግ ከጽዮን ይወጣል» እንደ ተባለው የመልካም አስተዳደር ምንጭ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በመሆኗ በየጊዜው የሞያ ማሻሻያ ሥልጠና መርሐ ግብር በማዕከል ደረጃ በማዘጋጀትና አስተዳደራዊ ሥልጠና በመስጠት፥ ዝርዝር የሥራ መመሪያ በማውጣትና ተገቢውን ሰው በተገቢው ቦታ ላይ በመመደብ የቤተ ክርስቲያኒቱ መልካም አስተዳደር የበለጠ እንዲጠናከር ይደረግ ዘንድ ጉባኤው ጠይቋል:: በተጨማሪም ቤተ' ክርስቲያን ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ሥራዎችን የምታከናውን ታላቅ መንፈሳዊት ተቋም እንደ መሆኗ ከመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጀምሮ እስከ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ድረስ በሠለጠነ የሰው ኃይልና በበጀት እንድትደራጅ አጥብቆ አሳስቧል::

   በውጭ ሀገር ለተቋቋሙትና እየተቋቋሙ ላሉት አብያተ ክርስቲያናት ከእናት ቤተ ክርስቲያናቸው እየተደረገ ያለው ድጋፍና ርዳታ በበለጠ ተጠናክሮ እንዲቀጥል፣ በሰበካ ጉባኤ ተደራጅተው እያገለገሉ ያሉት አብያተ ክርስቲያናትም የቤተ ክርስቲያን መመሪያ የሆነውን ቃለ ዓዋዲ በማክበር እንዲያገለግሉ አሳስቧል::

3. **ገዳማትን፣ አድባራትንና መንፈሳውያት ት/ቤቶችን ስለ ማጠናከር፡-** ገዳማትና አድባራት ቀደም ሲል ይተዳደሩባቸው የነበሩት የልማት መሬቶች በደርግ መንግሥት በመነጠቃቸው መተዳደሪያ እያጡ በመሆኑ መንግሥት በከተማ ያሉ የቤተ ክርስቲያን ይዞታዎች እንዲመለሱ ፍትሕ ርትዕ እየሰጠ ነው:: በመሆኑም በገዳማት፣ በአድባራትና በጥንታውያት አብነት ት/ቤቶች ለሚኖሩት ወገኖችም በክልሎች አማካይነት መብታቸውን እንዲያስከብሩላቸው በቅዱስ ሲኖዶስ አማካይነት ማሳሰቢያ እንዲሰጥ ጉባኤው በአጽንዖት ጠይቋል::

   ቅዱሳት መካናቱ ያሏቸውን ቅርሶች እየመዘገቡ በጥንቃቄ የመጠበቁ ተግባር የበለጠ ተጠናክሮ እንዲቀጥል፣ በዘመን ብዛት እየተጐሳቆሉ ያሉ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትን በሚመለከትም ቅዱስ ሲኖዶስ ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላት ጋር በመነጋገር ታሪካዊነታቸው የሚጠበቅበት ጥናት እንዲካሄድ ጉባኤው አጥብቆ ጠይቋል::

   ነባር ትምህርት ቤቶችን፣ መምህራኑንና ደቀ መዛሙርቱን በተመለከተም ሊቃውንቱና ደቀ መዛሙርቱ በምግብና መጠለያ እጦት የሚያደርጉትን ፍልሰት ለመግታት እያንዳንዱ ሀገረ ስብከት ክብካቤ እንዲያደርግ በአጽንዖት አስገንዝቧል::

   ከዚህም በተጨማሪ የቤተ ክርስቲያናችንን አገልግሎት በአስተዳደር፣ በትምህርትና በልማት ለማጠናከር፣ የተቋቋሙትና የሚቋቋሙት ከፍተኛ መንፈሳውያት ት/ቤቶች ለተልእኳቸው ብቁ የሚኾኑት በበጀትና በሰው ኃይል ሲጠናከሩ በመሆኑ ጉዳዩ በቅዱስ ሲኖዶስ በኩል ትኩረት እንዲሰጠው፣ የካህናት ማሠልጠኛዎቻችንም ደረጃቸው የሚያድግበትንና የሚጠናከርበትን መንገድ በመፈለግ በሁሉም በኩል ጥረቱ እንዲቀጥል ጉባኤው አሳስቧል::



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

**4.ለምእመናን የሚሰጠውን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ስለ ማጠናከር፡-** የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን መስፋፋት በመከላከል ረገድ ከብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ጀምሮ እየተደረገ ያለውን ጥረት አድንቆ ችግሩ ገና ስላልተወገደ የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጉባኤው አጥብቆ አሳስቧል። ከዚህም በተጨማሪ መንግሥት ባስቀመጠው ፖሊሲ መሠረት ለም ወደሆኑ ቦታዎች የሚሰፍሩ ወገኖቻችንን በመከተል የሚያስፈልጋቸውን ማኅበራዊና መንፈሳዊ ፍላጐቶች ዐቅም በፈቀደ መጠን ማሟላት እንደሚገባ ማሳሰቢያ ሰጥቷል። ከመቼውም ጊዜ በላይ ቤተ ክርስቲያናችን የልጆቿን ቁጥር በሚገባ ማወቅ ያለባት ወቅት በመሆኑ እያንዳንዱ አህጉረ ስብከት ያለውን የሰው ኃይል በማሠማራት ካህናትንና የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አባላትን በማስተባበር እያንዳንዱን ምእመን ከነቤተሰቡ በሚገባ እንዲመዘገብ ለማድረግ ሁሉም የየበኩሉን ጥረት ማድረግ እንደሚገባ ማሳሰቢያ ሰጥቷል።

**5. ወጣቶች በቤተ ክርስቲያናችን ሁሉን አቀፍ እንቅስቃሴ ተሳታፊ እንዲሆኑ ስለ ማድረግ፡-**በጉባኤው ከቀረበው አጠቃላይ ሪፖርት ለመረዳት እንደ ተቻለው በአሁኑ ጊዜ በሰንበት ት/ቤቶች የታቀፉት ወጣቶች ብዛት 2.7 ሚሊዮን ብቻ ነው። ከቤተ ክርስቲያናችን ምእመናን ብዛት አንጻር ሲታይ ይህ ቁጥር እጅግ ያነሰ እንደ ሆነ የተስማማው ጉባኤው ወደፊት ወጣቶችን በሰንበት ት/ቤት የማደራጀቱ ተግባር ተጠናክሮ እንዲቀጥል፣ በየሰንበት ት/ቤቱ አገልግሎት ላይ የሚውሉና ወጥነት ያላቸው የመማሪያና የመዝሙር መጻሕፍት እንዲዘጋጁ አሳስቧል።

23ኛው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አራት ቀናትን በወሰደው ቆይታው ካሳለፋቸው የጋራ መግለጫዎችና የውሳኔ ሐሳቦች በተጨማሪ በአዘጋጅ ኮሚቴው ተሰናድተው በቀረቡለት የድህነት ቅነሳንና የሰብአዊ መብቶችን መጠበቅ የተመለከቱ አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ የጋራ መግለጫዎችን አሳልፏል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን በቤተ ክርስቲያናችን የአገልግሎትና የአስተዳደር መዋቅር ውስጥ ያለ አካል እንደ መሆኑ መጠን በየዓመቱ የሚካሄደውን ይህን ታላቅ ጉባኤ በአጽንዖትና በጥሞና ይከታተለዋል። ተጀምሮ እስኪፈጸም ባለው ሂደትም ጉባኤው የሠመረና የተቃና እንዲሆን የሚሰጠውን ትእዛዝ ተቀብሎ የድርሻውን ይወጣል።

ጉባኤው በብሔራዊና በዓለም አቀፍ ደረጃ ቤተ ክርስቲያናችን የምታበረክተውን ዘርፈ ብዙ አገልግሎት፣ ያጋጠማትን ችግርና መፍትሔውን ለመገምገም በሚያበቃ ሁኔታ እንደ ተዋቀረ የሚታወቅ ነው። ጉባኤው የተሰበሰባቸው 23 ዓመታት ከነበራቸው ልዩ ሁኔታ አንጻር የየራሳቸው ተገቢ አካሄድና ይዘት ነበራቸው። ይሁንና በ23ኛ የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የጋራ አቋም መግለጫና የውሳኔ ሐሳብ መሠረት ጉባኤው እስከ አሁን ከነበረው ይልቅ የተሻለ አካሄድና ይዘት ሊኖረው እንደሚገባ መግባባት ላይ ተደርሷል። ማኅበራችን ይህን የጉባኤው የጋራ አቋምና የውሳኔ ሐሳብ በጽኑ ይደግፋል። በመሆኑም በቀጣይ የጉባኤው አካሄድ÷ በየደረጃው ያሉ የሰበካ መንፈሳውያት አስተዳደር ጉባኤያት /የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ፣ የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ፣ የመንበረ ጵጵስና አህጉረ ስብከት ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ/ ሚና በላቀ ሁኔታ መጠናከር ይገባዋል። ይኸውም፡-

1. በየራሳቸው በበጀት ዓመቱ ያከናወኗቸውን ተግባራት ካለፈው ጊዜያት ጋር እያነጻጸሩ በመገምገም፣ በክንውን ሂደት ያጋጠሟቸውን ችግሮች ለይተው ተነጻጻሪ መፍትሔ በማቅረብ፤ መታረምና መቀጠል የሚገባቸውን ደካማና ጠንካራ ጎኖች በመመዘን፤ በተከታዩ ዘመንም ባላቸው ዐቅም ላይ በመመሥረት ማድረግ የሚችሏቸውንና የሚገባቸውን ዝርዝር ዕቅዶች በማስቀመጥ፤
2. ቤተ ክርስቲያናችን ከዘመኑ ሁለንተናዊ አዝማሚያዎች፣ የአገልጋዮች፣ የምእመናንና የሌሎች ወገኖች ችግሮችና ጥያቄዎች አኳያ ውሳኔ ልትሰጥባቸው የሚገቡ ርእሰ ጉዳዮችን በመጠቆምና በመተንተን ሊገለጥ የሚችል ነው።

እንግዲህ ይህ ሲባል በመጨረሻ ላይ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚካሄደው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ስብሰባ ቅድመ ዝግጅት የሚረዱ፤ ሰፊ መሠረት ባለው ተሳትፎ የዳበሩ የመወያያ ርእሰ ጉዳዮችን ለማግኘት ተቻለ ማለት ነው፤ በእርግጥ እኒህ አንገብጋቢና ወቅታዊ ርእሰ ጉዳዮች በጠቅላይ ቤተ ክህነት የዋና ሥራ አስኪያጁ ጽ/ቤት፣ በሥሩ በሚገኙ ልዩ ልዩ መምሪያዎች፣ ወይም በአህጉረ ስብከት /በቡድን ወይም በተናጠል/ ተጠቃለው መቅረብ ይገባቸዋል።

3. ከዚህም ጋር የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤው በቀደመ ስብሰባው በጋራ ያወጣቸውን የአቋም መግለጫዎችና ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች አፈጻጸም በቅጡ በመመልከት ተግባራዊነታቸውን የሚገመግምበት በቂ ጊዜ ሊኖረው ያስፈልጋል።
4. አያይዞም የጉባኤው ተካፋዮች የተሳኩ ተሞክሯቸውን የሚለዋወጡበትን ምቹ ሁኔታ ቢፈጥር በእጅጉ ጠቃሚ ነው።
5. በሌላ በኩል በየትኛውም አካል በማንኛውም መልኩ የሚቀርብ የክንውን ሪፖርት በቀጣይ የሥራ ዘመን የሚኖረውን የተግባር ዕቅድና በጀት እንዲያካትት ቢደረግና አፈጻጸሙንም ለመከታተል የሚያስችሉ አዋጭ ስልቶች ቢነደፉ መልካም ነው እንላለን። በአጠቃላይ ይህን ሁሉ ማለታችን በ1991 ዓ.ም ለሦስተኛ ጊዜ ተሻሽሎ በወጣው የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ቃለ ዓዋዲ አገላለጽ መሠረት፡- «ቤተ ክርስቲያናችን በአስተዳደር፣ በፍትሕ መንፈሳዊ፣ በአገልግሎትና በምጣኔ ሀብት በኩል በራሷ ሕግና ሥርዓት በመመራትና በመደራጀት ትሠራ ዘንድ» ካለን ብርቱ ፍላጐት በመነሣት ነው።

በመጨረሻም ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ይህንን ዓይነት ጉባኤ ሠርታ ውሳኔዎችን የምታሳልፈው በየደረጃው ያሉ የቤተ ክርስቲያናችን አገልጋዮች፣ አካላትና አባላት ወደ ተግባር ይለውጡት ዘንድ ነው። በመሆኑም አባቶቻችን ያሳለፉልንን ውሳኔዎች ተቀብለን ለተግባራዊነታቸው የልጅነት ግዴታችንን እንወጣ እንላለን።

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ደብዳቤዎች

## ለበለጠ ነገር

በሐመር 12ኛ ዓመት ቁጥር ሁለትና ሦስት 1996 እና 97 ዓ.ም እትም ኪነ ጥበብ ዓምድ «ሰባኪ ሕይወት» በሚል ርእስ የቀረበው ልቦለድ በእጅጉ የሳበኝና ፍጻሜውንም ለማወቅ የጓጓሁለት ነበር። «የክርስትናና መንገድ ተከትዬ እየተጓዝኩ ነው» የሚል ምእመንን ሁሉ ራሱን በሂሚን አማካይነት እንዲፈትሽ ያነሣሣል፤ ክርስትና ለራስ ብቻ መኖር አለመሆኑን ያስረዳል። የአሻግሬ ዓይነት ሰዎች ብዙ መትጋት ይኖርብናል። እንደ ጽሑፉ አጀማመር እንደነ አሻግሬ ዓይነቶቹን ብቻ ሳይሆን እንደነ አስቴር የመሳሰሉትንም ወደፊት መንገድ ሳያሲይዝ አይ ቀርም። ምንም ሳታውቅ «ቡና ካዳሚ» ኹና የቀረችውን ቀዘባሽንም /የአስቴር እኅት/ ነጻ ቢያወጣትና የኮተቤው ዐዋቂም በነበረበት ተደላድሎ እንደ ተቀመጠ መተው ለሌላው መሰናክል ማቆየት ይመስለኛል። የሂሚን ፍጻሜ በጣም አስደስቶኛል። በአጠቃላይ መሰል ጽሑፎች በእናንተ በኩል እየተቃኑ በተከታታይ መቅረብ ይኖርባቸዋል እላለሁ።

ጸጋዬ ዘውዴ-ወልድያ
ጋሻው - ጭዳ

## «ሰውን ሰው 'የሚበላው' ቢሆን ኖሮ...»

በሐመር መጽሔት 12ኛ ዓመት ቁጥር ሦስት የጥያቄዎቻችሁ መልሶች ዓምድ «ቡዳ ምንድን ነው? ቡዳ እና ባለ እጅ ምን አገናኛቸው?» ተብሎ ከአንባብያን ለቀረበላችሁ ጥያቄ የሰጣችሁት መልስ አርክቶኛል። ለአብዛኛዎቻችን አስቸጋሪ ኾኖ መፍቻ የሌለው እንዲያውም ተፈጥሯዊ እውነታ መስሎን ስንፈራ ለነበርነው ወገኖች ወቅቱን የጠበቀ ጥያቄና ምላሽ ነው። በአንድ ወቅት መንገድ ላይ መሽቶብኝ የብረትና የሸክላ ሥራ ውጤቶችን በማምረት በሚተዳደሩት የጥበበ እድ ባለሞያዎች ቤተሰቦች ዘንድ ገብቼ በመልካም መስተንግዶ ተቀብለውኝ በበነጋው ሸኝተውኛል። ሰውን ሰው «የሚበላው» ቢሆን ኖሮ እስከ አሁን ዓለማችን «በቡዳና በባለ እጆች» ትቀር ነበር። ጠያቂዎቹን በአንባባያን ስም እያመሰገንኩ ለእናንተም ያለኝን አድናቆት ለመግለጽ እወዳለሁ።

ጸጋዬ ዘውዴ
ወልድያ

## ፈለጉን እንከተላለን

በሐመር መጽሔት 12ኛ ዓመት ቁጥር ሦስት እትም ዓምደ ወራዙት «የአብነት ትምህርት በግቢ ጉባኤያት» የሚለውን ጽሑፍ በማነብበት ወቅት ከጎንደር ሕክምና ሳይንስ ኮሌጅ የተመረቀውን የዲ.ን ዶ/ር ሲሳይ ደመቀን ቃለ ምልልስ አየሁና በጣም አዘንኩ። በመደሰት ፈንታ ለምን አዘንክ? ትሉኝ ይሆናል። ከዲ.ን ዶ/ር ሲሳይ ጋር በ1992 ዓ.ም በጎንደር ሕክምና ሳይንስ ኮሌጅ አብረን ሳለን እርሱ ሰዓታት ሲማር ሌሎቻችን ውዳሴ ማርያም እንማር ነበር። ይህንን ስንጨርስ መምህራችንና ዲ.ን ዶ/ር ሲሳይ ትምህርቱን ሳናቆም እንድንገፋበት ምክራቸውን ለገሡን። እንደ ምክራቸውም ወደ ሥራ ዓለም ከገባን በኋላ በበኩሌ መማሬን ቀጠልኩ። ከተወሰኑ ወራት በኋላ ግን ትጋት አንሶኝ ተውኩት። አሁን ቃለ ምልልሱን ሳነብ ምክሩ ትዝ ብሎኝ አዘንኩ። ከአሁን በኋላ ግን ፈለጉን ለመከተል በቁርጠኝነት ተነሥቻለሁ፤ ትምህርቱ ንም መማር ጀምሬአለሁ። እናንተም እንዲህ በአርአያነታቸው ሊያነሣሡን የሚችሉ ወገኖችን ጥረትና የአብነት ትምህርትን የተመለከቱ ጽሑፎችን በማቅረቡ ግፉበት።

ሀብታሙ ካሣሁን
ከሚሴ ቅዱስ ገብርኤል
ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት
ጽጌ ለማ
ባሕር ዳር
እኅተ ማርያም
ቤተ ሳይዳ ቅዱስ ገብርኤል
ቤተ ክርስቲያን

## ለአዲሱ «ሚሊኒየም» ምን ታስባል?

ሀገራችን ኢትዮጵያን ከሌላው ዓለም ልዩ በሚያደርጋት የዘመን አቆጣጠርዋ አማካይነት ከሦስት ዓመታት በኋላ 2000 ዓ.ም ላይ እንደርሳለን፤ ይህ የኢትዮጵያ «አዲስ ሚሌኒየም» ነው። የዘመናት ባለቤት ልዑል እግዚአብሔር ተርፎ ከሚቀረው ዕድሜ ይመጽውተንና በምን ቅድመ ዝግጅት ልንቀበለው፣ በምን የሥራ ዕቅድና ግብ ልንሻገረው አሰበናል? ወይስ በዚህ ጉዳይ ላይ ለመወያየት ቸኩ ያለሁ? ምላሻችሁን እሻለሁ።

መ/ር አንዱ ዓለም ታደሰ
ምዕ.ሸዋ-ድሬ ጉደር ት/ቤት

*ከአዘጋጁ፡- ውድ መ/ር፡- ፈጽሞ አልቸኩሉም። እንዲያውም ይህ የሁላችንም ወቅታዊ ጥያቄ ነው። አንባብያን ሁሉ ልንወያይበት ይገባልና በእኛ በኩል የቤተ ክርስቲያናችንን ዘርፈ ብዙ አገልግሎት ማዕከል ባደረገ መልኩ የምትሰነዝሯቸውን ሐሳቦች ለማስተናገድ ዝግጁዎች ነን።*

## ተጨማሪ መማሪያዎች ይኑሩ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን የዜማ፣ የንባብና የቅዳሴ ትምህርትን እንዲሁም ከኦርቶዶክሳዊ የዜማ መሣሪያዎች መካከል አንዱ የሆነውን የበገና መደርደር ሥልጠና ለመስጠት ባወጣው ማስታወቂያ መሠረት መስጠት መጀመሩ በእጅጉ አስፈላጊና ተገቢም ነው። ይሁንና የቅበላ ዐቅማችሁን በጣም ውስን አደረጋችሁት። ፍላጐት ያለው ሁሉ ተምሮ በግልም ኾነ በጋራ ለማገልገል ይበቃ ዘንድ በተቻለ መጠን ተጨማሪ የመማሪያ ሥፍራዎችን ብታመቻቹ መልካም ነው። ለምሳሌ፡ - በየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናቱ እንዲሰጥ ብታደርጉ። በሌላ በኩል በአቡነ ጎርጎርዮስ ዐጸደ ሕፃናት የሥነ ምግባር ትምህርት መሰጠቱ እንደ አጀማመሩ ተጠናክሮ ይቀጥል እያልኩ ከአዲስ አበባ ውጭ በክልል ከተሞችም የሚ



© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

ከፈትበት ሁኔታ ከወዲሁ ቢጤን እላለሁ:: እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን:: አሜን::

*ሲሳይ ሁንዴ*
*ደ/ገ/ቅ/ዐማኑኤል ካቴድራል*
*አዲስ አበባ*

## አእምሯዊና መንፈሳዊ መነቃቃትን ሰጥቶናል

በሐመር መጽሔት 12ኛ ዓመት ቁጥር ሦስት 1997 ዓ.ም እትም «ግእዝ ፈጽሞ አይሞትም፣ ማንም ሊገድለውም አይችልም» ያሉትን የፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሐቅ ቃለ ምልልስ አንብቤዋለሁ:: በሐመር መጽሔት ስለ ግእዝ ቋንቋና ቅዱሳት መጻሕፍት የገለጿቸውን እውነታዎች በ20/1/97 እና በ4/2/97 ዓ.ም ምሽት ከአሜሪካ ድምፅ ሬድዮ «ባሕል መድረክ» ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ አጽንተውታል:: «ወርቅና አልማዝ በውስጡ በተቀመጠበት ሣጥን ውስጥ ተቀምጠን ምን አለበት? ተብለን ብንጠየቅ ባለመመርመራችን አናውቅም ብለን ነው የምንገልጸው:: ይህ ታላቅ ቋንቋም በውስጡ ያካበተውና እኛ ያልደረስንበት ፈርጀ ብዙ ሀብት በሰፊው ሊጠናና ሊታወቅ ይገባል» ብለዋል:: በእውነቱ በተከበሩት ምሁር አማካይነት ስለ ግእዝ ቋንቋ ሕያውነት ማሳወቃችሁ ኦርቶዶክሳውያን ወጣቶች ስለ ቋንቋው ያለንን አእምሮአዊና መንፈሳዊ መነቃቃት ያጎለብትልናልና በመስል ዝግጅቶች ቀጥሉበት::

*መንግሥቱ ኃይሌ*
*ቡታጅራ*
*ሰሎሞን ግርማ*
*ባሌ ጊኒር*
*አዳነች አብዲ*
*አቡዳቢ*

## ጥያቄው ባይቋረጥ

በ«አቡጊዳ - የግእዝ ቋንቋ ትምህርት» ዓምድ እየተሰጠ ያለው ትምህርት በጣም ጥሩ ነው:: በዚሁ ቀጥሉ:: ነገር ግን ይኸን ያህል ሽፋን ሰጥታችሁ እያስተማራችሁ ሳለ ምን ያህል ሰው እየተከታተላችሁ ስለ መሆኑ የምታረጋግጡባቸው በርካታ መንገዶች ቢኖሩም ዋነኛው ዘዴ ግን ለሚወጡት ጥያቄዎች ተሳታፊዎች የሚሰጧቸው ምላሾች ናቸው:: ስለዚህ በየእትሙ በሚኖረው ክፍለ ትምህርት ተያያዥ ጥያቄዎች ባለ መቋረጥ ቢቀርቡ መልካም ነው::

*ተክለ ማርያም*
*ኮልፌ ደ/ብ/ቅድስት ሥላሴ*
*ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትቤት*

## በሚገባቸው ሥፍራ ቢቀመጡ

ብዙውን ጊዜ በክልልና በወረዳ ከተሞች ለቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ሥራ ወይም ጥገናና አገልግሎት ርዳታ ለማሰባሰብ ቅዱሳት ሥዕላት የተቀመጡባቸው፣ የተንጠለጠሉባቸው ወይም የተለጠፉባቸው ሙዳየ /መዝገብ/ ምጽዋት በሆቴሎችና በቡና ቤቶች ወዘተ ተቀምጠው እናያለን:: ዳንስና ዳንኪራው ሌሎችም አጸያፊ ነገሮች በሚፈጸሙባቸው ሥፍራዎች ቅዱሳት ሥዕላቱን ማኖር ለእነርሱ ልንሰጠው የሚገባንን ክብር አለማሳየት በመሆኑ እርምት ሊደረግበት ይገባል::

*ሰሎሞን እሸቱ*
*ደብረ ዘይት - አየር ኃይል*

## ቍልምጫ ወይስ...

ጥቂት የማይባሉ ምእመናን የልዑል እግዚአብሔርን ጨምሮ ስመ ቅዱሳንን በቁልምጫ መልክ ሲጠሩ ይሰማል:: በአንዳንድ የካሴት «መዝሙራት» የግጥም ስንኞች ላይም ይህ ችግር ይስተዋላል:: ለዚህም ዓይነተኛ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል «ተክልዬ» የሚለውን ማየት ብቻ ይበቃል:: ከጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገድል እንደ ምንረዳው «ተክለ ሃይማኖት» ማለት «ተክለ አብ፣ ተክለ ወልድ፣ ተክለ መንፈስ ቅዱስ» ማለት ነው:: ይሁንና እንደ አንድ ባልንጀራችን አድርገን ንግግር ያሣመርን መስሎኝ «ተክልዬ» ብንል የጻድቁ አባታችንን ስም አጠራር ሙሉ ትርጉም ስለምናሳጣው፤ ፈጽሞ ተገቢም ባለ መሆኑ መስተካከል ይገባዋል፤ «እግዚአብሔርዬ፣ መድዬ፣ ኪዳዬ፣ ሚክዬ፣» በምንለውም እንደዚሁ:: ስመ አምላክን፣ ስመ ቅዱሳንን እንደሚገባ ጠርተን መዘመር፣ መጸለይ /ማመስገን፣ መለመን/ ኦርቶዶክሳዊ ትውፊታችን ነው::

*ግርማዬ ማሞ*
*ግምጃ ቤት ቅድስት ማርያም*
*ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት*
*ፍሬንድከ – ባሕር ዳር*

ከዚህ በታች ስማችሁ የተዘረዘረው አንባብያን ያሰጣችሁን አስተያየትና ገንቢ ሂስ፣ ያደረሳችሁን ጥቆማና ማሳሰቢያ እንዲሁም የድጋፍና የርዳታ ጥያቄዎች ደርሰውናል:: ሁሉንም እንደ አገባቡ በጊዜውና በቦታው ሁሉ የምንጠቀምበት ይሆናል:: ለማንኛውም በተሳትፏችሁ አትለዩን



እያልን ከፍ ያለ ምስጋናችንን እናቀርባለን::

*መሠረት ፈቅይበሉና ሚሚ ዘውዴ /ቤሩት/፣ ዲ.ን እንግዳ ታደሰ /አርሲ-በቆጂ/፣ ተስፋዬ አምሃ /ባቲ/፣ አስገደች እሸቱ /የተባበሩት ዐረብ ኤምሬቶች/፣ ሰው ቢሆን ፈለቀ /ደቡብ ወሎ/፣ ደመቀ ወዕሜቦ /ሃዲያ ዞን ማረሚያ ቤት/፣ ወሰን ፈቃዱ /ናዝሬት/፣ ሰሎሞን በለጠ /ጉርሱም/፣ ገ/መድኅን አየለ /ናዝሬት/፣ እኅት አፈራሁ ፋንታሁን /ምሥ.ወለጋ-አኖ/፣ ወልደ ሰንበት ካሣ /ናዝሬት ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ/፣ ጫን ያለው ገነቲ /ኢሉባቦር -ገርጂ/፣ ዲ.ን ሚልዮን ዮሐንስ /ምሥ.ሸዋ-መቂ/፣ አድነው በርጋ /ደሴ/፣ ሲ.ኤክ. ደረጀ ማንደፍሮ /የኢትዮጵያ አየር ኃይል - ደብረ ዘይት/፣ ለምለም ቦጋለ /ናዝሬት/፣ ሰማይ ሣንቾ /ማሻ/፣ እመቤት ወልዴ /ሳዑዲ ዐረቢያ/፣ ኃይለ ማርያም /ቦንኬ ወረዳ - ገረሴ/፣ ደሳለኝ እሸቴ /አርሲ - አደሌ/፣ ዓባይነህ አየለ /አረካ/፣ ሰሎሞን ምሳሌ /ደብረ ዘይት/፣ ወለተ ትንሣኤ አስፋው /አቡዳቢ/፣ ዲ.ን ዘድንግል አበራ /አርሲ - ጎልጀታ/፣ ንጋቱ ከበደ /ክብረ መንግሥት/፣ ዐቢይ ኃይለ ጊዮርጊስ /አረካ/፣ ዲ.ን ወገኔ ሞላ /ወላይታ ሶዶ/፣ ገብረ ሥላሴ ኂሩተ አምላክ /ባሕር ዳር/፣ ካሣው ዋለልኝ /ደቡብ ወሎ-ወግዲ/፣ ሽበሽ ባሻ /ዲላ/፣ ዲ.ን ፈቃዱ ገመቹ /ሰሜን ወሎ-ወልድያ/፤ ብርሃኑ /ናዝሬት/፣ ኃይለ ኢየሱስ ጌታሁን /ሶያማ/፣ ሙሉጌታ በላይ፣ መ/ር ወርቅነህ አንዱ ዓለም /ሰላም በር/፣ ወልደ ሰማያት /መሀል ሜዳ/፣ ዲ.ን ሲሳይ ዳምጠው /ዓለማያ ዩኒቨርስቲ/፣ አበበ ምትኩ /ሲዳሞ/፣ ዘመኑ ታደሰ /ጐንደ ወይን/፣ ዲ.ን ገብሬ ጸጋይ /ምሥ.ወለጋ/፣ አሸናፊ አበራ /ወናጐ/፣ ሳሙኤል ተሾመ /ጊምቢ/፣ ዲ.ን ዓለማየሁ ወዳጆ /ባስኬቶ ልዩ ወረዳ/፣ ዓለማየሁ አበበ /ሙገር/፤ ቢልልኝ ወልደ ጻድቅ /ሰላ ደንጊያ/፣ በላይ ዘገየ /ከሚሴ/፣ ፣ዲ.ብዙአየሁ ወ/ሥላሴ/ይርጋ ጨፌ/፤ ዲ.ን ቦጋለ ገላዬ /ሰላም በር/፤ አንተነህ ማትያስ /ባሕር ዳር/ ፣ጽጌ ድንግል /ሐረር/፤ወ/ር ስጦታው ግርማዬ /ነቀምት/፤ እንግዳ በቀለ /አርሲ-ሁሩታ/፤ዲ.ኬ /አሰበ ተፈሪ/ ገዛኸኝ ደምሴ፣ ተስፋዬ ኃይለ፣ ዳንኤል ተስፋዬ፣ አሸብር ጥሩነህ፣ ሳሙኤል ተስፋዬ፣ ናሆም ቢ.፣ ተስፋዬ ፍሥሓ፣ ምንተስኖት ደምሴ፣ ደመወዝ አሰፋ፣ ፍሬው ተክሌ /አ.አ/ ::*



© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# «ከሥርዓቴ ፈቀቅ ብላችኋል።»

/ጎርጎርዮስ ደጀኔ /

/ሚል.3÷7/

*ባለፈው እትማችን÷ ጎርጎርዮስ፡- ስለ ሥርዓት ምንነት ቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርጋ የምታስተምረውን ትምህርት፣ እግዚአብሔር ሥርዓትን በማይጠብቁት ላይ ስለሚሰጠው ፍርድ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ተመዝግበው የሚገኙ ታሪኮችን በማቅረብ ሰፋ ያለ ትምህርት ሰጥቶናል። በዚህ ዝግጅታችን ደግሞ ሥርዓት በአዲስ ኪዳን ምን እንደ ሆነና እንዴት እንደሚፈጸም ከማጠቃለያ ሐሳቦች ጋር ያስነብበናል፣ መልካም ንባብ።*

## ሥርዓት በአዲስ ኪዳን

በዘመነ አዲስ በሁሉ ነገር አብነታችን የቅዱሳን አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ለዚህም ነው፡- «ቀንበሬን /ሕጌን/ በላያችሁ ተሸከሙ /አክብሩ/፣ ከእኔም ተማሩ፤» በማለት በሁሉ እርሱን አብነት ማድረግ እንዲገባን የነገረን። ማቴ.11÷29። ሕጉን ሥርዓቱን ቀንበር ያለው ያለ ምክንያት አይደለም። ቀንበር ሁለት በሬዎችን ጠምዶ በሥራ አንድ እንደ ሚያደርጋቸው ወንጌልም ሁለቱን ወገኖች ማለትም ሕዝብንና አሕዛብን እንደ ቀንበር ጠምዳ በእምነትና በሥርዓት አንድ ስለምታደርጋቸው ነው።

ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ በሁሉ አብነታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ሲናገር፡- «ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኲር ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወሰና አልና፤» ብሏል። ሮሜ.8÷29። እዚህ ላይ ወንድሞች የተባሉ ቅዱሳን ናቸው። በኲር ይሆናቸው ዘንድ ማለትም፡- «ለበጐ ሥራ ሁሉ አብነት ይሆናቸው ዘንድ፤» ማለት ነው። በመሆኑም ቅዱሳን ሁሉ እርሱን አብነት አድርገው በመጓዛቸው በሁሉ እርሱን መስለው ተገኝተዋል። ለዚህም ነው ሐዋርያው፡- «እኔ ክርስቶስን መስየዋለሁ፤» ያለው። 1ኛቆሮ.11÷1። በሮሜ መልእክቱም፡-«ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት፤»። ትርጉሙም ምሰሉት ማለት ነው። ሮሜ. 13÷14። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ደግሞ፡- «የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና፣ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራ ተቀብሎአልና፤» ብሏል። 1ኛጴጥ. 2÷21።

ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕግን የሠራ የሕግ ባለቤት ሲሆን ከላይ እንደ ጠቀስነው በሁሉ አብነት ሊሆነን በመዋዕለ ሥጋዌው ሕግንና ሥርዓትን አክብሯል። ይኸውም እንዲህ አክብሩ ሲለን ነው። ነገራችንን ይበልጥ ግልጥ ለማድረግ እንደሚከተለው በዝርዝር እንመለከታለን።

### ሀ. ሥርዓተ ኦሪትን እንደ ፈጸመ፤

1ኛ፡- ጌታችን በተወለደበት ዕለት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በመጠቅለያ ጠቅልላ÷አውራ ጣቱንም አስራ በግርግም አስተኝታዋለች። ሉቃ. 2÷4። አውራ ጣቱን ማሰሯ ሥርዓት ነው። ይኸውም የታላ ቅነት÷የበኵርነት ምልክት ነው። በኦሪቱ ዘመን የይሁዳ ወልደ ያዕቆብ ምራት መንታ ልጆችን ፀንሳ ነበር። የመውለጃዋ ወራት ደርሶ በምትወልድበት ጊዜ ከሁለቱ አንዱ ቀድሞ ለመወለድ እጁን አወጣ። አዋላጂቱም «ይህ ቀድሞ ይወጣል» ስትል ቀይ ፈትል ወስዳ በአውራ ጣቱ ላይ አሰረች። ዘፍ. 38÷27–30። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ ነገር በእሥራኤል ዘንድ ሥርዓት ሆኖ ቀርቷል። ጌታም በተወለደ ጊዜ ይኸው ሥርዓት ተፈጽሞለታል። ይኸውም ለባሕርይ አባቱ ለአብ ለእናቱ ለቅድስት ድንግል ማርያምም ተቀዳ ሚና ተከታይ የሌለው በኵር በመሆኑ ነው። ዕብ.1÷6። ሁለተኛም «ወደፊት ዮሴፍና ኒቆዲሞስ እንዲህ ይገንዙሃል» ስትለው ነው። እንግዲህ አንድ ሥርዓት ሳይፈጸም ከቀረ ምን ያህል ምሥጢር እንደ ሚፋለስ ከዚህ መረዳት ይቻላል።

2ኛ፡- ጌታችን ተወልዶ ስምንት ቀን በሞላው ጊዜም እንደ ኦሪቱ ሥርዓት ሥርዓተ ግዝረትን እንዲፈጽም ወደ ቤተ ግዝረት ወስደውታል። ግዝረት የማመን ምልክት÷ የጥምቀት ምሳሌ ነበር። «እግዚአብሔርም አብርሃምን አለው ፡- አንተ ደግሞ ቃል ኪዳኔን ትጠብቃለህ÷ አንተ ከአንተም በኋላ ዘርህ በትውልዳቸው። በእኔና በአንተ መካከል ÷ ከአንተም በኋላ በዘርህ መካከል የምትጠብቁት ቃል ኪዳኔ ይህ ነው፣ ከእናንተ ወንድ ሁሉ ይገረዝ። የቍልፈታችሁንም ሥጋ ትገረዛላችሁ፤ በእኔና በእናንተ መካከል ላለውም ቃል ኪዳን ምልክት ይሆናል። የስምንት ቀን ልጅ ይገረዝ፤» እንዲል። ዘፍ. 17÷9–12። ጌታችን እንደ ሥርዓቱ ወደ ቤተ ግዝረት ቢወሰድም ስለት አላረፈበትም÷ በተአምራት ተገዝሮ ተገኝቷል። ይኸውም ያለ ጊዜው ደሙ እንዳይፈስ ነው። ስሙንም መልአከ እግዚአብሔር አስቀድሞ እንደ ተናገረ ኢየሱስ ተብሎ ተጠራ። ሉቃ. 2÷21፤1÷31፤ማቴ1÷25። በስምንተኛው ቀን ከግዝረት በኋላ ስም መሰየምም ሥርዓት ነበር። «የኤልሳቤጥም የመውለጃዋ ጊዜ ደረሰ÷ወንድ ልጅም ወለደች። ጎረቤቶችዋም ዘመዶችዋም ጌታ ምሕረቱን እንዳደረገላት ሰምተው ከእርስዋ ጋር ደስ አላቸው። በስምንተኛውም ቀን ሕፃኑን ሊገርዙት መጡ÷ በአባቱም ስም ዘካርያስ ሊሉት ወደዱ። እናቱ ግን መልሳ፡- አይሆንም ዮሐንስ ይባል እንጂ አለች።» እንዲል። ሉቃ. 1÷57–60።

3ኛ፡- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሥርዓተ በኵርን ለመፈጸም ሕፃኑን ኢየሱስ ክርስቶስን በተወለደ በአርባኛው ቀን ወደ ቤተ መቅደስ ወስደዋለች። «እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፡- በእስራኤል ልጆች ዘንድ ከሰውም ከእንስሳም ማኅፀንን የሚከፍት በኵር ሁሉ ለእኔ ቀድስልኝ፣ የእኔ ነው።» እንዲል ዘጸ.13÷1፤ዘሌ.12÷1። እመቤታችን የሴቶች ልማድ የሌለባት ንጽሕተ ንጹሐን ቅድስተ ቅዱሳን ብትሆንም ሥርዓቱን ለማክበር አርባ ቀን ቆይታለች። «ሁለት ዋሊያ ወይም ሁለት የርግብ ጫጩቶች» ተብሎ በታዘዘው መሠረትም መሥዋዕት ሊያቀርቡ ወደ ኢየሩሳሌም ወስደውታል። ሉቃ.2÷22–24።

4ኛ፡- «በዓመት ሦስት ጊዜ በዓል ታደርግልኛለህ። የቂጣውን በዓል ጠብቅ፤ በአቢብ /በሚያዝያ/ ወር ከግብፅ ምድር ወጥታችኋልና፤ በዚህ ወር እንዳዘዝሁህ ሰባት ቀን ቂጣ እንጀራ ትበላለህ፤ በፊቴ ባዶ እጃችሁን አትታዩ፤ በእርሻም የምትዘራትን የፍሬህን በኵራት የመከር በዓል÷ዓመቱም ሳያልቅ ፍሬህን ከእርሻ ባከማቸህ ጊዜ የመክተቻውን በዓል ጠብቅ። በዓመት



© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

ሦስት ጊዜ በአንተ ዘንድ ያለው ወንድ ሁሉ በጌታ በእግዚአብሔር ፊት ይታይ::» /ዘጸ.23÷14-17/ ተብሎ በተሠራው ሥርዓት መሠረት ጌታችን ተወልዶ የዐሥራ ሁለት ዓመት ልጅ በሆነ ጊዜ እንደ በዓሉ ሥርዓት ከእመቤታችን እና ከጠባቂዋ ከዮሴፍ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ወጥቷል:: ሉቃ 2÷41::

5ኛ:- ጌታችን በገዳመ ቆሮንቶስ እንደ ጾመ÷ በፈቃዱ በዲያብሎስ እንደ ተፈተነ÷ ዲያብሎስንም እንደ አመጣጡ ድል እንዳደረገው በወንጌል ተጽፏል:: ማቴ.4÷1፤ማር. 1÷12፤ ሉቃ.4÷1:: በዚህም ዝቅ አድርጐ ሠላሳ ቀን÷ ከፍ አድርጐ ኀምሣ ቀን አልጾመም:: የጾመው አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት ነው:: ይኸውም የአበው አምላክ ሲሆን የአበውን ሥርዓተ ጾም ሲጠብቅ ነው:: ምክንያቱም ሊቀ ነቢያት ሙሴ የጾመው አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት ነው:: «በዚያም አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ፤ እንጀራም አልበላም÷ውኃም አልጠጣም::» እንዲል ዘጸ. 34÷28:: ነቢዩ ኤልያስም የጾመው አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት ነው:: «በዚያም ምግብ ኃይል እስከ እግዚአብሔር ተራራ እስከ ኰሬብ ድረስ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ሄደ::» እንዲል:: 1ኛ ነገ.19÷8::

ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕግን የሠራ የሕግ ባለቤት ሲሆን ሥርዓተ ኦሪትን አክብሮ ያሳየን ሥርዓተ ኦሪት ለሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መሠረትም ምሳሌም በመሆኑ ነው:: በትምህርቱ ም:- «እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ÷ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም::» ብሏል:: ማቴ.5÷17:: ከዚህም ሌላ የተለያዩ ሥርዓቶችን በመሥራት የሥርዓትን አስፈላጊነት አሳይቷል:: ይኸንንም እንደሚከተለው እናያለን::

## ለ. ሥርዓተ ምጽዋት

«ለሰዎች ትታዩ ዘንድ ምጽዋታችሁን በፊታቸው እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ፤ ያለዚያ በሰማያት ባለው አባታችሁ ዘንድ ዋጋ የላችሁም:: እንግዲህ ምጽዋት ስታደርግ ግብዞች በሰው ዘንድ ሊከብሩ በምኵራብ÷ በመንገድም እንደሚያደርጉ በፊትህ መለከት አታስነፋ፤ እውነት እላችኋለሁ÷ ዋጋቸውን ተቀብለዋል:: አንተ ግን ምጽዋት ስታደርግ ምጽዋትህ በስውር እንዲሆን ቀኝህ የምትሠራውን ግራህ አትወቅ፤ /በዝቷል÷ ቀንስ እንዳትልህ ሚስትህ እንኳ አትወቅ/፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ያስረክብሃል::» ማቴ.6÷1-4::

## ሐ. ሥርዓተ ጸሎት

«ስትጸልዩም እንደ ግብዞች አትሁኑ፤ ለሰው ይታዩ ዘንድ በምኵራብና በመንገድ ማዕዘን ቆመው መጸለይን ይወዳሉና፤ እውነት እላችኋለሁ÷ወደ እልፍኝህ ግባ፤ መዝጊያህንም ዘግተህ / ወደ ልብህ ተመልሰህ÷ አሳብህን ሰብስበህ/ በስውር ላለው አባትህ ጸልይ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ያስረክብሃል::» ማቴ.6÷5-6::

## መ. ሥርዓተ ጾም

«ስትጦሙም÷እንደ ግብዞች አትጠውልጉ፤ ለሰዎች እንደ ጦመኛ ሊታዩ ፊታቸውን ያጠፋሉና፤ እውነት እላችኋለሁ÷ዋጋቸውን ተቀብለዋል:: አንተ ግን ስትጦም÷በስውር ላለው አባ ትህ እንጂ እንደ ጦመኛ ለሰዎች እንዳትታይ ራስህን ተቀባ ፊትህንም ታጠብ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ያስረክብሃል::» ማቴ.6÷16-18:: «ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰ ድበት ወራት ይመጣል÷በዚያ ጊዜም ይጦማሉ::» ማቴ.9÷15:: «ይህ ዓይነት ግን ከጸሎትና ከጦም በቀር አይወጣም አላቸው::» ማቴ.17÷21::

## ሠ. ሥርዓተ ንስሐ

«ከተራራም በወረደ ጊዜ ብዙ ሕዝብ ተከተሉት:: እነሆም÷ ለምጻም ቀርቦ:- ጌታ ሆይ÷ ብትወድስ ልታነጻኝ ትችላለህ፤ እያለ ሰገደለት:: እጁንም ዘርግቶ ዳሰሰውና እወዳለሁ÷ንጻ አለው:: ወዲያውም ለምጹ ነጻ:: ኢየሱስም ለማንም እንዳትናገር ተጠንቀቅ÷ ነገር ግን ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ:: /ኃጢአትህን ተናዘዝ/ ለእነርሱም ምስክር እንዲሆን ሙሴ ያዘዘውን መባዕ አቅርብ አለው::» ማቴ.8÷1-4::

## ረ. ሥርዓተ ምናኔ

«ከዚያ ወዲያ ኢየሱስ ከዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ በመንፈስ /በፈቃዱ/ ወደ ምድረ በዳ ተወሰደ:: አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከጦመ በኋላ ተራበ::» ማቴ. 4÷1:: «ኢየሱስም:- ለቀበሮዎች ጉድጓድ ለሰማይም ወፎች መሳፈሪያ አላቸው÷ ለሰው ልጅ ግን /ለወልደ ዕጓለ መሕያው ክርስቶስ/ ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም አለው::» ማቴ.8÷20:: «ኢየሱስም÷ ፍጹም ልትሆን ብትወድ÷ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ÷ መጥተህም ተከተለኝ አለው::» ማቴ.19÷21:: «ስለ ስሜም ቤቶችን ወይም ወንድሞችን ወይም እኅቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ ሁሉ መቶ እጥፍ ይቀበላል:: የዘላለምንም ሕይወት ይወርሳል::» ማቴ. 19÷29::

## ሰ. ሥርዓተ መምህራን

«በከንቱ ተቀብላችሁ በከንቱ ስጡ:: ወርቅ ወይም ብር ወይም ናስ በመቀነታችሁ÷ ወይም ለመንገድ ከረጢት÷ ወይም ሁለት እጀ ጠባብ ወይም ጫማ ወይም በትር አታግኙ፤ ለሠራተኛ ምግቡ ይገባዋልና:: በምትገቡባትም በማናቸይቱም ከተማ ወይም መንደር በዚያ የሚገባው ማን እንደ ሆነ በጥንቃቄ መርምሩ÷ እስክትወጡም ድረስ በዚያ ተቀመጡ:: ወደ ቤትም ስትገቡ ሰላምታ ስጡ፤ ቤቱም የሚገ ባው ቢሆን ሰላማችሁ ይድረስለት፤ ባይገባው ግን ሰላማችሁ ይመለስ ላችሁ::» ማቴ.10÷8-13::

## ሸ ሥርዓተ ጉባኤ

«ገናም ለሕዝቡ ሲናገር እነሆ÷ እናቱና ወንድሞቹ ሊነጋገሩት ፈልገው በውጭ ቆመው ነበር:: አንዱም /ጉባኤ ቢፈታ የሚወድ ይሁዳ/ :- እነሆ÷ እናትህና ወንድሞችህ ሊነጋገሩህ ፈልገው በውጭ ቆመዋል አለው:: እርሱ ግን ለነገረው መልሶ:- እናቴ ማን ናት? ወንድሞቼስ እነ ማን ናቸው? አለው:: እጁንም ወደ ደቀ መዛሙርቱ ዘርግቶ እነሆ እናቴና ወንድሞቼ በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ÷ እርሱ ወንድሜ እኅቴም እናቴም ነውና አለ::» ማቴ. 12÷46-50:: ይህም የሕይወት መጽሐፍ ወንጌልን አጥፎ÷ የእግዚአብሔርን ጉባኤ ፈትቶ÷ ለድኅነት የተጠራን ሕዝብ በትኖ መሄድ እንደማይገባ ሲያስተምራቸውና አብነት ሲሆናቸው ነው:: በአጠቃላይ እርፍ ይዘው ወደ ኋላ እንዳይሉ ነው::

## ቀ. ሥርዓተ ምሕረት

«ወንድምህም ቢበድልህ÷ሂደህ አንተና እርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ ውቀሰው:: ቢሰማህ÷ወንድምህን ጠቀምኸው፤ ባይሰማህ ግን÷ በሁለት ወይም በሦስት ምስክር አፍ ነገር ሁሉ እንዲጸና÷ ዳግመኛ አንድ ወይም ሁለት ከአንተ ጋር ውሰድ፤ እነርሱንም ባይሰማ÷ለቤተ ክርስቲያን ንገራት፤ ደግ ሞም ቤተ ክርስቲያንን ባይሰማት÷ እንደ አረመኔና ቀራጭ ይሁንልህ:: ...በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ ወደ እርሱ ቀርቦ ጌታ ሆይ÷ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት? እስከ ሰባት ጊዜ ነውን? አለው:: ኢየሱስም እንዲህ አለው:- እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ አልልህም::» ማቴ. 18÷15፣21::

## በ.ሥርዓተ ደናግል

«ደቀ መዛሙርቱም የባልና የሚስት ሥርዓት እንዲህ ከሆነ መጋባት አይጠቅምም አሉት:: እርሱ ግን ይህ ነገር ለተሰጣቸው እንጂ ለሁሉ አይደለም፤ በእናት ማኅፀን ጃንደረቦች ሆነው የተወለዱ አሉ÷ /በድንግልና ለመኖር ከማኅፀን ጀምሮ የሚመረጡ አሉ/ ሰውም የሰለባቸው ጃንደረቦች አሉ÷ /መምህራን መክረው አስተምረው በድንግልና ሕይወት የሚያጸኗቸው ሰዎች አሉ/÷ ስለ መንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ:: /ከሕገ እንስሳ ሕገ መላእክት ይበልጣል ብለው÷ በገድል ተቀጥቅጠው በራሳቸው ብርታት በድንግልና ሕይወት



© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

የሚኖሩ አሉ::/ ሊቀበለው የሚችል ይቀበል አላቸው::» ማቴ.19÷10–12::

### ተ. ሥርዓተ ቤተ መቅደስ

«ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደስ ገባና በመቅደስ የሚሸጡትንና የሚገዙትን ሁሉ አወጣ÷የገንዘብ ለዋጮችንም ገበታዎች የርግብ ሻጮችንም ወንበሮች ገለበጠና ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ ተጽፎአል÷እናንተ ግን የወንበዶች ዋሻ አደረጋችኋት አላቸው::» ማቴ.21÷12–13::

### ቸ. ሥርዓተ ትሕትና

«እግራቸውንም አጥቦ ልብሱንም አንሥቶ ዳግመኛ ተቀመጠ÷ እንዲህም አላቸው:– ያደረግሁላችሁን ታስተውላላችሁን? እናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ፤ እንዲህ ነኝና መልካም ትላላችሁ:: እንግዲህ እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ÷ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል:: እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና::» ዮሐ.13÷12–15::

### ኀ. ሥርዓተ ጥምቀት

«ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ::...ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ::» ማቴ.3÷13፣16:: በዚህም ወደ ካህኑ ሄዼን በካህን እጅ በውኃ መጠመቅ እንዳለብን ሥርዓት ሠራልን:: እነርሱንም፦ «እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመን ፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው÷ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስ ተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድር ጓቸው::» አላቸው:: ማቴ.28÷19–20:: በአንዲት ጥምቀት የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ሃይማኖት ነው:: በውኃ መጠመቅ ደግሞ ክርስቶስ የሠራልን ቀዋሚ ሥርዓት ነው::

### ኘ. ሥርዓተ ቊርባን

«ሲበሉም ኢየሱስ ኅብስቱን አንሥቶ ባረከ፤ ቊርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና:– እንካችሁ÷ ብሉ፤ ይህ ሥጋዬ ነው አለ:: ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው:: እንዲህም አለ:– ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፤ ስለ ብዙዎች የኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው::» ማቴ.26÷26:: ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት÷ወይኑ ተለውጦ ደመ መለኮት መሆኑን አምኖ መቀበል ሃይማኖት ነው:: ሥጋው ከስንዴ ደሙ ደግሞ ከወይን መዘጋጀቱ ደግሞ ክርስቶስ የሠራልን ቀዋሚ ሥርዓት ነው::

እንግዲህ ከላይ በዝርዝር እንደ ተመለከትነው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእያንዳንዱ ነገር ሥርዓት ሠርቶ ያሳየን÷ መንፈሳዊ ሕይወት በዘፈቀደ የሚኋዙበት

ጉዳና ሳይሆን በሥርዓት የሚኋዙበት ጉዳና መሆኑን ሲነግረን ነው:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ :–«እግዚአብሔርስ የሰላም አምላክ ነው እንጂ የሁከት አምላክ አይደለምና፤ በቅዱሳንም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንዲህ ነው::» ያለው ለዚህ ነው 1ኛቆሮ.14÷33:: ስለዚህ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን በሃይማኖት አክብሮ መኖር የሚያስመሰግን እንጂ:–«ወገኛ÷አክራሪ÷ ፈሪሳዊ ወዘተ...» የሚያሰኝ አይደለም:: ሥርዓትን አክብሮ የሚኖር ሃይማኖት ያለው ሰው ነውና::

ቅዱሳን ሐዋርያትም ከጌታ በተማሩት መሠረት በሥርዓት ኖሩ እንጂ «ሥርዓት አያጸድቅም!» ብለው በዘፈቀደ አልተመላለሱም:: ተከታዮቻቸውንም « እንደ ዘመኑ ሁኑ» በማለት ያለ ሥርዓት እንዲኖሩ አልፈቀዱላቸውም:: በሁሉ ማለትም በእምነትም በሥርዓትም እነርሱን እንዲመስሉ ነው የመከሯቸው:: «እኔ ክርስቶስን እንደ ምመስል እኔን ምሰሉ::...እኔ በክርስቶስ ኢየሱስ በወንጌል ወልጄአችኋለሁና÷ እንግዲህ እኔን የምትመስሉ ሁኑ ብዬ እለምናችኋለሁ» 1ኛቆር. 11÷1፤4÷16 እንዲል:: ምእመናንም የሐዋርያውን ምክር ሰምተው በሥርዓት ዘመኑን ሳይሆን እርሱን መስለውና ሆነው በመገኘታቸው «ወንድሞች ሆይ÷በሁሉ ስለምታስቡኝና አሳልፌ እንደ ሰጠኋችሁ ወግን ፈጽማችሁ ስለ ያዛችሁ አመሰግናችኋለሁ::» በማለት ክብር ሰጥቷቸዋል:: 1ኛ.ቆሮ.11÷2:: ከዚህም ጋር እንደ ፈለገን እንሁን የሚሉትን ደግሞ «ነገር ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን፤» በማለት መክሯል:: 1ኛ.ቆሮ. 14÷40::

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ልዩ ትኵረት ነበረው:: ይኸውም የአምልኮተ እግዚአብሔር መፈጸሚያ÷ የሃይማኖት መጠበቂያና መገለጫዎች በመሆናቸው ነው:: «ባለቤቱን ካልናቁ÷ አጥሩን አይነቀንቁ !» እንዲሉ÷ ሰው እግዚአብሔርን ሲንቅ ነው÷ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት የሚንቀው:: ሰው በሃይማኖትም በምግባርም ሲደክም ነው ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን የሚንደው:: ይኸንን ደግሞ ሐዋርያው በሚገባ ያውቀዋል:: በመሆኑም «እኛ ግን÷ በጌታ የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ÷ ሁልጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን ልናመሰግን ግድ አለብን÷እግዚአብሔር በመንፈስ መቀደስ÷ እውነትንም በማመን ለመዳን እንደ በኵራት መርጦአችኋልና፤ ለዚህም የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር ለማግኘት በወንጌላችን ጠራችሁ:: እንግዲያስ÷ወንድሞች ሆይ÷ጸንታችሁ ቁሙ÷በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ::» በማለት ጽፏል:: 2ኛተሰ.2÷13–15:: ስለዚህ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ከመጠበቃችን የተነሣ «ወገኞች» በመባላችን ደስ ይለናል እንጂ አይከፋንም:: ምክንያቱም እንደ ሐዋርያው ቃል ለመዳን እንደ በኵራት የተመረጥን ነንና:: ከዚህም ጋር በቀደመው ሥርዓት ከማይሄዱት ጋር አንድነት ስለሌለን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከእነርሱ ራሳችንን ለይተናል:: ምክንያቱም «ወንድሞች ሆይ÷ ከእኛ እንደ ተቀበለው ወግ ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዝዛችኋለን:: እኛን ልትመስሉ እንዴት እንደሚገባችሁ ራሳችሁ ታውቃላችሁ፤ በእናንተ ዘንድ ያለ ሥርዓት አልሄድንም::» ተብለናልና:: 2ኛተሰ. 3÷6–7::

ከላይ ለመግለጥ እንደ ሞከርነው ሐዋርያው ያልተጠነቀቀለት ሥርዓት የለም:: እንዲጠነቀቅ ያደረገውም አድሮበት የሚኖር መንፈስ ቅዱስ ነው:: በመሆኑም ለጸጉራችን ለልብሳችን እንኳን ሥርዓት ሠርቶልናል:: «ራሱን ተከናንቦ የሚጸልይ ወይም ትንቢት የሚናገር ወንድ ሁሉ ራሱን ያዋርዳል:: ራስዋን ሳትሸፍን ግን የምትጸልይ

«አባቶች ዋሻ ዘግተው÷ሰሌን ላይ ተኝተው÷ሽንብራ ቆርጥመው አድሮባቸው በሚኖር በመንፈስ ቅዱስ የሠሩልንን ሥርዓት የምታፈርሱት እናንተ ማናችሁ?» ልትሉአቸው ያስፈልጋል:: «የመንፈስ ቅዱስ ድርሰት የሆነውን ቅዳሴ ይቀነስ÷ አያስፈልግም የምትሉ እናንተ ማን ናችሁ? ደግሞስ ለትውልዱ እንዲመች እያላችሁ በትውልዱ የምታሳስቡት ለምንድነው? እናንተ አላችሁ እንጂ እኛ መች አልናችሁ?» ልትሏቸው ይገባል:: ምክንያቱም ክርስትና የነፍስን ምቾት አልቆ መጠበቅ እንጂ የሥጋን ምቾት መጠበቅ አይደለምና::



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ወይም ትንቢት የምትናገር ሴት ሁሉ ራሷን ታዋርዳለች፤ እንደ ተላጨች ያህል አንድ ነውና:: ሴትም ራስዋን ባትሸፍን ጠጉርዋን ደግሞ ትቈረጥ፤ ለሴት ግን ጠጉርዋን መቈረጥ ወይም መላጨት የሚያሳፍር ከሆነ ራስዋን ትሸፈን:: ወንድ የእግዚአብሔር ምሳሌና ክብር ስለሆነ ራሱን መከናነብ አይገባውም::...በእናንተ በራሳችሁ መካከል ፍረዱ፤ ሴት ራስዋን ሳትሸፍን ወደ እግዚአብሔር ልትጸልይ ይገባታልን? ወንድ ጠጉሩን ቢያስረ ዝም ነውር እንዲሆንበት ሴት ግን ጠጉርዋን ብታስረዝም ክብር እንዲሆን ሳት ተፈጥሮ እንኳ አያስተምራችሁምን? ጠጉርዋ መጐናጸፊያ ሊሆን ተሰጥቶታልና:: ጻኑ ግን ማንም ሊከራከር ቢፈቅድ÷እኛ ወይም የእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት እንዲህ ያለ ልማድ የለንም::» በማለት የደመደመው ለዚህ ነው:: ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ለሁለት ሺ ዓመታት አክብራና አስከብራ ያቆየችውን ሥርዓት የሚንድ ነገር ሲመጣ ለምን? ማለት ይገባል::

ዛሬ በሥልጣኔ አሳበው ቤተ ክርስቲያንን ለመናድ የተነሡ ሰዎች አሉ:: ቤተ ክርስቲያን ሥልጣኔ እንዳልገባት እነርሱ ግን ሥልጣኔው የገባቸው አድርገው ይናገራሉ:: የሥልጣኔ በር ከፋችና ፍኖተ አእምሮ አደራጅ የሆነች ቤተ ክርስቲያንን «ሥልጣኔ አልገባትም» ማለት የራስን ትዕቢት ወይም ዐይን አውጣነት ከመግለጥ በስተቀር ቤተ ክርስቲያንን አያዋርዳትም:: ቤተ ክርስቲያን የዘመን ሥልጣኔ ያልገባት ጊዜ የለም:: ነገር ግን የሚጠቅማትን ይዛ የማይጠቅማትን ጥላ ትጓዛለች እንጂ ከሚያብዱት ጋር አታብድም:: ምነው! እነዚህ ሰዎች ከእነርሱ በፊት «ሥልጣኔው ገብቶናል» ብለው በፒያኖና በጊታር ሲጨፍሩ የነበሩ ሰዎች የት እንደ ደረሱ ማየት ተሳናቸው? በዐይናቸው ፊት አይደለም እንዴ! ወንድ ከወንድ÷ ሴትም ከሴት እየተጋቡና እያጋቡ ያሉት? ከመካከላቸውስ በዚህ ግብራቸው ማንን ከፍጹምነት ማዓርግ አደረሱ? ስለዚህ ምእመናን ይህንን ማስተዋል አለባቸው:: ምክንያቱም ለታቦቱ ሳይሆን ለጊታሩ÷ለክርስቶስ ሥጋና ደም ሳይሆን ለአሳማ ሥጋ የሚከራከሩ ሰዎች የቤተ ክርስቲያን አለመሆናቸውን ማወቅ አለባችሁ:: መንፈሳውያን የሠሩትን ሥጋውያን ሲያፈርሱት ዝም ብላችሁ ማየት የለባችሁም:: «አባቶች ዋሻ ዘግተው÷ሰሌን ላይ ተኝተው÷ሽንብራ ቆርጥመው አድሮባቸው በሚኖር በመንፈስ ቅዱስ የሠሩልንን ሥርዓት የምታፈርሱት እናንተ ማናችሁ? » ልትሉአቸው ያስፈልጋል::

«የመንፈስ ቅዱስ ድርሰት የሆነውን ቅዳሴ ይቀነስ÷ አያስፈልግም የምትሉ እናንተ ማን ናችሁ? ደግሞስ ለትውልዱ እንዲመች እያላችሁ በትውልዱ የምታሳስቡት ለምንድን ነው? እናንተ አላችሁ እንጂ እኛ መች አልናችሁ?» ልትሏቸው ይገባል:: ምክንያቱም ክርስትና የነፍስን ምቾት መጠበቅ እንጂ የሥጋን ምቾት መጠበቅ አይደለምና:: ስለዚህ እነዚህ በጓሮ ከመናፍቃን ተዋውለው በፊት ለፊት ቤተ ክርስቲያንን የሚያውኳትን ሰዎች ልታውቋቸው ይገባል:: እነዚህ ሰዎች በግልጥ÷በድፍረት «ከአባቶቻችን እንበልጣለን» እያሉ ነውና:: እኛ ግን የምንለው ነቢዩ ኤልያስ እንዳስተማረን «ከአባቶቻችን አንበልጥም» ነው:: «አቤቱ እኔ ከአባቶቼ አልበልጥምና ነፍሴን ውሰድ ብሎ እንዲሞት ' ለመነ::» እንዲል:: 1ኛ.ነገ.19÷4:: እነዚህ ሰዎች በሌላ በኩል ደግሞ:- «የተማርን ሰዎች ነን!» እያሉ በዕውቀታቸው ለመመጻደቅ ይፈልጋሉ:: ወገኖቼ÷ አርዮስም ንስጥሮስም እኮ! የተማሩ ሰዎች ነበሩ÷በዕውቀታቸው ሲመጻደቁ ወደቁ እንጂ:: ያም ሆነ ይህ የእነዚህ ሰዎች ጠብ ከእግዚአብሔር ጋር ስለ ሆነ ይወድቃሉ:: «ከእግዚአብሔር ጋር የሚጣሉ ይደቅቃሉ!» እንዲል:: 1ኛ ሳሙ.2÷10:: እነዚህ ሰዎች ከሥርዓቱና ከእምነቱ ፈቀቅ ከማለታቸውም በላይ የስድብ ናዳ ማውረዳቸው ይገርማል:: እኛ ግን እንመርቃለን:: «በገዛ እጃችን እየሠራን እንደክማለን፤ ሲሰድቡን እንመርቃለን÷ ሲያሳድዱን እንታገሣለን÷ክፉ ሲናገሩን እንማልዳለን፤ እስከ አሁን ድረስ የዓለም ጥራጊ የሁሉም ጉድፍ ሆነናል::» እንዲል:: 1ኛ. ቆሮ.4÷12–13:: ጌታችን በወንጌል «የሚያሳድዱአችሁን መርቁ÷ መርቁ እንጂ አትርገሙ:: ...ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ፤ በሰው ሁሉ ፊት መልካም አድርጉ፤ ስለ ሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ!» ብሏል:: ማቴ. 5÷44–45:: ከዚህ በተረፈ እኛ ከዐመፀኞች ጋር አንተባበርም:: ምክንያቱም «ከማያምኑ ጋር በማይመች አካኼድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ ከዐመፃ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው? ክርስቶስ ከቤልሆር ጋር ምን መስማማት አለው? ወይስ የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው? የእግዚአብሔር ታቦትንስ በጣዖት ቤት ውስጥ የሚያኖር ማን ነው?» ይላልና:: 2ኛቆሮ.6÷14–17:: እንግዲህ በቤተ ክርስቲያን እምነት እና ሥርዓት ጸንተን እንድንኖር የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን:: አሜን::

## ሥርዓቱን ከልማዱ ለይታችሁ ...

/ከገጽ ፲፯ የዞረ/

"የቅዳሴ ጠበል ክብር ከማየ ገቦ ጋር አንድ ነው::" በማለት የሚናገሩ ሰዎች ለሐሳባቸው መረጃ አድርገው የሚያቀርቡትን እንመልከት:: የልጅነት ሀብት የምናገኝበትን ጥምቀት ለመፈጸም አጥማቂው ካህን መስተብቍዕ /የምልጃ ጸሎት/፣ ሥርዓተ ቅዳሴ፣ መጽሐፈ ክርስትና ካደረሰ በኋላ በገንዳ ያለውን ውኃ በስመ ሥላሴ በባረከው ጊዜ ውኃው ወደ ማየ ገቦነት ይለወጣል:: "ውኃው ወደ ማየ ገቦነት የተለወጠው ካህኑ:- "አሐዱ አብ ቅዱስ፥ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፥ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ" በማለት ባደረገው ቡራኬ ነው:: የቅዳሴ ጠበልም በቤተ መቅደስ የሚቀመጥ ሲሆን ካህኑ በጸሎተ ቅዳሴው መጀመሪያ "አሐዱ አብ ቅዱስ፥ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፥ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ" ስለሚል ጠበሉ በጸሎቱ አማካይነት ከማየ ገቦ ጋር ይተካከላል::" ይላሉ:: በእርግጥም ለጥምቀት የቀረበው ውኃ "አሐዱ አብ ቅዱስ፥ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፥ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ" በሚለው ጸሎት ወደ ማየ ገቦነት እንደሚለወጥ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ:: ነገር ግን በጸሎተ ቅዳሴው ላይ "አሐዱ አብ ቅዱስ፥ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፥ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ" ሲባል የቅዳሴ ጠበሉም "እንደ ማየ ገቦ ይሆናል" የሚለው አነጋገር በመጽሐፍ የተደገፈ ሳይሆን "ሊሆን ይችላል" የሚል የየዋሃን አስተሳሰብ ነው:: በርግጥ ጠበሉ በቤተ መቅደስ ተቀምጦ ጸሎተ ቅዳሴ ሲደርስበት "ማየ ፈውስ፤ ማየ መቁረር" ወደ መሆን ይለወጣል:: ይህን ደግሞ "ማየ ገቦ" ልንለው አንችልም:: በሚደርሰው ጸሎትም ኾነ በአገልግሎት ቅዳሴ ጠበል /ማየ መቁረር/ እና ማየ ገቦ ለየቅል ናቸው::

በሌላ መልኩ ሁኔታውን ሰፋ አድርገን ስንመለከት ደግሞ በየዓመቱ ጥር ፲፩ ቀን የጥምቀት በዓል ሲከበር ቀሳውስቱና ዲያቆናቱ በተከተረው ውኃ ላይ ሥርዓተ ቅዳሴ አድርሰው፣ ካህኑም: -"አሐዱ አብ ቅዱስ፥ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፥ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ" በሚለው ጸሎት ውኃውን ይባርካል:: ከዚያም ጠበሉን በእጃቸው እያፈኑ ሕዝቡን ይረጫሉ:: እንግዲህ "አሐዱ አብ ቅዱስ፥ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፥ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ" በሚለው ጸሎት «ጠበሉ ወደ ማየ ገቦነት ይለወጣል» የሚለውን አስተሳሰብ ብቻ ይዘን ከተነሣን "ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ ልጆቿን የልጅነት ጥምቀት ታጠምቃለች" ወደሚለው የተሳሳተ ድምዳሜ እንደርሳለን:: በሌላ በኩል ደግሞ "ጥምቀት አንዲት ናት::" /ኤፌ.4፥5/ ከሚለው ትምህርተ ሃይማኖት ጋር የሚጋጭ ሐሳብ እናሥነሳለን:: ካህኑ "አሐዱ አብ ቅዱስ፥ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፥ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ" የሚለውን ጸሎት በተለያዩ ጊዜያትና ቦታዎች ሲያደርሱ የጸሎቱ ዓላማ የተለያየ ነው:: ለምሳሌ በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ

ወደ ገጽ ፲፬ ዞሯል



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ባለፈው እትም በዚህ ርዕስ «ሕዙን ወትኩዘ ልብ» ከሚለው የሰኞ ውዳሴ ማርያም ዘር በመነሣት «ክርስቶስ አዳምን ለማዳን ለምን አዘነ?» በሚለው ንዑስ ርዕስ ሰፋ ያለ ትምህርት ማቅረባችን ይታወሳል:: በዚህ እትም ደግሞ ያለፈውን ትምህርት አጠቃለን «ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ዘተሰብአ እምኔኪ» በሚለው የቅዳሜ ውዳሴ ማርያም ዘር ላይ በመመሥረት ስለ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት ሰፋ ያለ ትምህርት እናቀርባለን::

/መምህር ኀይለ ማርያም ላቀው/

# ምሥጢረ ሥጋዌ በውዳሴ ማርያም

በመጀመሪያው ክፍለ ትምህርት ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም:- "ጌታ ያዘነ የተከዘ ሁኖ አዳምን ያድነው ዘንድ መውደዱን" እንደነገረን ተመልክተናል:: ሊቁ ከነገረ ድኅነት በማስከተልም በትኩረት በየክፍለ ውዳሴው የሚያነሣቸው ሁለት ዐበይት ጉዳዮች አሉ:: እነርሱም «ምክንያተ ድኅነትና ምክንያተ ስሕተት» ናቸው::

ዘመን መቆጠር፥ ታሪክ መጻፍ ከተጀመረበት ጊዜ አንሥቶ ለማንኛውም ስሕተት በሠናይም ሆነ በእኩይ ምክንያትና ውጤት እንዳለው የተረጋገጠ ነው:: ስለ ሰው ልጅ ውድቀትና ድኅነት ስናጠና አሳዛኝ ታሪኩ ወደ ሁለት መሠረታዊ አቅጣጫዎች እንድናተኵር ይጋብዘናል:: የመጀመሪያው ጥያቄ:- ሰው ለምን ወደቀ? ከውድቀቱስ እንዴት ተነሣ? የሚል ነው:: አጥብበን የተመለከትነው እንደ ሆነ ለውድቀቱ በእኩይ ለድኅነቱ ደግሞ በሠናይ ምክንያቶችን እናገኛለን::

ለአዳም ምክንያተ ስሕተቱ ሔዋን ስትሆን ምክንያተ ድኅነቱ ደግሞ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት:: ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም ስለ ሁለቱ እናቶች በንጽጽር ትምህርት ይሰጣል:: ምክንያቱም ሔዋን የከይሲ ዲያብሎስን ምክር ሰምታ የሞት ጀማሪ የሆነውን ቃየንን ወልዳለችና:: በአንጻሩም እመቤታችን ድንግል ማርያም:- "ደስ ይበልሽ" የሚለውን የመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ብሥራት ሰምታ የድኅነት ባለቤት የሆነውን ዐማኑኤልን በድንግልና ጸንሳ በድንግልና ወልዳለችና:: ይኽንንም ሲገልጽ:- «በጻዕርና በምጥ ትወልድ ዘንድ በሔዋን የፈረደባት ነው፤ አንቺ ግን ጸጋን የተመላሽ ሆይ፥ ደስ ይበልሽ፤ የሚል ቃል ሰማሽ» ሲል ገልጦታል:: ዘፍ.4፥1:: ኢሳ.7፥14:: ማቴ.1፥20-23:: ሉቃ. 2፥7:: በማስከተልም በሔዋን ስሕተት የገነት ደጃፍ እንደ ተዘጋ የድንግል ትሕትና ለገነት መከፈት ምክንያት እንደ ሆነ ያስተምራል:: "ስለ ሔዋን የገነት ደጅ ተዘጋ፤ ዳግመኛ ስለ ድንግል ማርያም ተከፈተልን" እንዲል:: በዚህ የንጽጽር ትምህርቱ ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅም ይተባበረዋል:: "ቀድሞም ሔዋን ድንግል ነበረችና ዲያብሎስ አሳታት፤ ድንግል ማርያምን ግን ቅዱስ ገብርኤል አበሠራት:: ነገር ግን ሔዋንን ዲያብሎስ አሳታት፤ የሞት ምክንያት የሚሆን ቃየንን ወለደች:: ማርያምን ግን መልአክ በአበሠራት ጊዜ ሁሉን ወደ ዘለዓለም ሕይወት የሚመራ አካላዊ ቃልን በሥጋ ወለደች:: የሔዋን ልብላ ማለቷ ዕፀ በለስ የሞት ምክንያት እንደ ሆነ አስረዳ:: በዚያም ዕፅ አዳም ተድላ ደስታ ካለበት ከገነት ወጣ:: ከድንግል የተወለደ አካላዊ ቃል ግን መስቀል የድኅነት ምክንያት እንደ ሆነ ገለጠ:: በዚያም መስቀል ቀማኛ፥ ወንበዴ የነበረው ሰው ከአባቱ ከአዳምና ከቀደሙ አባቶች ሁሉ ጋር ተድላ ደስታ ወዳለበት ገነት ገባ:: እንዲል:: ዘፍ.3፥24:: ሉቃ.23፥41-44:: 1ኛቆሮ.1፥18:: ዮሐ. 1፥1-14:: 1ኛጢሞ.2፥14:: የሃይማኖተ አበው ዘዮሐንስ አፈወርቅ ም. 67፥ ክፍል 11፥4-5::

በከይሲ ዲያብሎስ ምክር ሔዋን ምክንያተ ስሕተት /የስሕተት ምክንያት/ ሆናለች:: እግዚአብሔር ለአዳምና ለልጆቹ፣ ለሥጋና ለነፍስ፣ ስለ ካሠ ሔዋን ምክንያተ ስሕተት ብትሆንም እግዚአብሔር ጥንተ ርግማኑን ሽሮ ነጻ አድርጓታል:: ሊቁም የሔዋንን ነጻ መውጣት :- "እግዚአብሔር ምጥሽንና ጻር ሽን አበዛዋለሁ» ብሎ ከፈረደባት በኋላ ሰውን ወደደና ነጻ አወጣት" በማለት ያስተምራል ::

ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም ለአገልግሎት በተጠራበት ዘመን የክርስትና ሃይማኖት አብቦ በማፍራት ላይ ነበር:: በአንጻሩም «ትክክለኛው የክርስትና ሃይማኖት እንዳይሰበክ የእግዚአብሔር የድኅነት ሥራ በግልጽ እንዳይታወቅ፥ እንዲሁም ድኅነቱ /ማዳኑ/ በአድልዎ እንደ ተፈጸመ» የሚያስተምሩ መናፍቃን ነበሩ:: ከእነዚህም ውስጥ «ሔዋን ምክን ያተ ስሕተት በመሆኗ ከሲኦል አልወጣችም» የሚሉ መናፍቃን ተነሥተው ነበር:: ሊቁ ግን በውዳሴው እንደ ቀደምት ነቢያት ምስጋናንና እና ትምህ ርትን አካቶ ስለ ጻፈ እግረ መንገዱን ከላይ ለተጠቀሱትም ሆነ በቀጣይ ለምን መለከታቸው መናፍቃን በአጽንኦት መልስ ሰጥቷል::

ሔዋን ምክንያተ ስሕተት ብትሆንም የእግዚአብሔር ምሕረት ተደርጐላታል:: ምክንያቱም የክርስቶስ ሞት በጥንተ አብሶ ለተፈጸመ በደል መደምሰሻ በመሆኑ «ሔዋን ነጻ አልወጣችም» የሚለው ትምህርት ከነገረ ድኅነት ያፈነገጠ ትምህርት ነውና:: ስለዚህ ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም:- "ወአግዓዛ፤ ነጻ አወጣት" በማለት በክርስቶስ የተፈጸመው ድኅነት ለአዳም ብቻ ሳይሆን ለሔዋንም ጭምር እንደሆነ አስረድቷል:: ለዚህም ነው፥ "እስመ አድኀንኮ ለአዳም እምስሕተት ወረሰይካ ለሔዋን አግዓዚተ እምጻዕረ ሞት፤ አዳምን ከስሕተት አድነኸዋልና፤ ሔዋንንም ከሞት ጻዕረኝነት ነጻ አድርገሃታልና::» ያለው::

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ስለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ኤፍሬም የሰጠውን ትምህርት እናቀርባለን::

## ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ዘተሰብአ እምኔኪ

«ኢየሱስ» የሚለው ስም ስመ ሥጋዌ ነው:: መድኀን፣ቤዛ፣መድኃኒት የሚል ትርጉም አለው:: ኢየሱስ ክርስቶስ የአብ የባሕርይ ልጅ ስለሆነ ወልደ እግዚአብሔር ነው:: ማር.1÷1፤ ሉቃ. 1÷35፣ 22፣70፤ ዕብ.1÷2:: የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ ቃለ እግዚአብሔር ይባላል:: ዮሐ.1-1-14:: መሲሕ ወይም ንጉሥ ስለሆነ ክርስቶስ ይባላል:: ዮሐ.1÷22፤መዝ.2÷2፤ዳን.25-27:: ከኃጢአት በስተቀር የእኛን ባሕርይ ገንዘብ አድርጐ /ከሥጋችን ሥጋ ከነፍሳችን ነፍስ ነስቶ/ ዘወትር ከእኛ ጋር ስለሚኖር ዐማኑኤል ተብሏል:: በአጠቃላይ የሥጋና የነፍስ ፈጣሪያችን፣ገዥያችን ስለሆነ በተለይም በሥጋው መሥዋዕትነት÷ በከበረ ደሙ ፈሳሽነት ከግብርናተ ዲያብሎስ ነጻ አውጥቶ ፍዳን መርገምን አርቆ በቸርነቱ ስለሚመግበን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንለዋለን::

ክርስቶስ፣ኢየሱስ፣ዐማኑኤል የሚባሉት ስሞች በተጠሩ ጊዜ ትስብእ



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ትን ለብቻ ወይም መለኮትን ለብቻ ለይተው የሚያሳዩ ስሞች አይደሉም:: እነዚህ የአምላካችን ስሞች በተዋሕዶ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ሆኖ ሲወለድ የተጠራበት ሕያዋን ስሞች ናቸው:: ይኸንንም ትምህርተ መለኰት የሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ምስክር የኾነው ቅዱስ ቄርሎስ ሲያጠናክር:- «ወእነግር አነሂ ከመ ኢመፍትው ለእግዚአብሔር ቃል እስምዮ ክርስቶስ ዘእንበለ ትስብእት ወኢለትስብእቱሂ ዘእንበለ መለኮት ክርስቶስሃ ይሰመይ፤ እኔም መለኮትን ከትስብእት ለይቼ ክርስቶስ እለው ዘንድ፣ ትስብእትንም ከመለኮት ለይቼ ክርስቶስ እለው ዘንድ እንዳይገባ እናገራለሁ:: አንድም መለኮት ከትስብእት ተለይቶ ትስብእትም ከመለኮት ተለይቶ ክርስቶስ ይባል ዘንድ እንዳይገባ እናገራለሁ:: እግዚአብሔር ቃል በማይመረመር በማይለይ ተዋሕዶ ከሥጋው ጋር አንድ ሆኖ ክርስቶስ ተብሏልና» ብሏል:: ተረፈ ቄርሎስ ምዕራፍ 17::

«ኢየሱስ፣ዐማኑኤል፣ክርስቶስ» በተባሉት ስሞች መለኰት ለብቻው ትስብእትም ለብቻው ሊጠራበት እንደማይችል ተመልክተናል:: ምክንያቱም መለኮት ቅድመ ዓለም የነበረ በመሆኑ ነው:: ስለዚህ ያለ ትስብእት መለኮት ለብቻው ሊጠራበት አይችልም:: እንደዚሁም ትስብእትም ለብቻው «ኢየሱስ፣ዐማኑኤል» በሚለው ስም ሊጠራበት አይችልም:: በአጠቃላይ ኢየሱስ፣ዐማኑኤል፣ ክርስቶስ የተሰኙት ስሞች ሁለቱ ማለትም ባሕርየ መለኮትና ባሕርየ ትስብእት÷ አካለ መለኮትና አካለ ትስብእት ከተዋሐዱ በኋላ የወጡ ስሞች ናቸው:: ይኸውም የመለኮት ባሕርይና የትስብእት ባሕርይ አንድ በመሆን÷ ባለመለያየት፣ ባለመቀላቀል በፍጹም ተዋሕዶ ስለ ተወለደ የወጣለት ስም ነው እንጂ የትስብእት ብቻ ÷ወይም የመለኮት ብቻ ስም አይደለም::

## የኢየሱስ ክርስቶስ ቃልነት

ቅዱስ ኤፍሬም:- «ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል» በማለት ኢየሱስ ክርስቶስ ወይም አካላዊ ቃል ከድንግል ማርያም ሰው እንደ ሆነ ያስተምረናል:: «መጀመሪያ ቃል ነበር:: ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ:: ቃልም እግዚአብሔር ነበረ:: ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ:: ቃልም ሥጋ ሆነ::» /ዮሐ. 1÷1–14/ እንዲል:: «ቃል» «ሲባል አአት ሪኮን÷ በርፎሪኮን÷ አተርጋዋን» የሚባሉ ዝርዋን ቃላት አሉ:: እኒህም ቃለ ሰብእ /የሰው ቃል/፣ ቃለ እንስሳት፣ ቃለ መላእክትም ናቸው:: እነዚህ ሁሉ ዝርዋን /አካል የሌላቸው/ ቃላት ናቸው:: የኢየሱስ ክርስቶስ ቃልነት ከላይ ከተመለከት ናቸው ቃላት በተለየ አካላዊ ቃል ነው:: የላይኞቹ ዝርዋን ናቸው፤ የራሳቸው የሆነ አካል የላቸውምና:: ኢየሱስ ክርስቶስ ግን አካላዊ ቃል ነው:: ይህም ቃል ከድንግል ሰው እንደ ሆነ ሊቁ በውዳሴው ትክክለኛውን የሐዋርያትን ትምህርት ያስተምራል::

ከሰው አንደበት ወጥቶ በቃል ገዝፎ የሚሰማ የሚታይ ከሆነ ቃል ሊባል ይችላል:: ይኸውም ሁለት መገለጫ አለው:: የሰው ቃል ለጆሮ እንደ ሚስማማ በሚነገርበት ጊዜ በምላስ ይነገራል:: በጽሑፍ ለመግለጽ የተፈለገ እንደ ሆነ ግን በልብ ያለውን በብራና ወይም በወረቀት ላይ ማስፈር ይቻላል:: ቃል ከልብ ሳይለይ በቀለም ገዝፎ በወረቀት ወይም በብራና ላይ በሚገለጽበት ጊዜ አካሉን ለማሳየት ተቻለ ማለት ነው::

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቃልነቱ ከአብ ተገኝ:: ሰው በሚሆንበት ጊዜም ከልብ የነበረው ቃል ከልብ ሳይለይ በወረቀት ገዝፎ እንደሚታይ እርሱም በመለኰት ከልብ ሳይለይ ሰው ሆኖ ገዝፎ ታየ:: ስለዚህ ነው ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት:- «ልቤ መልካም ነገርን አፈለቀ:: እኔ ሥራዬን ለንጉሥ እናገራለሁ:: አንደበቴ እንደ ፈጣን ጸሓፊ ብርዕ ነው::» ማለትም «አንደበቴ ጠብጠብ እንደ ሚል እንደ ፈጣን ጸሐፊ ቀለም ይጽፋል» ያለው:: /መዝ.44÷1/:: ይህም በመሆኑ «ኅደረ በብእሲ» ወይም በሰው አደረ የሚል ሳምሳጢ ጳውሎስን፣ እንዲሁም «ለፌ እማርያም ክዋኔሁ ለወልድ፤ የወልድ ህልውና ከማርያም ወዲህ ነው» ለሚሉ ለእነ ፎጢኖስ የክህደት ትምህርት መልስ ይሰጣል::

ጳውሎስ ሳምሳጢ የተወለደው በታናሽ እስያ በሶርያ አካባቢ ሲሆን የነበረበት ዘመን በሦስኛው መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ ነበር:: የጳውሎስ ሳምሳጢ ክህደት «ቃል አካል ሳይኖረው በአብ አካል ውስጥ የኖረ ኃይል ነው» የሚል ነው:: በእርሱ አስተሳሰብ «ከሥጋዌ በፊት ቃል አካል አልነበረውም፤ በአብ ህልውና ውስጥ የሚኖር ዝርው ቃል÷ ዝርው ኃይል ነው:: ይኸውም በሰው ጭንቅላት ንባብ አእምሮ እንደሚኖር ማለት ነው::» ይህም ምሥጢረ ሥላሴን ማፍለስ ስለሆነ አንድ አካል አንድ ገጽ ካለው ከሰብ አልዮስ ክህደት ጋራ አንድ ነው::

ከዚህም በተጨማሪ ጳውሎስ ሳምሳጢ በምሥጢረ ሥጋዌም ብዙ የተሳሳተ ሰው ነበር:: በምሥጢረ ሥጋዌ :- ከማርያም የተወለደው ዕሩቅ ብእሲ ነው፤ ስሙም ኢየሱስ ይባላል፤ ዕሩቅ ብእሲ ኢየሱስ በዮርዳኖስ በተጠመቀ ጊዜ በአብ ህልውና ውስጥ የነበረው ዝርው ቃል መጥቶ አደረበት:: ከዚያ በኋላ ራሱ ባደረገው ተጋድሎና በሠራው ትሩፋት በጸጋ /በግብር÷ በማደጎ/ የእግዚአብሔር ልጅ ለመባል በቃ:: «ሶበ ተረክበ ወልደ እግዚአብሔር ለወልደ ማርያም በዮርዳኖስ ረሰዮ አምላከ በጸጋ፤ የእግዚአብሔር ልጅ የማርያምን ልጅ በዮርዳኖስ ባገኘው ጊዜ የጸጋ አም ላክ አደረገው» ያለው ለዚህ ነው:: /የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድ ረክ÷ ገጽ 73/::

ከላይ ለተመለከትነው መናፍቅና ኑፋቄ የቅዱስ ኤፍሬም ውዳሴ መልስ ይሆናል:: ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ ያለ መለወጥ ያለ ኅድረት ፍጹም ሰው የሆነ የባሕርይ አምላክ መሆኑን ሲገልጽ:: «ዘተሰብአ እምኔኪ ዘእንበለ ውላጤ ፤ ያለመለወጥ ከአንቺ ሰው ሆነ» በመሆኑም:- ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ሰው የሆነው በመለወጥ ወይም ሳምሳጢ ጳውሎስ እንደሚለው በኅድረት አይደለም:: እነ ፎጢኖስም ከአባቱ ጋር ህልው ሆኖ ቅደመ ዓለም የነበረውን አምላክ ህልውና ከድንግል ማርያም ከተወለደ ወዲህ እንደ ሆነ የሚያስተምሩ መናፍቃን ናቸው::

ሊቁ ቅዱስ አፍሬም ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌሉ :-«በኛም አደረ» በማለት የኩነትን÷ የተዋሕዶን ነገር እንዳስተማረ እርሱም «ከአንቺ ሰው ሆነ» ካለ በኋላ «በእኛ አደረ» ብሏል:: በነዚህ ሁለት ቃላት ማለትም «ኀደረ» የሚለውን ቃል ይዘው ነድረት እንዳይሉበት «ተሰብአ» /ሰው ሆነ/ በማለት ለተጠቀሱት መናፍቃን መልስ ይሰጣል:: መናፍቃን ለክርክር አያርፉምና «ተሰብአ» /ሰው ሆነ/ ያለውን ይዘው:- «የሎጥ ሚስት የጨው ሐውልት ወደ መሆን እንደ ተለወጠች፣ የሙሴ በትር ወደ እባብነት እንደ ተለወጠች የመለኮት ኃይል ወደ ትስብእትነት÷ ትስብእትነት ወደ መለኮት ተለወጠ» ይላሉ:: ነገር ግን «በእኛ አደረ» በሚለው ቃል መናፍቃን ይረታሉ:: «ተሰብአ ኀደረ፤ ሰው ሆነና በእኛ አደረ» የሚሉት ቃላት እንደ አለቃና እንደ ጠበቃ የሚጠባበቁ ናቸው::

«ኀደረ» የሚለው ግስ ክብር የሚቀንስ እንዳይሆን:- «እንደ አባቱ በአባቱ ዘን ድ ያለውን ክብር አየን» ብሏል:: ከላይ ለተጠቀሰውም ምስክር ሲጠቅስ÷ «ነቢዩ ኢሳይያስ የዐማኑኤልን ምሥጢር አየ:: ሕፃን ተወለደልን÷ ወልድም ተሰጠን» ብሎ አሰምቶ ተናገረ::

«በኛም አደረ» በሚለው ኃይለ ቃልም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን «ነፍስ አልነሳም፤ ምትሐት ነው፤ ሥጋ በቅድምና ነበረ፤ ባሕርዩን አግዝፎ ታየ፤» የሚሉ መናፍቃን ይረቱበታል÷ ይሸነፉበታል:: ምክንያቱም አካላዊ ቃል ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷም ነፍስን በመንሳት ሰው እንደ ሆነ መጻሕፍት ይተባበራሉ:: «በኛም» ባለጊዜ ነፍስን መንሳቱን÷ ምትሐት ሳይሆን ሰው መሆኑን እንገነዘባለን:: በዚህም በቅድምና የነበረው ቃል እንጂ ሥጋ እንዳልነበረ በውዳሴው ምሥጢረ ሥጋዌን ያስተምረናል:: ዮሐ.1÷1–2:: ዕብ.2÷14::

በማስከተልም እግዚአብሔር ሰውን እንዴት እንዳዳነው ሲገልጥም:- «ዘር ምክንያት ሳይሆነው ከድንግል በሥጋ ተወለደ፤ ተወልዶም አዳነን::» ይላል:: ሊቁ በጥልቀት የሚያስገነዝበን ነገር መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከድ



© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

ንግል ማርያም በሥጋ ተወልዶ አዳምን ማዳኑን ነው፡፡ «በሥጋ ተወለደ» የሚለን ድንግል ማርያም በሥጋ እንጂ በመለኮቱ እግዚአብሔር ወልድን ስለ ማትወልደው ነው፡፡ «አኮ ወልደ ማርያም በመለኮቱ አላ በከመ ሥርዓተ ትስብእት፤ በመለኮቱ የማርያም ልጅ አይደለም፡፡ በትስብእቱ እንጂ» እንዲል፡፡ «ድንግል ማርያም በመለኮቱ አትወልደውም» ሲባል ወልድ በመለኮቱ ዘላለማዊ /ቀዳማዊ/ እንደ ሆነ ለመግለጽ ተፈልጎ ነው፡፡ ይህ ወላዲተ አምላክነቷ በምሥጢረ ሥጋዌ÷ በደኃራዊ ልደቱ እንጂ በምሥጢረ ሥላሴ በቀዳማዊ ልደቱ አይደለም ለማለት ነው፡፡ «ከእመቤታችን ተወለደ» ሲባል ከዚያ በፊ ት አልነበረም የሚሉ አሉ፡፡ ነገር ግን መለኮታዊው አምላክ ከእመቤታችን ሰው ሁኖ ከመወለዱ» ፊት ነበር፡፡ እመ ቤታችን በሥጋ ወለደችው ማለትም መለኮት የተዋሐደውን ሥጋ ነው፡፡ ስለሆነም «ወላዲተ አምላክ» ትባላለች፡፡

## ቅድመ ዓለም መኖሩ

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘር ምክንያት ሳይሆነው ከድንግል ማርያም የተወለደው ልደት ቀዳማዊ ልደቱን ይገልጻል፡፡ 5500 ዘመን ሲፈጸም «በሥጋ» ከእመቤታችን ያለ አባት መወለዱ፣ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት እንደ ተወለደ ያጠይቃል፡ ሊቃውንትም ለማይመረመረው ለቅድመ ዓለም ልደቱ ድኅራዊ ልደቱ ምስክር እንደ ሆነ ሲያመስጥሩ «ልደት ቀዳማዊ ተሀውቀ በድኅራዊ ልደት፤ ቀዳማዊ ልደት በደኃራዊ ልደት ታወቀ፡፡» ብለዋል፡፡ ቅዱስ ኤፍሬምም የቅድመ ዓለም ልደቱን፡– «የነበረው÷ የሚኖረው÷ የመጣው ዳግመኛ የሚመጣውም ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ያለ መለወጥ ፍጹም ሰው ሆነ» ይለናል፡፡ ዮሐ.1÷1–14፡፡ ይህ የቀዳማዊ ልደቱ ትምህርት አርዮሳውያንን የሚያደቅ መዶሻ ስለሆነ ደገኛ ትምህርቱ በየዋሃን ምእመናን ልቡና እንዲቀረጽ የአካላዊ ቃል እናት ድንግል ማርያም መልሶ መላልሶ እንዲጽፍ ገልጻለታለች፡፡ ሊቁም አበክሮ ቀዳማዊ ልደቱን ሲሰብክ፡– «ከዓለም በፊት የነበረው የአብ ቃል ከአብ ዘንድ መጥቶ ልዩ ከሆነች እናቱ ሰው ሆነ፡፡» «ከዓለም በፊት» በማለት የሰበከው ቀዳማዊ ልደቱን ነው፡፡ «ዋሕድ ቃል ዘእም አብ ዘእም ቅድመ ዓለም ሀልው፤ ከአብ የተወለደው ከዓለም በፊት የነበረ አንዱ ቃል ራሱን /ባሕርዩን/ ሰወረ÷ ከአንቺም የተገኘን የሰውን አርአያ ነሳ» እንዲል፡፡ በዚህም የቅድመ ዓለሙ ቃል በድኅረ ዓለሙ ሥጋ ተዋሕዶ ሰው እንደ ሆነ ሊቁ ያስተምረናል፡፡

የሊቁ የቅዱስ ኤፍሬም ድርሰት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተደረሰ ስለ ሆነ ከቅዱስ መጽሐፍ ጋር አንድ የሆነ መልእክት አለው፡፡ ለምሳሌ ቅዱስ ዮሐንስ «በመጀመሪያ ቃል ነበር» እንዳለ፡፡ ሊቁም «ከዓለም በፊት የነበረው የአብ ቃል» በማለት ይከተላል፡፡ «ቃል ሥጋ ሆነ» ያለውን ደግሞ :– «የአብ ቃል ከአብ ዘንድ መጥቶ ልዩ ከሆነች እናቱ ሰው ሆነ» በማለት ወንጌላዊውን በድርሰቱ ይተባበራል፡፡ ዮሐ.1÷1፡፡ በመልእክቱም፡–«ንዜንወከሙ በእንተ ውእቱ ዘሀሎ እምቅድም፣ ውእቱ ዘሰማዕናሁ ወዘርኢናሁ በአዕይንቲነ፤ ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያ የነበረውን የሰማነውን በዐይናችንም ያየነውን...እናወራለን፡፡» ብሏል፡፡ 1ኛ.ዮሐ1÷1፡፡ ይህም «ቃል» ቀዳማዊ /ቅድመ ዓለም የነበረ/÷ ያለም የሚመጣም/ መሆኑን አጉልቶ የሚያሳይ ነው፡፡ በራእይ መጽሐፉም የቃልን ቀዳማዊነትና ደኃራዊነት፡– «አነ ውእቱ አልፋ ወዖ ይቤ እግዚአብሔር ዘሀሎ ወይሄሉ ወዘይመጽእ ዘውእቱ ይመልክ ኵሎ፤ ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ ይላል» ሲል ገልጦልናል፡፡ በዚህም ቀዳማዊነቱን ለመግለጥ አልፋ፣ደኃራዊነቱን ለመግለጥ ደግሞ ዖሜጋ /ወዖ/ ብሎ በግሪክ ፊደላት መጀመሪያና በመጨረሻ መስሎ ተናገረ፡፡ ራእ.1÷8፡፡ ከዚህም በማስከተል ዓለሙን አሳልፎ ለመኖር ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለተኛ መምጣቱን ለማስረዳት÷ የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ በማለት አስረድቷል፡፡ ቅዱስ ኤፍሬምም፡፡ «ቅድመ ዓለም የነበረው፤ ዓለምን አሳልፎ የሚኖረው ለኩነተ ሥጋ /ሰው ለመሆን/ የመጣው÷ ዳግመኛ ዓለምን ለማሳለፍ የሚመጣው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ያለመ ለወጥ ሰው ሆነ» እያለ የወንጌላዊውን መልእክትና ራእይ ያጠናክራል፡፡

ምንም እንኳ የቃልን ቀዳማዊነት ደኃራዊነትና የሁሉም ገዥ መሆኑን በዚህ መልክ ቢገልጥም ብዙዎች መናፍቃን አሁን የወልድን አምላክነት በመጠራጠር ወልድን ዕሩቅ ብእሲ /ፍጡር/ ለማድረግ ሙከራ ማድረጋቸው አልቀረም፡፡ ለእነዚህ ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም መልስ ሲሰጥ÷ ወልድ የተገኘ የአዳምን ሥጋ ቢለብስም በሥራው /በግብሩ/ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ የዐይን ጥቅሻና የንስር ክንፍ መምታት ያህል እንዳልተለየ ይገልጣል፡፡ «ከአባቱ ያልተለየ አንድ እርሱን የተሸከምሽ ሆይ ደስ ይበልሽ» ብሏል፡፡ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው ወልድ ዋሕድ /አካላዊ ቃል/ ከነሳው ሥጋ እንዳልተለየ፤ ሲገልጥ ደግሞ፡– «አንዱ ወልድ በሥራው ሁሉ አልተለየም፤ የእግዚአብሐር ቃል መለኮት አንድ ነው እንጂ» ብሏል፡፡ ወንጌላዊ ቅዱስ ዮሐንስ እንደ ገና «አልፋ ዖሜጋ» የተሰኘው የአብ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሆነ ቀዳማዊነቱን፣በፍጻሜ ዘመን ግን ስለ ሰው ልጅ ደኅንነት ሲል ሕማምን ሞትን እንደ ተቀበለ ሰፋ አድርጎ በመግለጽ ሲያስረዳ :–«ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ፤ ሞቼም ነበርሁ፤ እነሆም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፡፡» ሲል አስረድቷል፡፡ ራእ.1÷17–18፡፡ ይኸም በማያሻማ መልኩ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነቱንና ቀዳማዊነቱን የሚያስረዳ ነው፡፡ ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬምም «ኑ÷ ይህን ድንቅ እዩ፡፡ ስለ ተገለጠልን ምስጢር ምስጋና አቅርቡ፤ ሰው የማይሆን፡– ሰው ሆኖዋልና፤ ቃል ተዋሕዶዋልና፡፡ ጥንት የሌለው ሥጋ ጥንታዊ፣ ቀዳማዊ ሆነ፡፡» ይለናል፡፡ ዕብ.13÷8፡፡

በብሉይ ኪዳንም የቃል ቀዳማዊነት በስፋት ተገልጾአል፡፡ ይኸንንም በተመለከተ ነቢዩ ኢሳይያስ «ይህን የሠራና ያደረገ፤ ትውልድንም ከጥንት የጠራ ማን ነው? እኔ እግዚአብሔር÷ፊተኛው በኋለኞችም ዘንድ የምኖር እኔ ነኝ» ሲል ተናግሯል፡፡ ኢሳ.41÷4፡፡ «ማነው ይህን የሠራና ያደረገ» ያለው «ሁሉ በርሱ ሆነ፤ ያለእርሱ ግን ምንም የሆነ የለም» ከሚለው ጋር አንድ ነው፤ «እኔ እግዚአብሔር የፊተኛው ነኝ» ሲል ደግሞ «ዘመን የማይቆጠርለት መለኮት ዘመን ተቆጠረለት፤ የማይታወቅ ተገለጠ፤ የማይታይ ታየ፤ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ በርግጥ ሰው ሆነ፤ ትላንት የነበረው ዛሬም ያለው መቼም የሚኖረው ኢየሱስ ክርስቶስ እንሰግድለትና እናመሰግነው ዘንድ አንድ ባሕርይ ነው፡፡» ከሚለው ከቅዱስ ኤፍሬም ድርሰት ጋር አንድ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም «ኢየሱስ ክርስቶስ ትላንትና ዛሬ እስከ ዘላለም ያው ነው፡፡» ብሏል፡፡ ኢሳ.41÷4፤ ዮሐ.1÷3፤ ዕብ.13÷8፡፡

## ያለመለወጥ ሰው መሆኑ

ሊቁ የእግዚአብሔርን ቸርነት ሲገልጽ፡– «ልዑል ክንዱን ሰደደልን» ካለ በኋላ፡፡ «ቅድመ ዓለም የነበረው ዓለሙን አሳልፎ የሚኖር ከአንቺ ዛሬ ሰው ሆነ፡፡» ብሏል፡፡ ሰው የሆነው አካሉ ባሕርዩ ተለውጦ አይደለም፡፡ አካሉ ባሕርይው ሳይለውጥ ሰው ሆነ፤ «ኮነ» ሊላውን ግስ አፍርሶ የሚገባ ግስ ስለሆነ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ «ኮነ» ሊላውን አፍርሶ የሚመጣ ስለ ሆነ እንዳለ ሆኖ አያውቅም፡፡ «ኮነ» የሚለው ግስ ውሳጤን ሊያመጣ ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡–የሎጥ ሚስት «ሐውልተ ፄው» /የጨው ሐውልት/ ሆናለች፡፡ ይኸውም የጨ ሐውልት ወደ መሆን ተለወጠች ያሰኛል፡፡ ምክንያቱም ቀድሞ የነበራት የሰውነት ባሕርይ ወደ ጨው ተለውጧል፡፡ ሊቁ ግን ከሎጥ ሚስትና ከሌ ሎች በእግዚአብሔር ተአምራት ከተለወጡ ነገሮች ሲለየው «ያለ መለወጥ ከአንቺ ሰው ሆነ» ይለናል፡፡

ምክንያቱም የሎጥ ሚስቱ በራሷ ኃይል የላትም፡፡ ሁሉ ነገር የማይሳነው አምላክ በፈቃዱ የፈለገውን መሆን ስለሚችል በፈቃዱ ባለ መለወጥ ሰው ሆኗል፡፡ ስለዚህ «ቅድመ ዓለም የነበረው ዓለምን አሳልፎ የሚኖረው ቃል ከአንቺ ያለ መለወጥ ሰው ሆነ፡፡» በማለት ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ቢሆንም ባለመለወጥ ሰው የሆነ አምላክ መሆኑን ያስረግጣል፡፡

ከላይ «ከድንግል በሥጋ ያለ ወንድ ዘር ተወለደ» ብሎ ነበር፡፡ ደግሞ «ሰው ሆነ» ሲል «ያለ መለወጥ» አለ፡፡ በዚህም ሲፀነስ ያለ ወንድ ዘር÷ ሰው ሲሆንም ያለ መለወጥ እንደ ሆነ እማኝነት ይሰጠናል፡፡ «ኢተበአደ ወኢተፈልጠ በኵሉ ግብሩ፤ አንዱ ወልድ በሥራው ሁሉ አልተለየም፡፡» ሰው ስለሆነ ሰውነቱ የአምላክነቱን ሥራ አልከለከለውም፡፡ አምላክነቱም ሰው የሆነበትን ሥራ አልከለከለውም፡፡ ሁሉም አንድ ግብር አንድ ሥራ ሆነ፡፡

**ይቀጥላል፡፡**



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የቃና ዘገሊላ ተአምር በአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ድርሰት /መጽሐፈ ምሥጢር/

በስመ ሥሉስ ቅዱስ የማይገኝ ልዑል፣ የማይታይ ኅቡዕ፣ በአንድነት በሦስትነት ጸንቶ በሚኖር በእግዚአብሔር ስም፣ የማይነኩት እሳት፣የማይዳስሱት መንፈስ፣የማያስተውሉት ኃይል የማይሾሙት ንጉሥ ነው:: በመለኮቱ አምላካችን፣ በቸርነቱ አባታችን ለሆነ ለእርሱ ለዘላለም ምስጋና ይገባል:: አሜን::

«የመለኮት ቃል ሥጋ፣ ደም፣ ዐፅም፣ፀጉርና ደም ሥር ወደ መሆን ተለወጠ» የሚሉ የዝንጉአንን ዘለፋ እንጽፋለን:: እናንተ ሰነፎች! የመለኮት ኃይል ሥጋ ወደ መሆን÷ ትስብእትም መለኮት ወደ መሆን እንደ ተለወጠ ይመስላችኋል? የሎጥ ሚስት የጨው ሐውልት እንደ ሆነች አይደለም:: የከለዳውያን ንጉሥ ናቡከደነፆር የዱር አውሬ እንደ ሆነ ዳግመኛ ሰው ወደ መሆን እንደ ተመለሰ አይደለም:: የቃና ውኃ ወይን እንደ ሆነ አይደለም:: እነዚህ ሦስቱም ከህልውናቸው ተለውጠዋል:: በፈቃደ እግዚአብሔር እንጂ በፈቃዳቸው አይደለም:: የሎጥ ሚስት ወደ ሰዶምና ገሞራ ዞራ እንዳት መለከት ያዘዛትን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመተላለፏ የጨው ሐውልት ሆነች:: ሰዶምን ለመመልከት በተመለሰች ጊዜ እንደ ምድጃ መጨሷን ተመለከተች:: ከዚህ በኋላ ፍጹም የጨው ሐውልት ሆነች:: ለማሽተት እስትንፋስ ለመንቀሳቀስ ነፍስ አልነበራትም:: እግዚአብሔር ድንጋይ አድርጓት ወደ ሐውልነት ተለውጣለችና ንጉሥ ናቡከደነፆር ልቡናውን አሳብዮ አልና የምድር አውሬ ሆነ:: እርሱ በሥልጣኑ የዓለም ጌታ እንደ ሆነ አስቦ በአጽናፈ ዓለም ሁሉንም ሥልጣንና ማሸነፍን ለሰጠው እግዚአብሔር አልተገዛም:: ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር የምድር አውሬ አደረ ገው:: በአውሬነት አስቀምጦ በማ መላለስ ገሠጸው:: የአራዊት ፀጉርና የእንስሳ ጥፍር አደረገለት እንጂ የሰው ልጅ ፀጉርና ጥፍር አላስቀረለትም:: ከአራያዎች ጋር ተሰማርቶ ሣር እየበላ በገዳም ውስጥ ሰባት ዓመት ተቀመጠ፤ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይበቀላ ልና:: ዳግመኛ እግዚአብሔር ኅሊናውን ሰውን ወደ ማስተዋል መልኩንም እንደ ሰው ልጅ መልክ መልሶ በመንግሥቱ አስቀመጠው:: እግዚአብሔር ለተነሳሒያን ይቅር ባይ ነውና ከዚህ በኋላ እርሱም ለእግዚአብሔር ክብር ተገዛ:: የመንግሥትና የነገሥታት ጌታ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ዐወቀ::

ወይን የሆነ የቃና ውኃም በወይን መርገጫ ረግጠው በመጭመቂያ ውስጥ ጠምቀው የሠሩት የልማድ ወይን አይደለም:: ሙሽራው እንዳያፍር÷ ሰርገኞችም እንዲረኩ የእግዚአብሔር ልጅ የተአምር ወይን ነው እንጂ:: የጌታችን እናት:- የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም፤ ወይናቸው አልቆአልና ይህንን አቅልል÷ ብላዋለችና ጌታችን «ኢየሱስ አንቺ ሆይ÷ ምን ትያለሽ? ጊዜዬ ገና አልደረሰም» አላት:: በልቡ ውስጥ የተጻፈ ፍቅሯ የሚሻለውን መለሰ:: እሷ ስለ ምድራዊ ወይን ማለደችው:: እርሱም አመስጥሮ ከጐኑ ስለሚቀዳው ወይነ ደሙ ተናገረ:: «ጊዜዬ ገና አልደረሰም» ማለቱ ግን «ከጐኔ በሚፈሰው በምሥጢር ወይን ምእመናንን አረካቸው ዘንድ በጦር የምወጋበት ሰዓት አልደረሰም» በሚለው ይተረጐማል:: ከኃጥአን ጋር በመቀመጥ፣ በመዳሰስ ከአንቺ በነሳሁት ሥጋ ረኀብና ጥምን ማንኛውንም መከራ በመቀበል የአባቴን ተአምራት በምድር ላይ አሳይ ዘንድ ሦስት ዓመታት ቀርተውኛልና:: ከላይ ስለ ተናገረው ስለ ተአምራቱ ወይን ይህንን አለ:: እኔም ጊዜው ደርሶ ሥራውን አላዘገየም እለዋለሁ:: ያን ጊዜ ውኃ ቀድተው በስድስት የደንጊይ ጋኖች ይሞሉ ዘንድ አዘዘ:: ወደ ወይንነት ተለወጠ:: ውኃውን ወደ ወይን የለወጡት እንስሮች አይደሉም:: ውኃውን ወደ እንስሮች ይሞሉት ዘንድ ያዘዘው ውኃውን ወይን ወደ መሆን መለሰው እንጂ:: እንስሮች ግን እነርሱ ውኃውን ወይን ወደ መሆን የመለሱት አይደለም:: አይሁድ ዘወትር ሁለትና ሦስት እንሥራ በሚይዙ ጋኖችን የሚጠምቁ አይደሉምን? የቃና ወይን በሕገ ኦሪት ተመስላለች:: የጠጧትን አላጸደቃቻቸውም፤ ነገር ግን በመዓዛዋ ጣዕም ልባቸውን አስደሰተች:: እንደዚሁም ኦሪት አስቀድመው የተቀበሏትን አላጸደቀቻቸውም፤ በመም ጣቷ ልቡናቸውን አስደስታለች:: የእግዚአብሔር ቃል ናትና:: ስለዚህ ጳውሎስ በሕገ ኦሪት መጽደቅ በተሳናቸው ጊዜ በኦሪት ያሉትን ወደ ወንጌል ይመልሳቸው ዘንድ እግዚአብሔር «ከሴት የተወለደ ልጁን ላከ» አለ::

ውኃው በቃና ወይን ወደ መሆን እንደ ተለወጠ÷ እንደዚሁ ሙሴ ፈርቶ ከፊቱ እስከሚሸሽ ድረስ የሙሴ በትር በደብረ ኮሬብ እባብ ወደ መሆን ተመልሷል:: ዳግመኛ ሙሴ እስከሚያጐነብስ በትር ወደ መሆን ተመልሷል:: ሙሴ በትሩን አንሥቶ በፈርዖንና በመኳንንቱ ፊት በዚያ በትር ተአምራት አድርጓል:: የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወይነ ደሙ በሕገ ወንጌል ተመስሏል:: አውሬ ማድረግና መጽደቅ ችሏልና::

መድኃኒታችን «ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነው» ብሏልና:: ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ በእኔ ይኖራል:: ሞትንም አይቀምስም::» ስለ ወንጌልም «ያመነ የተጠመቀ ይድናል÷ ያላመነ ግን ይፈረድበታል» አለ::

እመ አምላክ ከልጇ ዘንድ ወይን ወደ ፈለገችበት ዜና እንመለስ:: «የወይን ጠጅ የላቸውም÷ ወይን አልቆባቸዋልና፤» ስትል ስለ ምን ለመነችው? ከውኃ ወይንን ይቀዳ ዘንድ ዐውቃ /ተረድታ/ ይሆንን? ከዚያ ሰዓት በፊት እንደዚህ አላደረገምና:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን የተአምራት መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ፤ ክብሩንም ገለጠ:: «ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ» ብሏል:: ዮሐንስ ወንጌላዊው እንደ ተናገረ ውኃውን ወደ ወይን እንደሚለውጠው ድንግል አላወቀችምን? ነገር ግን በአብ ጽላሎት እንደ ፀነሰች፣ በልዑል ኃይል እንደ ወለደችው ታውቃለች:: ስለዚህ ድንግል ስለ ወይን ትማልደው ዘንድ ደፈረች:: አባቱ ሰማያዊ እንደ ሆነ ካበሠራት መልአክ ዘንድ ተረድታለችና /ተገንዝባለችና/:: ስለዚህ በልቧ «እስመ ወልዱ ለገባሬ መንክራት ይገብር መንክረ ከመ አቡሁ፤ የተአምራት አድራጊ ልጅ እንደ አባቱ ተአምራትን ያደርጋል፤» አለች:: ደቀ መዛሙርቱ ግን ስለ ወይን አልማለዱትም፤ አባቱን አያውቁምና እርሱ የዮሴፍ ልጅ ይመስላቸዋል:: መልአኩ ለእናቱ እንደ ተናገረ ለእነ ርሱ አልነገራቸውምና:: ተአምራትም ካደረገ በኋላ ከነቢያት አንዱ እንደ ሆነ እንጂ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አላመኑትም:: ስለዚህ በፊልጶስ ቂሣርያ ሀገር:- ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደ ሆነ ይሉታል? ብሎ ጠየቃቸው:: እነርሱም:- መጥምቁ ዮሐንስ፣ ሌሎችም ኤልያስ፣ ሌሎችም ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ አሉት:: እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው:: ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ:- «አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ::» ቅዱስ ጴጥሮስ ከወልድ ጋር በፊልጶስ ቂሣሪያ አገር ሲነጋገር የቅዱስ ጴጥሮስ ልቡና ድንገት



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በመንፈስ ቅዱስ ክንፎች ከአብ ህልውና ደርሶ ተነጠቀ /ተመሰጠ/:: በዚያም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በአብ ቀኝ ተቀምጦ አገኘው:: ስለዚህ «አንተ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ» አለው:: እርሱም ሥጋና ደም እንዳልገለጠለት ምስክር ሆነለት:: «በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና:: ብፁዕ ነህ» አለው:: ቅዱስ ጴጥሮስ ከመንፈስ ቅዱስ ዘንድ ተመርቶ ከአብ ዘንድ ልቡናን አግኝቶ ከወልድ ዘንድ ኤጲስ ቆጶስነትን ተሾመ:: «እኔም እልሃለሁ÷ አንተ ጴጥሮስ ነህ፤ በዚህችም አለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ:: የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም::» አለው::

«የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤ በምድር የምታስረው በሰማያት የታሰረ ይሆናል፤ በምድር የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል::» ስለዚህ ደቀ መዛሙርቱ ከነቢያት አንዱ እንደሆነ ልቡናቸው እየተዛባባቸው እንጂ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አምነውበት እንዳልተከተሉት ዐወቁ /ተረዱ/:: የመለኮት ትስብእት ግን ከቅድስት ድንግል ማርያም፣የሎጥ ሚስት የጨው ሐውልት እንደ ሆነች ሙሴ በመመልከቱ እስከሚሸሽ ድረስ የሙሴ በትር እባብ እንደ ሆነች ዳግመኛ ጭራውን በመያዝ እስከሚያነሣ ድረስ እባቡ በትር ወደ መሆን እንደ ተመለሰ በመለወጥ አይደለም:: ዳግመኛ የመለኮት ትስብእት የጌታችን ህልውና የልማድ ኃይል ወደ መሆን አልተመለሰም /አልተለወጠም/:: ዳግመኛ የቃና ዘገሊላ ውኃ ወደ ወይን እንደ ተለወጠ አልተለወጠም:: በመለኮት ኃይል ሰው ለመሆን ቢለወጥ ኑሮ ያለ ሩካቤ ባልተጸነሰ ነበር:: ትስብእት መለኮት ወደ መሆን ተለውጦ ቢሆን በድንግልና ተጸንሶ ቀስ በቀስ አድጐ ባልታየ ነበር:: ዳግመኛ መለኰት ሰው ወደ መሆን ተለውጦ ቢሆን በድንግልና ተጸንሶ ቀስ በቀስ አድጐ ባልታየ ነበር::. ዳግመኛ መለኰት ሰው ወደ መሆን ተለውጦ ቢሆን ከድንግል ማኅፀን በድንግልና ባልተወለደ:: ትስብእት መለኮት ወደ መሆን ቢለወጥ በክንድ ባልታቀፈ÷ በሰሎሜ እጅ ባልተዳሰሰ:: ዳግመኛ ግን የመለኮት ኃይል ሰው ለመሆን ቢለወጥ ከድንግል ጡቶች ወተትን ባለመነ ነበር:: ዳግመኛ የመለኮት ኃይል ሰው ለመሆን ቢለወጥ ግን ኮከብ /የልደቱን ምልክት/ ለሰብአ ሰገል ባላሳያቸው ነበር፤ ከዚህ አስቀድሞ የውሉደ ሥጋ መጀመሪያ በሆነ በቃየን ልደት፣ ወይም በእስራኤል በመንግሥ ቀዳማውያን በሚሆኑ በሳዖልና በዳዊት ልደት እንደዚህ አልታየምና:: ዳግመኛም የመለኰት ኃይል ሰው ለመሆን ተለውጦ ቢሆን ግን በሕፃናት ሥርዓት በበረት ተኝቶ ለእረኞች ባልታየ ነበር:: ዳግመኛ መለኮት ሰው ለመሆን ተለውጦ ቢሆን ስለ ራሱ:- «አብርሃም ሳይወለድ እኔ ነበርኩ» ባላለ ነበር:: ዳግመኛ ትስብእት መለኰት ለመሆን ተለውጦ ቢሆን ቀስ በቀስ ባላደገ ÷ በሰው መጠንም ባልጐ ለመሰ ነበር:: ዳግመኛ የመለኮት ኃይል ሰው ለመሆን ተለውጦ ቢሆን በቃና ዘገሊላ ውኃውን ወይን ባላደረገ ነበር፤ ትስብእት መለኰትን ለመሆን ተለውጦ ቢሆን ሳምራዊቷን ውኃ አጠጭኝ ባላለ ነበር:: ዳግመኛም አይሁድ በዕፀ መስቀል ላይ በሰቀሉት ጊዜ በመስቀል ላይ ተጠማሁ ባለለ ነበር:: ዳግመኛ የመለኮት ኃይል ሰው ወደ መሆን ተለውጦ ቢሆን ግን ሞትን ባልቀመሰ ነበር:: ሞትን ቀምሶ ቢሆን የሰማይ ጠፈር በፈረሰ÷ የምድርም መሠረት በተበተነ ነበር:: ዓለምን የያዘው የመለኮት ኃይል ነውና:: ትስብእት መለኰት ለመሆን ተለውጦ ቢሆን ለሰቃልያን ባልተያዘ፣ የመስቀልንም ሃፍረት ባልታገሠ ነበር:: መለኰት አይዳሰስም፤ በዐይንም አይታይም፤ ለልብም አይገኝም:: ዳግመኛ የመለኰት ኃይል ሰው ለመሆን ተለውጦ ቢሆን ግን:- «ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፤ በሦስት ቀን አስነሣዋለሁ» ባላለ ነበር:: ትስብእት መለኮት ለመሆን ተለውጦ ቢሆን ሕማምንና ሞትን ባልተቀበለ ነበር:: «ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት» ያለው «እኔ በሦስት ቀን አነሣዋለሁ» ብሏልና:: እነሆ በተዋሕዶ ሞቶ የተነሣ ባለመለወጥ የተጠበቀ ባለ መጨመር አንድ የሆነ÷ ባለ መለየት በአንድ÷ እርሱ በተዋሕዶ የተነሣው በአንድ መልክ ወደ ሰማያት አርጐ በአንድ አካል በአባቱ ቀኝ ተቀመጠ:: ስለ እርሱ «ከፊታችን ለዐረገው በመለያየት ለትስብእቱ÷ ለፈጠረን ለመለኮቱ እንሰግዳለን» ይባል ዘንድ አይቻልም:: ለኢየሱስ ክርስቶስ ሰግደን እንገዛለን ይባላል እንጂ:: ለእርሱ ለዘላለም ምስጋና ይሁን:: አሜን::

«የመለኮት ቃል ወደ ትስብእት÷ ትስብእት ወደ መለኮት ተለወጠ» የሚሉ ዘለፋቸው ተፈጸመ:: እነርሱ የሐሰት መዛግብት ናቸው:: ከአጋንንት ይከፋሉ፤ ከውሻም ይረክሳሉ:: ሃይማኖቱ የጸና ጊዮርጊስ ይህንን ተናገረ:: በሥርዓት ደም የተቀደሳችሁ ለኃጢአቱ ስርየትን ለምኑለት:: ለዘላለሙ አሜን::

## ሥርዓቱን ከልማዱ ለይታችሁ ...

/ከገጽ ፱ የዞረ/

- ኅብስቱንና ወይኑን ለመለወጥ፣ በክርስትና ጥምቀት ጊዜ ውኃውን ወደ ማየ ገቦነት ለመለወጥ ነው::

የቅዳሴ ጠበል የአምልኮት ማዕከል የሆነው ጸሎተ ቅዳሴ የደረሰበት በመሆኑ ከሌሎች ጠበላት በእጅጉ የከበረ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል:: ስለዚህም ጠበሉ መሬት ላይ ፈስሶ እንዳይረገጥ በመጠጫ አልያም በእጃችን ተቀብለን መሬት ላይ ሳናፈስ መጠጣት፣ የታመመ የሰውነት ክፍላችንን መቀባት መይም ማሻሸት የሚቻል ነው:: የታመመ ሰው ቢኖርና ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ፈጽሞ ባይችል ጠበሉን በዕቃ ወደ ቤት ወስዶ እንዲጠጣና ሰውነቱንም እንዲያሻሽ ማድረግም ይቻላል:: የቅዳሴ ጠበልን እንደ "ማየ ጸሎት" በየቤቱና በአጥር ጥግ መርጨቱ ግን አግባብ አይደለም:: ቅዳሴ ጠበልን የሚያድሉ ዲያቆናት ሕዝቡን ለማዳረስ ባይችሉ የደንብ ልብስ የለበሱ ወንዶች የሰንበት ት/ቤት አባላት ጠበሉን በማደል ሊራዱ ይችላሉ:: ይህንን ማድረጉ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን መጣስ አይሆንም::

በቅዳሴ ጠበል ዙሪያ በብዙ አድባራት የሚታይ የጋራ ችግር አለ:: ይኸውም «አሜን» እንደ ተባለ ዲያቆናቱ ትምህርተ ወንጌልና ቡራኬ ሳይሰጥ ለሕዝቡ ጠበል ስለሚሰጡ ጫጫታና ግፊያ ተፈጥሮ የሚሰጠው ትምህርተ ወንጌል እንዳይደመጥ ተጽዕኖ ያደር ጋል:: ስለዚህ የሰበካ መንፈሳውያን አስተዳደር ጉባኤያት ለትምህርተ ወንጌል ትኩረት በመስጠት የቅዳሴ ጠበሉ ከትምህርቱ በኋላ እንዲሰጥ ቢያደርጉ መልካም ነው::

<u>የግርጌ ማስታወሻ</u>:-


1.የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ንባቡና ትርጓሜው÷፩ መልእክት ኀበ ሰብአ ቆሮንቶስ÷ ገጽ 166-167::
2. ፍትሐ ነገሥት ንባቡና ትርጓሜው÷
3.አንቀጽ13÷ቁጥር 504፣505፣512-514፣517::
4.ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው÷ ቁጥር 5-7÷ ገጽ 15-24::
5. ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ÷ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን÷ ገጽ 24፣50
6. ፍት.ነገ.ፍት.መን.አንቀጽ 13÷ ረስጠብ 47፤ በደስ 28 ረስጠብ 43::
7. ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ÷ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ÷ገጽ 50
8. ፍት.ነገ.ፍት.መን. አንቀጽ 13÷ ረስጣ 53 ኒቅያ 17፤ ረስጣ. 53 በስ. 99
9. ቅዳሴ ሐዋርያት
10. ፍት.ነገ.ፍት.መን.አን. 12÷ በስ 99
11. ፍት.ነገ.ፍት.መን.አን. 13÷ ክርስጣ 65
12 ሥንክሳር ዘወርኃ መስከረም /4/
.13.መጽሐፈ ቅዳሴ÷ሥርዓተ ቅዳሴ÷ቁጥር 166::
14.ፍት.ነገ.ፍት.መን. አንቀጽ 13÷ቁጥር 514
15 ፍት.ነገ.ፍት.መን.አን. 12÷ በደስ 17
16. ፍት.ነገ.ፍት.መን.አን. 13÷ በደስ 44
17. ፍት.ነገ.ፍት.መን.አን. 13÷ በስ 72
18. ፍትሐ ነግሥት ንባቡና ትርጓሜው÷ 1958 ዓ.ም::


ወስብሐት ለእግዚአብሔር




© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ሥርዓቱን ከልማዱ ለይታችሁ አሳውቁን

\- አንድ ሰው ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ለመቀበል ማድረግ ያለበትን ቅድመ ዝግጅት፣ ለመቀበል በቀረበ ጊዜ መፈጸም የሚገባውን ሥርዓት፣ ከተቀበለ በኋላ ከምን መጠበቅ እንዳለበት የተለያዩ ሰዎች የተለያየ ነገርን ይናገራሉ:: በዚህም ሳቢያ ብዙ ጊዜ የልማዱን ከሥርዓቱ ለይተን ለማወቅና ለመፈጸም እንቸገራለን:: ትክክለኛውን ብታሳውቁን ?

መኮንን ወጋሴ<br>
እንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም<br>
አዲስ አበባ

\- ቅዳሴ ጠበል የሚዘጋጀው ለማን ነው? አንዳንዶች ለቆራቢዎች ብቻ ነው ይላሉ፤ ሌሎችም ደግሞ ለሁሉም ሕዝበ ክርስቲያን ነው ይላሉ:: እኔ የማውቀው ቅዳሴ ጠበል ለቆረቡ ሰዎች ወዲያው እንደሚሰጥና ባስቀደሱ ምእመናን ደግሞ ከጸሎተ ቅዳሴው ፍጻሜው በኋላ እንደ ሚሰጥ ነው:: ቀዋሚውን ትምህርት ብትገልጡልን?

ቸርነት ዘውዴ<br>
ባሌ ጂሩ ደ/ፀ/ቅዱስ ሚካኤል<br>
ሰንበት ት/ቤት

\- የቅዳሴ ጠበል ከማየ ገቦ ጋር አንድ /እኩል፥ ትክክል/ ነውን? የቅዳሴ ጠበልን በእጅ አስጨምሮ መጠጣት፣ የወጩ ገላችንን መቀባት፣ በዕቃ ወደ ቤት ይዞ መግባት፣ በቤቱና በግቢው አጥር ዙሪያ መርጨት ይፈቀዳልን?

ዲ.ን ግዛቸው ወልደ ሰንበት<br>
\- እምድብር<br>
ዘሪሁን አሰፋ– ጅማ ሆስፒታል

\- አንድ ሰው ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ለመቀበል ማድረግ ያለበትን ቅድመ ዝግጅት፣ ለመቀበል በቀረበ ጊዜ መፈጸም የሚገባውን ሥርዓት፣ ከተቀበለ በኋላ ከምን መጠበቅ እንዳለበት የተለያዩ ሰዎች የተለያየ ነገርን ይናገራሉ:: በዚህም ሳቢያ ብዙ ጊዜ የልማዱን ከሥርዓቱ ለይተን ለማወቅና ለመፈጸም እንቸገራለን:: ትክክለኛውን ብታሳውቁን ?

መኮንን ወጋሴ<br>
እንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም<br>
አዲስ አበባ

በጥምቀት ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ ዳግም ተወልደን መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ /ዮሐ. 3፥5/ የተዘጋጀን ክርስቲያኖች ሕያዋን እንሆን ዘንድ ዘወትር መንፈሳዊውን መብል ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን መቀበል አለብን:: ዮሐ.6፥50-59:: ሥጋዊ መብል መጠጥ ዘወትር እንደሚያሻን ሁሉ አምላካችንንም ዘወትር እንድንሻው ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን በሚበላና በሚጠጣ ሰጥቶናል:: ዮሐ.6፥34:: ስለዚህም ምእመናን ዘወትር ከቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ የተለየ ሕይወት ሊኖረን አይገባም:: ይሁን እንጂ በተለያዩ ዘመናት በተከሰቱ ማኅበራዊ ችግሮች፣በቤተ ክርስቲያን ላይ በተነሡ የተለያዩ ፈተናዎች ምእመናን ከቅዱስ ሥጋውና ከክቡር ደሙ ለረጅም ዘመናት ርቀው በመቆየታቸው የተነሣ እንዲሁም አንዳንዶች ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ያከበርሁ መስሏቸው የግል አስተሳሰባቸውን እንደ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት በማስተላለፋቸው፥ ምእመናን በማይገባ ፍርሃት ተውጠው ከቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ርቀው ቆይተዋል:: ብዙዎች ያለ ሥጋ ወደሙ ስርየተ ኃጢአት እንዲሁም የዘላለም ሕይወት እንደማይገኝ በማመን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ቢቀበሉም የተለያዩ ትምህርቶችን በመስማታቸውና ባለማወቅ ቅድመ ቁርባን፣ጊዜ ቁርባንና ድኅረ ቁርባን ማድረግ የሚገባቸውን ዝግጅት በተመለከተ የተዘበራረቀ ነገር ሲያደርጉና የተለያዩ ጥያቄዎችን ሲያነሡ ይሰማል:: በጥያቄው እንደ ተመለከትነው ቅዳሴ ጠበልን በተመለከተም ከምንነቱ ጀምሮ እስከ አገልግሎቱ ድረስ ያለው ግንዛቤ ልዩ ልዩ ነው:: ስለዚህም በዚህ እትማችን ጥያቄዎቹን በማንሣት ብዙም ወደ ዝርዝር መግባት ሳያስፈልግ ከቤተ ክርስቲያን የሥርዓት መጻሕፍት አንጻር ትክክለኛውንና መሠረታዊ የኾነውን ትምህርት ብቻ ይዘን ቀርበናል::

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በቀዳማዊ ቆሮንቶስ መልእክቱ ምዕ.11፥26:– «ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት:: ሰው ግን ራሱን ይፈትን:: እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ፤ ከጽዋውም ይጠጣ፤ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና፥ ይጠጣልምና::» በማለት እንዴት ወደ ቅዱስ ቁርባን መቅረብ እንዳለብን ተናግሯል:: ስለዚህ ወደ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ የሚቀርቡ አስቀድመው ራሳቸውን በንስሐ ሊፈትኑ ይገባል:: ከኃጢአት ሳይነጹ፣ ከበደል ሳይርቁ መቀበሉ ታላቅ ፍዳን ያመጣል:: ሐዋርያው «እንዘ ኢይደልዎ፤ ሳይገባው፤» በማለት የተናገረው ኃይለ ቃል ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን መቀበል የሚገባቸውና የማይገባቸው ሰዎች መኖራቸውን ይጠቁመናል/1/:: ስለዚህም ወደ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ቀርበው መቀበል የሚገባ ቸው እነማን ናቸው ቢሉ:–

1. ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን የሚፈጽሙ ቀሳውስትና ዲያቆናት፤
2. በጥምቀት ልጅነትን ገንዘብ ያደረጉ ምእመናን፤
3. በንስሐ ሕይወት ተወስነው ያሉ፤ ቀኖናቸውን ሳይፈጽሙ ለሞት የሚያበቃ ደዌ የታመሙ፤ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሚፈጽሙላቸው ምእመናንና ምእመናት ሁሉ ናቸው:: አንድም ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት ወይኑ ተለውጦ ደመ መለኮት መሆኑን፣ የዘላለም ሕይወት እንደሚሰጣቸው፤ ደዌ ሥጋን፣ደዌ ነፍስን እንደሚያርቅላቸው አምነው የቀረቡ ምእመናን ሊቀበሉ ይገባል:: አንድም ወደ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ የሚቀርቡት አስቀድመው ሥጋወደሙን ለምን እንደሚቀበሉ፣ምን ብለው እንደሚቀበሉ እና እንዴት መቀበል እንዳለባቸው የተረዱ ናቸው:: የሥጋወደሙ ክብርና ሕይወትነት ሳይገባቸው የሚቀበሉ ቢኖሩ ዕዳ አለባቸው:: ስለዚህ የሚቀበሉ አስቀድመው ራሳቸውን መፈተን፥ እንዲሁም የሥጋወደሙን ክብርና ሕይወትነት መረዳት ይኖርባቸዋል::

ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ የማይገባቸው እነማን ናቸው ቢሉ:–1. ኢአማንያን፤ 2/ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ተወግዘው የተለዩ ሰዎች፤ 3/ ንስሐ ያልገቡ ሰዎች፤ 4/ የቅዳሴ ጸሎት ሲጀመር ያልነበሩ ሰዎች፤ 5/ ሕልመ ሌሊት /ዝንየት/ ያገኛቸው ወንዶችና በወር ግዳጅ /በወር አበባ/ ላይ ያሉ ሴቶች ናቸው:: ርኩስ መንፈስ ቢያድርበትም ሰው የማይሳደብ፣ ከጣለው በኋላ የማያስላግገው /አረፋ የማያስደፍቀው፥የማያስተፋው/ በበዓል፣ በበዓል ሥጋውን ደሙን ሊያቀብሉት ይገባል:: /2/::

## ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን መቼ መቀበል አለብን?

ምእመናን ዕድሜና የጾታ ልዩነት ሳይገድባቸው በየጊዜው ሥጋወደሙን ሊቀበሉ ይገባል:: ቁም ነገሩ የዕድሜ ጉዳይ ሳይሆን የንጽሕና /ተዘጋጅቶ የመቅረብ/ ነው:: <ንጹሕ ያልሆነ ግን አይቅረብ> እንዲል:: ምእመናን ልጅነትን ለማግኘት በተጠመቁበት ዕለት፣ጋብቻቸውን በሥርዓተ ተክሊል በሚፈጽሙበት ዕለት፣ ወንዶች ሥልጣነ ክህነት በተቀበሉበት ዕለት፣ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን መቀበል አለባቸው:: ቅዱስ ሥጋው ክቡር ደሙ የምሥጢራት ሁሉ ጉልላት፣የአገልግሎት ሁሉ መደምደሚያ በመሆኑ ሁላችንም ከመቀበል ቸል ማለት አይገባንም:: አማንያን ሁሉ ቢያንስ በዐበይትና በንዑሳን በዓላት መቀበል አለባቸው:: ለሥጋችን ብርታትንና ንጽሕናን÷ ለነፍሳችን ድኅነትንና ዕረፍትን ገንዘብ የምናደርግበት አምላካዊ ስጦታ በመሆኑ በሕይወት ዘመናችን ከሥጋወደሙ ልንርቅ አይገባም:: ዘወትር «ነጋ ለኪዳን፣መሸ ለቁርባን» በማለት ወደ ቤተ ክርስቲያን ልንገሠግሥ ይገባል:: ወደ ቤተ ክርስቲያን መገሥገሣችንም ሥጋወደሙን ልንቀበል እንጂ ሲቀበሉ አይቶ ለመምጣት አይደለም:: ቅዱሳን ሐዋርያት በሲኖ



© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ዶሶቸው ፡- «በቅዳሴ ጊዜ ከምእመናን ወገን ወደ ቤተ ክርስቲያን የገባ ሰው ቢኖር ቅዱሳት መጻሕፍትን ሰምቶ የቅዳሴውን ጸሎት እስኪጨርሱ ባይታገሥ፣ ከቁርባንም ባይቀበል፣ ከቤተ ክርስቲያን ይለይ፡፡ የእግዚአብሔርን ሕግ አፍርሷልና፣ የነፍስና የሥጋ ንጉሥ በሚሆን በሰማያዊ ንጉሥ ፊት መቆምንም አቃሏልና፡፡ ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው እንዲህ አስተማሩን፡፡» በማለት ሥጋወደሙን የማይቀበል ሰው ከምእመናን እንዲለይ አዝዘዋል፡፡ /3/፡፡

**ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ለመቀበል የሚያስፈልገው ዝግጅት ምንድን ነው? ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን በምንቀበልበትና ከተቀበልን በኋላ ባሉት ጊዜያትስ መፈጸም የማይገባን ምንድን ነው?**

ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን መቀበላችን ለመፈራረጃና ለመወቃቀሻ ሳይሆን ለሥጋችን መጠገኛ፣ለነፍሳችን መዳኛ ይሆን ዘንድ በአትሕቶ ርእስ፣ በምክረ ካህን፣በፈቃደ ካህን ራሳችንን አንጽተን መቅረብ አለብን፡፡ ንጽሕና ሁለት ወገን ነው፡፡ አንደኛው በሃይማኖት መቅረብ ማለትም -ሥጋውን ደሙን በመቀበል ስርየተ ኃጢአት አገኛለሁ፣ የልቡናዬ ተምኔት ይፈጸምልኛል፣ በማለት በፍጹም እምነት መቅረብ ሲሆን ሁለተኛው ወገን ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ጸጋ፣ የወዲያኛውን ዓለም የሚያዩበት፣ ድንቅ ምሥጢርን የሚረዱበት ሀብት ነው፡፡ ሥጋወደሙ እንደ ምድራዊ ኅብስት ብላሽ ሳይሆን እሳተ መለኮት በመሆኑ በድፍረት ለሚቀርብ ጽኑዕ፣ ከሳሽ፣እውነተኛ ፈራጅ ነው፡፡ ፍርዱ ሁለት ወገን ነው፡፡ አንደኛው ለዐመፀኞች የዐመፃቸውን ዋጋ የሚሰጥ ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ ለየዋሃን በቸርነቱ ብዛት በደልን ይቅር ብሎ በነጻ የሚያሰናብት ነው፡፡ ቅዱስ ሥጋው ክቡር ደሙም ስሙን ለሚክዱ ለዐመፀኞች የሚያቃጥል እሳት፣ ፈቃዱን ለሚያደርጉ፣መንፈሳቸውን ላቀኑ ሰዎች ደግሞ የሚያድን እሳት፣ በደልን ይቅር ባይ፣ሀብተ ፈውስን የሚሰጥ መድኃኒት ነው፡፡ ስለዚህም ወደ ሥጋወደሙ ስንቀርብ በፈታሒቱ አንጻር መሐሪነቱን፣ በመሐሪነቱ አንጻር ፈታሒነቱን ተረድተን መቅረብ አለብን፡፡ አለበለዚያ በድኅነት ፈንታ መቅሰፍት፣ በበረከት ፈንታ ገሃነመ እሳት ይደርስብናል፡፡ /4/፡፡ ወደ ቅዱስ ሥጋው ክቡር ደሙ ስንቀርብ ቅድመ ቁርባን፣ጊዜ ቁርባንና ድኅረ ቁርባን ልንፈጽመው የሚገባውን ሥርዓት ማወቅ ተገቢ በመሆኑ በሦስት ንዑሳን አርእስት ከፍለን እንመለከታለን፡፡

1.<u>ቅድመ ቁርባን</u>፡- ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ከምንቀበልበት ሰዓት አስቀድሞ ባሉት ዐሥራ ስምንት ሰዓታት ልንፈጽመው የሚገባውን ሥርዓት ያሳያል፡፡ በቅድመ ቁርባን የሚፈጸሙ ሥርዓቶች፡-

ሀ. ከሩካቤ ሥጋ መከልከል፡- ቀዳስያንና ሥጋውን ደሙን የሚቀበሉ ምእመናን በጋብቻ ተወስነው የሚኖሩ ከሆነ ሥጋወደሙን ከመቀበላቸው ከሦስት ቀናት አስቀድመው ከሩካቤ ሥጋ መከልከል አለባቸው፡፡ "ጋብቻ ክቡር መኝታውም ንጹሕ" /ዕብ.13÷4/ እንዳለ በሕግ የኾነ ሩካቤ ኃጢአት ኾኖ አይደለም፡፡ ካህኑ /አቀባዩ/ ክርስቶስን መስሎ ምእመኑም /ተቀባዩም/ ሐዋርያትን መስሎ የሚቀርብ በመሆኑ ነው፡፡ አንድም በመሠረቱ ግብሩ የሥጋ እንደ መኾኑ መጠን ስለ ሚቀበሉት ምሥጢር ክብር መንፈሳዊ ጥንቃቄ ለማድረግ ነው፡፡ /5/፡፡

ለ. በንስሐ መታደስ፡- የሚያቀብሉና የሚቀበሉ ሰዎች ከንስሐ አባታቸው ጋር መመካከርና የንስሐ አባታቸውን ፈቃድ ማግኘት አለባቸው፡፡ የበደሉትን ሳይክሱ፣ የወሰዱትን ሳይመልሱ፣ከቂም ከበቀል ሳይነጹ፣ክፉ ኅሊናን ሳያርቁ ወደ ሥጋወደሙ መቅረብ አይገባቸውም፡፡

ሐ. ለዐሥራ ስምንት ሰዓታት መጾም፡- ጌታ በምሴተ ኀሙስ በሦስት ሰዓት በአይሁድ ጭፍሮች ተይዞ እስከ ዓርብ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ለዐሥራ ስምንት ሰዓታት በፈቃዱ ጽኑዕ መከራን ተቀብሏል፡፡ ይህን ለማስታወስ ሥጋውን ደሙን የሚቀበሉ ሰዎች ለዐሥራ ስምንት ሰዓታት የተመገቡት ከሆዳቸው ጠፍቶ÷ ለአፋቸው ምሬት÷ ለሆዳቸው ባዶነት እስኪሰማቸው እንዲጾሙ ቤተ ክርስቲያን ታስተምራለች፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ ሰዎች ከጤንነት አንጻር ይህን ያህል ሰዓት መቆየት ባለመቻላቸው ሥጋወደሙን ለመቀበል ቤተ ክርስቲያን መጥተው ሲታመሙና ራሳቸውን ስተው ሲወድቁ ይታያል፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ችግር ለማቃለል ከንስሐ አባታቸው ጋር በቅድሚያ ሊማከሩበት ይገባል፡፡ "ጴጥሮስ በሁለተኛው ቀሌምንጦስ በ46ኛው አንቀጽ ጠንቅቆ ሳይጾም ማንም ማን ሥጋውን ደሙን አይቀበል፡፡ ከወንዶቹም ከሴቶቹም ወገን ምንም ምን የቀመሰ ሰው ቢኖር÷ ከቀመሰ በኋላ ሥጋውን ደሙን ቢቀበል ÷ተደፋፍሮ ይህን ቢያደርግ ለዘለዓለም ከምእመናን በውግዘት ይለይ፡፡" /6/ /7/

መ. ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ለመቀበል በተዘጋጁበት ዕለት ሰውነትን መታጠብ አይገባም፡፡ ምክንያቱም ሲታጠቡ ውኃ ወደ አፍ በቀላሉ ሊገባ ስለሚችል ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ጥርስ መፋቁም መድማትን ሊያስከትል ይችላል፡፡ ስለዚህ ሰውነትን መታጠቡ፣ጥርስ መፋቁ፣ጢም መላጨቱ ከመቀበሉ 18 ሰዓት በፊት ማድረግ፣ የሚለብሱትን ልብስ ንጹሕ አድርጎ ማዘጋጀት ይገባል፡፡

2. ጊዜ ቁርባን፡- ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ለመቀበል በቀረብንበት ጊዜ የሚፈጸምን ሥርዓት ያሳያል፡፡ ካህናቱ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ለመቀበል ድርገት ሲወርዱ ምእመናን በስግደት እጅ ሊነሡ ይገባል፡፡ ሥጋ ወደሙን ለመቀበል በየማዕርጋቸው ተሰልፈው የሚቀርቡ ምእመናን እጃቸውን በትእምርተ መስቀል አመሳቅለው፣ምእመናት ደግሞ ክንብንባቸውን ገልጠው ሊቀርቡ ይገባል፡፡ ይህም ትእምርተ ትሕትና ነው፡፡ "ሐዋርያት በመጀመሪያው ቀሌምንጦስ በ53ኛው፣ ሠለስቱ ምእት በኒቂያ በጻፉት መጽሐፍ በ17ኛው አንቀጽ... <ወይዘምሩ በጊዜ ተመጥዎ ቍርባን ኵሎሙ ምእመናን፤ በሚቀበሉበት ጊዜ ምእመናን ሁሉ ቅዱስ ሥሉስን ይጸልዩ» አሉ፡፡ ሐዋርያት በመጀመሪያው ቀሌምንጦስ በ53ኛው፤ ባስልዮስ በጻፈው መጽሐፍ በ99ኛው አንቀጽ፡ - ካህን በሚያቀብልበት ጊዜ ኃጢአታችንን ለማስተሰረይ ለኀጢአት ለሞት አሳልፎ የሰጠው የክርስቶስ ሥጋ ይህ ነው ይበል፡፡ የሚቀበልም ሰው አሜን ይበል፡፡ ዲያቆኑም ጽዋን ይዞ ደሙን የሚያቀብል ካህን ስለ እኛ የፈሰሰው የክርስቶስ ደም ይህ ነው ይበል፡፡ ደሙንም የሚቀበል ሰው ሁለት ጊዜ አሜን÷ አሜን ይበል፡፡ በፍጹም ፍርሃትና ንጽሕና ይቀበለው፡፡ ደሙን ሲቀበል ሁለት ጊዜ አሜን ማለቱ ደማዊት ነፍስን÷ ነባቢት ነፍስን ሲያይ አንድም የሥጋውን ጨምሮ ነው፡፡» /7/ /8/፡፡

ሥጋወደሙን እንደ ተቀበሉ አፋቸውን በእጃቸው ሊሸፍኑ ይገባል፡፡ ይኸውም ሥጋ ወደሙ እንዳይነጥብ ለመጠንቀቅ ነው፡፡ የተቀበሉትንም ሥጋ ወደሙን በጥናጋቸው መካከል አድርገው /በአፋቸው መካከል አዘዋውረው/ /10/ በቀስታ ወደ ጉሮሮአቸው ሊላኩት ይገባል እንጂ እንደ ምድራዊ ኅብስት በጥርሳቸው ሊያኝኩት አይገባም፡፡ በጥርሳቸው መካከልና በላን ቃቸው ተጣብቆ የቀረ እንዳይኖር የቅዳሴ ጠበል ሊጠጡ ይገባል፡፡ አንዳንድ ሰዎች አፋቸውን ለረጅም ሰዓት ይዘው መቆየት አይችሉም፡፡ ስለዚህ የሚበሉ ነገሮችን ይዘው ገብተው ከተቀበሉ በኋላ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲመገቡ ይስተዋላሉ፡፡ ይህ በጣም ትልቅ ስሕተትና ድፍረት ነው፡፡ ምክንያቱም እጃቸውን በአፋቸው ላይ እንዲያኖሩ የታዘዙት በአፋቸው ያለውን ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ከጉሮሮአቸው አጥርተው እስኪያወርዱ ድረስ አንድም ለአክብሮተ ሥጋ ወደሙ ነው፡፡

በቤተ ክርስቲያን ውስጥም አፍን ለማደፍ ዘቢብ ወይም ሌላ ማናቸውንም ነገር እንዲበሉ ሥርዓት ያስቀመጠ መጽሐፍ የለም፡፡ ቅዳሴ ጠበሉ ራሱ አፍ ማደፊያ ነው፡፡ ማየ መቁረር እንዲል፡፡ "ክርስቶዶሉ ክርስጣ በሚባል መጽሐፉ በ65ኛው አንቀጽ <ሑሩ በሰላም> ብሎ ሳያሰናብት አንድስ ስንኳ ቁርባኑን በተራ ኅብስት አያብርደው፡፡ ማየ መቁረርስ /ቅዳሴ ጠበልስ/ ብትል ማየ መቁረርስ ከአፍ እንዳይነጥብ ለቃልቆ ለማውረድ ነው፡፡" /11/፡፡

ምእመናንና ምእመናት አባቶችን አብነት ማድረግ ሲገባቸው በራሳቸው መንገድ ከሥርዓት የወጣ ነገር መፈጸም አይገባቸውም፡፡ አፋቸውን ለማደፍ የሚቻኮሉ ከሆነም ከቤተ ክርስቲያን ሲወጡ ይደርሱበታል፡፡ ቤተሰቦቻቸው ማደፊያ የሚሆን ነገር ይዘው ውጭ እንዲጠብቋቸው አልያም በእናቶች የሚታደለውን ዳቤና ንፍሮ ተቀብለው አፋቸውን ማደፍ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ይህን ዓይነቱን ስሕተት የሚፈጽሙ ሰዎች ሊታረሙ ይገባል፡፡

3. ድኅረ ቁርባን፡- ሥጋውን ደሙን ከተቀበሉበት ሰዓት ጀምሮ እስከ ሠርክ ባሉት ሰዓታትና እስከ ሦስተኛው ቀን ድረስ ባሉት ዕለታት ልንፈጽማቸው



© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

የሚገቡና የማይገቡ ነገሮችን ያሳያል:: ሥጋ ወደሙን ከተቀበሉበት ሰዓት ጀምሮ እስከ ሠርክ እጅና እግርን መታጠብ አይገባም:: ከልብስ መራቆት /ዕርቃን መሆን/ አይገባም፤ ምክንያቱም "ሥጋ ወደሙን መለኮት ተለየው" ያሰኝብናልና:: መንበርከክና ስግደትም አይገባም፤ ምክንያቱም ድካም ያስከትላልና:: አንድም "በሥጋው በደሙ ድካም አለበት" ያሰኛልና:: አንድም ወዝ ይነጥባልና:: አንድም "መንግሥተ ሰማያትን በትሩፋታችን በድካማችን አገኘን" ያሰኝብናል:: አንድም ሥጋወደሙ የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ነው:: ስለዚህም "በመንግሥተ ሰማያት ድካም አለ" ያሰኛልና ነው::

ከተቀበሉ በኋላ ምራቅ መትፋት አይገባም:: ለወጣንያን ከተቀበሉበት ሰዓት ጀምሮ ለሃያ አራት ሰዓታት፣ ለፍጹማን ደግሞ እስከ ተቻላቸው ድረስ ምራቅ ከመትፋት መከልከል አለባቸው:: ታላቁ አባት አባ መቃርዮስ የቅዱስ ሥጋውን የክቡር ደሙን ታላቅነትና ክብር ለመግለጽ ሥጋወደሙን ተቀብሎ ለስድሳ ዓመታት ምራቁን ሳይተፋ ኑሯል:: /12/::

ከተቀበሉ በኋላ መበጣት፣ መታገም፣ ጥፍርን መቁረጥ፣ጢም መላጨት አይገባም:: ምክንያቱም «ከሥጋ ወደሙ መለኮት ተለይቶታል» ያሰኝብናልና:: ሩቅ ጎዳና መሄድም ፈጽሞ አይገባም:: ድካምን ያስከትላልና:: ክርክር መግጠም፣ መጨቃጨቅ አይገባም፤ ክፉ ነገር ወደ መናገር ያደርሳልና:: ያለ መጠን መመገብ፣ በሕገ ጋብቻ ተወስነው ላሉቱም ከሁለት ቀናት አስቀድሞ ሩካቤ ሥጋ መፈጸም አይገባም:: የቆረበ ሰው ካለ መጠንቀቅ ነስር፣ ትውኪያ፣ የአካል መድማት፣ መቁሰል፣ ወደ አፍ የሚገባ እንደ ትንኝ፣ ዝንብ ቢያጋጥመው ንስሐ ሊሰጠው ስለሚገባ ለንስሐ አባቱ መናገር ይኖርበታል:: በንስሐው የተሰጠውን ቀኖና ሳይፈጽም እንደገና መቁረብ አይችልም:: /13/::

አንዳንድ ሰዎች፡- «ከተቀበሉ በኋላ እህል ሳይቀምሱ መነጋገር ወይም ተሰጥኦ መቀበል አይቻልም፤» የሚል ልማዳዊ አነጋገር ሲናገሩ ይደመጣል:: ይህ ፈጽሞ ስሕተት ነው:: በመሠረቱ ሥጋወደሙን በተቀበሉበት ሰዓት ብቻ ሳይሆን ዘወትርም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተሰጥኦን ከመቀበል÷ ቃለ እግዚአብሔርን ከመነጋገር በቀር ሌላ ነገር መጫዎወት እንደ ማይገባ የቤተ ክርስቲያን የሥርዓት መጽሐፍ ያዛል:: የሚፈልጉት ነገር ቢኖር በእጅ ጥቅሻ ማመላከት እንጂ ድምፅ አሰምቶ መነጋገሩ አግባብ አይደለም::» ማንም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ፈጽሞ አይናገር፤ ቤተ እግዚአብሔር የነገር ቦታ አይደለምና፤ ከፍርሃት ጋር የጸሎት ቦታ ነው እንጂ:: በቤተ ክርስቲያን የሚናገር ሰው ይውጣ:: በዚያን ጊዜ ሥጋውንና ደሙን አይቀበል:: » "ወንዶችና ሴቶች ምእመናንም በጸሎት ጊዜና በቍርባን ጊዜ በእግራቸው መቆም ይገባቸዋል:: ባለፈው እያመሰገኑ ለሚመጣው ስርየትን እየለመኑ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሌላ ነገር ከመናገር ይጠበቁ::» «በቅዳሴ ጊዜ የሚስቅ የሚሳለቅ ቢኖር ካህን ቢሆን ተቀብሎ ወጥቶ አንድ ሱባኤ ይቀጣ፤ ይጹም፤ ይስገድ:: ሕዝባዊ ቢሆን ሳይቀበል ያን ጊዜ ፈጥኖ ይውጣ::» /14/ /15/ /16/:: ከዚህ ውጭ ግን የተቀበሉ ሰዎች ተሰጥኦ እንዳ ይቀበሉ ወደ ውጭ ሲወጡም አፋቸውን ካደፉ በኋላ ከሰው ጋር እንዳይነጋገሩ የሚከለክል መጽሐፍ የለም:: በሌላ በኩልም ከተቀበሉ በኋላ በእጅ መጨባበጥ፣በትክሻ በመሳሳም ሰላምታ መለዋወጥና ከሌሎች ጋር በአንድ ማዕድ ተቀ ምጦ መመገብን የሚከለክል ሥርዓት የለም:: "የቆረበ ሰው የቀረበለትን ማስተረፍ የለበትም፤ ጨርሶ መብላት ጨርሶ መጠጣት አለበት" እያሉ ማስጨነቅ ተገቢ አይደለም:: ይህም "አብዝቶ ሳይ ሆን መጥኖ ይብላ" የሚለውን ሥርዓትና ትእዛዝ መጋፋት ነው:: "እርሱ በበላበት ሌላ አይብላ÷ አይጠጣ" የሚሉትና የመ ሳሰሉትም ሁሉ በዚህ መልኩ የሚታዩ ናቸው::

አንዳንዶች ሥጋወደሙን ከተቀበሉ በኋላ ብቻቸውን ወደ ቤታቸው ሲመለሱ የተለየ ችግር ሊገጥመን ይችላል ብለው ስለሚያስቡ የሚጠብቃቸው ሰው እንዲከተላቸው ይፈልጋሉ:: ለአክብሮተ ሥጋወደሙ ሰው ማስከተል የማያስነቅፍ ቢሆንም ክፉ ነገር እንዳይገጥመን በሚል የፍርሃት ስሜት የሚጠብቅ ሰው ማስከተሉ ግን ፍጹም ስሕተት ነው:: በነቢዩ ዳዊት "የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል÷ ያድናቸውማል::" /መዝ.፴፫÷፯/ ተብሎ እንደ ተጻፈ ሥጋውን ደሙን በተቀበልንበት ሰዓት ግሩማን ሠራዊተ መላእክት በዙሪያችን እንደሚከቡን ልናስብ ይገባል:: የነቢዩ ኤልሳዕ ረድእ የሶርያ ንጉሥ የሰደዳቸውን ጭፍሮች በማየቱ በፍርሃት ተሸብሮ ነበር:: ፪ነገሥ.፲÷፲፯:: ነገር ግን በዙሪያው ያሉትን እንዲያይ ውስጣዊ ዐይኖቹ ሲገለጡለትና እሳታውያን መላእክት የሚጠብቁት መሆኑን ሲመለከት ፍርሃቱ ርቆለታል:: እኛም ውስጣዊ ዐይኖቻችን ቢገለጡልን በእኛ ዘንድ ቁጥራቸው ታላቅ የሆኑ ሠራዊተ መላእክት መኖራቸውን እናስተውል ነበር:: ሰዎች እንዲጠብቁን ማስከተሉ ከእምነት ማነስ የመጣ ልማድ እንጂ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት አይደለም:: አባቶች "ሰይጣንን ሳይሆን ልማድን ፍሩ::" በማለት የሚናገሩት ልማድ ከሰይጣን በበለጠ ለቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ተቃራኒ የሆነውን ነገር ያለምንም ፍርሃት እንድንፈጽም ስለሚያስገድደን ነው:: ስለዚህ ይህን ክፉ ልማድ በብርቱ ልንቃወመው ይገባል::

## የቅዳሴ ጠበል እቁዲጠጡ የተፈቀደው ለእነማን ነው? ያልተቀበሉ ሰዎች መጠጣት ይችላሉን?

ጠበል-በተለያዩ ቅዱሳት መካናት በተአምራት የሚፈልቅ ወይም በጸሎት ታላቅ ሀብተ ፈውስ የሚያድል የተቀደሰ ውኃ ማለት ነው:: በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ጠበልን በሦስት ዓይነት መልክ እናገኛለን:: ይኸውም፡- ፩. ማየ ጸሎት፡- በጸሎት የተቀደሰ ውኃ ሲሆን፣ ካህናት በቤታችን የሚረጩት÷ ካህናትና ምእመናን ውኃ አድርገው ጸሎት ካደረሱ በኋላ "እፍ" በማለት የሚያከብሩት የጠበል ዓይነት ነው:: በግብሩ በፊታችን፣ በቤታችን... በመረጨቱ ማየ ምንዛኅ /የሚረጭ ውኃ/ ተብሎ ይጠራል::

፪. በገዳማትና በአድባራት ዐጸድና ሰበካ በቅዱሳን ስም የሚፈልቅ ጠበል፤ ፫. የቅዳሴ ጠበል፡- በጸሎተ ቅዳሴ የከበረ፣ ከሌሎች ጠበላት ሁሉ የተለየ ጠበል ነው:: ጥያቄያችን ስለ ቅዳሴ ጠበል በመሆኑ ሥጋወደሙን ከመቀበል ጋር በቅዳሴ ጠበል ዙሪያ የቀረቡልንን ጥያቄዎች ምላሽ እንዲህ እናቀርባለን::

የቅዳሴ ጠበል አገልግሎት ሥጋውን ደሙን ለተቀበሉ ምእመናን በአፋቸው ተጣብቆ ቀርቶ ወደ ውጭ እንዳይ ነጥብ ለማድረግ ነው:: ስለዚህም የተቀበሉ ሰዎች ቅዳሴ ጠበል እንዲጠጡ ይታደላቸዋል:: በተጨማሪም በተለያየ ምክንያት ሥጋውን ደሙን መቀበል ያልተቻላቸው ሰዎች ቢኖሩ ሌሎች ሲቀበሉ እያዩ ብቻ እንዳይመለሱ፣ ንስሐ ገብተው ቀኖናቸውን ጨርሰው ሥጋ ወደሙን እስኪቀበሉ ድረስ ተስፋ እንዳይቆርጡ፣ ቅዳሴ ጠበሉን እየጠጡ ከደዌ ሥጋ እየተፈወሱ እንዲቆዩ፣ ለሥጋ ወደሙ መቅድም እንዲሆናቸው የቅዳሴ ጠበል እንዲጠጡ ይፈቀድላቸዋል:: የቅዳሴ ጠበል ጥቅምን በሦስት ወገን ከፍለን ማየት እንችላለን:: ፩. ሥጋውን ደሙን ለተቀበለ፤ ፪. በደዌ ለተያዙ ሰዎች ፫. ሥጋውን ደሙን ለመቀበል ላልበቁ ነገር ግን በጸሎተ ቅዳሴው ተሳታፊ ለነበሩት ሁሉ የሚጠቅም ነው:: ይሁን እንጂ ሁሉም ቅዳሴ ጠበል የሚጠጡበት ዓላማና የሚያገኙት ጥቅም የተለያየ ነው:: /16/::

## የቅዳሴ ጠበል ክብር

አንዳንድ ሰዎች የቅዳሴ ጠበልን ከማየ ገቦ ጋር አንድ አድርገው ሲናገሩ ሌሎች ደግሞ የቅዳሴ ጠበል ክብር ከማየ ገቦ ጋር አንድ እንደ ሆነ ይናገራሉ:: በመሠረቱ ሁለቱም አስተሳሰቦች ፈጽመው የተሳሳቱ ናቸው:: ምክንያቱም ማየ ገቦ በዕለተ ዓርብ ሌንጊኖስ የተባለው ሐራዊ የጌታን ቀኝ ጎን በጦር ሲወጋው በ "ለ" ፊደል ቅርጽ ከደም ጋር የወረደ ውኃ ነው:: ማየ ገቦ ማለትም "የጎን ውሃ" ማለት ነው:: በቤተ ክርስቲያን መሠረተ እምነት ማየ ገቦ ልጅነት የምናገኝበት÷ መዝገበ ዉሉድ የተባለች አማናዊት ጥምቀት አንዲት ናት፤ አትከለስም፣ አትደገምም:: የቅዳሴ ጠበል ማየ ገቦ አይባልም፤ የምንለውም የልጅነት ጸጋ ስለማያሰጠን ነው:: የቅዳሴ ጠበል ማየ ገቦ ቢሆንማ ለሕፃናት ሀብተ ዉልድና ስመ ክርስትና ለመስጠት መጽሐፈ ክርስትና መድገሙ፣ ሥርዓተ ቅዳሴ አድርሶ ሥርዓተ ጥምቀት መፈጸሙ ባላስፈለገ ነበር:: ነገር ግን የቅዳሴ ጠበልና ማየ ገቦ ሁለት የተለያዩ ነገሮች በመሆናቸው ቤተ ክርስቲያን የተለያዩ ስያሜዎችን ሰጥታ በተለያየ ጊዜና ቦታ እንዲሰጡ ሥርዓት ሠርታለች:: ስለዚህም "የቅዳሴ ጠበልና ማየ ገቦ አንድ ናቸው::" በማለት መናገሩ ፈጽሞ የተሳሳተ በመሆኑ ሊታረም ይገባል::

/ወደ ገጽ ፱ ዞሯል /



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# «ዘማዊቷ»

እሌኒ ክፍሌ
ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ

ኅ ሀ ሊቀድ ነው፡፡ ደመናው ከፀሐይ ጋር ግብግብ የገጠመ ይመስል፣ ንጋቱን ጨለማ አልብሶታል፡፡ የወፎቹ ጩኸት እንኳ የልቅሶ ያህል ያስፈራል፡፡ ዙሪያዬን አንዳች ነገር የተጫነኝ ያህል ከብዶኛል፡፡ ከእንቅልፌ የቀሰቀሰኝ በአቅራቢያዬ ያለው ጫጫታ ነበር፡፡ ፈርቼ እጆቼን ዘርግቼ አብሮኝ ያደረውን ሰው ፈለግሁ፣ የለም፥ ተነሥቶ ሄዷል፡፡ የሰው ሁካታ አጠገቤ ደርሶ ተሰማኝ፡፡ ደንግጬ ዐይኖቼን ከፍቼ ዙሪያዬን ቃኘሁ፡፡ ያየሁትን ግን ማመን አልቻልኩም፡፡ በድንጋጤ በድን የሆንኩ መሰለኝ፡፡ ጥርሴ ተንገጫገጨብኝ፣ መሬት ሊጠርግ በሚደርሰው ቀሚሶቻቸውና ሸበጥ በሚመስለው ጫማቸው ለየኋቸው፡፡ ጻፎችና ፈሪሳውያን ናቸው፡፡ በቁጣ የሚንቀለቀሉት ዐይኖቻቸው ቁልቁል እያዩኝ ነው፡፡ «አበቃልኝ!» አልኩ እየተን ቀጠቀጥኩ፡፡ ከተኛሁ በት እየጎተቱ አውጥተው በመካከላቸው አቆሙኝ፣ አንገቴ በሃፍረት ተደፍቷል፣ ከመካከላቸው አንዱ «አንቺ ሴሰኛ! የአባታችን የሙሴን ሕግ አላከበርሽምና በድንጋይ ትወገሪ ያለሽ» አለኝ፡፡ ድምፁ ያስበረግጋል፣ ልጅ ሳለሁ ያየኋትን ሴት አስታውሼ ዐይኖቼ በእንባ ተሞሉ፡፡

በባሏ ላይ ሌላ ወንድ ይዛ ስታመነዝር የተደረሰባት ሴት ነበረች፡፡ ፈሪሳውያን ከቤት እየጎተቱ አውጥተው በአደባባይ አቆሟት፡፡ ቀሚሷ በእንግልት ብዛት ተቀዳዷል፣ ፀጉሯ ተንጨባሮ እብድ ትመስላለች፡፡ ጻፎችና ፈሪሳውያን አንዳች ትርኢት የሚያዩ ይመስል ፈሪሳውያን ከበዋታል፣ ሃፍረትና ፍርሃት ያሸማቀቀው አንገቷ ወደ መሬት ተደፍቷል፡፡ ለረጅም ጊዜ ለልመና የተዘረጉት እጆቿ ዝለው ወደ ቦታቸው ተመልሰዋል፡፡ ከንፈሮቿ ግን አሁንም አንዳች ነገር ያጉተመትማሉ፣ የሚያዳምጣት ግን አልነበረም፣ ሁሉም የራሱን ወሬ ያወራል፣ ከፊሉ «ማን ኃጢአትን ሥሪ አላት? ይገባታል፥ ይገባ ታል፥ በላት!!» እያለ ይጮኻል፡፡ ከፊሉ ምራቁን ይተፋባታል፡፡ የሰዉ ትርምስና ሁካታ ሥፍራውን ገበያ አስመስሎታል፡፡ በአንድነት የተወረወረባት ድንጋይ ፊቷን ደም አለበሰው፣ አከታትለው ሲወግሯት ግን እግሮቿ መቆም አልቻሉም፣ ተዝለ ፍልፋ በፊት ለፊቷ ተደፋች፣ ደሟም ይበልጥ ተንቀረቀረና መሬቱን አራሰው፣ ይሄኔ የብዙ ሴቶች የጩኸት ድምፅ በአንድነት ተሰማ፡፡ ፈሪሳውያን ግን እስት ንፋሷ ፀጥ ማለቱን ሲያዩ «የሙሴን ሕግ አከበርን» ብለው ፊታቸው በደስታ ተሞላ፡፡ የእነርሱ ጭካኔና የእርሷ ስቃይ ሳይረሳኝ በዐይኖቼ ፊት ተሥሎ ቀርቷል፡፡ አሁን እኔም በእርሷ ቦታ ቆሜያለሁ፡፡

ዝሙት ስፈጽም ማደሬን ፈሪሳውያን ዐውቀዋል፡፡ ፍርዴም የታወቀ ነው፣ በድንጋይ መፈርከስ፡፡ ከዚህ ስቃይ እናቴ እንኳ ልታስጥለኝ እንደማይ ቻላት ዐውቃለሁ፣ ካቀረቀርኩበት እንደ ምንም ቀና ብዬአለሁ፣ ድንጋዮች ከየአቅጣጫው መሰብሰብ ጀምረዋል፣ የእነርሱም ቁጥር ቀስ በቀስ እየጨመረ መጣ፡፡

ለነገሩ እንግዳ የኾነው በሙሉ «ምን ድን ነው?» እያለ ይጠይቃል፡፡ ፈሪሳውያን ከስድብ ጋር «አመንዝራ ናት» እያሉ ይመልሳሉ፡፡ የሚጸየፉኝ ዐይኖች በረከቱ፣ ስድባቸው አጥንቴ ድረስ ዘልቆ ተሰማኝ፡፡ ጩኸታቸው ጆሮዬን አደንቁሮታል፣ ነፍሴ የሰላም ሞትን ናፈቀች፣ ሰውነቴም እየተንቀጠቀጠ ነው፡፡ እንባዬ ግድቡን ጥሶ መውረድ ሲጀምር ግን አጠገቤ ከቆሙት ጻፎች አንዱ ኃይለኛ ጥፊ አሳረፈብኝ፡፡ ያኔ የሚንቀጠቀጡት እግሮቼ ይበልጥ ብርክ ያዛቸው፣ ተንደርድሬ እግራቸው ሥር ተደፋሁ፣ «ማሩኝ እባካችሁ፥ ማሩኝ... የዛሬን ብቻ...» በማለት ተማፀንኩ፡፡ «አትንኪን !!» ሲሉ ጮኹብኝ፡፡ ዐይኖቻቸው በንቀት ተሞልተዋል፣ እጆቻቸው የመውገሪያውን ደንጊያ ጨብጠዋል፡፡ ጭንቅላቴ በድንጋይ ሲበረቀስና ደሜ ሲንገረገር ላለማየት ዐይኖቼን ጨፈንኩ፡፡ ከተንበረከኩበት ጎትተው አንሥተው አቆሙኝ፡፡ ከኋላ የአንድ ሰው ድምፅ ተሰማኝ፡፡ «ለምን አንወግራትም፣ የሙሴን ሕግ እኮ ተላልፋለች፣» ሲል ጮኸ፡፡ ሁሉም የሚያወሩት ስለ ሙሴ ሕግ ነው፣ የሚያስተምሩትም እንዲሁ፣ እንደማይምሩኝ አረጋገጥኩ፡፡ ተስፋዬ ከውስጤ በኖ ጠፋ፡፡ ቢሆንም ለመጨረሻ ጊዜ ለመንኳቸው፡፡

«እባካችሁ አትውገሩኝ፥...ማሩኝ... ማሩኝ... ስለ እግዚአብሔር ማሩኝ!!» ከእንባ ጋር አንጋጥጬ እያየሁ ተማፀንኳቸው፡፡ በመሐል የብዙ ሰዎች ጭቅጭቅ ተሰማኝ፡፡ የልመናዬን ቃል ሰምተው አቤት የሚሉልኝ ሰዎች ይኖሩ እንደ ሆነ ልሰማቸው ጓጓሁ፡፡ ዐይኖቼ ምሕረትን ናፍቀው ዙሪያውን ተንከራተቱ፡፡ ለካስ ነገሩ ሌላ ነው፡፡ ከፊሎቹ፡-, «ከኢየሱስ ዘንድ እንውሰዳትና ስለ እርስዋ የሚለውን እንስማ» ሲሉ ከፊሎቹ ደግሞ «አይሆንም! እዚሁ እንውገራት!!» የሚሉ ነበሩ፡፡ ከብዙ ደቂቃ ጭቅጭቅ በኋላ ተስማሙ፡፡ «ወስደን እንፈትነው፣ አትውገሯት ካለ "የሙሴን ሕግ ተላለፍክ" እንለዋለን፣ "ውገሯት" ካለ ደግሞ እዚያ የተሰበሰበው ሕዝብ ሁሉ ጨካኝነቱን ይረዳል፡፡ እንውሰዳት፥ እንውሰዳት!!» ተባባሉ፡፡ እግሮቼ መንቀሳቀስ አልቻሉም፡፡ እንባዬም ልብሴን አርሶታል፡፡ ጥቂት የሚያውቁኝ ሰዎች አብረውኝ ያነባሉ፡፡ ከኋላ ወደ ፊት እየገፈተሩ፣እየሰደቡና እየረገሙኝ ከኢየሩሳሌም በስተ ምሥራቅ ወደ ምትገኘው ኢየሱስ ወደ ሚያስተምርባት ቤተ መቅደስ ማምራት ጀመርን...፡፡

ወደ ቤተ መቅደሱ ስንቃረብ የኢየሱስን ትምህርት ለመስማት የተሰበሰበው ብዙ ሕዝብ ነበር፡፡ በሽተኞችና ድሆች የቤተ መቅደሱን ዙሪያ አጣበውታል፡፡፡ በሕዝቡ መካከል እየጐተቱ አስገብተው በመካከል አቆሙኝ፡፡ ልብሶቼ ተቀዳደዋል፡፡ አንገቴን ሃፍረት ደፍቶታል፣ ኢየሱስ ማስተማሩን አቁሞ ዝም አለ፡፡ ስለ እርሱ ደግነት ብዙ ሰምቻለሁ፡፡ ድውያንን መፈወሱን፣ የተራቡትን ማብላቱን፣ ማንንም እንደ ማይንቅ የነገሩኝ ትውስ አለኝና ተስፋዬ ብልጭ አለ፡፡ ቀና ብዬ ላየው ወደድኩና አንገቴን ቀና ማድረግ ስጀምር . . . ፡ - «ዝሙት አትፈጽሙ፣ኃጢአት አትሥሩ፣ ይላል» ያሉኝን አስታውሼ መልሼ አቀረቀርኩ፡፡ የማስበውን ሁሉ የሚያውቅብኝ መሰለኝ፡፡ ወዲያው ግን ወደ ኢየሱስ ካመጡኝ አንዱ :-«መምህር ሆይ፥ ይህች ሴት ስታመነዝር ተገኝታ ተይዛለች፣ ሙሴም እንደነዚህ ያሉት እንዲወገሩ በሕግ አዘዘን፣ አንተስ ስለ እርሷ ምን ትላለህ?» ሲል ጠየቀ፡፡ መልሱን ለመስማት በሥፍራው የተሰበሰበው ሕዝብ ሁሉ በጉጉት እየጠበቀ ነው፡፡ የኔም የመኖር አሊያም የስቃይ ሞት ፍርድ በእርሱ ሆኗል፡፡ ኢየሱስ ግን ዝም አለ፡፡ ውስጥ ለውስጥ የሕዝቡ ጉርምርምታ ይሰማኛል፡፡ እንዳቀረቀርኩ ዐይኖቼን ወደ እርሱ አቀናሁ፣ በምድር ላይ በጣቱ እየጻፈ ነበር፡፡ ዝም በማለቱ ከየአቅጣጫው ብዙ ሰው ይጠይቀው ጀመር፡፡ የሚጠይቁት ጥያቄ ግን ተመሳሳይ ነበር፡፡

«መምህር ሆይ፥ ይህች ሴት አመንዝራ ናት፣ ሙሴ እንደዚህች ዓይነቷን እንድንወግራት አዝዟል፣ አንተስ ምን ትለናለህ?» የሚል ነበር፡፡ ኢየሱስም ካቀረቀረበት ቀና ብሎ ዙሪያውን ቃኘና፡- «ከእናንተ መሐል ኃጢአት የሌለበት ቢኖር አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት፣» አላቸውና እጆቹ ምድር ላይ መጻፋቸውን ቀጠሉ፡፡ ድምፁ የሚንቀጠቀጡ እግሮቼን አበረታቸው፡፡ ቢሆንም ቀና ብዬ ላየው አልደፈርኩም፡፡ ከእርሱ መልስ በኋላ የሚያጉረመርሙት በሙሉ ፀጥ አሉ፡፡ አሁን የሚያወራም የለም፡፡ «ፈሪሳውያኑ ወዴት ሄዱ?» ስል አሰብኩ፡፡ ከደቂቃ ወደ ገጽ ፳፩ ዞሯል



© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን የተጠኑ፥ የተተገበሩና በመተግበር ላይ የሚገኙ የልማት ፕሮጀክቶች አጭር ዳሰሳ



*በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ደብረ ብሥራት አቡነ ዜና ማርቆስ ገዳም የንብ ርባታ ፕሮጀክት /ከአጋፔ ቅዱስ ሚካኤል የጽዋ ማኅበር በተገኘ ድጋፍ የተተገበረ/*

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን በ1991 ዓ.ም በዳሰሳ ጥናት ባገኘው መረጃ መሠረት የቤተ ክርስቲያንን እምነትና ሥርዓት ጠብቀው ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ ከኖሩት፥ የማንነታችን መገለጫ ከሆኑት ጥንታውያት ቅዱሳት መካናት መካከል በ67% ያህሉ ውስጥ የሚገኙት መነኮሳት በከፋ ረሃብ፣ እርዛትና በሽታ እየተሰቃዩ ናቸው:: እንዲሁም ሕንፃ አብያተ ክርስቲያናቱ ከዘመን ብዛት የሚያድሳቸው ባለመገኘቱ እየፈራረሱ በውስጣቸው የሚገኙት ውድና ብርቅዬ ቅርሶች ለብልሽትና ለዝርፊያ እየተጋለጡ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል::

ይህንን ሁኔታ አስመልክቶ በቂ መረጃ ለመሰብሰብና ችግሩንም ዘለቄታ ባለው መልኩ ለመቅረፍ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን በ1991 ዓ.ም በ24 ቅዱሳት መካናት ላይ የፕሮጀክቶች ጥናት ለማድረግ እና ታሪካቸውን ለትውልድ ለማቆየት የፕሮጀክት ጥናት አዘጋጅቶ ከ1993 እስከ 1996 ዓ.ም መጨረሻ ጥናቱን አካሂዶ አጠናቋል::

ይህን የ24 ቅዱሳት መካናት የፕሮጀክት ጥናት ተግባራዊ ለማድረግ በገንዘብ ሲተመን 1,262,250 /አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ስድሳ ሁለት ሺ ሁለት መቶ ኀምሳ/ ብር ወጪ የሆን ሲሆን፥ ከዚህ ውስጥ 231,000 ብር ያህሉ ገንዘብ በአሜሪካ እና በአውሮፓ ግንኙነት ጣቢያ አማካይነት ከምእመናኑ የተሰበሰበ እና ለትራንስፖርት፥ ለውሎ አበል፥ ለቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች የዋለ ነው:: ይህን ያህል ገንዘብ ለመሰብሰብ በአሜሪካ ንዑስ ማዕከል በየቀኑ በኢ-ሜይል ቅስቀሳ ተደርጓል:: በአውሮፓ ደግሞ ይህንኑ አስመልክቶ ምእመናን በጾም ወራት የቁርሳቸውን ወጭ ለዚሁ እንዲያውሉ የሚረዳ በራሪ ወረቀት በማዘጋጀት እና በሰንበት ት/ቤቶች እና በጽዋ ማኅበራት ገለጻ በማድረግ የተሰበሰበ ነበር:: ቀሪው 1,031,250 ብር የማኅበሩ አባላት የፕሮጀክት ሰነዱን ለማዘጋጀት ያበረከቱት ሞያዊ አስተዋፅዖ ነው::

በዚህ ጥናት በዋናው ማዕከል፣ በንዑሳን እንዲሁም በወረዳ ማዕከላት የሚገኙ የማኅበሩ አባላት የሆኑ የማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መስኮች፣ የግብርና፣ የውኃ ምሕንድስና፣ የጂኦሎጂ የፋይናንስ አስተዳደርና ሌሎች ባለሞያዎችን በመስክ ሥራም ሆነ በጽ/ቤት መረጃዎችን በመተንተን እና የፕሮጀክት ሰነዶችን በማዘጋጀት ከፍተኛ አስተዋፅዖ አበርክተዋል:: በመሆኑም ይህ ፕሮጀክት ማኅበሩ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሊያበረክት የሚችለውን ሞያዊ እገዛ በስፋትና በጥልቀት በተግባር ያሳየበት ነበር ለማለት ይቻላል::

ከዚህም ባሻገር የማኅበሩ አባላት ወደ ገዳማቱ ለመድረስ ፈታኝ የሆነውን የሀገራችንን ወጣ ገባ የሆነ መልክዐ ምድር ድካም ሳያሸንፋቸው ለቀናት በእግርና በጋማ ከብት በመጓዝ ማኅበራቸው የሰጣቸውን ሓላፊነት ለመወጣት ያላቸውን ቁርጠኝነት አሳይተዋል::

የፕሮጀክት ጥናቱን ለማካሄድ በገዳማቱ ረዘም ያለ ቀናትን ተቀምጦ አስፈላጊውን መረጃ ከመሰብሰብ በተጨማሪ የፕሮጀክቱ አጠናን ዘዴ ተሳትፎአዊ የገጠር ግመታ /ተ.ገ.ግ/ ዘዴን በመጠቀም በገዳሙ ማኅበረሰብና በአካባቢው ኅብረተሰብ ተሳትፎ የተጠና ነው::

በአጠቃላይ በጥናቱ ቀደም ሲል በዳሰሳ ጥናት የተረጋገጠው ችግር ትክክለኛ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል:: ከዚህ በመቀጠል የጥናት ፕሮጀክቱ ተግባራዊ የሆነባቸውን 24ቱን ቅዱሳት መካናት እና 55 ፕሮጀክቶች ከተጠኑላቸው በአጭሩ እንመለከታለን::

## የደብረ ወገግ አሰቦት ቅድስት ሥላሴና አቡነ ሳሙኤል ገዳም

በቅድሚያ የምንመለከተው በምሥራቁ የሀገራችን ክፍል በብቸኝነት የቤተ ክርስቲያናችንን ታሪክ ሲያስመሰክር የኖረውን የደብረ ወገግ አሰቦት ቅድስት ሥላሴ እና አቡነ ሳሙኤል ገዳም ነው:: ከተመሠረተ 700 ዓመት የሆነው ይህ ገዳም በምዕራብ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት በሚኤሶ ወረዳ ልዩ ስሙ አሰቦት በሚባል በአፋርና ኢሳ በረሃማ ሸለቆ አካባቢ ይገኛል:: ገዳሙ ከ30-40 ደቂቃ በሚወስድ የእግር መንገድ ልዩነት የወንዶችና የሴቶች ገዳም አለው:: የሴቶች ገዳም ከተራራው አጋማሽ ላይ የሚገኝ ሲሆን በጻድቁ አባ ሳሙኤል ስም ይጠራል:: ከተራራው ጫፍ ላይ የሚገኘው የወንዶች ገዳም ደግሞ በቅድስት ሥላሴ ስም ተሰይሟል::

ገዳሙ እንደ ተመሠረተ የተሠራው ቤተ ክርስቲያን በግራኝ አሕመድ ወረራ ጊዜ በመጥፋቱ በ1911 ዓ.ም እንደ ገና ተቋቋመ:: ይሁን እንጂ ገዳሙ በድጋሚ በጣልያን ወረራ ዘመን ከፍተኛ ጥቃት ደረሰበት:: በወረራው ዘመን መነኮሳቱና ንዋያተ ቅድሳቱ ከፊሉ ወደ ደብረ ሊባኖስ ከፊሉ ደግሞ ወደ ሞቃዲሾ ተጓዙ:: ከነጻነት በኋላ በ1936 ዓ.ም የተረፉትን መነኮሳት እና ንዋያተ ቅድሳቱን ወደ አሰቦት ደብረ ወገግ በማምጣት ገዳሙ እንደ ገና እንዲቋቋም ተደረገ:: ይህ ገዳም ዛሬም ቢሆን በአጽራረ ቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ገባውን የተለያዩ ጥቃቶች እየደረሰበት ይገኛል::

ከዚህም በተጨማሪ ገዳሙ ከፍተኛ የሆነ የመጠጥ ውኃ ችግር ያለበት በመሆኑ መነኮሳቱ በዝናም ወቅት የሚጠራቀመውን ንጹሕ ያልሆነ የኩሬ ውኃ በመቁነን ይታደላሉ፤ ወይም የመጠጥ ውኃ ለማግኘት ከአንድ ሰዓት ያላነሰ ጊዜ በየቀኑ ይጓዛሉ:: ለገዳሙ መነኮሳት የሰውን እጅ ከማየት ያለፈ ገቢ ባለመኖሩ ገዳሙን ራሱን ለማስቻል በ1994 ዓ.ም የመጠጥ ውኃ፣ የሽመና እና የወፍጮ ፕሮጀክቶች ጥናት ተካሂዷል:: ከዚህ ውስጥ የሽመና ፕሮጀክቱ ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ ከታዕካ ነገሥት በኣታ ለማርያም ገዳም ባርኪኝ የጽዋ ማኅበር በተገኘ 23,000 ብር ድጋፍ በሴቶቹ ገዳም ተግባራዊ እየሆነ ይገኛል:: የመጠጥ ውኃ ፕሮጀክቱም በ1996 ዓ.ም መጨረሻ ላይ በአሜሪካ ከሚገኘው «ገዳመ ተክለ ሃይማኖት የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር» አስቸኳይ የወገን ነፍስ አድን ኮሚቴ በተገኘው የ124,000 ብር የገንዘብ ድጋፍ



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ሥራው በመከናወን ላይ ይገኛል::

## የዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳምና የካህናት ማሠልጠኛ

ከዚህ ከምሥራቁ ወደ መካከለኛው የሀገራችን ክፍል ስናመራ፡- የዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳምና የካህናት ማሠልጠኛን እናገኛለን:: ታላቁ የዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳምና የካህናት ማሠልጠኛ በምሥራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት ከአዲስ አበባ በስተ ደቡብ 159 ኪ.ሜ ከዝዋይ ከተማ 4.5 ኪ.ሜ÷ ርቀት ላይ ይገኛል:: ገዳሙ ከመመሥረቱ በፊት በቦታው በ1960 ዓ.ም ለካህናት ማሠልጠኛ የሚሆን ሕንፃ ተገንብቶ «የዝዋይ ካህናት ማሠልጠኛ» የሚል ስያሜ በማግኘት ለአራት ዓመታት በዲፕሎማ ደረጃ የቤተ ክርስቲያንን ደቀ መዛሙርት ሲያስመርቅ ቆይቶ በ1966 በነበረው የመንግሥት ለውጥ ማሠልጠኛው ተዘጋ:: በ1971 ዓ.ም ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሆነው ሲሾሙ ለቦታው ልዩ ትኩረት በመስጠት ከተለያዩ የመንግሥት አካላት ጋር ተደራድረው ማሠልጠኛው ለቤተ ክርስቲያን እንዲመለስ አድርገዋል:: ብፁዕነታቸው ከበጎ አድራጊዎች ርዳታ በማፈላለግና ተቋርጦ የነበረው ትምህርት እንዲቀጥል÷ በቦታውም ላይ የልማት ሥራዎችን በማከናወን ማሠልጠኛውን በገንዘብ በመደጎም ተጠናክሮ እንዲቀጥል አስችለዋል:: በተለይም ብፁዕነታቸው በወቅቱ የተማረውን ትውልድ ወደ ቤተ ክርስቲያን በማቅረብ እምነቷንና ሥርዓቷን ዐውቆ የቤተ ክርስቲያን ተረካቢ እንዲሆኑ በነበራቸው ጽኑ ፍላጎት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የነበሩ ተማሪዎችን በክረምት ወራት ወደ ማሠልጠኛው ገብተው እንዲማሩ አድርገዋል::

በ1974 ዓ.ም በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ አማካይነት ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶ የቅዱስ ገብርኤል ጽላት እንዲገባ በመደረጉ ቦታው:- «የሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳምና የካህናት ማሠልጠኛ» ተብሏል::

ገዳሙ በአሁኑ ሰዓት ወደ 72 የሚጠጉ ተማሪዎችን በማስተማር እና 130 የሚሆኑ ገዳማውያንን በማስተዳደር ላይ ይገኛል:: ለካህናት ማሠልጠኛው መተዳደሪያም ከጠቅላይ ቤተ ክህነት በዓመት አንዴ የሚደረግለት አነስተኛ ድጎማና ከእርሻ የሚገኘው ገቢ በገዳሙ ለሚኖሩ መነኮሳትና የአብነት ተማሪዎች ከዘወትር ቀለብ አልፎ ያለባቸውን የመጻሕፍትና የልብስ ችግር ለማስወገድ የሚያስችል አልሆነም:: ወደፊት ገዳሙ ካህናት ማሠልጠኛውን ለማጠናከርና ለማስፋፋት እንዲያስችል ግምቱ 93 ሺ ብር የሆነ የወተት ላምና 60 ሺ ብር የሆነ የዶሮ ርባታ አማራጭ ፕሮጀክቶች ተጠንተው ለተግባራዊነቱ የበጎ አድራጊዎችን ድጋፍ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል::

## የሳይኮ ኪዳነ ምሕረት እና የዙር አባ አቡነ አረጋዊ ገዳማት

ወደ ሰሜን ምዕራብ የሀገራችን ክፍል ስናመራ በጥናት ፕሮጀክቱ የተካተቱትን የሳይኮ ኪዳነ ምሕረት እና የዙር አባ አቡነ አረጋዊ ገዳምን እናገኛለን:: የሳይኮ ኪዳነ ምሕረት ገዳም በደቡብ ጎንደር ሀገረ ስብከት በእብናት ወረዳ በሰላማያ ሳንኮ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ልዩ ስሙ ሳይኮ ኪዳነ ምሕረት በተባለ ቦታ የሚገኝ የወንዶች የአንድነት ገዳም ነው::

በ1587 ዓ.ም የተመሠረተው ይህ ገዳም በአሁኑ ጊዜ 125 መነኮሳትና ቀሳውስት እንዲሁም ወደ 40 የሚጠጉ የአብነት ተማሪዎች ይገኙበታል:: ገዳሙ በርካታ ዐይነ ስውራንንና አካል ጉዳተኞችን አቅፎ በማስተማር ድርሻውን እየተወጣ ቢሆንም ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ከፍተኛ የድርቅ አደጋ በሚደጋገምበት ቦታ ላይ የሚገኝ በመሆኑ መነኮሳቱ በከፋ ረኀብና ውኃ ጥም እየተሰቃዩ ይገኛሉ:: የአብነት ተማሪዎቹም ቢሆኑ በአካባቢው ባለው ድርቅ ምክንያት በገዳሙ ዙሪያ ካለው ኅብረተሰብ «በእንተ ስማ ለማርያም» ብለው የዕለት ጉርሳቸውን እንኳን ማግኘት ባለመቻላቸው መምህራኑ ወንበር ለማጠፍ እየተቃረቡ ይገኛሉ:: ይህንኑ ጥንታዊ ገዳም ከደረሰበት አስከፊ ችግር ለመታደግ ግምቱ 163,570 ብር የሆነ የመጠጥ ውኃ በቅድሚያ÷ በመቀጠልም ግምቱ 25,000 ብር የሆነ የንብ ርባታ ፕሮጀክቶች የተጠኑለት ሲሆን ለተግባራዊነቱም የበጎ አድራጊዎችን ድጋፍ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል::

ከዚሁ ከደቡብ ጎንደር ሀገረ ስብከት ሳንወጣ ሌላው በጥናቱ የተካተተው ከ300 ጫማ በላይ ከፍታ ባለው በገሊላ ተራራ ላይ ጥንታዊነቱን እንደ ጠበቀ የሚገኘው የርዕሰ ገዳማት ዙር አባ አቡነ አረጋዊ ገዳም ነው:: ከተመሠረተ 1400 ዓመታት ዕድሜ ያለው ይህ ገዳም በጋይንት ወረዳ በዙር አባ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ልዩ ስሙ «ሰዓሊ» በሚባል መንደር ይገኛል:: በአባታችን በጻድቁ በአቡነ አረጋዊ የተገደመ ሲሆን ገዳሙ በሚገኝበት በገሊላ ተራራ ላይ ማኅሌታዊው ቅዱስ ያሬድ ዝማሬ መዋስዕት ከሰ·ቱኤል መልአክ ድምፅ እየተቀበለ በዜማ እየደረሰ ሲያስተምር ቆይቷል:: እስከ ዛሬም ድረስ ገዳሙ ብቸኛ የሀገራችን የዝማሬ መዋስዕት አድራሾች ማስመስከሪያ ነው:: በገዳሙ ቅዱስ ያሬድ ያስተምርበት የነበረ መቋሚያና ብዛት ያላቸው ጥንታዊና ታሪካዊ ቅርሶች ቢገኙም በዕቃ ቤት ችግር ምክንያት እነዚህ ቅርሶች እየተበላሹና የቀድሞ ውበታቸው እየጠፋ ይገኛል::

እነዚህን በተለያዩ ጊዜያት ከነገሥታቱ የተሰጡትን የማንነታችን መግለጫ ቅርሶችን በጥንቃቄ ጠብቆ ለትውልድ ለማስተላለፍ ግምቱ 573,000 ብር የሆነ የቤተ መዘክር ፕሮጀክት ሰነድ ተዘጋጅቷል:: በዚሁ ጥንታዊ ገዳም ዝማሬ መዋስዕት ለማስመስከር የሚቆዩት ተማሪዎች በአካባቢው በሚከሰተው ድርቅ ሳቢያ ቁጥራቸው እየቀነሰ መጥቷል:: ይህንን መንፈሳዊ ዩኒቨርስቲ ለትውልድ ለማስተላለፍና ተተኪ ሊቃውንትን ለማፍራት ከገቢው ተማሪዎቹን ለመደጎም የሚያስችል ግምቱ 70,000.00 የሆነ የወፍጮ ፕሮጀክት ሰነድ ተዘጋጅቶ የበጎ አድራጊዎችን ድጋፍ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል::

## የመካነ ሕይወት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም

በሰሜን ምዕራብ የሀገራችን ክፍል የተዳሰሱትን ሌሎች ገዳማት ለጊዜው አቆይተን ወደ ደቡቡ የሀገራችን ክፍል እናምራ:: በአሁኑ ጊዜ በደቡቡ የሀገራችን ክፍል ያሉት የገጠር አብያተ ክርስቲያናት በካህናት እጦት ምክንያት አገልግሎታቸውን እያቋረጡ በመዘጋት ላይ ይገኛሉ:: የአጽራረ ቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴም በአካባቢው እየጎላ በመምጣቱ ችግሮቹን ለመፍታት ያሉትን ገዳማት ማጠናከር ወሳኝነት ያለው መሆኑን ማኅበረ ቅዱሳን ያምናል:: በመሆኑም የዚህ ፕሮጀክት ጥናት ለደቡቡ እና ለምዕራቡ የሀገራችን ክፍል ትኩረት ሰጥቷል::

የመካነ ሕይወት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም በባሌ ሀገረ ስብከት ከጎባ ከተማ የ45 ደቂቃ የእግር መንገድ ወጣ ብሎ በስተ ደቡብ÷ ከማንፍሌ በስተ ሰሜን ደግሞ በባሞ ወንዝ መካከል በደን በተሸፈነ ኮረብታማ ቦታ ላይ የሚገኝ ነው:: ገዳሙ በ1979 ዓ.ም በብፁዕ አቡነ ሰላማ የተገደመ ሲሆን በውል አይታወቅ እንጂ ቅድመ ታሪክ እንደ ነበረው የሚገልጹ÷ በውስጣቸው ጽላት እንደ ነበሩ የሚነገርላቸው ጥንታውያን ዋሻዎችና በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን የተቀበሩ ዐፅሞች ቦታው ላይ ተገኝተዋል:: በሀገረ ስብከቱ ብቸኛ የሆነው ይህ ገዳም በውስጡ መነኮሳቱን ለማስተዳደር የሚያስችል ገቢ የሌለው በመሆኑ ገዳማውያኑ ለችግር ተጋልጠዋል:: ገዳሙን በዘላቂነት ራሱን ለማስቻል የወተት ላም ርባታ÷ የመሬቱ ይዞታ ጥያቄ ከተፈታ ደግሞ÷ የእርሻ ልማት ፕሮጀክት የተጠና ሲሆን ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ለማድረግ በጠቅላላ የ97 ሺ 924 ብር ድጋፍ ያስፈልጋል:: የወተት ላም ርባታውን ለመነሻነት ከአንድ የግል በጎ አድራጊ በተገኘ 35,000 ብር የገንዘብ ድጋፍ ተግባራዊ ለማድረግ ሥራው ተጀምሯል:: በአካባቢው ያለውን የካህናት ችግር ለማስወገድ፣ ገዳሙን የትምህርት ማዕከል ለማድረግ የበጎ አድራጊዎች ድጋፍ እየተጠበቀ ይገኛል:: ለዚህ ገዳም ማኅበረ ቅዱሳን ከበጎ አድራጊዎች ባገኘው ድጋፍ ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ በቦታው ለአንድ የአብነት መምህር በወር 300 ብር የገንዘብ ድጎማ በማድረግ የገዳሙ ማኅበረሰብ እንዲማሩ በማድረግ ላይ ይገኛል::

## እንቀጾ ብፁዓን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም

ወደ ደቡብ ምዕራብ ስንዘልቅ ከአዲስ አበባ 715 ኪሎ ሜትር ርቀት በጂንካ ከተማ ላይ የተቋቋመውን የእንቀጾ ብፁዓን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳምን



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

እናገኛለን፡፡ በሀገረ ስብከቱ የሚገኙት አብዛኞቹ ነዋሪዎች አርብቶ አደሮች ወይም አንድ ቦታ ተወስነው የማይኖሩ ናቸው፡፡ የክርስትና ትምህርት ያልተሰበከላቸው ከመሆኑም በተጨማሪ በተለይም በቆላማው አካባቢ ቤተ ክርስቲያን እንኳን አልተቋቋመም፡፡ በሀገረ ስብከቱ የተወሰኑ አብያተ ክርስቲያናት ያሉ ሲሆን አብዛኛዎቹ ምንም ዓይነት አገልግሎት የማይሰጥባቸው ወይም በአንድ ካህን ብቻ የሚገለገሉ ናቸው፡፡ ይህን ሕዝብ የቤተ ክርስቲያን እምነት እና ሥርዓት ተቋዳሽ ለማድረግ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሕዝቡን በሀገሩ ባሕል እና ቋንቋ ለማስተማር ጥር 7 ቀን 1992 ዓ.ም ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ እና ሊቃነ ጳጳሳት የመሠረት ድንጋይ አኑረዋል፡፡ በዚሁ መሠረት ግንቦት 1995 ዓ.ም ይህ በሀገረ ስብከቱ ብቸኛ የሆነው የአንቀጸ ብፁዓን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም እና ካህናት ማሠልጠኛ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤልያስና ሌሎች ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በተገኙበት ተመርቆ ተከፍቷል፡፡

በአሁኑ ሰዓት የገዳሙ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን፣ የተማሪዎቹ መኖሪያና ምግብ ማብሰያ ግንባታ ተጠናቆ ከየጠወረዳው የተውጣጡ የአካባቢው ተወላጆች የግብረ ዲቁና እና ቅስና ትምህርት በመማር ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህም የሀገረ ስብከቱን የአገልጋይ ካህናት እና የሰባኬ ወንጌል እጥረት ለመቀነስ ተስፋ ሰጭ ጅምር እንደ ሆነ ይታመናል፡፡ የካህናት ማሠልጠኛው ከጠቅላይ ቤተ ክህነት በተመደበለት በጀት የሚተዳደር ሲሆን ወደ ፊት በሙሉ ኃይል ሥራውን ሲጀምር ግን አሁን የተያዘለት በጀት በቂ አይሆንም፡፡ ስለዚህም በገዳሙ ከሚሰጠው ትምህርት ጎን ለጎን ተማሪዎቹ ገዳሙ ባለው ሰፊ መሬት ላይ የልማት ሥራ እያከናወኑ ራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግ ማኅበረ ቅዱሳን ግምቱ 53,000 ብር የሆነ የወተት ላም ርባታ እና 25,000 ብር የሆነ የአትክልት ልማት ፕሮጀክት አጥንቶ የበጎ አድራጊዎችን ድጋፍ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል፡፡

እዚያው በደቡብ የሀገራችን ክፍል እንዳለን ጉዞአችንን ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ስናደርግ ሌላው በጥናቱ የተካተተውን የደብረ በረከት ኮከብ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳምን እናገኛለን፡፡ ገዳሙ በከፋ ሸካ ቤንች ማጂ ሀገረ ስብከት በሚዛን ከተማ ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ ሥፍራው ቀደም ሲል ከሱዳን ተመላሽ የሆኑ ስደተኞችን መቀበያ ማዕከል ነበር፡፡ በ1981 ዓ.ም ስደተኞቹ ወደ ሌላ ቦታ ሲዘዋወሩ በወቅቱ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ቦታውን ለልማት ቢጠይቁም ሳይፈቀድ ለረጅም ጊዜ ቆይቷል፡፡ በ1992 ዓ.ም በብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ አማካይነት የስደተኞች መመገቢያ የነበረው አዳራሽ በቤተ ክርስቲያን ሕንጻነት ተዘጋጅቶና ተባርኮ ነሐሴ 24 ቀን 1992 ዓ.ም የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት እና የቅዱስ ዑራኤል ጽላት ገባ፡፡ ቦታውም «ደብረ በረከት ኮከብ አቡነ ተክለ ሃይማኖት እና ቅዱስ ዑራኤል የሴቶች ገዳም» ተብሎ ተሰየመ፡፡ ፕሮጀክቱ በተጠናበት 1993 ዓ.ም ገዳሙ ሰባት የሚሆኑ መነ ኮሳዪያት የነበሩት ሲሆን ቀደም ሲል በጥበበ እድ ሞያ የሠለጠኑት እነዚህ መነ ኮሳዪያት የተለያዩ አልባሳት፣ ጥሳ፣ ሙካ ሽና የመሳሰሉትን ቢሠሩም ለገበያ መቅ ረብ ባለመቻሉ ገቢ የሌላቸው ሆነዋል፡፡ ገዳሙ በአሁኑ ሰዓት በአካባቢው ያለውን የካህናት ችግር ለማስወገድ የአካባቢውን ልጆች በማስተማር በዲቁና እንዲያገለግሉ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

የዚህ ገዳም መጠናከር ለአካባቢው ምእመናን የሚኖረውን አስተዋፅዖና በተለይም ተማሪዎቹ በገዳሙ ውስጥ እየኖሩ እንዲማሩ ለማድረግ ገዳሙን በገቢ ሊደጉም የሚችል ግምቱ 25,985 ብር የሆነ የወፍጮ እና ግምቱ 56,048 ብር የሆነ የወተት ላም ርባታ ፕሮጀክቶች ተጠንተው የበጎ አድራጊዎችን ድጋፍ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል፡፡

## የቆየፃ አቡነ ሳሙኤል ገዳም

በደቡብ የሀገራችን ክፍል ያለንን በዚህ አቆይተን ጉዞአችንን ቀጥታ ወደ ሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ስናደርግ በትግራይ ክልል የምዕራባዊ፣ ማዕከላዊ እና ምሥራቃዊ ዞን አህጉረ ስብከት የተጠኑትን ገዳማት እናገኛለን፡፡ የቆየፃ አቡነ ሳሙኤል ገዳም በምዕራባዊ ትግራይ ሀገረ ስብከት በታሕታይ ቆራሮ ወረዳ የሚገኝ ሲሆን በአራተኛው ክፍለ ዘመን እንደ ተገደመ፣ በ12ኛው ክፍለ ዘመን በአቡነ ሳሙኤል ምክንያት እንደ ታወቀ ይታመናል፡፡ በገዳሙ ያለው አነስተኛ የእርሻ መሬት ቀደም ብሎ በገዳሙ ለነበሩት መነኮሳት የተከፋፈለና በግላቸው እያመረቱ የሚተዳደሩበት ነበር፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ወደ ገዳሙ የሚገቡት ወጣት መነኮሳት የመሥራት ዐቅም ቢኖራቸውም በድኅነት መኖርና ሁልጊዜ ተመጽዋች መሆን ስለ ሚያስቅቃቸው ገዳሙን እየለቀቁ ይሰደዳሉ፡፡ በገዳሙ ዙሪያ ያሉ የአብነት መምህራን የሚያስተምሯቸው ወደ 150 የሚጠጉ ተማሪዎች ይገኛሉ፡፡ መምህራኑ አስታዋሽና ጧሪ በማጣት ለችግር የተጋለጡና ተማሪዎቹም በምግብ፣ በልብስ፣ በመጠለያና የመጻሕፍት እጦት ችግር የተጎሳቆሉ ናቸው፡፡ ችግሩን በተወሰነ ደረጃ ለመቀነስ ግምቱ 32,500 ብር የሆነ የንብ ርባታ እና 93,000 ብር የሆነ በሽሬ ከተማ ሊከራይ የሚችል ቤት ለመገንባት ፕሮጀክት ተጠንቶ ለተግባራዊነቱም የበጎ አድራጊዎችን ርዳታ ገዳሙ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል፡፡

## የደብረ ገሪዛን ቅድስት ማርያም ጉንዳጉንዶ ገዳም

በዚሁ ክልል ወደ ምሥራቃዊ ዞን ሀገረ ስብከት ስንዘልቅ ከአዲግራት ከተማ ከአንድ ቀን የእግር ጉዞ በኋላ የሚገኘውን የደብረ ገሪዛን ቅድስት ማርያም ጉንዳጉንዶ ገዳም እናገኛለን፡፡ በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት እንደ ተመሠረተ የሚታመነው ይህ ገዳም ምንም እንኳ የዘመን ብዛት ቢፈትነውም ዛሬም ተፈጥሮ ተክሎ አስተ ካክሎ በጠረባቸው የድንጋይ ቋጥኞች ዙሪያውን በከበበው ወንዝ መሀል ከደ ልዳላ ኮረብታ ላይ ከነግርማ ሞገሱ ይገኛል፡፡ ገዳሙ አጽራረ ቤተ ክርስቲያን በተለያዩ ጊዜያት በተነሡበት ወቅት እንኳን አንዳችም ጉዳት ያልደረሰበት እና የብዙ ገዳማት እና አድባራት ቅርሳ ቅርስ በአደራ የተቀመጠበት ታሪካዊ ሥፍራ ነው፡፡

ቀደም ብሎ በገዳሙ በርከት ያሉ መነኮሳት የነበሩ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት አብዛኛዎቹ በችግር ምክንያት በመሰደዳቸው አራት መነኮሳት ብቻ ቀርተዋል፡፡ እነርሱም በረሃብ እና በእርዛት እየተሰቃዩ በገዳሙ ያሉትን ብርቅ እና ድንቅ ንዋያተ ቅድሳት በመጠበቅ ላይ ይገኛሉ፡፡ ገዳሙና አካባቢው በሙሉ በተራራማ አለቶች በመሸፈኑና የመሬት ይዞታም የሌለው በመሆኑ የልማት ሥራን ለማከናወን አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡ ስለዚህ ያሉትን መነኮሳት እንኳን በቦታው ለማቆየት እንዲቻል አዲግራት ከተማ ላይ ባለው የገዳሙ መሬት ሊከራይ የሚችል ግምቱ 135 ሺ ብር የሆነ ቤት ለመሥራት የግንባታ ፕሮጀክት ተጠንቶ የበጎ አድራጊዎችን ርዳታ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል፡፡

## የአባ ሃደራ ገዳም

በዚሁ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል እያለን በፕሮጀክቱ የተቃኘውን የአባ ሃደራ ገዳም እናገኛለን፡፡ የአባ ሃደራ ገዳም በትግራይ ክልል በማዕከላዊ ዞን ሀገረ ስብከት ከሃላ መንደር የሦስት ሰዓት የእግር መንገድ ከተጓዙ በኋላ የሚገኝ ነው፡፡ ገዳሙ ከተለያዩ ነገሥታት የተበረከቱ' ልዩ ልዩ ቅርሶችን ይዟል፡፡ በውስጡም ወደ 25 የሚጠጉ መነኮሳትና 25 የሚሆኑ የአብነት ተማሪዎች ይገኛሉ፡፡ በአብዛኛው መነኮሳቱ በዕድሜ የገፉ ሲሆኑ ያለባቸውን የምግብና የዘወትር ልብስ ችግር በመቋቋም በበኣታቸው ጸንተው ይኖራሉ፡፡ ገዳሙ በመቐሌ ከተማ ሊከራዩ የሚችሉ አምስት ክፍል ቤቶች ያሉት ሲሆን በጥሩ ዋጋ ሊከራዩ ባለመቻላቸው የገዳሙ መተዳደሪያ በጠበል ከሚመጡ ምእመናን በሚገኝ ገቢ ብቻ የተወሰነ ሆኗል፡፡ ይህም የተተኪ ተማሪዎችን ቁጥር እና በገዳሙ ያሉትን ቅርሶች ጥያቄ ውስጥ የሚከት ሆኗል፡፡ ስለዚህ ገዳሙ ያለበትን የተለያዩ ችግሮቹን በማስወገድ ራሱን እንዲችል ለማድረግ በቀዳሚነት በግምት 37,000 ብር በሆነ ወጭ በመከራየት ላይ ያለውን ቤት በተሻለ ደረጃ እንዲገኝ ለማድረግ ነው፡፡ በአማራጭም ግምቱ 23,000 ብር የሆነ የንብ ርባታ እና ግምቱ 28,000 ብር የሆነ የእንስሳት ርባታ ፕሮጀክቶች ተጠንተው ገዳሙ የበጎ አድራጊዎችን ድጋፍ በማጠባበቅ ላይ ይገኛል፡፡



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## የደብረ ብሥራት አቡነ ዜና ማርቆስ ገዳም

ወደ መካከለኛው የሀገራችን ክፍል በሰሜን አቅጣጫ ስንዘልቅ በቅድሚያ በፕሮጀክቱ የታቀፈውን የደብረ ብሥራት አቡነ ዜና ማርቆስ ገዳምን እንመለከታለን:: በ13ኛ ክፍለ ዘመን በዐፄ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት እንደ ተመሠረተ የሚታመነው ይህ ገዳም በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ከእነዋሪ ከተማ በግምት ስድስት ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል:: ገዳሙ እንደ ተመሠረተ ወደ 8,000 የሚጠጉ መነኮሳት ሰፊ የመሬት ይዞታ እንደ ነበራቸው የሚነገር ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ቁጥራቸው ወደ 130 የሚጠጉ መነኮሳት ብቻ በገዳሙ ውስጥ ይኖራሉ:: ከእነዚህ ውስጥ አብዛኛዎቹ ቦታው ባለው ቃል ኪዳን የተነሣ በዕድሜ ጠገብ አረጋውያን ናቸው:: ገዳሙ ቀደም ሲል ከነበረው የመሬት ይዞታ አብዛኞቹ በመንግሥት በመወረሳቸውና የቀረውም መሬት በተፈጠረው የሰው ኃይል እጥረት ምክንያት ተይዞ ለአርሶ አደር መስጠቱ ያለውን ገቢ በጣም አነስተኛ እንዲሆን አድርጓታል:: ይህም አረጋውያኑን ርዳታ በመጠባበቅ በተስፋ እንዲኖሩ አስገድዷቸዋል::

በገዳሙ ያሉትን ችግሮች ለማስ ወገድና ይህንን ጥንታዊ ገዳም ጠብቆ ለትውልድ ለማስተላለፍ በገዳሙ ያለውን ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ተጠንተዋል:: ከተጠኑት ፕሮጀክቶች ውስጥ ሁለቱ በሌሎች ፕሮጀክቶች ተጠንተዋል:: ከተጠኑት ፕሮጀክቶች ውስጥ ሁለቱ በሌሎች በጐ አድራጊዎች ተከናውነዋል:: የንብ ርባታ ፕሮጀክቱ በከፊል «ከአጋፔ የቅዱስ ሚካኤል የጽዋ ማኅበር» በተገኘ የዐሥር ሺ ብር ድጋፍ በመተግበር ላይ ይገኛል:: ወደፊት የዚህ ውጤት ታይቶ ይህንኑ የንብ ርባታ ኘሮጀክት ለማስፋፋት ታስቧል::

### የምዕራፈ ቅዱሳን በልበሊት ኢየሱስ ገዳም

ሌላው ከዜና ማርቆስ ገዳም በስተ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ የምናገኘው ይህ የምዕራፈ ቅዱሳን በልበሊት ኢየሱስ ገዳምን ነው:: በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት በእንሳሮና ዋዩ ወረዳ ልዩ ስሙ በልበሊት በሚባል ቦታ ላይ ይገኛል:: ይህ ገዳም ከሌሎች ገዳማት ለየት የሚያደርገው ራሱን ችሎ በእርሻ መተ ዳደሩ ነው:: ከ1991 ዓ.ም ወዲህ በአካባቢው በደረሰው የጐርፍ አደጋ ምክንያት ወደ 48 ሄክታር በሚሆን ቦታ ላይ የሚገኘው የፍራፍሬ፣ የጥጥና የሸንኮራ አገዳ ተክል በጐርፍ ተወስዷል:: መሬቱም ከጥቅም ውጭ ሆኗል:: በገዳሙ 150 የሚሆኑ መነኮሳትና መነኮሳይያት ይገኛሉ:: በደረሰው የተፈጥሮ አደጋ ለችግር ከመጋለጣቸውም በተጨማሪ ቦታው ቆላማ አካባቢ የሚገኝ በመሆኑ በየጊዜው በሚነሣ የወባ በሽታ ተጠቂዎች እንዲሆኑ አድርጓቸዋል:: በ1993 ዓ.ም ፕሮጀክቱ ሲጠና በርከት ያሉ ተማሪዎች የቅዳሴ፣ የዜማና የንባብ ትምህርት እየተከታተሉ የነበሩ ቢሆንም መምህሩ በወባ በሽታ ታመው በማረፋቸው ተማሪዎቹ መምህር ፍለጋ ወደ ሌላ ገዳም ለመሰደድ ተገደዋል::

ገዳሙ በተፈጥሮ የደረሰበትን አደጋ ለመታደግና ችግሩን ለማስወገድ በገዳሙ ቀሪ መሬት ላይ ግምቱ 355,980.00 የሆነ የመጠስኖና የአትክልት ልማት ፕሮጀክት ተጠንቶለታል:: ለዚህ ሥራ ማኅበረ ቅዱሳን በአሜሪካ ማንኙነት ጣቢያ አማካይነት ባገኘው የ200,000 ብር ድጋፍ ሥራውን ለማስጀመር በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛል::

ይቆየን

# ቅዱስ ሐርቤ...

/ከገጽ ፳፫ የዞረ/

ዲዮስቆሮስ፣አባ አርከ ድንግል፣አባ ብንያም አባ ተክሥተ ብርሃን፣ አባ ዘመደ ፊልጶስ የሚባሉ ቆሞሳት ተመርጠው የኢትዮጵያን ክፍላተ ሀገር ተከፋፍለው እንዲያስተምሩ ተደረገ::

ጥቂት ቆይቶም ቅዱስ ገ/ማርያም ለጳጳሱ:- «አባቴ ሆይ÷ ባይሆን የኤጲስ ቆጶስነት ማዓርግ ይጨመርላቸው:: ምክንያቱም በየሀገረ ስብከታቸው ካስተማሩት ሕዝብ መካከል ለተማሩት ሊቃውንት ቅስና ዲቁና ለመስጠት እንዲችሉ ነው» ብሎ ሊቀ ጳጳሱን ስለ አግባባቸው ፈቃደኛ ሁነው ሰባቱን ቆሞሳት ኤጲስ ቆጶስ ብለው አባ ሚካኤል ሹመዋቸዋል:: እነርሱም በተሰጣቸው ሥልጣን ዲያቆናትን ቀሳውስትን በየሀገረ ስብከታቸው ይሾሙ ጀመር:: ይህም ጉዳይ በእስክንድርያ ስለ ተሰማ ፓትርያርኩ አባ ገብርኤል ተቆጥቶ አባ ሚካኤልን ለመገሠጽ ጥሪ አደረገላቸው::

አባ ሚካኤልም የፓትርያርኩን ጥሪ የጠብ መሆኑን ዐውቀው የሆነ ይሁን ብለው የኢትዮጵያውያን ተወላጅ የሆኑትን ሰባት ኤጲስ ቆጶሳትን ሢመተ ሊቀ ጵጵስና ሹመዋቸው ወደ ሀገራቸው ተነሥተው ሄደዋል:: ሊቀ ጳጳሱ ግብፅ እንደ ደረሱ ከፓትርያርኩ ጋር ሳይገናኙ በድንገት ካይሮ ከተማ ላይ ዐረፉ:: የእስክንድርያው ፓትርያርክ አባ ሚካኤል ከሞቱ በኋላ አባ ሚካኤል በኢትዮጵያ ላይ ጳጳሳትን ሹመው እንደ ተመለሱ በመሞታቸው አዘነ፣ ምክንያቱም ጳጳሱ በሕይወታቸው ቢሆኑ የሾሙአቸውን ጳጳሳት እንዲሽሩና እንዲያግዱ መልሶ ለመላክ ነበር፤ ግን የፓትርያርኩ ሐሳብ ሳይሳካ ከቀረ በመካከል የግብፅ ንጉሥ ሰምቶ:- «ሊቃነ ጳጳሳት ከኢትዮጵያውያን መካከል እንዲሾም ለምን አደረግህ» ብሎ ተቆጥቶ የእስክንድርያውን ፓትርያርክ አሰረው፣ ጉዳዩን ግን ንጉሡ ጠበቅ አድርጎ አልመረመረውም ነበር:: በዚህም ምክንያት በእስክንድርያ ውስጥ ብጥብጥ ተነሣ:: ጉዳዩም ፓትርያርኩ ያለ አግባብ ስለ ታሰረባቸው ነው:: ይህ ነገርም ተመርምሮ ከፍጻሜ ሳይደርስ ከእስር ቤት እንዳለ ፓትርያርኩ አባ ገብርኤል በድንገት ዐረፈ:: የኢትዮጵያውያን ጳጳሳትም እስከ ንጉሥ ሐርቤ /ገብረ ማርያም/ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ ድረስ የጵጵስና መዓርጋቸውን ይዘው በየሀገረ ስብከታቸው ብዙ መንፈሳዊ ትሩፋት ሠርተዋል:: በዚህ ሁናቴ ንጉሥ ገብረ ማርያም /ቅዱስ ሐርቤ/ ኢትዮጵያን በመንፈሳዊና በሥጋዊ አጣምሮ በመምራቱ ታላቅ÷ ስመ ጥሩ ንጉሥ ሆኖ ስለ ተገኘ ዓለም በመላክም ዝና ታሪኩን የሚያስታውሰው ኹኖአል::

ንጉሡ ቅዱስ ሐርቤ /ገ/ማርያም/ 36 ዘመን ኢትዮጵያን ከመራ በኋላ ከአብራኩ ለወጣው ለልጁ ለነአኩቶ ለአብ የመንግሥቱን ሥልጣን ከማውረስ ቅድሚያ ለወንድሙ ለቅዱስ ላሊበላ መስጠት እንደሚገባው ከእግዚአብሔር ስለ ተገለጸለት የመንግሥቱን ሥልጣን ለወንድሙ ለቅዱስ ላሊበላ አስረክቦ ከፈጣሪው ክብር ለማግኘት ከሰው ተለይቶ በጾም በጸሎት በስግደት ከቆየ በኋላ ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ተቀብሎ የካቲት 16 ቀን 1164 ዓ.ም. በሮሀ ቤተ መንግሥት ውስጥ ዐረፈ::

የቀብሩም ሥነ ሥርዓት ንጉሥ ላሊበላ በተገኘበት በታላቅ ሥነ ሥርዓት በሕይወቱ ባሠራው በቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተቀበረ:: አሁን ዛሬ ቅዱስ ገ/ማርያም የተቀበረበት ከጥንት ስሙ የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን መሆኑ ቀርቶ ቅዱስ ሐርቤ እየተባለ የሚጠራ ቤተ ክርስቲያን ሆኗል:: የቅዱስ ሐርቤ ቤተ ክርስቲያን አዋሳኝ አረማ ማርያምና ሣራባ ጊዮርጊስ ናቸው::

ቅዱስ ሐርቤ ስመ መንግሥቱ ገብረ ማርያም ይባል እንጂ የሀገሬው ሕዝብ ጻድቁ ቅዱስ ሐርቤ እያለ ነው የሚጠራው፤ የቅዱስ ሐርቤን ታሪካዊ ቦታ ለሚጎበኝ ሰው ከቅዱስ ላሊበላ ከተማ ተነሥቶ እስከ ዓይኑ ቡግና ከተማ ድረስ መኪና ገብቶአል:: ከዓይና ከተማ ቅዱስ ሐርቤ ቤተ ክርስቲያን ድረስ በእግር 2 ሰዓት ተኩል ያስኬዳል:: ስለዚህ በመንገድ በኩል ችግር የለም:: የቅዱስ ሐርቤ በዓለ ዕረፍት የካቲት 16 ቀን ይከበራል:: የቦታውን አፈር ቢቀቡት ለታመመ ሰው መድኃኒት ነው:: በቦታው ያለውም ጠበል በፈዋሽነቱ የታወቀ ነው::

ቅዱስ ሐርቤ በዘመኑ የሠራው የቅድስና ሥራ ብዙ ነው:: ስለዚህ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የስመ ጥሩውን ጻድቅ ሥራ ተመልክታ÷ ቅዱስ የሚያሰኘውን የክብር ስም ሰጥታ ገድል ጽፋለታለች:: በዓለ ዕረፍቱንም የካቲት 16 ቀን በየዓመቱና በየወሩም በደመቀ ሁኔታ ታከብራለች::

ይህ ከዚህ በላይ የተዘረዘረው ታሪክ ከገድሉ ጥንታዊ የግእዝ ጽሑፍ ውስጥ በአጭሩ የወጣ ነው::

ምንጭ:- <u>ትንሣኤ መጽሔት</u>

### እርማት

ባለፈው እትም በእናስተዋውቃችሁ ዓምድ ባወጣነው የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከገጽ 17 ዓምድ ሁለት ላይ ዐፄ ሚኒልክ በ1574 ዓ.ም. በእንጦጦ ተራራ ላይ ከተማ እንደ ቆረቆሩ የተገለጸው በስሕተት በመሆኑ በ1870 ተብሎ እንዲስተካከል፤ በተጨማሪም ከገጽ 17 ወደ ገጽ 33 በዞረው ጽሑፍ መጀመሪያ «ስለ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ታቦት የት መጣ ሲነገር አባ በላይነህ የተባሉ መነኩሴ» የሚል ሐረግ የተገደፈ በመሆኑ አንባቢያን በዚህ አምልታችሁ እንድታነቡ ከይቅርታ ጋር እንጠይቃለን::

በዚህ አጋጣሚ የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ቤት 125ኛ ኣብረ በዓል ጥር 1 ቀን 1997 ዓ.ም በደማ ሥነ ሥርዓት የሚከበር በመሆኑ ምእመና በደብሩ ተገኝታችሁ የበረከቱ ተሳታፊ እንድትሆኑ የደብሩ አስተዳደር ያሳስባል:: ዝግጅት ክፍሉ



© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# ቅዱስ ሐርቤ

በአባ ገብረ መስቀል ዘገነተ ማርያም

ቅዱስ ሐርቤ በኢትዮጵያ ከነገሡ ከነገደ ዛጉዌ ነገሥታት ውስጥ 11ኛ ንጉሥ ነው፤ መናገሻ ከተማውና ተወልዶ ያደገው በላስታ አውራጃ ቡግና ወረዳ ውስጥ ሮሃ ከምትባል ከተማ ነው። በዚህችም ከተማ ከርሱ በፊት፤

1. መራ ተክለ ሃይማኖት
2. ጠጠውድም
3. ዣን ሥዩም
4. ሐርበይ
5. ግርማ ሥዩም
6. መይራሪ
7. ቅዱስ ይምርሐ

የሚባሉ ደጋግ ነገሥታት ነግሠው ባታል። ቅዱስ ሐርቤ ከነዚህ ውስጥ የንጉሥ ዣን ሥዩም ልጅ ነው። አባቱ ዣን ሥዩም ከመንገሡ በፊት የዋግ ሹም ሆኖ ሲያስተዳድር ዑጽፍተ ወርቅ የምትባል ሴት አግብቶ ይህን ስመ ጥሩውን ጻድቅ ሐርቤን የካቲት 1093 ዓ.ም ወለደ፤ ሕፃኑም በመልካም ክብካቤ አድጎ ዘጠኝ ዓመት ሲሆነው በቤተ መንግሥቱ ውስጥ መምህር ተቀጥሮለት ንባብና ዳዊት ከቃል ትምህርት ጋር በሚገባ ተማረ። ቀጥሎም ወደ ብልባላ ጊዮርጊስ ሂዶ ከመምህር ሰይፈ ያሬድ ዘንድ ቅኔና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ከጽሕፈት ሞያ ጋር በሚገባ ተማረ። ከዚያም ወደ ደብረ ሮሃ ተመልሶ ሥርዓተ መንግሥት እየተማረ ቆይቷል፤ ቤተ ክርስቲያንንም ዲያቆን በመሆን አገልግሎአል።

ቅዱስ ሐርቤ 25 ዓመት ሲሆነው መርኬዛ የምትባል ሴት በሥርዓተ ተክሊልና በሥጋ ወደሙ አግብቶ በ1120 ዓ.ም. ከአባቱ ከንጉሥ ዣን ሥዩም ቀጥሎ ነገሠ። ስመ መንግሥቱንም ገ/ማርያም ብሎ ሰየመ። እንደ ነገሠም ከአባቶች ሲያያዝ የመጣውን ሥርዓትና ወግ ጠብቆ የሚኖር ኹኖአል። ቅዱስ ሐርቤ ብዙውን ጊዜ ወደ መንፈሳዊ ዓለም ያደላ ነበር። የቅዱስ ሚካኤልን ዝክረ በዓል በዓመት ሁለት ጊዜ በከፍተኛ ሥነ ሥርዓት ይዘክር ነበር። እንዲሁም በስሙ ቤተ ክርስቲያንን ተክሎ ይማፀንበት ነበር። እመቤታችን ከልጅዋ ቃል ኪዳን የተቀበለችበትን የካቲት 16 ቀን ይዘክር ነበር። በየአውራጃው ብዙ ቤተ ክርስቲያን እንዲተከል አድርጓል።

የተማሩ ሊቃውንትንም እያሰባሰበ በየቤተ ክርስቲያኑ እንዲያስተምሩ በማድረግ ብዙ ደቀ መዛሙርትን እንዲያፈሩ አድርጓል። የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትም በመላ ኢትዮጵያ እንዲስፋፋና እያንዳንዱ ሕዝብ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ ዐውቆ ከመጥፎ ነገር እንዲጠበቅ ምኞት ነበረው። በዚህም ሐሳብ ላይ ሳለ የኢትዮጵያ ጳጳሳት የነበሩት አቡነ አትናቴዎስ 30 ዓመት በጵጵስናቸው መርተው ወደ ሀገራቸው ግብፅ ሲሄዱ በምት ካቸው አባ ሚካኤል የሚባሉ ጳጳስ ከእስክንድርያ ወደ ኢትዮጵያ ተሹመው መጡ። ንጉሡም በክብር ተቀበላቸው። ጳጳሱም እንደ መጡ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ተቀምጠው ቋንቋ የማያውቁና ዐቅመ ደካማ ከመሆናቸው የተነሣ የአካባቢውን ሕዝብ ከመባረክ በቀር ተዘዋውረው ለማስተማር የማይችሉ ሆኑ። ቅዱስ ሐርቤም ጉዳዩ አሳዝኖት፦ «አባቴ ,ሆይ÷ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዙ ነው፤ ስፋቱም የዚያኑ ያህል ነው፤ እርስዎ ከእስክንድርያ የመጡት የኢትዮጵያን ምድር እየዞሩ እንዲባርኩና እንዲያስተምሩ ነው። ነገር ግን ብቻዎን የኢትዮጵያን ሕዝብ እየተዘዋወሩ ለማስተማር ስለማይችሉ ባይሆን ከርስዎ ጋር ተጨማሪ የሚሆኑ ሰባት ጳጳሳት ከእስንድርያ እንዲላኩልዎት ይጠይቁ። የማይቻል ከሆነ ግን ከኢትዮጵያ ሊቃውንት መካከል ሰባት ቆሞሳት ይምረጡና ተሾመው በኢትዮጵያ ምድር የሚገኘውን ሕዝብ የሃይማኖት ትምህርት እንዲያዳርሱ ያድርጉ» ብሎ ጥያቄ አቀረበላቸው።

ጳጳሱ አቡነ ሚካኤልም «ንጉሥ ሆይ÷ ሐሳብህ መልካም ነበር። ነገር ግን ከእስክንድርያ ተጨማሪ ጳጳሳት·ለማስመጣት አይቻልም። ከዚህም ከኢትዮጵያውያን መነኮሳት ውስጥ መርጦ ጳጳሳትን ለመሾም ከበላይ አይፈቀድልኝም። ምክንያቱም በ325 ዓ.ም. ላይ ተነሥተው የነበሩት "318 ሊቃውንት በፍትሐ ነገሥት፦ ኢትዮጵያውያን ከመካከላቸው ለመንፈሳዊ አገልግሎት ችሎታ ያላቸው ሊቃውንቶቻቸውን መርጠው ሊሾሙ አይችሉም፤" የሚል ውሳኔ አለ። ስለዚህ ጉዳዩ ላይፈጸም ከንቱ ድካም ይሆንብኛል» አሉት። ንጉሡ ቅዱስ ገ/ማርያም ግን፦ «አባቴ ሆይ÷ ቢሆን ሆነ፤ ባይሆን ጉዳዩን በኋላ እናስብበታለንና ሆነ ብለው ይጻፉ» አላቸው።

ጳጳሱም የንጉሡን ቃል ለማክበር ሲሉ ለእስክንድርያው ፓትርያርክ አባ ገብርኤልና ለግብፁ ንጉሥ ከሊፋ አል ሀፌዝ «ቢቻል ከእስክንድርያ ሰባት ጳጳሳት ተሹመው ይላኩልኝ፤ ባይቻል ከኢትዮጵያውያን ውስጥ ሰባት ቆሞሳት ተመርጠው ለእኔ ረዳት እንዲሆኑ ጳጳስ ሁነው እንዲሾሙልኝ እጠይቃለሁ» የሚል ደብዳቤ ጻፉ። ፓትርያርኩና ከሊፋውም ይህ ደብዳቤ እንደደረሳቸው ጉዳዩን ተመልክተው ተቆጡ፤ የቁጣ ቃል የተጻፈበት መልእክት መልሱ መጣላቸው።

ደብዳቤውም እንዲህ የሚል ነበር፦ «ለኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ አባ ሚካኤል÷ አንተ ራስህ ለኢትዮጵያ ትበቃለህ ብለን ልከንሃል፤ ለማሾምም ሆነ ለመሾም ሥልጣን የለህም፤ የተወሰነልህን ዘመን በሥርዓት ጨርሰህ በሰላም መመለስ ነው እንጂ። በዚህ ጉዳይ የሚያገባህ የለም» የሚልና የመሳሰሉትን የሚያሳዝን ጽሑፍ ጽፈው ላኩላቸው፤ ጉዳዩንም ንጉሡ ቅዱስ ገ/ማርያም ሰማው፤ በዚህም ጉዳይ ንጉሡ ገ/ማርያም። ለዚህ መልስ አጸፋውን ለእስክንድርያው ፓትርያርክ ለአባ ገብርኤልና ለግብፁ ንጉሥ ከሊፋ አል ሀፌዝ በደብዳቤ እንደዚህ የሚል ጻፈ። የኢትዮጵያ ንጉሥ የቅዱስ ሐርቤ ቃል÷ ለእስክንድርያ ፓትርያርክ ለአባ ገብርኤል፤ ለግብፅ ንጉሥ ከሊፋ አል ሀፌዝ ሰላም ለናንተ ይሁን...

... ኢትዮጵያ ሀገሯና ሕዝቧ ብዙ ስለሆነ የተላኩልን ጳጳስ ብቻቸውን የኢትዮጵያን ሕዝብ በሃይማኖት ለማነፅ የማይችሉ መሆኑን አምኜ ቢቻል ከእስክንድርያ ተጨማሪ ጳጳሳት ይላኩልን። ያለበለዚያ ከኢትዮጵያውያን ውስጥ የተማሩና በመንፈሳዊነታቸው የታወቁ ተሹመው ለተላኩት ጳጳስ ርዳታ እንዲደረግላቸው የሚለው ቁም ነገሩ ጥያቄ ለእናንተ የሚያስከፋ ከሆነ እኔም ወደ ግብፅ የሚመጣላችሁን የኢትዮጵያ ዐባይ ለእናንተ ለግብፃውያን ጥቅም በመሆኑ አስከፍቶኛልና የዐባይን ወንዝ መገደቤን ዕወቁት» ብሎ የቁጣ ደብዳቤ ወደ ግብፅ ላከ።

የንጉሡ ደብዳቤም ግብፅ ደርሶ ጳጳሱና የግብፁ ንጉሥ ከሊፋ አል ሀፌዝ በንባብ ሰምተውት ደነገጡ። በጉዳዩም ከተወያዩ በኋላ አሳሳቢ መሆኑን ተመልክተው ለኢትዮጵያ ንጉሥ ለቅዱስ ገብረ ማርያም፦ «እኛ ኢትዮጵያውያንን ለመጨቆን ሳይሆን «318 ሊቃውንት በፍትሐ ነገሥት፦ ኢትዮጵያውያን ከመካከላቸው ጳጳሳት መርጠው መሾምም ማሾምም አይችሉም፤» የሚል ውሳኔ ስለአለብን ነው እንጂ ለሌላ አይደለም፤ ከዚህ እንዳን ልክላችሁ በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ለአንድ ሀገር አንድ ሊቀ ጳጳስ እንዲሾም ነው የሚያዘው። ነገር ግን ንጉሡ አንተ ከምታዝዘን የላክነው ሊቀ ጳጳስ በውስጡ ጳጳሳት ማድረጉን ትቶ ቆሞስ እያለ ከሊቃውንት እስከ ሰባት ኤጲስ ቆጶሳት እንዲሾሙ ፈቅደናል» የሚል መልስ ጽፈው ላኩ። ደብዳቤውም ለቅዱስ ገ/ማርያም እንደ ደረሰ አስነብቦ ከሰማ በኋላ ከቁጣው ታግሦ ለጊዜው ቀስ በቀስ ከፍጻሜ ለማድረስ ሰባቱ ቆሞሳት ከኢትዮጵያ አውራጃ እንዲመጡ ሆኖ አባ አብርሃም፣ አባ ሲኖዳ፣ አባ ኤዎስጣቴዎስ፣ አባ ዘፈረ

ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል






© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሞያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ግቢ ጉባኤ




*የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሞያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ግቢ ጉባኤ ከምሥረታው አንሥቶ ያስመረቃቸው ተማሪዎች ሥዕላዊ መግለጫ*

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ስር በመሆን ሰፊ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በማበርከት ላይ የሚገኘው ማኅበረ ቅዱሳን በቅዱስ ሲኖዶስ መተዳደሪያ ደንብ ጸድቆለት ሥራ ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ አያሌ ተግባራትን አከናውኗል::

ማኅበሩ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች ከዘመናዊው ትምህርት ጐን ለጐን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት እንዲማሩ በማድረግ በርካታ ተማሪዎችን አስመርቋል::

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ በሚገኙ ዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆች አንድ መቶ ዐሥራ አንድ የሚሆኑ ግቢ ጉባኤያት በማኅበሩ ዕውቅና ተሰጥቷቸው አገልግሎት እያገኙ ሲሆን አርባ ዘጠኝ የሚሆኑ ግቢ ጉባኤያት በክትትል ላይ ይገኛሉ::

ዕውቅና ተሰጥቷቸው ከዘመናዊ ትምህርታቸው ጐን ለጐን የቤተ ክርስቲያናቸውን ትምህርት በመከታተል ላይ ከሚገኙት ግቢ ጉባኤያት አንዱ የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሞያና ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ግቢ ጉባኤ ነው::

ይህ በደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ከአዲስ አበባ 445 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘው ግቢ ጉባኤ በባሌ ሀገረ ስብከት ወደ ሰሜን ምሥራቅ 47 ኪሎ ሜትር ገባ ብሎ በአጋ ርፋ ወረዳ ቤተ ክህነት በአምቤንቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ አጥቢያ ቤተ ክር ቲያን ይገኛል::

ግቢ ጉባኤው በ1989 ዓ.ም በማኅበሩ ዕውቅና አግኝቶ አገልግሎት ከማግኘቱ በፊት በ1983 ዓ.ም በኮሌጁ ሠራተኞችና ሠልጣኞች እንዲሁም በጦርነት ምክንያት ከአሥመራ ዩኒቨርሲቲ በመጡ ተማሪዎች፣ በጐባ መድኃኔዓለም የጽዋ ማኅበር አባላትና በአጋርፋ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሰንበት ት/ቤት አባላት አማካይነት በቢፍቱ ከጅዋ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት ከኀምሳ እስከ ስድሳ በሚደርሱ አባላት መንፈሳዊ እንቅስቃሴ እንደ ተጀመረ መረጃዎች ይጠቁማሉ::

በዚያን ወቅት የመምህራን እጥረት ስለነበረ ዘጠኝ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ከሚገኘው ከአጋርፋ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሰንበት ት/ቤት ሰባኬ ወንጌል በማስመጣት ቅዳሜና እሑድ ትምህርት ይሰጥ ነበር:: በተጨማሪም የመድኃኔ ዓለም ጽዋን በመዘከር ለግቢ ጉባኤው መጠንከር ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል::

ጉባኤው በቢፍቱ ከጅዋ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት ሲካሄድ ከቆየ በኋላ የተለያዩ ፈተናዎች ስላጋጠመው ከትምህርተ ቤቱ ውጪ በኮሌጁ መማሪያ ክፍሎች አካባቢ በሚገኝ የግራር ዛፍ ሥር ይካሄድ ነበር::

በ1985 ዓ.ም የአጋርፋ ሁለ ገብ የገበሬዎች ማሠልጠኛ ማዕከል ወደ አጋርፋ ሁለገብ የግብርና ልማት ሠልጣኞች ማዕከል ሲቀየር ጉባኤው ለተወሰነ ጊዜ ተቋርጦ ከቆየ በኋላ በሠራተኞችና በጎባ መድኃኔ ዓለም ጽዋ ማኅበር አባላት አነሣሽነት እንደ ገና አንሰራርቶ ሠልጣኝ ተማሪዎችን በማቀፍ በሠራተኛ መኖሪያ ቤት ለብዙ ጊዜ ሲካሄድ ቆይቷል::

ነገር ግን ብዙ ንብረት ባለበት አካባቢ ሠራተኛውና ሠልጣኝ ተማሪዎች ሰፊ የሰንበት ት/ቤት ጉባኤ ማካሄድ ከፍተኛ ፈተና የሚበዛበትና ለአገልግሎቱም አመቺ አልነበረም:: በመሆኑም ከንብረት ራቅ ወደ አለ÷ ከሠራተኞች መኖሪያ ጀርባ በሚገኘው ሰፊ ሜዳ ላይ ጉባኤው እንዲካሄድ አባላቱ ተስማምተው የባሌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በነበሩት በብፁዕ አቡነ ሰላማ ቦታው ተባርኮ እስከ 1994 ዓ.ም መጨረሻ ጉባኤው በዚህ ቦታ ሲካሄድ ቆይቷል::

በፈቃደ እግዚአብሔር እንቅስቃሴው የተጀመረው የአጋርፋ ግቢ ጉባኤ በዚህ ሁኔታ ሲካሄድ ቢቆይም የጉባኤው ቦታ ከሠራተኞች መኖሪያ ቤት ቅርበት ያለው በመሆኑ በኮሌጁ አመራር ቦታው እንዲቀየር ትእዛዝ ተላልፎ ራቅ ብሎ በሚገኘው ተመሳሳይ ሜዳ ላይ እስከ አሁን ድረስ ጉባኤው እየተካሄደ ይገኛል::

እስከ 1988 ዓ.ም ድረስ «በአምቤንቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰንበት ት/ቤት የሠልጣኞች ጉባኤ» በመባል ይጠራ የነበረው ይህ ጉባኤ በማኅበረ ቅዱሳን ዕውቅና ከተሰጠው በኋላ ከ1989-1994 ዓ.ም «የአጋርፋ ሁለገብ የግብርና ልማት ሠራተኞች ግቢ ጉባኤ» ተብሎ ሲጠራ ቆይቷል:: ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ በመንግሥታዊ መዋቅር «የአጋርፋ ሁለገብ ግብርና ልማት ሠልጣኞች ማዕከል» ወደ «አጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሞያ ሥልጠና ኮሌጅ» ሲቀየር ግቢ ጉባኤውም «የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሞየ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ግቢ ጉባኤ» ተብሎ መጠራት ጀምሯል::

ግቢ ጉባኤው በማኅበሩ ዕውቅና ባገኘበት ወቅት የጐባ ጊዜያዊ ንዑስ ማዕከል ገና ያልተጠናከረ ስለ ነበር በኮሌጁ ውስጥ በሚኖሩ የማኅበሩ አባላት አማካይነት ከዋናው ማዕከል ጋር የጠበቀ ግንኙነት በማድረግ ግቢ ጉባኤው እንደ ሌሎች ግቢ ጉባኤያት አገልግሎቱ እንዲጠናከር ከፍተኛ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል:: በ1993 ዓ.ም የአጋርፋ ወረዳ ማዕከል ከተመሠረተ በኋላ ግቢ ጉባኤው ከንዑስ ማዕከሉ የራቀ በመሆኑ ወረዳ ማዕከሉ በቅርብ ሆኖ እየ



© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

ተከታተለው አገልግሎቱ በተጠናከረ መልኩ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

የአጋርፋ ግቢ ጉባኤ ተማሪዎች መንፈሳዊ ትምህርታቸውን ከመከታተላቸውም ባሻገር ከግቢ ጉባኤያቸው አምስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘውን የአምቤንቱ ደብረ ፀሐይ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ሲሠራ ድንጋይ በመፍለጥ፣ የልስን ጭቃ በማቡካት፣ ሥልጣነ ክህነት ያላቸው በተልእኮ በመሳተፍ ገንዘብ አዋጥተው አልባሳት በመግዛት አገልግለዋል፡፡

በዚህ ሳይገደቡ በዘመናዊ ትምህርት ባገኙት ዕውቀት በመጠቀም ለቤተ ክርስተያኒቷ ችግኝ በመትከል፥ አጥር በማጠር፥ የውጭውንና የውስጡን ጽዳት በመጠበቅ በአጠቃላይ በዕውቀታቸውና በገንዘባቸው እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡

ከምረቃ በኋላም ቢሆን በሰበካ ጉባኤና በሰንበት ት/ቤት በመታቀፍ እንዲሁም ሰንበት ት/ቤት በሌለባቸው ቦታዎች ሰንበት ት/ቤት በማቋቋም ጉልህ የሆነ አስተዋፅዖ በማበርከት ላይ ይገኛሉ፡፡ ተመራቂዎች የተማሩበትን ግቢ ጉባኤ ባለመዘንጋት ለግቢ ጉባኤው መገልገያ የጸሎት መጻሕፍት፣ የፎቶ ግራፍ ካሜራ፣ ጸናጽልና መቋሚያ ገዝተው አበርክተዋል፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን ለግቢ ጉባኤያት ወጥ የሆነ ሥርዓተ ትምህርተ ቀርፆ ተግባራዊ እስካደረገበት እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ በተለያዩ ጊዜያት ወደ ኮሌጅ ለሚገቡ ተማሪዎች የተለያዩ ኮርሶች የተሰጡ በመሰጠት ላይ ያሉ ሲሆን፡-

- የትምህርተ ሃይማኖት መግቢያና አዕማደ ምሥጢር፤
- ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን፤
- ክብረ ቅዱሳን፤
- ነገረ ማርያም፤
- የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፤
- ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር፤
- የቤተ ክርስቲያን ታሪክ /በኢትዮጵያና በዓለም መድረክ/፤
- ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን፤
- የስብከት ዘዴ፤
- የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር፤
- ወጣትነትና መንፈሳዊነት፤
- ሕይወት ከምረቃ በኋላ፤
- ንዋያተ ቅድሳት፤
- የቤተ ክርስቲያን ወቅታዊ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው፤

በሚሉ ርእሶች ትምህርት ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ በየዕለታዊና በሳምንታዊ መርሐ ግብር ላይ የተለያዩ ስብከቶችና መዝሙር ጥናት እንዲሁም ድራማ የሚቀርብ ሲሆን ዘወትር ዓርብ የጸሎት መርሐ ግብር ይካሄዳል፤ የተሰጥዖ ትምህርትም አንዱ ሲሆን ከተለያዩ ግቢ ጉባኤያት የሚላኩ ደብዳቤዎችም ጊዜ ተሰጥቷቸው ይነበባሉ፡፡

የግቢ ጉባኤው ተማሪዎች በዘመናዊ ትምህርታቸው ጥሩ ውጤት እንዲያመጡ የአጠናን ዘዴ፣ የፈተና አሠራር ሥልት፣ የምክር አገልግሎትና በዕረፍት ሰዓታቸው በክርስቲያናዊ ሕይወትና በተለያዩ ርእሶች ዙሪያ በወረዳ ማዕከሉ አማካይነት ትምህርት ይሰጣል፡፡

ግቢ ጉባኤው ይህንና የመሳሰሉትን ተግባራት ሲያከናውን ሁሉም ነገር ተሟልቶለት ሳይሆን የተለዩ ችግሮችን በመቋቋም ነው፡፡ የግቢ ጉባኤው ተሳታፊዎች በአቅራቢያው ቤተ ክርስቲያን ባይኖርም ብርድ፥ ነፋስ፥ ውርጭ፥ ፀሐይና ዝናም እየተፈራረቀባቸው እንዲሁም የተለያዩ ድምፆችን ታግሠው መርሐ ግብሩን በማጠናከር ሜዳ ላይ ውዳሴ ማርያም እየደገሙ በፍጹም ጥንካሬ እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡

አንዳንድ ጊዜ በዝናም ምክንያት ዕለታዊ መርሐ ግብሮችና ተከታታይ ትምህርቶች የሚቋረጡበት ወቅት በመኖሩ የተዘጋጀውን ሥርዓተ ትምህርት ተከትሎ ለመሄድና በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡

ከ1994 ዓ.ም በፊት የተማሪዎች የግቢ ቆይታ ዘጠኝ ወራት ብቻ ስለነበር፥ በየዓመቱ ጉባኤው አዲስ አባላትን ስለሚቀበል፥ ጠንካራ ጉባኤን ለመፍጠር አሉታዊ ተፅዕኖ ሲፈጥር ቆይቷል፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ሰዓት ተማሪዎች የሁለት ዓመት ቆይታ እንዲኖራቸው ስለ ተደረገ ቅዳሜና እሑድ ሳይቀር ማካካሻ ትምህርት ሳቢያ በት ምህርታቸው ጫና ቢኖርባቸውም መን ፈሳዊ ትምህርታቸውን ሳያቋረጡ በመማር ላይ ይገኛሉ፡፡

ወደ ግቢው የሚገቡት ተማሪዎች በአብዛኛው ሰንበት ት/ቤት ካልተ ቋቋመባቸው አካባቢ የሚመጡና የተለያየ የዕድሜ ክልልና መንፈሳዊ ብስለት ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ ከዚህም ባሻገር በቂ የመማሪያ መጻሕፍትና መምህራን በሌሉበት ሁኔታ ችግሮችን አጣጥሞ ጉባኤው እንዲጠናከር ማድረግ የሚያስመሰግን ተግባር ነው፡፡

በወረዳ ማዕከሉ ውስጥ የሚገኙ የማኅበሩ አባላት ያላቸውን መጻሕፍት ለትምህርት ማስተማሪያነት በመስጠት ወረዳ ማዕከሉም ግቢ ጉባኤውን በቅርብ ሁኖ በመከታተል አስፈላጊ የሆነውን ሁሉ በማሟላት የሚያከናውኑት ተግባር ሊበረታታ ይገባዋል፡፡

የማኅበረ ቅዱሳን ዋናው ማዕከል ሥልጠና ክፍል በክረምት ወራት ከግቢ ጉባኤው የተመረጡ ወጣቶችን ሥልጠና እንዲያገኙት በማድረጉ የአገልጋይ ችግር እንዲቀረፍ አድርጓል፡፡ ይህ ቤተ ክርስቲያን በሌለበት ቦታ ተጠናክሮ መንፈሳዊ አገልግሎት እየፈጸመ ያለው ግቢ ጉባኤ ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1996 ዓ.ም 164 ሴት 658 ወንድ በድምሩ 822 ሠልጣኞችን በቤተ ክርስቲያን ትምህርት አስተምሮ በማስመረቅ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ አገልግሎት እንዲያበረክቱ አድርጓል፡፡

*__ምንጭ፡-__ «የአጋርፋ ግቢ ጉባኤ ታሪካዊ ዳሰሳ» ፥በግቢ ጉባኤው የተዘጋጀ፥ 1996 ዓ.ም*

# ዘማዊቷ…

/ከገጽ ፲፰ የዞረ/


በኋላ የብዙ ሰው ኮቴ ተሰማኝ፡፡ ትተውኝ እየወጡ ነበር፡፡ ማመን ተሳነኝና ቀና ብዬ አየኋቸው፡፡ የነካኝ አልነበረም፡፡ በመልሱ የተገረሙ ይመስል ጭንቅላታቸውን እየወዘወዙ ከሽማግሌዎች ጀምረው እስከ ትንንሾቹ ድረስ አንድ አንድ እያሉ ትተውኝ ወጡ፡፡ ከቆምኩበት አልተንቀሳቀስኩም፤ ከሳሾቼን ከላዬ ላይ የጣለልኝ፣ ስቃዬን ማየት ያልወደደውን ጌታዬን ዝም ብዬ ሳየው ካቀረቀረበት ቀና ብሎ፡- «አንቺ ሴት፥ እነዚያ ከሳሾችሽ ወዴት ሄዱ?» ሲል ጠየቀኝ፡፡ ዐይኖቹ እንደ ጻፎችና ፈሪሳውያን በንቀት አላዩኝም፤ እጆቹ ድንጋይ አልጨበጡም፤ ድምፁ አላስበረገገኝም፤ የጌታዬ ደግነቱ ገዛኝ፤ እግሩ ሥር ተደፍቼ ቀኑን ሙሉ ሳነባ ብውል በወደድኩ ነበር፤ ግን ረክሼያለሁ፤ የእግሩ መረገጫ ምንጣፍ በሆንኩም ስል አሰብኩ፤ ግን በድዬዋለሁ፤ የበደልኩት እንዲህ ያለውን ደግ አባት እንደ ሆነ ሳውቅ አዘንኩ፡፡ ኃጢአት የዘጋው አንደበቴን በምሕረት ከፈተው፤ አሁን ከንፈሮቼ አይንቀጠቀጡም፤ እንባዬም ቆሟል፤ «ጌታዬ ሆይ፥ አንድ ሰው እንኳ አልነካኝም» ስል መለስኩለት፡፡ በርኅራኄ እየተመለከተኝ «እኔም አልፈርድብሽም ሂጂ፤ ደግመሽ ግን ኃጢአትን አትሥሪ» አለኝ፡፡

ከደስታ ብዛት የምናገረው አልነበረኝም፤ በኃጢአት የጨቀየው እኔነቴን በፍቅር አጠበው፤ በውርደት የተደፋው አንገቴን በይቅርታ አቃናው፤ ደስታዬን መገመት የሚቻለው የለም፡፡ ከመወገር መዳኔ የፈጠረብኝ ስሜት እላዬ ላይ የተበጫጨቀውን ልብሴን እንድዘነጋው አደረገኝ፡፡ እግሮቼም ወዴት እንደሚያዘግሙ አላውቅም፡፡ ረጃጅም ቀሚሶች አይታዩኝም፤ ድንጋይ የጨበጡ፥ በንቀትና በመጸየፍ የሚያዩኝም ዐይኖች የሉም፤ የስቃይ ሞቴም በጌታዬ ተወግዷል፡፡ ከቤተ መቅደሱ ወጥቼ በወይራ ዛፎቹ መሐል ቁልቁል ስወርድ ግን ጸጸት የቆመ እንባዬን ከእግሮቼ ጋር ቁልቁል ሰደደው፡፡ ስላለፈው ኃጢአቴ አለቀስኩ፡፡ በደሌን ሳያይ ይቅር ያለኝ ጌታ ፍቅሩ አንበረከከኝ፤ ውለታው ከዐቅሜ በላይ ነው፤ ሞቴን በምሕረት ገቶታል፤ ሁሉም የእርሱ ነው፡፡ ወደ ቤቴ እስክደርስ ድረስ ለብቻዬ እያወራሁ ነበር፡፡ «ጌታዬ ሆይ፥ አመሰግንሀለሁ፤ ደግሞ በፍጹም በፍጹም… ዳግመኛ አልበድልህም!!» አልኩት፡፡

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org



ይህ ዓምድ በሥርጭቱ ፍጥነትና በጥቃቱ ስፋት አሳሳቢ ደረጃ የደረሰውን ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ ማኅበረ ቅዱሳን ከአክሽን ኤይድ ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር የጀመረው ሰፊ ሥራ አካል ሆኖ ከዚህ እትም ጀምሮ የተከፈተ ነው:: ማኅበራችን ይህንን ሥራ ሲጀምር ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ባገኘው መልካም ፈቃድና መመሪያ መሠረት ሲሆን፤ አጠቃላይ የሥራ ሂደቱም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መምሪያ ክትትል እንዲደረግበት ሆኖ ነው::

# መፍትሔው ከዚህ አለ

ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ስናወራ ይኸውና 20 ዓመታትን አስቆጠርን:: መዛግብት እንደሚገልጹት በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ ቫይረሱ የተገኘው እ.ኤ.አ በ1984 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ትኖር በነበረች ሸዋዬ በምትባል አንዲት ሴት ደም ውስጥ ነበር:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ቀናት ቀናትን ሲወልዱ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖች ቁጥር በከፍተኛ ፍጥነት እየጨመረ መጥቶ ዛሬ ከ1.5 ሚልዮን በላይ ኾኖአል::

የዛሬ 20 ዓመት በሸዋዬ ደም ውስጥ የገባው ይህ ቫይረስ ሸዋዬን ጨምሮ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያንን ለኀልፈት ዳርጓል:: በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሕፃናትን ያለ ወላጅ አስቀርቷል:: አረጋውያንንና አረጋውያትን ጧሪ ቀባሪ አሳጥቷቸዋል:: ዛሬም ለቫይረሱ መስፋፋት ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ አደገኛ አካሄዶች እንደ መኖራቸው መጠን ጉዳቱ ከዚህም የከፋ ሊሆን እንደሚችል እሙን ነው:: ይህንን ጥቃት ለመከላከልም ዓለም በአንድነት የተነሣ እስኪመስል ድረስ መጠነ ሰፊ ዘመቻ ሲደረግ ይሰማል፤ ይታያልም:: በሀገራችንም ቫይረሱ በሸዋዬ ደም ውስጥ በተገኘ በሁለተኛው ዓመት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የቫይረሱን ሥርጭት የሚያጠናና የመፍትሔ ሐሳብ የሚያ ቀርብ ኀይለ ግብር አቋቋሞ ነበር:: ከዚያ ወዲህ በየሥፍራው ተቋቁመው የሚንቀሳቀሱ በርካታ ምግባረ ሠናይ ድርጅቶች ተፈጥረዋል:: እነዚህ ድርጅቶች የሚሠሩበት ገንዘብ አልቸገራቸውም:: የመንግሥትም ሆነ የግል መገናኛ ብዙኃን ስለ ቫይረሱ የሥርጭት ሂደት፣ እያደረሰ ስላለው የከፋ ጉዳት፣ መደረግ በሚገባው መከላከል ዙሪያ በስፋው ያስተምራሉ::

ከምንም በላይ «ማን ያርዳ የቀበረ÷ ማን ይናገር የነበረ» እንዲሉ የዚሁ ችግር ተጠቂ የሆኑ ወገኖች የሰዎችን ፊት ሳይሰቀቁ፣ መገለልንና አድልዎን ሳይፈሩ «ትውልድ ይዳን÷ በእኛ ይብቃ» የሚል የተቀደሰ ዓላማ አንግበው በመካከላችን ቆመው ማስተማር ከጀመሩ ውለው አድረዋል:: ይሁን እንጂ «የቫይረሱ ሥርጭት ጨመረ፤ የሞቱ ሰዎች ቁጥር ጨመረ፤ ከዚህ ዓመት በኋላ ቁጥሩ ቀላል የማይባል ሕዝብ በዚሁ ቫይረስ ይጠቃል፤ ይሞታል... ወዘተ፤» የሚል መርዶ እንሰማለን:: በአንጻሩ መሻሻል ስለ መምጣቱ÷ ሕዝቡ የቫይረሱን ስደድ ሰምቶና ተመልክቶ ራሱን እየጠበቀ፤ ቫይ ረሱን እየተቆጣጠርነው ስለ መሆኑ ብዙም የምሥራች አንሰማም::

ከዛሬ አምስትና ዐሥር ዓመት በፊት ለቫይረሱ ሥርጭት መፋጠን ሰበቡ ሕዝቡ ማግኘት የሚገባውን መረጃ በተገቢው መንገድ አለማግኘቱ ነበር:: ቢያገኝም ስለ ቫይረሱ ሊኖረው የሚገባውን ግንዛቤ የሚያዛባ መረጃ ነበር:: አሁን አሁን ግን ከአጠቃላይ የቫይረሱ ጠባይ ጀምሮ እስከ ዝርዝርና ተጓዳኝ ጉዳዮች ድረስ በዘርፉ የተሰማሩ አካላት ተጨንቀው መረጃውን በሚገባ እያሰናዱ ለሕዝቡ ያቀርባሉ:: በዚህ የተነሣም ዛሬ ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ተጠይቆ ቢያንስ የመተላለፊያ መንገዶቹንና ገዳይ ስለ መሆኑ የማያውቅ ኢትዮጵያዊ ይገኛል ብሎ ለመናገር ይከብዳል:: ምናልባት «ኤድስ፣ አመንምን፣ ቦንቡ፣ ጥላት ቀቢው፣ የዘመኑ፣ አውሬው፣ ጆከሩ... ወዘተ» እያለ እንደ አካባቢው ባሕልና ቋንቋ የራሱን ስም ሊሰጠው ይችል ይሆናል እንጂ::

ነገር ግን መረጃው ሁሉ ሕዝቡ በሚገባው መንገድ እየተሰናዳ ቢቀርብም፣ ሕዝቡም ስለ ቫይረሱም ሆነ ስለ ሚያመጣው ጉዳት ዕውቀቱ ቢያኖረውም በመርዶ ፈንታ የምሥራች አልተሰማም፤ በሙሾ ፈንታ የሚያስፈንድቅ የደስታ ዜማ አልተዜመም:: ለመሆኑ ይህ ለምን ሆነ? ገንዘቡ፣ መረጃው፣ ዕውቀቱ እያለ ለምን ሕዝቡ የጠባይ ለውጥ ሊያመጣ አልቻለም? ይህንን እውነታስ የሚመለከታቸው አካላት ምን ያህል ተገንዝበውት ይሆን? ከተገነዘቡትስ የአሠራር ስልታቸውን ለማ ካከል ወይም ለመቀየር ምን ያህል ዝግጁዎች ሆነዋል? እነዚህ ጥያቄዎች ከመንግሥት ጀምሮ ባሉ አካላት በአፋጣኝ ካልተመለሱ ሀገራችንም ሆነች እኛ ሕዝቦቿ ሙሾአችንን ስናወርድ እንኖራለን::

በእኛ በኩል ግን በመፍትሔነት ሊሰጡ ከሚችሉት በርካታ ነጥቦች አንዱን ልንጠቁም እንወዳለን:: የሰው ልጅ ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ /ውኃ፣ ነፋስ እሳት፣ መሬት/ እና ከሦስቱ ግብራተ ነፍስ /ለባዊነት፣ ነባቢነት፣ ሕያውነት/ የተፈጠረ፤ በእነዚህ ባሕርያቱ ተደጋጋፊነትም ግእዛኑን ጠብቆ የሚኖር ፍጡር ነው:: ሰው ይህ ሚዛናዊ ተፈጥሮው ተጠብቆ ጠባይዕ አእምሮ አዊውና ጠባይዕ ሥጋዊው ተስማም ተውለት ይኖር ዘንድም ከአምላኩ ጋር ዕለት ዕለት በመገናኘት÷ መንፈሳዊ ብልጥግናን ንብረቱ አድርጐ መኖር አለበት:: የሥጋ ባሕርያት አንድነት የሚጓተት ሳይሆን የሚተባበር፣ የሚነካከስ ሳይሆን የሚስማማ በአጭሩ አምላክ ቀምሮ እንደ ሠራለት ነው:: ይህ ካልሆነ ግን ጠባይዕ እንስሳዊን ይዞ ይኖራል:: ዕለታዊ ፍላጐቱ ተሟልቶ ይረካ ዘንድ ብቻ ይጥራል:: ሆኖም የሚመክሩትንም÷ የሚወቅሱትን አይሰማም:: የዛሬን ልደሰት÷ ልፈንጥዝና ልዝናና ይላል::

በአንጻሩ የሥጋው ባሕርያት ሚዛናቸውን የጠበቁ፣ የሚተባበሩና የሚስማሙ ከሆኑለት ግን መጥፎውን ከደግ የሚለይ፣ ጥቅምንም ሆነ ጉዳትን በዕለት ስሜቱ ሳይሆን አምላክ በሰጠው አእምሮአዊ ጥበቡ የሚመዝን ይሆናል:: የሰው ልጅ ባሕርያቱ ሚዛናቸውን የጠበቁ እንዲሆኑለት ደግሞ ዕለት ዕለት ሥጋዊ ጠባዩን የሚጐስሙለት፣ የባሕርያተ ሥጋውን ሚዛን የሚጠብቁለት መንፈሳውያት ኃይላት ያስፈልጉታል:: እነዚህም መንፈሳውያት ትምህርቶችና በእነርሱ አማካይነት የሚያመጣቸው መንፈሳውያት ምግባራት ናቸው::

የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ሥርጭት በአስተማማኝ ሁኔታ ለመግታት አሁን ያለው የትምህርት አሰጣጥ ሥልት ሙሉ በሙሉ ይለወጥ የሚል ጠባብ አቋም ባይኖረንም በእንቅስቃሴያችን ውጤታማ እንድንሆን ለሃይማኖቱ፣ ለታሪኩና ለባሕሉ ልዩ ትኩረት የሚሰጠውን ሕዝባችንን በእምነት ቋንቋ እናስተምረው እንላለን:: ኢትዮጵያን በአንድ ወቅት የጐበኘ አንድ አውሮፓዊ «ኢትዮጵያውያን መጽሐፍ ቅዱስን በሕይወታቸው እየተረጐሙ ይኖሩታል እንጂ እንደ አውሮፓውያኑ ሲናገሩት ብቻ አይሰሙም::» ብሏል:: የዚህን ምክንያት ሲያስረዳም «የኢትዮጵያውያን ባሕል የሚገለጹባቸው ነገሮች በሙሉ መጽሐፋዊ ናቸው:: ከስም አሰያየማቸው ጀምሮ ክርስቲያንነታቸውን በልብሶቻቸው፣ በሰውነቶቻቸው፣ በሥነ ቃላቸው ወዘተ ይገልጹታል:: የሃይማኖት አባቶቻቸውን ቃል እንደ እግዚአብሔር ቃል ያከብራሉ:: ሰምተው በጥንቃቄ ይፈጽማሉ:: ከሞት በኋላ ስለሚኖረው ሕይወት ትልቅ ትኩረት



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org



ብፁዕ አቡነ ናትናኤል የአርሲ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በሆስፒታል ተገኝተው ሕሙማንን እንዳጽናኑ

ሰጥተው ለቃለ እግዚአብሔር ይገዛሉ» ብሏል። ይህ ደግሞ ሀገሪቱን የሚወዱም ሆኑ የማይወዱ በአንድነት ተባብረው ሲመሰክሩት የኖሩትና የተናገሩት እውነት ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፦ «ለኢትዮጵያውያን የማንነት አንድነት ታላቅ አስተዋፅዖ አድርጋለች» ሲባል ሕዝቡ ከሥጋዊነቱ ይልቅ መንፈሳዊነቱን አክብሮና ወዶ እንዲኖር ማድረጓ ነው። በመሆኑም በዚህች ሀገር ባላት ተሰሚነት ሕዝቡ በሥጋውም ይሁን በነፍሱ ከሚመጣበት ፈተና ሁሉ ነጻ እንዲሆን በዘማችነትም ሆነ በአዝማችነት ግንባር ቀደም ሆና ስትሳተፍ ኖራለች። አሁንም በመሳተፍ ላይ ትገኛለች።

ታድያ ባለ በሌለ ኃይሉ እያጠቃን ያለውን የዚህን ቫይረስ መዛመትና ጉዳት በመዋጋትም ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ወሳኝ ሚና እንዳላት እናምናለን። በተለያዩ አካላት የተደረገው ጥረት ሁሉ ምንም ዓይነት ውጤት አላስገኘም ባይባልም ብዙ ገንዘብ ወጥቶ፣ በርካታ የሰው ኃይል ተመድቦና ብዙ ስብሰባዎች ተካሂደው የሥራው ውጤት የዚያን ያህል ሲሆን አልታየም። ሠራተኞች በበዙ ቁጥር የሚሞተው እየበዛ እናያለን። ብዙ ገንዘብ በፈሰሰ ቁጥር ብዙዎች በቫይረሱ ሲያዙ እንመለከታለን። ስለዚህ የሚያልቀው ወገን እስከ ሆነ ድረስ ጊዜ ሳንወስድ አካሄዳችንን መፈተሽና የሚስተካከለውን ማስተካከል አለብን እንላለን።

በእኛ በኩል አነዋወሩ ሁሉ በክርስትና ሕግጋት በታሸው በዚህ ኦርቶዶክሳዊ ምእመን መካከል ቫይረሱን በመዋጋት ሁነኛ ለውጥ ለማምጣት ክርስቲያናዊ መፍትሔ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርትና በውስጡም የሚገኘውን ምክርና ተግሣጽ ልንከተል፥ ልንጠቀምበትም ይገባል። ለዚህ ደግሞ ለሕዝቡ የክርስትናን ሀ...ሁ ከማስቆጠር ጀምሮ ቃለ እግዚአብሔርን እየፈተፈተች ስታጉርስ ለኖረችዋ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀዳሚው ቦታ ሊሰጣት ይገባል።

ቤተ ክርስቲያናችን ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ኢትዮጵያውያንን ከመጣባቸው ችግር ለመታደግ ቆርጣ ተነሥታለች። ለዚህ ውሳኔዋ ተግባራዊነትም ችግሩ በየጉባኤዎቿ ቀዳሚ የመወያያ ርዕሷ ሆኗል። ታድያ ምናልባት ይህንን ዝግጁነቷንና በዚች ሀገር የነበራትንና ያላትን የለውጥ ሐዋርያነት ያልተገነዘቡ አካላት ካሉ በፍጥነት ተገንዝበው ለቤተ ክርስቲያናችን የቴክኒክና የፋይናንስ እገዛ በመስጠት ሊያግዟት ይገባል እንላለን።

እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት በጥቅምት ወር በሚደረገው የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ አባቶች ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ቤተ ክርስቲያናችን ችግሩን በመቅረፍ ረገድ እስከ አሁን ያደረገችውን እንቅስቃሴ ገምግመዋል። ያጋጠሙትን ችግሮች ለይተው አስቀምጠዋል። ከዚህም ባለፈ የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ እየተካሄደ ከነበረባቸው ዕለታት መካከል ለሦስት ቀናት ያህል በየአካባቢው ተሰማርተው ልጆቻቸውን አስተምረው ተመልሰዋል። ሐዋርያዊ ጉዞአቸውም ሌሎች ተመሳሳይ ጉዞዎች ቢካሄዱ ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል አስገንዝቧል። ስለዚህም በቫይረሱ በስፋት የመጠቃታችን ችግር መፍትሔ ከዚህ አለና የሁሉም ርዳታና ርብርብ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በቀዳሚነት የሚያካትት ይሁን እያልን ከተጓዙት አባቶች መካከል ብፁዕ አቡነ ኤልያስ የጋሞ ጎፋና ደበብ ኦሞ ሀገረ ስብከት ጳጳስ የሰጡንን ሐሳብ እንደ ማጠቃለያ አቅርበነዋል።

*ከጥቅምት 18-21 ቀን 1997 ዓ.ም የተደረገው ሐዋርያዊ ጉዞ መልካም ነበር። እኔ የደረስኝ ምሥራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት ናዝሬት ነበር። ሕዝቡ በተመስጦ ትምህርቱን ይከታተል ነበር። በእርግጥ አንዳንዱ ስለ በሽታው መነሣቱ ቀርቶ ትምህርት ብቻ ለመማር ፍላጐት ነበረው። ሆኖም ግን ቃለ እግዚአብሔር ሰዎች ከዝሙት እንዲሸሹ የውስጥ ንጽሕናቸውን እንዲጠበቁ የሚያዝ በመሆኑ እኛም መንፈሳዊ ይዘቱን ያለቀቀ በሽታውን የተመለከተ ትምህርት አስተላልፈናል። እንዲህ ዓይነቱ ጉባኤ ብዙ የድኅነት ምርት የሚያስገኝ ስለሆነ ተጠናክሮ ቢቀጥል መልካም ነው።*

*ሌላው፦ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ በቤተ ክርስቲያን አባቶች፥ በአበው ካህናት መሐል እጅ እንደ ሆነ ከሀገር ተርፎ መላው ዓለም የሚያምንበት ጉዳይ ነው። በዚህ መሠረት ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ የዋለችውን ውለታ ያህል ኢትዮጵያ ለራሷ አልዋለችም። በቀድሞ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የሀገር፥ የሕዝብ ጠባቂ በመሆኗ ሕዝብን እንድትጠብቅ የእግዚአብሔርን ቃል እንድታስተላልፍ የሬድዮ ጣቢያ ነበራት። በትምህርት ቤት ተማሪው ክፍል ከመግባቱ በፊት የግብረ ገብ ትምህርት ታስተምር ነበር። በየሆስፒታሉ ሕሙማንን የሚባርኩና የሚያጽናኑ አባቶችን መድባ ታስተምር ነበር። ለሚሞቱትም የኑዛዜ ሥርዓት ትፈጽም ነበር። በማረሚያ ቤትም እንደዚሁ፤ ዛሬ ይህ ሁሉ መንፈሳዊ የአገልግሎት ድርሻዋን መንግሥት መልሶ ቢፈቅድላት ቤተ ክርስቲያኒቱ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከልና የችግሩ ተጠቂዎችንም መኖር እንደሚቻል ተስፋ እየሰጠች በመንከባከብ መልካም ውጤት ልታስመዘግብ ትችላለች። ምክንያቱም ክርስቲያኑ ሕዝብ ለቤተ ክርስቲያን ድምፅ ታዛዥ ነውና።*

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*


አዲስ መጽሐፍ

**መርሐ ልዑካን**

* አገልግሎት ምንድነው?
* ከአገልጋይ ምን ይጠበቃል?
* አገልጋይ ማነው?
* አገልጋዮች ለምን ይጠራሉ?
* የአገልግሎት ዝግጅት
* አገልጋይና የሥራው ዘርፍ

እነዚህንና ሌሎች ነጥቦችን በማካተት በአገልግሎት ዙሪያ የተዘጋጀ መጽሐፍ በሥርጭት ላይ ውሏል።

አዘጋጅ፦ ዲ/ን ክፍያለው ጥላሁን

መጽሐፉ የሚገኝበት አድራሻ

* በሁሉም የሐመር መጽሔትና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ማከፋፈያዎች /ማኅበረ ቅዱሳን/
* በቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት መሸጫ ሱቆች /መርካቶ/
* በአርያም መንፈሳዊ መዝሙር ቤት /አውቶብስ ተራ/
* በዋሸራ መጻሕፍት መሸጫ መደብር /አዲስ ከተማ ት/ቤት ፊት ለፊት/




© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ፈተና የሚመጣው ከየት ነው?

## በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው::» /ያዕ. 1÷12/

/መምህር ደጀኔ ሽፈራው/

ባለፈው እትም እንደ ተመለከትነው ፈተናን እንደ ወጥመድ፥ እንደ መረብ፥ እንደ መሰናክል የሚያመጣው ጥንተ ጠላታችን ሰይጣን ነው:: ምክንያቱም ጥንት አዳምንና ሔዋንን በምኞት ፈትኖ የጣላቸው እርሱ ነውና:: ዘፍ.3፥1 ፣ራእ.12፥7-9:: በአዲስ ኪዳንም ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገዳመ ቆሮንቶስ በፈቃዱ በተፈተነው ፈተና ስስትን በትዕግሥት፥ ፍቅረ ንዋይን በጸሊአ ንዋይ፥ ትዕቢትን በትሕትና ድል በማድረግ ፈተና ከሰይጣን መሆኑን አሳይቶናል:: ይኸውም ለእኛ አብነት ሲሆነን ነው:: ማቴ.4፥1-11:: ቅዱስ ማቴዎስ በዚህ ምዕራፍ ላይ ሰይጣንን ፈታኝ ብሎታል::

ሰይጣን ሰውን ለመፈተን የሚገባበት በር፥የሚሾልክበት ቀዳዳ አለው:: ይህም የእያንዳንዱ ሰው ድካም ነው:: ስለሆነም የፈተና መምጫውን መንገድ ዐውቀን ለሕይወታችን መጠንቀቅ ይገባናል:: ባለፈው እትማችን ፈተና ከየት እንደሚመጣ በዝርዝር ተመልክተናል:: በዚህም መሠረት፦ 1ኛ. ፈተና ከራስ ይመጣል፤ 2ኛ. ፈተና ከባልንጀራ ይመጣል፤ 3ኛ. ፈተና ከሥልጣን ይመጣል፤ የሚሉትን ለማየት ሞክረናል:: የተቀሩትን ደግሞ እንደሚከተለው እንመለከታለን::

4ኛ/ ከገንዘብ፦ አያያዙን ካላወቅንበት÷ ሠርተን ሳይሆን ሰርቀን ማግኘት ከፈለግን÷ በተሰጠን ማመስገን ሲገባን ያልተሰጠንን የምንሻ ከሆነ÷ ዓሥራት ለማውጣት ምጽዋት ለመመጽወት የምንሰስት ከሆነ÷ ከእግዚአብሔርና ከሰው ይልቅ ገንዘብን የምንወድ ከሆነ ፈተና ነው:: ይኸንን በተመለከተ በብሉይም በሐዲስም ብዙ ተብሏል:: ይልቁንም በአዲስ ኪዳን ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ገንዘብ የሰውን ልጅ ምን ያህል እንደ ገዛው ለመግለጥ «ጌታ» ብሎታል:: «ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም፤ ወይም አንዱን ይጠላል፤ ሁለተኛውንም ይወዳል፤ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል፤ ሁለተኛውንም ይንቃል፤ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም፤» እንዳለ:: ማቴ.6÷24:: ጌታችን በገዳመ ቆሮንቶስ በፈቃዱ ከተፈተናቸው ፈተናዎች አንዱ ፍቅረ ንዋይ ነበር:: በወንጌል እንደ ተጻፈው፦ «ዲያብሎስ እጅግ ረጅም ወደ ሆነ ተራራ ወሰደው ÷የዓለምንም መንግሥታት ሁሉ ክብራቸውንም አሳይቶ ፦ ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ አለው:: ያን ጊዜ ኢየሱስ፦ ሂድ አንተ ሰይጣን፤ ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአልና አለው::» ማቴ.4÷8–10:: ጌታችን በሁለቱ ፈተናዎች ላይ የፈታኙን ስም ሳይጠራ መልስ በመመለሱ ማንነቱን ያወቀበት አልመሰለውም ነበር:: ለዚህም ነው በሦስተኛው ፈተና ላይ፦ «ሰይጣን» ብሎ ስሙን ጠርቶ የገሠጸው:: እርሱም እንደ ጢስ በኖ÷እንደ ትቢያ ተበትኖ ጠፍቷል:: ጌታችን በምድራዊ ክብር በወርቅና በብር በፈቃዱ የተፈተነው ለእኛ አብነት ለመሆን ነው:: ይኸውም ጥንተ ጠላታችሁ ዲያብሎስ በምድራዊ ክብር በወርቅና በብር ይፈትናችኋልና ዕወቁበት ሲለን ነው:: ስለዚህ ሰይጣን በፍቅረ ንዋይ እንዳያጠምደን መጠንቀቅ አለብን:: በፍቅረ ንዋይ የተያዘ ሰው ማንንም መውደድ አይችልምና:: ለምሳሌ አንድ ከወንድሙ ይልቅ የወንድሙን ሀብት ንብረት የሚወድ ሰው፦ «መምህር ሆይ÷ ርስቱን ከእኔ ጋር እንዲካፈል ለወንድሜ ንገረው::» በማለት በጌታ ፊት ተናግሮ ነበር:: ጌታችን ግን «የሰው ሕይወቱ በገንዘቡ ብዛት አይጠ ደለምና ተጠንቀቁ፤ ከመጐምጀትም ሁሉ ተጠበቁ::» በማለት እርሱንም ሌሎችንም አስጠንቅቋቸዋል:: ከዚህም ጋር ገንዘብን የሚወድ ሰው ፍጻሜው ምን እንደ ሆነ በምሳሌ አስተምሯቸዋል:: «አንድ ባዕለ ጸጋ ሰው እርሻው እጅግ ፍሬያማ ሆነችለት:: እርሱም፦ ፍሬዬን የማከማችበት ስፍራ አጥቻለሁና ምን ላድርግ ብሎ አሰበ:: /ዓሥራት አወጣለታለሁ÷ ለድሆች እመግባለሁ አላለም/:: ጐተራዬን አፍርሼ ሌላ የሚበልጥ እሠራለሁ÷ በዚያም ፍሬዬንና በረከቴን ሁሉ አከማቻለሁ፤ ነፍሴንም /ሰውነቴንም/፦ አንቺ ነፍሴ÷/አንቺ ሰውነቴ/÷ ለብዙ ዘመን የሚቀር ብዙ በረከት አለሽ፤ ዕረፊ÷ብዪ÷ጠጭ÷ደስ ይበልሽ÷ እላታለሁ አለ:: እግዚአብሔር ግን፦ አንተ ሰነፍ በዚህች ሌሊት ነፍስህን ከአንተ ሊወስዱአት ይፈልጓታል፤ ይህስ የሰበሰብኸው ለማን ይሆናል? አለው:: ለራሱ ገንዘብ የሚያከማች÷ በእግዚአብሔር ዘንድም ባዕለ ጸጋ ያልሆነ እንዲህ ነው::» እንዳለ:: ሉቃ. 12÷13–21::

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ፍቅረ ንዋይ ምግባርን ብቻ ሳይሆን ሃይማኖትንም ጭምር እንደሚጐዳ ተናግሯል:: በተለይም በእርሱ እግር ለሚተካው ለልጁ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍለት፦ «ወደ ዓለም ምንም እንኳ አላመጣንምና÷ አንዳችንም ልንወስድ አይቻለንም፤ ምግብና ልብስ ከኖረን ግን÷ እርሱ ይበቃናል:: ዳሩ ግን ባዕለ ጸጎች ሊሆኑ የሚፈልጉ በጥፋትና በመፍረስ ሰዎችን በሚያሰጥምና በሚያሰንፍ በሚጐዳም በብዙ ምኞትና በፈተና በወጥመድም ይወድቃሉ:: ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና÷ አንዳንዶችም ይህን ሲመኙ÷ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ::» ብሎታል:: 1ኛ ጢሞ.6÷7–10:: በዚህም መሠረት ከጥንት ጀምሮ ብዙ ሰዎች በፍቅረ ንዋይ ሲጐዱ እናያለን:: በመጽሐፈ ኢያሱ እንደ ተጻፈው የዛራን ልጅ አካንን በድንጋይ ተወግሮ በእሳት ተቃጥሎ እንዲሞት ያደረገው ለፍቅረ ንዋይ ብሎ የእግዚአብሔርን ሥርዓት በመተላለፉ ነው:: ከዚህ በኋላ በእርሱ ምክንያት ተቆጥቶ የነበረ እግዚአብሔር ከቁጣው ተመልሷል:: ኢያ.7÷1–26:: እግዚአብሔር ስለ ሳኦል፦ «ሳኦል እኔን ከመከተል ተመልሶአልና÷ ትእዛዜንም አልፈጸመምና፤ ስላነገሥሁት ተጸጸትሁ፤» ብሎ ለባለሟሉ ለሳሙኤል የተናገረው የሳኦል ልብ በፍቅረ ንዋይ ተነድፎ የአማሌቃውያንን ሀብት ንብረት በመሰብሰቡ ነው:: ይህንን እንዳያደርግ እግዚአብሔር አስጠንቅቆት ነበር:: 1ኛሳሙ.15÷10–11:: ነቢዩ ሳሙኤልም፦ «የእግዚአብሔርን ቃል ንቀሃልና እግዚአብሔር ንጉሥ እንዳትሆን ናቀህ፤» ብሎታል:: 1ኛሳሙ. 15÷23:: የነቢዩ የኤልሳዕ ደቀ መዝሙር ግያዝ በመምህሩ በኤልሳዕ ርግማን ከራስ ፀጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ በለምፅ የነደደው÷ልቡ በፍቅረ ንዋይ ተቃጥሎ በጉን ከሶርያው ሰው ከንዕማን ወርቅና ብር በመቀበሉ ነበር:: 2ኛነገ.5÷20–27:: ከዚያም በፊት በሕግ ልቡና ዘመን የያዕቆብ ልጆች ዮሴፍን ከመሰለ ወንድማቸው ይልቅ ብርን አስበልጠው ለእስማኤላውያን ነጋዴዎች በሃያ ብር ሸጠውታል:: ዘፍ.37÷28:: ያ ብር ግን ከረሀብ ዘመን አላዳናቸውም:: ዘፍ.42÷1–2:: ከዮሴፍ ጋር ግን የእግዚአብሔር በረከት ነበር:: «ዮሴፍም በጌታው ፊት ሞገስን አገኘ፤ እርሱንም ያገለግለው ነበር፤ በቤቱም ላይ ሾመው÷ያለውንም ሁሉ በእጁ ሰጠው:: እንዲህም ሆነ፤ በቤቱ ባለውም ሁሉ ላይ ከሾመው በኋላ እግዚአብሔር የግብፃዊውን ቤት ባረከው፤ የእግዚአብሔር በረከት በውጭም በግቢም ባለው ሁሉ ላይ ሆነ::» እንዳለ:: ዘፍ.39÷4–6:: በአዲስ ኪ.



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ዳንም ዘመን ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ ይሁዳ ከሙዳየ ምጽዋት ይሰርቅ የነበረው÷በኋላም ጌታን በሠላሳ ብር የሸጠው ልቡናው በፍቅረ ንዋይ የተቃጠለ ሰው በመሆኑ ነበር። ዮሐ.12÷5–7፤ ማቴ.26÷14–16። ዛሬም በይሁዳ መንገድ ተጉዘው ሙዳየ ምጽዋቱን የሚመዘብሩ÷ወልድ ዋሕድ የምትል ሃይማኖታቸውን የሚሸጡ ሰዎች አሉ። ጌታችን ሞትን ድል አድርጐ በተነሣ ጊዜ በመቃብሩ ዙሪያ የነበሩ ጠባቂዎች፦ «እኛ ተኝተን ሳለን ደቀ መዛሙርቱ በሌሊት መጥተው ሰረቁት።» ብለው የዋሹት አይሁድ በገንዘብ ስለ ደለሏቸው÷ፍቅረ ንዋይ አሸንፎአቸው ነው። ማቴ.28÷11–15። ዛሬም በየፍርድ ቤቱ የሚቀርቡትን ምስክሮች ብንመለከት በገንዘብ ተደልለው በሐሰት የሚመሰክሩ አይጠፉም። ከጠበቆችም ቅንጣት ያህል እውነት የሌለውን ጉዳይ ስለ ገንዘብ እውነት ነው ብለው የሚከራከሩ ይኖራሉ። ከዳኞችም ፍርድ የሚያጓድሉ ድሀ የሚበድሉ ይኖራሉ። በዘመነ ሐዋርያትም ሐናንያንና ሰጲራን ከምእመናን ተለይተው እንዲቀሰፉ ያደረጋቸው ፍቅረ ንዋይ ነው። የሐዋ.5÷1–11።

ከዚህም ሌላ ለሠራተኞቻቸው መክፈል ከሚገባቸው ግማሹን እንኳን የማይከፍሉ ግለሰቦች እና ድርጅቶች አሉ። ከዚህም አልፈው በየምክንያቱ የሠራተኞቻቸውን ላብ የሚያስቀሩ ጥቂቶች አይደሉም። እንዲህም የሚያደርጋቸው ፍቅረ ንዋይ ነው። ስለ እነዚህም ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ፦ «አሁንም እናንተ ባዕለ ጠጎች÷ ስለሚደርስባችሁ ጭንቅ ዋይ ዋይ እያላችሁ አልቅሱ። ሀብታችሁ ተበላሽቷል÷ ወርቃችሁም ብራችሁም ዝጓል÷ዝገቱም ምስክር ይሆንባችኋል፤ ሥጋችሁንም እንደ እሳት ይበላል። ለኋለኛው ቀን መዝገብን አከማችታችኋል። እነሆ÷ እርሻችሁን ያጨዱት የሠራተኞች ደመወዝ በእናንተ ተቀምቶ ይጮኻል÷ የአጫጆችም ድምፅ ወደ ጌታ ፀባዖት ጆሮ ገብቶአል። በምድር ላይ ተቀማጥላችኋል÷ በሴሰኝነትም ኖራችኋል፤ ለእርድ ቀን እንደሚያወፍር ልባችሁን አወፍራችኋል። ጻድቁን ኰንናችሁታል÷ገድላችሁትማል፤ እናንተን አይቃወምም።» ብሏል። ያዕ.5÷1–6። ስለዚህ ክርስትና ማለት በፍቅረ እግዚአብሔር÷በፍቅር ቢጽ መኖር እንጂ በፍቅረ ንዋይ መኖር አለመሆኑን ዐውቀን እንደ ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት «ከአእላፋት ወርቅና ብር ይልቅ የአፍህ ሕግ ይሻለኛል።... ከወርቅና ከዕንቁ ይልቅ ትእዛዝህን ወደድሁ።» ልንል ይገባል። መዝ.118÷72፤ 127። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ፦ «ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን÷ነውርና እድፍ እንደ ሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደ ተዋጃችሁ ታውቃላችሁ።» በማለት የተናገረውንም በልቡናችን ጽላት መቅረጽ አለብን። 1ኛጴጥ.1÷18–19። እዚህ ላይ ማወቅ የሚገባን ነገር ቢኖር ወጥቶ ወርዶ ገንዘብ ማግኘት ኃጢአት አለመሆኑን ነው። ነገር ግን ወጥተው ወርደው ያገኙትን ገንዘብ ማምለክ÷ ወጥተው ወርደው ባገኙት ገንዘብ መንፈሳዊ ሥራ አለመሥራት÷ የእግዚአብሔርን ዓሥራት አለማውጣት ኃጢአት ነው። «ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃልን? እናንተ ግን እኔን ሰርቃችኋል። እናንተም የሰረቅንህ በምንድን ነው? ብላችኋል። በዓሥራትና በበኵራት ነው። እናንተ ይህ ሕዝብ ሁሉ÷ እኔን ሰርቃችኋልና፤ በእርግማን ርጉሞች ናችሁ።» እንዳለ። ሚል.3÷8–4። በአጠቃላይ፥ የግለሰብንም ሆነ የመንግሥትን እንዲሁም የእግዚአብሔርን ገንዘብ አለአግባብ መውሰድ በፍቅረ ንዋይ መታወር÷በገንዘብ የመጣውን ፈተና መውደቅ ነው። ስለዚህ እንደ ነቢዩ እንደ ኤልሳዕ እንቢ ልንል ይገባል። 2ኛነገ.5÷16። ኃጢአተኞችም በገንዘብ ሲደልሉን እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ፦ «ብርህ ከአንተ ጋር ይጥፋ።» ማለት ይጠበቅብናል። ዮሐ.8÷21።

5ኛ ከዘር፦ ብዙ ሰዎች በሌላው ነገር ደኅና ይሆኑና በዚህ ይሸነፋሉ። በዘረኝነት ተፈትነው ይወድቃሉ። ዘር ቆጥረው የሚያቀርቡት÷ዘር ቆጥረው የሚያርቁት አሉ። ከሌላው ዘር ዐዋቂና ቀና ይልቅ የራሳቸውን ዘር ዐላዋቂና ጠማማ ይመርጣሉ። «ለእውነት እየታዘዛችሁ ግብዝነት የሌለበት ለወንድማማች መዋደድ ነፍሳችሁን አንጽታችሁ እርስ በርሳችሁ ከልባችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ። ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም÷በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ። ሥጋ ሁሉ እንደ ሣር ክብሩም ሁሉ እንደ ሣር አበባ ነውና፤ ሣሩም ይጠወልጋል÷ አበባውም ይረግፋል፤ የጌታ ቃል ግን ለዘላለም ይኖራል። በወንጌልም የተሰበከላችሁ ቃል ይህ ነው።» የተባለውን እያወቁ በዘረኝነት ተተብትበው ይኖራሉ። 1ኛጴጥ.1÷22–25። ኢሳ.40÷6–9። «ለተቀበሉት ሁሉ ግን÷በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም፤» የተባለውን ይዘነጋሉ። ዮሐ.1÷12–13። በጥምቀት ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ወንድማቸው÷እኅታቸው÷አባታቸው÷እናታቸው÷ወገናቸው መሆናቸውን አያስተውሉም። ይኸንን በተመለከተ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፦ «ሽማግሌ የሆነውን አትገሥጸው÷እርሱን ግን እንደ አባት÷ ጐበዞችን እንደ ወንድሞች÷ የሸመገሉትን ሴቶች እንደ እናቶች÷ ቆነጃጅቱን እንደ እኅቶች በፍጹም ንጽሕና ለምናቸው።» በማለት ለልጁ ለጢሞቴዎስ የጻፈለት ከሥጋዊ ዝምድና ስለሚበልጠው ስለ መንፈሳዊ ዝምድና ሲነግረው ነው። 1ኛጢሞ.5÷1–2። ምክንያቱም ሁላችንም በክርስቶስ አንድ አካል ነንና። ሮሜ.12÷5። በተጨማሪም፦ «አካልም አንድ እንደ ሆነ ብዙም ብልቶች እንዳሉበት ነገር ግን የአካል ብልቶች ሁሉ ብዙዎች ሳሉ አንድ አካል እንደ ሆኑ÷ ክርስቶስ ደግሞ እንዲሁ ነው፤ አይሁድ ብንሆን÷የግሪክ ሰዎችም ብንሆን÷ ባሪያዎችም ብንሆን÷ ጨዋዎችም ብንሆን እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና። ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል።» የሚል አለ። 1ኛቆሮ. 12÷12-13፡ ይህ ሐዋርያ በገላትያ መልእክቱም ላይ፦ «በእምነት በኩል ሁላችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፤ ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና፤ አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም÷ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም÷ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ሰው ናችሁና።» ብሏል። ገላ.3÷26-29። እንግዲህ ዘረኛ መሆን ይኸንን መንፈሳዊ አንድነት ማፍረስ ነው። ከእግዚአብሔር ልጅነት የሥጋን ልጅነት ማስበለጥ ነው።

ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ከተለያዩ ዐሥራ ሁለት የእስራኤል ነገዶች መምረጡ በቤተ ክርስቲያን ዘረኝነት÷ጐሰኝነት እንዳይኖር ነው። እነዚህ ደቀ መዛሙርት ከተለያየ ነገድ ቢመረጡም በክርስቶስ አንድ አካል በመሆናቸው አንድ ልብ አንድ ቃል ነበራቸው÷ በመካከላቸው መለያየት መገፋፋት አልነበረም። «በዓለ ኀምሳም የተባለው ቀን በደረሰ ጊዜ÷ ሁሉም አንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ÷ ድንገት እንደ ሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ÷ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው። እንደ እሳትም የተጠከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው፤ በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው÷ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው÷ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።» እንዳለ። የሐዋ.2÷1-4። ስለዚህ የሐዋርያት ተከታዮች የሆንን ክርስቲያኖች እኛም እነርሱን ልንመስላቸው ይገባል።

እየመሰለን ነው እንጂ ለማናቸውም ነገር ዘረኝነት መፍትሔ አይደለም። ለምሳሌ ቃየን የእናት የአባቱን



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ልጅ አቤልን የገደለው፤ /ዘፍ.4÷8፤ ኖኅ የልጅ ልጁን ከነዓንን የረገመው /ዘፍ.9÷25/ ፤ዔሳው ወንድሙን ያዕቆብን ለመግደል ያሰበው÷ እንዲሰደድም ያደረገው፤ /ዘፍ.37÷28/ የያዕቆብ ልጆች ወንድማቸውን ዮሴፍን የተመቀኙት ባሪያ አድርገውም የሸጡት፤ ዘፍ.37÷28:: እስራኤል ዘሥጋ በምድረ በዳ እግዚአብሔር የሾመላቸውን መሪ ሊቀ ነቢያት ሙሴን የተጣሉት፤ /ዘጸ.17÷2/ ዳታን÷ አቤሮንና ቆሬን በምስፍናውና በክህነቱ ምክንያት ሙሴንና አሮንን የተጣሉት፤ /ዘኁ. 16÷1-3/ አቤሜሌክ ሰብዓ ወንድሞቹን በአንድ ድንጋይ ላይ ያሳረዳቸው /መሳ. 9÷5/፤ ንጉሡ ሳኦል ብላቴናውን ዳዊ ትን ከዋለበት አላውል÷ ካደረበትም አላሳድር ብሎ ያሳደደው /1ኛ ሳሙ.19÷1፤24÷1/፤ ንጉሡ ዳዊትም በዘመነ መንግሥቱ በጦር ሜዳ ያለ የኦርዮንን ሚስት መድፈሩ ሳያንሰው÷ ኦርዮንን በጥበብ በጦር ሜዳ ያስገደለው /2ኛሳሙ.13÷28/፤ አቤሴሎም የሕዝቡን ልብ በጥበብ ሰርቆ በማሳደም መፈን ቅ ለመንግሥት አድርጐ አባትን ያሳደደው፤ 2ኛሳሙ. 15÷1-37 አድራሜሌክና ሳራሳር:- አባታቸውን ሰናክሬምን በሰይፍ የገደሉት የዘር ችግር ኖሮባቸው አይደለም:: 2ኛነገ.19÷37:: ስለዚህ ዓለም ከዚህ መማር አለበት::

በሌላ በኩል ደግሞ ዘራቸው ላልሆነ ሰው የርኅራኄን ሥራ ሲሠሩ የምናገኛቸው ሰዎች አሉ:: ለምሳሌ:- በግብፅ ዕብራውያን ሴቶች ወንድ ልጅ በሚወልዱበት ጊዜ እንዲገደሉ ንጉሡ በማዘዙ የሙሴ እናት ሙሴን ወልዳ ሦስት ወር ሸሸገችው:: ይኽንንም ያደረገችው በእምነት ነው:: «ሙሴ ከተወለደ በኋላ ወላጆቹ ያማረ ሕፃን መሆኑን አይተው በእምነት ሦስት ወር ሸሸጉት÷ የንጉሥንም ዐዋጅ አልፈሩም::» እንዳለ:: ዕብ.11÷23:: በኋላ ላይ ግን በደንገል ሣጥን አድርጋ በወንዝ ዳር ባለ ቄጠማ ውስጥ አስቀምጣዋለች:: እኅቱም የሚደረግበትን ታውቅ ዘንድ በሩቅ ቆማ ትጐበኘው ነበር:: ፈቃደ እግዚአብሔር ሆኖ የንጉሡ የፈርዖን ሴት ልጅ አግኝታው አዘነችለት:: ወደ ቤተ መንግሥትም አስገብታ እንደ ልጅ አድርጋ /ወልጄ ዋለሁ ብላ/ አሳድጋዋለች:: የንጉሡ ልጅ ይኽንን ሁሉ ቸርነት ለዚያ ሕፃን ያደረገችው ዘሯ ስለሆነ አይደለም:: ምክንያቱም እርሷ ግብፃዊ እርሱ ግን ዕብራዊ ነውና:: ከወደቀበት ስታነሣውም ዕብራዊ መሆኑን በሚገባ ዐውቃለች:: «ሙሴ» ብላ የጠራችውም እርሷ ናት:: ዘጸ.2÷1-10:: እንግዲህ እግዚአብሔርን የማታውቅ÷ከአሕዛብ ወገን የሆነች ይህች ሴት ይኽንን ያህል ካደረገች ከእኛ ደግሞ የሚጠበቀው ከዚህ የበለጠ ነው:: ጽድቃችን እንኳን ከአሕዛብ ከጸሐፍትና ከፈሪሳውያን እንኳ መብለጥ አለበት:: ይኽንን በተመለከተ «ጽድቃችሁ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን ጽድቅ ካልበለጠ÷ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም::» በማለት ጌታችን የተናገረው ለዚህ ነው:: ማቴ.5÷20:: ጋለሞታይቱ ረዓብ ኢያሱ ወደ ኢያሪኮ የላካቸውን ሁለት ሰላዮች ከሰገነት ላይ ሸሽጋ ሕይወታቸውን ያተረፈቻቸው ዘር ቆጥራ አይደለም:: እንዲያውም ያለዚያ ቀን አይታቸው አታውቅም:: ነገር ግን በኢያሪኮ ንጉሥ እጅ ወድቀው በሰይፍ እንዳይመተሩ ታድጋቸዋለች:: ኢያ. 2÷1-6:: ይህቺን ሴት ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ:- «እንደዚሁም ጋለሞታይቱ ረዓብ ደግሞ መልእክተኞቹን ተቀብላ በሌላ መንገድ በሰደደቻቸው ጊዜ በሥራ አልጸደቀችምን?» በማለት ምግባሯን አድንቆ የአዲስ ኪዳንን ምእመናን አስተምሮባታል:: ያዕ. 2÷25:: ስለሆነም ሀገርህ የት ነው? ዘርህ ምንድን ነው? ማለት አይገባም:: ለክርስቲያን ሀገሩ በምድር ቤተ ክርስቲያን÷ በሰማይ ደግሞ መንግሥተ ሰማያት ናት:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ:- «እኛ ሀገራችን በሰማይ ነውና÷ ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኃኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን::» እንዳለ:: ፊልጵ. 3÷20:: በኤፌሶን መልእክቱም:- «እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና /ባለ ሀገሮችና/ የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም::» ብሏል:: ኤፌ.2÷19::

ብዙ ጊዜ ሰዎችን ወደ ዘረኝነት የሚገፋፋው በሰዎች ድካም የሚፈጠረው መናናቅ ነው:: አንድ ሰው የራሱን የሥጋ ዘር ወርቅ÷ የሌላኛውን ግን ዐፈር ካደረገ፤ ሌላውን ሰው እልህ ውስጥ ይከተዋል:: እልህ ደግሞ መርፌ ያስውጣል÷ እንደ ማርም ይጣፍጣል ይባላል:: እንዲህ ከሆነ ደግሞ ተያይዞ መጠፋፋት ነው:: የሚገርመው ነገር የሌላውን ዘር ዝቅ ሲያደርግ የማይሰማው ሰው የራሱን ዝቅ ሲያደርጉበት እብድ ነው የሚሆነው:: ሁሉም በራሱ ላይ እንዲደረግ የማይፈልገውን ነው በሌላው ላይ የሚያደርገው:: ይህም ለጊዜው ነው:: ምክንያቱም ዘረኝነት በጐሳ÷በጐጥና በሥጋ ዝምድና እየተከፈለ ስለሚሄድ ማቆሚያ የለውምና:: አንድ ዘር ቢሆኑም÷ ከዚያም አልፈው የአንድ እናት ልጆች ቢሆኑም በሁሉም ውስጥ መገፋፋት አለ:: ለዚህ ሁሉ መፍትሔው መንፈሳዊነት ነው:: ምክንያቱም መንፈሳዊ ሰው÷ ሰውን የሚመዝነው በሃይማኖቱና በምግባሩ ነውና::

6ኛ. ክትዳር:- ይኽንን በተመለከተ ብዙ ማለት ይቻላል:: ነገር ግን ለግንዛቤ ያህል ብቻ አጠር አድርገን ለመመልከት እንሞክራለን:: ይኽንንም ከመሠረቱ እንጀምራለን:: ይኸውም ቅድመ ጋብቻ ነው:: እንደሚታወቀው አብዛኛው ትዳር የሚበላሸው ከአመሠራረቱ ነው:: ምክንያቱም እየተመሠረተ ያለው ከዘር÷ ከመልክና ከገንዘብ አንጻር ነውና:: ይህም ቤቱን በአሸዋ ላይ እንደ መሠረተው ሰነፍ ሰው መሆን ነው:: «ይህን ቃሌን ሰምቶ የማያደርገው ሁሉ ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሰነፍ ሰውን ይመስላል:: ዝናምም ወረደ÷ ጐርፍም መጣ÷ ነፋስም ነፈሰ÷ ያንንም ቤት መታው÷ ወደቀም÷ አወዳደቁም ትልቅ ሆነ::» እንዳለ:: ማቴ.7÷27:: ስለዚህ የሰው ዘሩ ክርስትናው÷ መልኩ ምግባሩ÷ ገንዘቡም ሃይማኖቱ መሆኑን መርሳት አይገባም::

ሌላው ቅድመ ጋብቻ ያለው ፈተና ዝሙት ነው:: ይኸውም:- «የምትጋቡ ስለሆነ ችግር የለውም» በሚል የኀሊና ውጊያ ሰይጣን ስለሚፈትናቸው ብዙዎች ይወድቃሉ:: ነገር ግን ከጋብቻ በፊት የሚፈጸም ሩካቤ ዝሙት ነው:: በመሆኑም ይኽንን ፈተና ማለፍ ግድ ነው:: ይኸውም በስሕተት ወይም በድፍረት ላለመውደቅ ከክፉ የጐልማስነት ምኞት በመሸሽ ራስን መጠበቅ ነው:: ለዚህም ጾም፣ ጸሎትና ምክረ ካህን ያስጠፈልጋል:: ቅድመ ጋብቻ በእጮኝነት ዘመን ያለው ፈተና ከባድ ስለሆነ እንደ ሰው ብዙ መጠንቀቅ አለብን:: ምክንያቱም ከሁለቱ አንዱ ባልጠበቁት ሰዓት እጮኝነቱ ሊቋረጥ ይችላልና ነው:: በተለይም:- ይሆናል ብሎ ላልጠበቀው ሰው ከባድ ፈተና ነው:: መከዳቱ ያበሳጨዋል:: ያባከነው ጊዜ÷ በተለያዩ ደረጃ የከፈለው መሥዋዕትነት ያቃጥለዋል:: ወንዱም ሆነ ሴቷ አብዛኛውን ጊዜ በጐን ሌላ እጮኛ ይዘው

**በአጠቃላይ የግለሰብንም ሆነ የመንግሥትን እንዲሁም የእግዚአብሔርን ገንዘብ አለአግባብ መውሰድ በፍቅረ ንዋይ መታወር÷በገንዘብ የመጣ ውን ፈተና መውደቅ ነው:: ስለዚህ እንደ ነቢዩ እንደ ኤልሳዕ እንቢ ልንል ይገባል:: 2ኛነገ.5÷16:: ኃጢአተኞችም በገንዘብ ሲደልሉን እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ:- «ብርህ ከአንተ ጋር ይጥፋ::» ማለት ይጠበቅብናል:: የሐ.8÷21::**



© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ስለሆነ፡- «ብቃኸኝ÷ በቃሽኝ፤ አትሆኚኝም÷ አትሆኚኝም፤» የሚባባሉት ለጊዜው በጣም አደገኛ ነው፡፡ ለፍጻሜው ግን እግዚአብሔር የማያስችለው ነገር ስለሌለ ይቻላል፡፡ ዋናው ነገር ትዕግሥትን ገንዘብ ማድረግ ነው፡፡ አለበለዚያ እልህ ውስጥ ይገቡና ነገር ይበላሻል፡፡ «እሠራለታለሁ÷ እሠራላታለሁ፤» ማለት ይመጣል፡፡ ጭፍን ውሳኔ ያስወስናል፡፡ በእልህ ወይም ተስፋ በመቁረጥ ወይም «ላብሸቀው÷ ላብሽቃት» በሚል ካገኙት ጋር የጥድፊያ ጋብቻ በመፈጸም፡ - «ከድጡ ወደ ማጡ፤» እንዲል÷ ከባሰ ችግር ውስጥ መውደቅ ይመጣል፡፡ ለዚህ ሁሉ መድኃኒቱ አንድ ሰው ከማጨቱ በፊት ፈቃደ እግዚአብሔርን በጸሎት መጠየቅ አለበት፡፡ ዘፍ.24÷12-14፡፡

በጊዜ ጋብቻ ደግሞ የእጮኝነታቸውን ዘመን ጨርሰው ለዚያ የሚደርሱ ሰዎች ትልቅ ፈተና የሚሆንባቸው ለአንድ ቀን ውሎ ተብሎ የሚደረገው የሰርግ ዝግጅት ነው፡፡ ይህም ብዙ ወደ ትዳር የገቡ ሰዎችን ተፈታትኗቸዋል፡፡ ከማይወጡት ዕዳ ውስጥ የዘፈቃቸውም አይታጡም፡፡ ስለዚህ ይሉኝታን ወደ ጐን በመተው ዐቅምን ባገናዘበ መልኩ መሰረግ÷ ደስታን መግለጥ ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም ጋብቻ ታላቅ መንፈሳዊ ምሥጢር የሚገለጥበት የቤተ ክርስቲያን ጸጋ ነውና፡፡ ጌታችን በቃና ዘገሊላው ሰርግ ቤት በተገኘ ጊዜ የሚበላውም የሚጠጣውም ነበረ፡፡ እንዲያውም የሚጠጣው የወይን ጠጅ ባለቀ ጊዜ በእናቱ በቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት ውኃውን በመለወጥ ወይነ ቃና አድርጐታል፡፡ ይኸውም «የመጀመሪያውን ተአምር በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ፤» ተብሎ ተመዝግቧል፡፡ ዮሐንስ 2÷1-11፡፡ በትምህርቱም፡- «መንግሥተ ሰማያት ለልጁ ሰርግ ያደረገ ንጉሥን ትመስላለች፡፡... ደግሞ ሌሎች ባሮችን ልኮ የታደሙትን፡- እነሆ ድግሴን አዘጋጀሁ÷ ኮርማዎቼና የሰቡት ከብቶቼ ታርደዋል÷ ሁሉም ተዘጋጅቷል፤ ወደ ሰርጉ ኑ በሉአቸው አለ፡፡» የሚል ምሳሌያዊ ትምህርት አስተምሯል፡፡ በዚህም፡ - ድግስ ያለበት ሰርግ ቤት ለመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ሆኖ መገኘቱን እንረዳለን፡፡ ድግሱ የደስታ መግለጫ ነውና፡፡ ማቴ.22÷1-4፡፡ ጠፍቶ የነበረውን ልጁን አግኝቶ ደስ ያለውም አባት የተሰማውን ደስታ የገለጠው እንደ ዐቅሙ በደገሰው ድግስ ነው፡፡ ሉቃ.16÷22፡፡ ጥሎሽም ቢሆን አቅም በፈቀደ ነው፡፡ ዘፍ.24÷53፡፡ በመሆኑም መሠረታዊው ነገር ከተሟላ ይኸ ቀረ÷ ይኸ ጐደለ÷ ብሎ ማስጨነቅ አይገባም፡፡ ከዚህ ይልቅ ዘለቄታ ላለው ትዳራቸው ማሰብ ነው፡፡

በመጨረሻም የምንመለከተው ድኅረ ጋብቻ ስለሚያጋጥመው ፈተና ነው፡፡ ይኸውም አጠቃላዩ የኑሮ ውድነት ከገቢያችን ጋር ባለመመጣጠን የሚፈጠረው ግጭት ነው፡፡ ይህም ሰውን እያማረረ እንዲኖር ያደርጋል፡፡ እያማረሩ መኖር ደግሞ በትዳር ውስጥ ያለውን ሰላምና ፍቅር ያደፈርሳል፡፡ እርሱ ሲማረር እርሷ ትረበሻለች፡፡ እርሷ ስታማርር እርሱ ይረበሻል፡፡ ከዚህም የተነሣ ትዳርን መጥላት ይመጣል፡፡ ትዳርን እየጠሉ በትዳር ውስጥ መኖር ደግሞ የፈተና ፈተና ነው፡፡ ልጆችን ለመውለድ እየፈለ ጉም በምን ያድጋሉ በሚል ምክን ያት አለመውለድም ፈተና ነው፡፡ ምክንያቱም ላለመውለድ ሲባል ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር ወደሚጋጭ ተግባር ማዘንበል ይመጣልና፡፡ በተጥባበ ሥጋ እንዳይፀነስ ማድረግ÷ ከተፀነሰም በኋላ ፅንሱ እንዲቋረጥ ማድረግም ተፈትኖ መውደቅ ነውና፡፡ አዮ.38÷9፤ ኢዮ.3÷16፡፡ መፍትሔው በተፈጥሮ ፅንስ የሚይዝበትና የማይዝበት ጊዜ ስላለ ላለመውለድ የፈለገ ሰው ራሱን በመግዛት በሚፀነስበት ጊዜ ከግብረ ሥጋ መታቀብ ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ከሁለት አንዳቸው በተለያየ ምክንያት ሕመምተኞች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በሕክምናም በጠበልም ላይድኑ ይችላሉ፡፡ እንደሚታወቀው ሕመምተኛ ሰው በአብዛኛው ተለዋዋጭ ጠባይዐት አሉት፡፡ ስለዚህ ሕመምተኛውን ስለ በሽታው ልዩ ክብካቤ ማድረግ÷ ስለ ጠባዩም ፈጽሞ መታገሥ ይገባል፡፡ «ነገር ሁሉ ለበጎ ነው፤» /ሮሜ. 8÷28/ እንደ ተባለ በጸጋ መቀበል ነው፡፡ ነገር ግን እንደ ኢዮብ ሚስት ትዕግሥት ማጣት ፈተና ነው፡፡ ኢዮ፡ 2÷9፡፡ ስለዚህ ሰይጣን በዚህ ፈትኖ እንዳይጥለን መጠንቀቅና እስከ መጨረሻው እግዚአብሔርን ደጅ መጥናት ነው፡፡

እንግዲህ ሰው ሁኖ የማይፈተን ስለሌለ በራሳችን ሲደርስ ተስፋ መቁረጥ÷ በሌላው ሲደርስ ደግሞ መፍረድ አይገባም፡፡ ምክንያቱም ክርስቲያን በበግ የተመሰለው ያለ ምክንያት አይደለምና፡፡ በግ ሃፍረቷን በላቷ እንደ ምትሸፍን እንደ ፍየል እንደማትገልጠው ሁሉ ክርስቲያንም የራሱን ኃጢአት በንስሐ÷ የባልንጀራውን ደግሞ አይቶ እንዳለየ÷ ሰምቶም እንዳልሰማ በትዕግሥት መሸፈን ይጠበቅበታል፡፡ ስለዚህ በተፈተንን ቁጥር «በቃ÷ እኔ መንፈሳዊ መሆን አልችልም፡፡» ማለት የለብንም፡፡ «የጸኑትን አስቡ፤» /ዕብ. 12÷4/ እንደ ተባለ እነርሱን አስበን÷ ለእኛም ይደረግልናል ብለን ማመን አለብን፡፡ ባልንጀሮቻችንም ሲፈተኑ ከላይ እንደ ገለጥነው፡- «መንፈሳዊ ሆነው እንዴት?» ብለን ለፍርድ መቸኰል የለብንም፡፡ ይልቁንም ነቢዩ ሳሙኤል ስለ ንጉሡ ስለ ሳኦል ኃጢአት እንዳለቀሰ እኛም በወገኖቻችን ላይ ስለ ደረሰ ፈተና ማልቀስ ይጠበቅብናል፡፡ 1ኛሳሙ.16÷1፡፡ ሥጋ ለባሽ ከራሳችን ጀምሮ ደካማ ነውና፡፡ አጋዥ ይፈልጋል፡፡ የባልንጀራ ምክር÷ የንስሐ አባት ምክር÷ የእመቤታችን አማላጅነት÷ የቅዱሳን ረድኤት÷ የእግዚአብሔር ቸርነት ያስፈልገዋል፡፡

እግዚአብሔርን ዓምባ መጠጊያ ካደረግን እርሱ ከፍቅረ ንዋይ፣ ከዘረኝነት÷ ከጋብቻ በፊት፣ በጋብቻ ጊዜና ከጋብቻ በኋላ ከሚያጋጥም ፈተና ይጠብቀናል፡፡ ከራስ÷ ከባልንጀራና ከሥልጣን ከሚመጣ ፈተናም ይሰውረናል፡፡ ብንወድቅም ያነሣናል፡፡ በንስሐ ይቀበለናል፡፡ የሰይጣንን ወጥመዱን ይሰብርልናል፡፡ በበረከቱ ያኖረናል፡፡ የሰራፕታዋን ሴት ጭላጭ ዘይት ባርኮ ከዕዳ ነጻ የምትሆንበትንና ልጆቿን የምታሳድግበትን በረከት የሰጣት÷ በአዲስ ኪዳንም አምስቱን እንጀራና ሁለቱን ዓሣ ባርኮ ሴቶችና ሕፃናት ሳይቆጠሩ አምስት ሺ ወንዶችን መግቦ ዐሥራ ሁለት መሶብ ያተረፈ÷ ውኃውንም ለውጦ የወይን ጠጅ ያደረገ እርሱ ነውና፡፡ 1ኛነገ.17÷16፤ 2ኛነገ.4÷1-7፤ ማቴ.14÷13-21፤ ዮሐ.2÷1-11፡፡ ብንታመምም ወይ ይፈውሰናል÷ ወይም ሕመሙን የምንታገሥበት ጸጋ ይሰጠናል፡፡ በቤተ መቅደስ ወደ እርሱ የቀረቡትን በሽተኞች የፈወሰ እርሱ ነውና፡፡ ማቴ. 21÷14፤ ቅዱስ ጳውሎስ የጐኑን ውጋት የመንፈስ ልጁ÷ ጢሞቴዎስም የሆዱን ሕመም እንዲችሉ ያደረጋቸው እርሱ ነውና፡፡ 2ኛቆሮ.12÷7፤ 1ኛጢሞ.5÷23፡፡ በመሆኑም ይኸንን ተስፋ አድርገን በፈተና ምክንያት ከሃይማኖታችን ሳንናወጥ በጐ ምግባር እየሠራን እንድንኖር የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን፡፡ አሜን፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ድህነት እንዲቀነስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሚና ምን መሆን አለበት?

/ዶ/ር ዓለማየሁ ረዳ/

*ይህ ጽሑፍ ከጥቅምት 6-11 ቀን 1997 ዓ.ም. ተካሂዶ በነበረው በ23ኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ላይ በዶ/ር ዓለማየሁ ረዳ ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው:: ዶክተር ዓለማየሁ ረዳ በኢኮኖሚ ልማት የተለያዩ ዲፕሎማዎችና በተፈጥሮ ሳይንስ የዶክትሬት ዲግሪ አላቸው:: በግላቸው የማማከር አገልግሎት የሚሰጡ ሲሆን የ«ቸር ኢትዮጵያ የልማትና ሰብአዊ ተራድዖ ድርጅት» መሥራች ናቸው:: አንባብያን እንደምትገነዘቡት በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ ለተከሰተው ድህነት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ግንባር ቀደም ተጠያቂ እንደ ሆነች ተደርጐ በስፋት እየተወራ ነው:: ይሁን እንጂ የቤተ ክርስቲያናችንን መጠነ ሰፊ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች ያላጤነውን ይህንን የተሳሳተ አስተያየት ወደ ጐን ትተን በቀጣይነት ማድረግ ያለብንን ሁሉ እናደርግ ዘንድ የምሁሩን ጥናት ጥሩ ሆኖ ስላገኘነው ይኸውና አቅርበነዋል:: ዶ/ር ዓለማየሁ ረዳን ከልብ እያመሰገንን ቤተ ክርስቲያናችን እየታማችበት ባለው በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ አንባብያን አስተያየቶቻችሁን ብታደርሱን ወደ ፊት ለማስተናገድ ዝግጁዎች መሆናችንንም በዚሁ አጋጣሚ ለማሳወቅ እንወዳለን:: መልካም ንባብ::*

## 1. መግቢያ

ይህ ጉባኤ /ከብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ጀምሮ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣የየሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጆች፣ የምእመናንና ሰንበት ት/ቤቶች ተወካዮች የተሳተፉበትን ጉባኤ ማለታቸው ነው/ ስለ ድህነትና መፍትሔዎቹ ልወያይ ቢል ምክንያቶች ያሉት ይመስለኛል:: ከነዚህም ዋነኛው ቤተ ክርስቲያኒቱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ምእመናን አገልጋዮችዋን ድህነት እግር ተወርች አስሮ የሚያሰቃያቸው በመሆኑ ነው:: ይህ ክቡር ጉባኤ የድህነታችንን መጠንና ደረጃ አያውቀውም ባይባልም በጥሞና ተወያይቶበት ቤተ ክርስቲያኒቱ ተገቢና የሚጠበቅ ሚናዋን እንድትጫወት የሚያስችላት የተግባር አቅጣጫ ማስቀመጥ ይኖርበታል:: ይህ የመወያያ ጽሑፍም መንደርደሪያውን ያቀርባል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ::

## 2. ድህነትና ኢትዮጵያ

ድህነት ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን የተመደበ የኑሮ ክልል አይደለም:: ሌሎች ሀገሮችና ሕዝቦችም ከድህነት ጋር ይኖራሉ:: የኛ ድህነት ግን ፈርጀ ብዙ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ምክንያቶች ለየት ይላል:: ላለፉት በርካታ ዐሠርት ዓመታት ያለ አንዳች ርኅራኄ ሲቀጣን የኖረው ድህነታችን ከሌሎች ሀገሮችና ሕዝቦች በተለየ ሁኔታ የሕዝብነት ክብራችንንና ኩራታችንን እንዲሁም የዘመናት የሀገርነት ታሪክ ቀምቶ ወደ ዓለም አቀፍ ተመጽዋችነት ደረጃ አውርዶ የጣለን፣ የረሃብና የቸነፈር ምሳሌ፣የድፍን ዓለሙ መሳለቂያና ያለንበት አህጉር ማፈሪያ ያደረገን በመሆኑ ግንባር ቀደም ጠላታችን ነው::

ይህን ዓይነተኛ ጠላት የመዋጋቱ እንቅስቃሴ አጠቃላይ ለውጥን ለማረጋገጥ የሚደረገው ትግል አካል ቢሆንም አሁን ባለንበት ሁኔታ ድህነት ለለውጥና መሻሻል የምናደርገውን ይበልጥም፣ ያለንበትን ሁኔታ በቅጡ ተገንዝበን የገጠሙንን ችግሮች በጋራ ታግለን ከማስወገድ ይልቅ ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሮአችንን ለማሰንበት በየፊናችን እንድንሮጥ የበታተነን በመሆኑ ልዩ ትኩረት ሰጥተን ልናየውና ልንተነትነው ይገባል ብዬ አምናለሁ::

## 3. ድህነት ምንድን ነው?

ድህነት ምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ በተለያየ መንገድ ሊመለስ ይችል ይሆናል:: የመጀመሪያው ምላሽ ለሁላችንም ቶሎ የሚከሰትልን በዕለት ኑሮአችን ተመን /Livelihoood expression of poverty/ የምንሰጠው ትርጉም ነው:: «ድህነት ምንድን ነው?» ሲባል የኬንያው ገበሬ የሰጠው ምላሽ ዓይነት መሆኑ ነው:: ገበሬው ጠያቂዎቹን «ድህነት ምን እንደ ሆነ ለማወቅ ከፈለጋችሁ ኑሮዬን ተመልከቱ:: የምኖርበትን ቤት፣ የምበላውን ምግብ፣ የለበስኩትን ልብስ፣ የምጠጣውን ውኃ እንዲያው በአጠቃላይ እኔን እዩኝ ምንን እመስላለሁ?» ነበር ያለው::

በቅርቡ በደቡብ ኢትዮጵያ በሚገኝ አንድ ወረዳ ውስጥ በተካሄደውና እኔም በተሳተፍኩበት ጥናት በርካታ የገበሬ ቤተሰቦች የድህነትን ትርጉም /Livelihood expression of poverty/ እንዲያስረዱ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ «<u>ድህነት ማለት መሬት አልባነት ወይም በጣም አነስተኛ ማሳ ላይ ለራስ የማይበቃ ምግብ ማምረት፣ለኑሮ አመቺ ባልሆነና በፈራረሰ ቤት ውስጥ መኖር፣ተንቀሳቃሽም ሆነ ቋሚ ንብረት አለመኖር፣በቂ ምግብ አለማግኘት፣በዓላትን አለማክበር፣ክፉ ቀን ሲመጣ ቶሎ ለችግር መጋለጥ</u> ወዘተ ነው» ነበር ያሉት:: ገበሬዎቹ ድህነት በምን ዓይነት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ውስጥ እንደሚያኖር ነበር የገለጹት:: ድህነት በገጠርም ሆነ በከተማ ለኑሮ ተፈላጊ በሆኑ ነገሮች ሲተመን ምግብ፣መጠለያ፣ሕክምና፣ ንጹሕ ውኃ፣ በአጠቃላይ የኑሮ መደጎሚያ የሚሆን ሥራና በቂ ገቢ ከማጣት ጋር የተያያዘ ክስተት መሆኑ ግልጽ ይመስለናል::

የድህነት ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ትንታኔም ከላይ የተገለጹትን ትርጉሞች መሠረት ባደረገ የሚሠራው ስሌታዊ አቀራረብ ነው:: የዓለም ባንክ፣የተባበሩት መንግሥታትና የሌሎች ተቋማት ሰነዶች ድህነትን ከነፍስ ወከፍ ገቢ፣ ከአገልግሎቶች አቅርቦት፣ወዘተ አንጻር በመተንተን በስሌት ይገልጹታል::

በአኗኗር ተመን የሚገለጸውም ሆነ የኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ገላጮች /Socio-economic indicators / የሚቀርበው የድህነት ትንታኔም ይሁን በአብዛኛው ድህነትን ከገቢ ማነስ ጋር አዛምዶ የሚመለከተው ነባሩ አተያይ የድህነትን ሙሉ ገጽታዎች እንደማያሳይ ዛሬ ግልጽ ሆኗል:: በቤተሰብ የኑሮ ደረጃ ላይ ተመሥርቶ የሚሠራው የድህነት ጥናት /Household survey/ መሠረታዊ መለኪያዎች የዕለት ገቢ፣የጤናና የትምህርት ዕድል ወዘተ ስለሆኑ የድህነትን አንድ ገጽታ ማለትም ከዕለት ገቢ ከአገልግሎቶች አቅርቦት ጋር የተያያዘውን ገጽታ ይበልጥ የሚያጎላ በመሆኑ ሌሎቹን ገጽታዎች ጋርዷቸዋል::

አዲሱ የድህነት አተያይ :- የገቢ ማነስ፣የጤና ማጣትና አለመማር ብቻ ሳይሆን ለተለያዩ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮች መጋለጥ ጭምር መሆኑን ያስምርበታል:: «ድህነት መጋለጥ / vulnerability/ ነው» ሲባል:-

- አካላዊና ማኅበራዊ መገለል /isolation/
- ዋስትና ማጣት /insecurity/
- ግላዊ ክበሬታን መነፈግ /self-respect/
- ለሕይወት ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን አለማግኘት
- ዐቅመ ቢስ መሆን /powerlessness/ ወዘተ

ማለት መሆኑን አዲሱ አተያይ ያስገነዝባል:: አንድ ሩስያዊ ዜጋ ስለ ድህነት በሰጠው አስተያየት:- «ድህነት በየቀኑ ነገን እየፈሩ መኖር ነው» ብሏል:: «ነገን እየፈሩ መኖር» ደግሞ ከፍተኛ መጋለጥ መሆኑ ለማንም ይሰማል:: ድህነት ከሰብአዊ መብት ጋር ተገናዝቦ ሲታይም «ሰብአዊ መብትን መነፈግ» መሆኑን የተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም ሪፖርት ያመለክታል:: /UNDP,1998/. ለዚህም ነው ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም ድህነትን የእርሱ ተቃራኒ ከሆነው ከሰብአዊ ልማት አንጻር /Human Development/::



© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

በመተንተን የድህነት ይዘትና ገጽታ በገቢ ማነስ ብቻ የሚወሰን አለመሆኑንና ሌሎች ገጽታዎችም እንዳሉት ለማሳየት ጥረት የሚያደርገው:: ይህ አዲስ አተያይ ልማትን ሰብአዊ መብትን ያቀራኘ ሲሆን የድህነት ይዘትና ባሕርይ ከሰብአዊ ልማት አንጻር ለመረዳት የሚጥር ይሆናል:: ለዚህም ይረዳ ዘንድ ሰብአዊ ልማት ራሱ ምን እንደ ሆነ መረዳት ተገቢ ይመስለኛል::

❖ ሰብአዊ ልማት ምንድን ነው? ድህነትስ?

ሰዎች ረጅምና ጤናማ ሕይወት መምራት እንዲችሉ፣ ስለ ራሳቸውና ስለ አካባቢያቸው በቂ ዕውቀት እንዲኖራቸውና ተገቢ ለሆነ የኑሮ ሁኔታ አስፈላጊ የሆኑትን ግብዓቶች ማግኘት ይችሉ ዘንድ መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸው /basic needs/ በቅድሚያ እንዲሟሉላቸው ይፈልጋሉ:: በቂ ምግብ፣ ተገቢ መጠለያ፣የሕክምና አገልግሎት፣ትምህርት፣ዋስትና ያለው ሕይወት ወዘተ መሠረታዊ ፍላጎቶች ሲሆኑ እነዚህ ደግሞ ለተሟላ የኑሮ ደረጃ መረጋገጥ መነሻዎች ናቸው:: የሰብአዊ ልማትም ቀዳሚ ተግባር እነዚህን ማሟላት ይሆናል:: «ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም»/ማቴ.4፥4/ እንዲል፣ የመሠረታዊ ፍላጎቶች መሟላት ብቻውን የተሟላ ሰብአዊ ልማት እንዲኖር አያደርግም:: ምክንያቱም ሰዎች የተሟላ ኑሮ ይኖሩ ዘንድ ሌሎች ማኅበራዊ እሴቶችንና ነጻነቶችን ይፈልጋሉና ነው:: እነዚህ ማኅበራዊ እሴቶችና ነጻነቶች ደግሞ:-

- ፖለቲካዊ፣ማኅበራዊና ባሕላዊ ነጻነቶችን መቀዳጀት ማለትም ከቦታ ቦታ በነጻነት መንቀሳቀስና ሠርቶ መኖር፣በነጻነት ሐሳብንና እምነትን መግለጽ ፣ከማናቸውም ጭቆናዎች ነጻ መሆን፤
- በማኅበራዊነት መኖር ፣ተስፋንና በራስ መተማመንን፣ከሌሎች ጋር በጋራ መኖርን መላበስ፤
- ማኅበራዊ ትስስርና አንድነት ባሉበት የፈጠራ ሥራዎችን በሚያዳብርና ምርታማ በሆነ ኑሮ ውስጥ መኖር፤
- የተሟላ መንፈሳዊ ሕይወትን መቀዳጀት፤
- በተከበረ ግላዊ ሕይወትና ሰብአዊ መብቶችም በምልዓት በተረጋገጡበት ሁኔታ ውስጥ መኖር መቻል ናቸው::

ይህም ብቻ አይደለም፤ ሰብአዊ ልማት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ፣በማኅበራዊ ተሳትፎ፣በምርታማነትና በዘላቂነት የተሟላ እንዲሆን ይጠበቃል:: እንግዲህ በአጭሩ ሰብአዊ ልማት ማለት መሠረታዊ ፍላጎቶች፣ ማኅበራዊ እሴቶችና ነጻነቶች ፍትሐዊና ተሳትፎአዊ በሆነ ሁኔታ ተሟ ልተው የሚገኙበት ሂደት ነው ማለት ይቻላል:: የሰብአዊ ልማት ሂደት የሰዎች የኑሮ አማራጮች የሚሰፉበት ሂደት ነው:: የሰብአዊ ልማት ሂደት አሁን ላለው ትውልድ የኑሮ አማራጮችን ሲያሰፋ የቀጣዩን ትውልድ ዕጣ ፈንታም እያገናዘበ በመሆኑ ሂደቱ ዘላቂነት ያለው ነው:: ስለሆነም ሰብአዊ ልማት ጥሩ ገቢ ማግኘት ብቻ አይደለም:: ከልዩ ልዩ ተጽዕኖዎች ነጻ የሆነ ሕይወትም መምራት መቻል ነው:: ለዚህም ነው ሰብአዊ ልማት:- ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ማኅበራዊ፣ ባሕላዊ ወዘተ ገጽታዎች የሚኖሩት:: የነዚህ ገጽታዎች ድምር ነፀብራቅ የሆነው ሰብአዊ ልማት በሰዎች ኑሮ ውስጥ ተስፋንና የኑሮ ችሎታን /empowerment/ ፣በመከባበር ላይ የተመሠረተ ማኅበራዊ ትስስርን /cooperation/ ፣ ፍትሐዊነትን /equity/ ፣የቀጣይ ትውልድን ዕጣ መገንዘብን /sustainability/ ፣የኑሮና የሕይወት ዋስትናን /secuirty/ ያረጋግጣል::

እንግዲህ የድህነትን ትርጉም መረዳት ያለብን ከዘረዘርነው የሰብአዊ ልማት ምንነት አንጻር ከሆነ የድህነትም ይዘትና ትርጉም ያን ያህል ውስብስብ መሆኑን እንገነዘባለን:: በመሆኑም ድህነት ከላይ ከዘረዘርናቸው ቁም ነገሮች አንጻር ሲተመን የኑሮ አማራጮችን መነፈግ ወይም ጨርሰውኑ ማጣት፣ ሰብአዊ መብቶችን፣እሴቶችንና ነጻነቶችን አለመቀዳጀት፣ማኅበራዊነትን መነጠቅና በቀቢጸ ተስፋ መኖር፣የመሠረታዊ ፍላጎቶች በተሟላ ሁኔታ አለመገኘት ወዘተ ነው፤ ማለት ይቻላል::

ነጻነት በሌለበትና ሰብአዊ መብቶችም በተደፈሩበት ሁኔታ ውስጥ ረጅምና ጤናማ ሕይወት በሰላምና በደስታ መምራት ይቻላል ብሎ ማሰብ፡ - «የሰዎች ፍላጎት ሆድን ሞልቶ ማደር ብቻ ነው» የማለት ያህል ይሆናልና ድህነት የገቢ ማነስ ብቻ አለመሆኑ ይረጋገጣል:: ለዚህም ነው እንግዲህ ድህነት ዋነኛ ችግራችን መሆኑን ተገንዝበን ልንዋጋው ተገቢ የሚሆነው::

## 4. የድህነታችን መንሥኤዎች ምንድን ናቸው?

ድህነት የገቢ ማነስ ብቻ አይደለም ስንል ሰዎች በልቶና ጠጥቶ በቤት ውስጥ ከማደር በተጨማሪም የሚፈልጓቸው ነገሮች አሏቸው ማለታችን ነው:: እናም የድህነት መንሥኤዎች በርካታ ይሆናሉ:: ድህነት ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ማኅበራዊ፣አስተዳደራዊ፣ባሕላዊ ወዘተ መንሥኤዎችና ምክንያቶች ሊኖሩት ይችላል:: አንዳንዶቹ የድህነት መንሥኤዎች መሠረታዊና ድህነት በሰፋት እንዲከሰት ዋነኛ ምክንያቶች ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ድህነት እንዲባባስና ዕድሜው እንዲረዝም የሚያደርጉ ናቸው:: ለምሳሌም:- የተፈጥሮ ሀብት አለመኖር ወይም መሟጠጥና የሕዝብ ብዛት መጨመር ወዘተ ዓይነተኛ ምክንያቶች ለድህነት ቀጥተኛ መንሥኤ ሲሆኑ የተዛባ የፖለቲካ ሥርዓትና የመልካም አስተዳደር አለመኖር፣አለመግባባትና ጦርነት ማጣት ወዘተ ድህነትን የሚያባብሱ ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ::

ባሕላችን ራሱ አብዛኛውን ጊዜ ድህነት እንዲሰነብት የማድረግ ይዘቱ ይጎላል:: ከሁሉ በፊት ባሕላችን አብዛኛውን ጊዜ ድህነትን እንደ ማኅበራዊ ችግር አያይም:: ድህነት የአርባ ቀን ዕድል፣ወይም በፈጣሪ የተወሰነ ዕጣ ፈንታ እንደ ሆነ የሚያስበው ሕዝባችን ቁጥር ዛሬም ቀላል አይደለም:: «ድህነት ይመቸናል» ባንልም ባሕላችን ድህነትን እንደ ማኅበራዊ ችግርና በጋራ ልናስወግደውም እንደ ሚገባ አያመላክተንም፣ ሥርዓቱ የጣለብን ዕዳ እንዳለ ሆኖ ሠርቶ ጥሮ ግሮ በማኅበራችን ወዝ የመኖር ስሜታችን ደካማ ነው:: እናም:-

- ሥራንና ሠራተኛን የመናቅና የማንጓጠጥ ነባር ባሕላችን ዛሬም ቢሆን ሰንኮፉ ገና አልተነቀለም፤
- ሠርቶ ከመብላት ይልቅ ወደ ልመና የማዘንበሉም ባሕል ገና እግሩን ከቤታችን አላነሣም፤
- ሥራ የሚያስፈቱ አጉል ማኅበራዊ ልማዶች ዛሬም አልቀቀሩም፤
- የሚገጥመንን የኑሮ ችግር ሁሉ ከፈጣሪ እንደ ተላከ ቁጣ ወይም ሌሎች እንደ ጣሉብን ዕዳ የማየት፤
- ስለ ዓለምና ስለ ራሳችን ያለን ግምትና ዕውቀት የዳበረ አለመሆንና በማይምነት ጥላ ሥር መገኘታችን፤
- ለጊዜ ያለን ግምት አናሳ መሆን፤
- ለዛሬ የምንኖር መሆናችን፤ ስናገኝ ደግሰን የምንጨፍር፣ነገ መኖሩን የምንረሳ፣ስናጣ ደግሞ የሌላው ቀብር ላይ ለራሳችን የምናነባ ቡቡዎች፣ ሞትን ከማንም በላይ የምናከብር መሆናችንም ለድህነታችን እንጂ ለኛ የበጀ አልሆነም::

## 5. ድህነታችን እንዴት ይወገዳል?

«ድህነታችን ዋነኛ ጠላታችን ነው» ቢባልም በቅርቡ በወረራ የያዘን አይደ ለም:: ይህ ማኅበራዊ ባለጋራ ለረጅም ዘመናት አብሮን ኖሯል:: በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወገኖቻችንንም ሕይወት በድህነትና በተፈጥሮ መዛባት ሳቢያ ገብረናል:: እናም በቤታችን ጎዝጉዞና ተመቻችቶ ስለኖረ ጠላት ነው የምናወራውና እንዲህ በቀላሉ እናስወግደዋለን ማለትም ዘበት ነው:: ስለሆነም በግንዛቤ ደረጃ መያዝ ያለባቸው የመፍትሔ አቅጣጫዎች የሚከተሉት ይሆናሉ::

**ድህነት ማኅበራዊ ዕዳ እንጂ የተወሰነ ኅብረተሰብ ክፍል ችግር ተደርጎ መወሰድ የለበትም::** ሚሊዮኖች በድህነት እየማቀቁ በሚኖሩበት ሀገር ውስጥ ጥቂቶች «ከድህነት ነጻ ነን» ቢሉ የሚያሞኙት ራሳቸውን ብቻ ይሆናል:: ለምን ቢሉ፥ ኑሮአቸው የፍርሃትና የጥርጣሬ መሆኑን ከእነርሱ በላይ የሚያውቅ የለምና ነው:: ዛሬ ትንሽ ሀብት አለኝ የሚል ሁሉ አጥሩን ወደ ሰማያት እያስጠጋ አስረዝሞ ሳያጥር፣በሮቹን በብረት ሠንሠለቶች ሳይተበትብ ተኝቶ ሹን ቅልፍ እንደማይወስደው ሁላችንም እናውቃለን:: በሀብታሞች ቀበሌ ለጥበቃ



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

የሚወጣው የወር ወጭ መቶዎችን ቀልበ የሚያሳድር መሆኑም እውነት ይመስለኛል:: ስለሆነም ድህነት ህብታም፣ ድሃ፣ሊቅ፣ደቂቅ ሳይል የሁላችንም ችግር መሆኑን በቅድሚያ መገንዘብ አንዱና ዋነኛው ርምጃ ነው:: እያንዳንዱም ዜጋ ድህነት አዋራጅና ከሰው በታች የሚያውል ማኅበራዊ ጉድፍ መሆኑን በጥብቅ መገንዘብ አለበት::

- ከእንግዲህ ነባሩ ባሕላችን ሥራንና ሠራተኛን እያሸሚጠጠ ለተተኪው ትውልድ የተሳሳተ አመለካከት እያወረሰ እንዲሄድ መፈቀድ የለበትም:: የሥራ ጊዜን፣ሀብትንና ንብረትን የሚያባክኑ፣በሰዎች መካከል መቃቃርንና መራራቅን የሚፈጥሩ ኋላቀር አስተሳሰቦችንና ባሕሎችን መዋጋት አለብን::

በአጠቃላይ እንግዲህ ድህነት እንዲቀንስ ከፈለግን ኅብረተሰቡ ሓላፊነት መውሰድ አለበት፤ መንፈሱ አካሉና ሥነ ልቡናው በዚህ ግንዛቤ መቃኘት አለበት ለማለት ነው:: ከዚህ በተረፈ እንግዲህ ከአንድ ሀገር ድህነትን ለመቀነስና በሂደትም ለማስወገድ ይቻል ዘንድ ፖለቲካዊ ፣ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሥርዓቱ እንዲሁም አስተዳደራዊ ተግባሮች ተደራጅተው የሚመሩበት ሁኔታ ድህነትን ለማስወገድና ማኅበራዊ ብልጽግናን ለማምጣት የሚጠቅሙ መሆን አለባቸው:: በሕዝብ እምነት፣ ስምምነትና ፍላጎት ላይ ያልተገነባ ሥርዓት የኅብረተሰብን ነጻና ግልጽ ተሳትፎ ስለሚገድብ ድህነትን ለማስወገድ ብዙም አይረዳም:: ሰውም ሆነ የተፈጥሮ ሀብታችንን በአግባቡ አደራጅተን ድህነታችንን ለመቀነስ በሂደትም ለማስወገድ እንድንችል በሕዝብ የታቀፈ የፖለቲካ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር ወሳኝ ሚና ይኖራቸዋል:: ዛሬ ዛሬ የድሆች ሀገሮችን የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም ለመመርመር ሓላፊነት የወሰዱ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች /የዓለም ባንክ፣ የዓለም አቀፍ ገንዘብ ፈንድ ወዘተ/ ዘንድ አስፈላጊ ግብዓት ተደርገው ከሚታዩት ነገሮች መካከል መልካም አስተዳደርና የሰብአዊ መብቶች መከበር ዋነኞቹ ናቸው:: «መልካም አስተዳደርንና ዴሞክራሲን ለማይቀበሉ ሀገሮች ብድርም ሆነ ርዳታ አንሰጥም» በማለት እያንገራገሩ ይገኛሉ:: ዓለም አቀፍ የድህነት ቅነሳ እንቅስቃሴዎች በሌሎች መልኮች እየተከሰቱ ነው:: ከነዚህም ጥቂቱ:-

- የድሃ ሀገሮች የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂዎች፤
- የክፍለ ዘመኑ የልማት ግቦች (MDGs)
- የአፍሪካ ሀገሮች ለልማትና ድህነት ቅነሳ ያሠፈሩት ቃል ኪዳን (NEPAD)፤
- የተባበሩት መንግሥታት ልዩ ልዩ የልማት ድጋፎች ድህነት ተኮር መደረጋቸው፤
- የአውሮፓና አፍሪካ ካሪቢያን የንግድና የልማት ትብብር ወዘተ ይገኙበታል::

እነዚህ ሁሉ እንቅስቃሴዎች የውስጥ ዝግጅታችንንና ተግባራችንን የሚተኩ ሳይሆኑ የሚያግዙ ብቻ ተደርገው መታሰብ አለባቸው:: ድህነትን የማስወገዱ ሓላፊነት በቅድሚያ የሚመለከተው እኛን እንደ ሆነ መገንዘብ ይኖርብናል::

## 6. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሚና ምን መሆን አለበት?

ቤተ ክርስቲያናችን የሃይማኖት ብቻ ሳትሆን ማኅበራዊ ተቋምም ነች:: ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋርም ያላት ታሪካዊ ቁርኝት የሕዝብን ችግር በቅርብ እንድትጋራ ያስገድዳታል:: በድህነት ቅነሳ ሂደት ውስጥም በበጎ አድራጎት ስም ከውጭ የመጡ ድርጅቶችና ሌሎች የሃይማኖት ዘርፎች ቤተኛ ሆነው ሲንቀሳቀሱ ቤተ ክርስቲያናችን «የራሷን ጉድ» ከዳር ቆማ የምትመለከትበት የሞራል ሥልጣን የላትም:: ተጠሪነትዋ ለክርስቶስ ቢሆንም የተሠየመችው ሕዝብን ልትመራ፣ ማኅበራዊ ሕይወቱን እያበለጸገች መንፈሳዊ ሕይወቱን ልታለመልም መሆኑን ከዚህ ጉባኤ አባላት በላይ የሚረዳው ያለ አይመስለኝም:: ቤተ ክርስቲያናችን በድህነት ቅነሳው ሂደት ውስጥ መሪ ተሳታፊ እንጂ ድጋፍ ሰጪ ተመልካች ልትሆን አትችልም:: በዚህ ቁም ነገር ከተስማማን ቤተ ክርስቲያናችን ሚናዋ ምን መሆን እንዳለበት እንመልከት::

6.1. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበራዊ ተቋም እንደ መሆንዋ መጠን ኅብረተሰቡ በኅብረት ሆኖ ድህነትን እንዲዋጋ ማስተማር፣ ማደራጀትና መምራት ትችላለች:: ድሆችን ሳይሆን ድህነትን መጥላት እንዳለብን ምእመናንን በጉባኤ ልታስተምር ትችላለች::

6.2. የሰላምና የእውነተኛ ፍቅር ቤት ናትና በኅብረተሰቡ ውስጥ ሰላምና ፍቅር እንዲስፋፋ፣ መደማመጥና መቻቻል እንዲኖር በልዩ ልዩ መንገድ ልትሠራ ትችላለች::

6.3. ቤተ ክርስቲያናችን በኅብረተሰባችን ውስጥ የሚፈጸሙ ግፍና በደሎችን በማንም ይፈጽሙ በዝምታ ልታልፍ አይገባም:: እውነት የመናገር ሰማያዊ ተልእኮዋን መወጣት ይኖርባታል:: ሀገርንና ሕዝብን የሚጎዱ ሁኔታዎች ሲከሰቱ ልክ እንደ ቀደምት ነቢያትና ሐዋርያት ድምጿን ልታሰማ፣ ልትመክርና ልትገልጽ ይገባታል:: እነዚህ ሁሉ ተግባሮቿ ኅብረተሰቡን ተስፋና አለኝታ እንዲኖረው ስለሚረዱት በማኅበራዊ ተግባሩ ውስጥ መንፈስ ንቁ ሆኖ እንዲሳተፍ፣ ነገ የተሻለ ቀን ሆኖ ይመጣል ብሎ እንዲያስብ ያደርጉታል:: ተስፋ ያለው ሕዝብ ደግሞ ኑሮውን ለማሻሻል ያለ ኃይሉን ይጠቀማል:: ይህ ደግሞ ከድህነት ለመውጣቱ ዋስትናው ይመስለኛል:: ቤተ ክርስቲያናችን የተስፋና የሰላም ምንጭት ሁን:: ይህም ዓይነተኛ ሚናዋ ነው::

6.4. ቤተ ክርስቲያናችን የድሃውን ኅብረተሰብ፣ የመሥራት ዐቅም ሊገነቡ የሚችሉ የልማት ተግባራትን ማደራጀት ትችላለች:: ሕፃናትን የመከባከብና አረጋውያንን የመርዳት ተግባሮችዋ የሚስፋፉ ሆነው ለሥራ አጥ ወጣቶች ሥራ የመ ፍጠርና ራሳቸውን የማስቻል ስልት ቀይሳ መንቀሳቀስ ትችላለች:: ለዚህ ደግሞ ብቁ ሊያደርጓት የሚችሉ ድርጅቶችን የፈጠረች በመሆኑ እነዚሁ ድርጅቶች ድህነት ተኮር የሆኑ ሥራዎችን እንዲያከናውኑ ልትረዳቸው ይገባል::

6.5. በሀገር አቀፍ፣ በአፍሪካና በዓለምም ደረጃ ቤተ ክርስቲያናችን የኢትዮጵያን ድሃ ሕዝብ ጉዳይ በመወከል ከዓለም አቀፋዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር አሁን ከምታደርገው በበለጠ መንቀሳቀስ ይኖርባታል::

ከውስጥም ቢሆን ቤተ ክርስቲያናችን ሀብትና ንብረቶችዋን በአግባቡ በመጠቀም በድህነት ውስጥ የሚኖሩ አገልጋዮችዋን ኑሮ ለማሻሻል፣ ስልት መንደፍ አለባት:: በሺ የሚቆጠሩ በተለይ በገጠሪቱ ያሉ የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋዮች ከነቤተሰቦቻቸው በረሃብና በችግር እየተጠበሱ የሚኖሩባት ቤተ ክርስቲያን መሆን የለባትም:: የቤተ ክርስቲያኒቱን አገልጋዮች ኑሮ ለማሻሻል የሚረዱ የልማት ዕቅዶች ወጡ ማለት እነርሱ ለሚያገለግሏቸውም ምእመናን ተስፋው ብቻ ሳይሆን ተግባሩም ተረፈ ማለት ይመስለኛል:: በዚህ ረገድ የተሻለ ትኩረት በመስጠት ከውስጥ ተንሠራፍቶ የሚገኘውን ድህነት ማቃለል ግብ ሆኖ መያዝ አለበት::

ከላይ በመጠኑ የቀረቡትን ለማጠቃለል ከቤተ ክርስቲያናችን የድህነት ቅነሳን ማስወገድ ተግባር ውስጥ ፊት ቀድማ የመምራትና የማስተባበር ሚና እንዳላት ትገንዘብ::

- ሰላምን÷ ፍቅርን÷ ተከባብሮና ተደማምጦ መሥራትን ታስተምር፤
- የልማት ፕሮግራሞችዋን ድህነት ተኮር በሆኑ ፕሮጀክቶች ላይ ታነጣጥራቸው::
- አገልጋዮችዋንና ኳዳዋን አትርሳ፤ ለእነርሱም ተስፋ ትሁናቸው::
- ምእመናን ሀብቶችዋ መሆናቸውን አትዘንጋ:: ድህነትን በማስወገድ ሂደት ውስጥ አስተባብራ ትጠቀምባቸው::
- ገንዘቧንና ንብረቶችዋን ያለ ብክነት በአግባቡ ትጠቀም:: ለሌሎችም አርአያ ትሁን::

እኔ እንደ አንድ ምእመን የሚሰማኝን ተናግሬያለሁ:: ንግግሬ ዕውቀት ሳይሆን ስሜት የተሞላበት ሆኖ ከሆነ እንደ ድፍረት እንዳትወስዱት እለምናለሁ:: በመጨረሻም ይህ ዕድል ስለ ተሰጠኝ ደግሜ አመሰግናለሁ::



© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# በአንዳንድ አህጉር እየተከሰተ ያለው የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ችግርና መንሥኤው

/ቀሲስ ስንታየሁ አባተ/

*ባለፈው እትማችን የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ምንነት፣አመሠራረት፣አስፈላጊነትና ሌሎች አጠቃላይ ጉዳዮችን «ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን» በሚል ዐቢይ ርእስ ሥር ማቅረባችን ይታወሳል:: በአሁኑ ዝግጅታችን በሀገር ውስጥና በባሕር ማዶ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን አስመልክቶ ለሚፈጠሩ ችግሮች መንሥኤ የኾኑ ነጥቦችንና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን አጽንቶ ለመጠበቅ ምን መደረግ እንዳለበት እንመለከታለን:: አንባብያን÷በጉዳዩ ላይ የምታደርሱን አስተያየቶች፣ጥያቄዎችና ተጓዳኝ መረጃዎች የመፍትሔው አንድ አካል በመሆናቸው በተሳትፏችሁ ግፉበት እንላለን::*

በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በተለያዩ ዓለማት በሥራ፣በትምህርት፣ በንግድ፣ በስደት ተበትነው ባሉ ልጆቿ አማካይነት አገልግሎቷን በስፋት በመስጠት ላይ ትገኛለች:: በዚህም ለኢትዮጵያውያን ልጆቿ ዘመድ ወገን በሌለበት ቦታ ተስፋ፣አምባ፣መጠጊያ፣ መጽናኛ ለመሆን በቅታለች:: ከዚህም አልፋ ማንነታቸውን ላጡ÷ ከእምነት ለተለዩ ሁሉ ተስፋ እየሆነች ነው:: ለዚህም በኬንያ፣በደቡብ አፍሪካ፣ በአሜሪካ በካሪቢያን ግዛቶች ለሚገኙ ሕዝቦች እያበረከተች ያለውን አገልግሎት ብቻ ማንሣቱ ይበቃል::

ይሁን እንጂ ይህ የቤተ ክርስቲያናችን የአገልግሎት አድማስ መስፋትና የተለያዩ አህጉር ዜጎች ትኩረት መስጠት ገና በሊጋነቱ ፈተና እየገጠመው ይገኛል:: በተለያዩ የአሜሪካ ግዛቶች በምትገኘው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ አንዳንድ ግለሰቦች ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አላስፈላጊ እንደ ሆነ በመናገር ምእመናንን ያውካሉ:: እንክርዳድ ትምህርታቸውን ምእመናን እንዲቀበሏቸው መነሻ ያደረጉት በአካባቢያቸው ያለውን «ችግር» ነው:: ቅዳሴው እንዲያጥር፣የተወሰኑ ቅዳሴያት ብቻ እንዲቀደሱ፣ምእመናን ጫማ አድርገው ቤተ ክርስቲያን እንዲገቡ፣ሥጋ ወደሙን ለመቀበል ዐሥራ ስምንት ሰዓት እንዳይጾሙ፣ቤተ ክርስቲያኒቱ የመዝሙር መሣሪያዎች እነዚህ መሆን አለባቸው ብላ በቅዱስ ሲኖዶስ ያጸደቀቻቸውን ትተው «ዘመናዊ» የሚሉትን እንዲቀበሉ፣ሴቶች በወር አበባ ላይ እያሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲገቡ... ምእመናንን በመገፋፋት ላይ ይገኛሉ:: የእነዚህ ችግሮች መንሥኤዎች ምን ይሆኑ? ቀጥለን ለመመልከት እንሞክራለን::

### 1. ኑፋቄ

ኑፋቄ ጥርጥርና ክህደት ነው:: አንዳንድ ሰዎች ከትምህርት ጉድለት፣ ከእምነት ማነስ፣ከሰይጣን ፈተና የተነሣ የእግዚአብሔርን ህልውና፣የቅዱሳንን ክብር፣ በቤተ ክርስቲያን የሚፈጸመው ሥርዓታዊ አገልግሎት ሰማያዊ ጸጋ የሚያሰጥ መሆኑን ይጠራጠራሉ:: ጥርጥራቸውም ሲያድግ አቋም ይሆንና በይፋ መቃወም ይጀምራሉ::

በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች በሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አጥቢያዎች ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን አስመልክተው እንግዳ ትምህርት ከሚያስተምሩት ሰዎች መካከል አብዛኛዎቹ የሃይማኖት ችግር ያለባቸው ናቸው:: እነዚህ ሰዎች በሀገር ውስጥ ሳሉ ያስተምሩት የነበረው የኑፋቄ ትምህርት በቤተ ክርስቲያናችን አባቶችም ሆነ በምእመናን ዘንድ ስለ ታወቀና ጥያቄ ስላስከተለባቸው በተለያዩ መንገዶች የወጡ ናቸው:: ቤተ ክርስቲያኒቱ ሳትልካቸው የተላኩ፣ሳትሾማቸው የተሾሙ፣ ጥንተ ማንነታቸውን የማያውቀውን ሕዝብ ግራ ያጋቡታል::

በመሠረቱ እነዚህ ሰዎች ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ነቅፈው በማስተማራቸው ልንገረም አይገባም:: ምክንያቱም የሥርዓትና የሕግ ሁሉ ባለቤትና ፈጻሚ የሆነውን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሳይቀር ከባሕርይ አባቱ ዝቅ አድርገው የሚያዩ ሰዎች ስለሆኑ ነው:: ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት አምነው ላልተቀበሉት ሁሉ ሸክም ይሆንባቸዋል:: ከሃይማኖት ባዶ በሆነ ልቡና የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን መከበር የሚሻ ሰው ቢኖር ከኩርንችት ወይን የመልቀም ዓይነት ይሆንበታል::

### 2. የሥልጣኔን ምንነት በትክክል ካለ መረዳት :-

ሥልጣኔ ከሰው ልጅ የአእምሮና የኑሮ ዕድገት ጋር የተያያዘ ነው:: እያንዳንዱ ትውልድ የራሱ የሆነ ሥልጣኔ አለው:: ባገኘው ሥልጣኔ የተሻለ ኑሮን ለመኖር የሚያስችለውን ጥበብ ተከትሎ ይሠራል:: ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የአእምሮና የኑሮ ዕድገት ውጤት ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ የሰው ልጆች በእምነት የጀመሩትን የሕይወት ጉዞ አግባብ ባለው መንገድ ይመሩ ዘንድ ልቡናቸውን ባቀኑ ቅዱሳን በኩል የሰጠው መመሪያ ነው:: ይሁንና ከሥልጣኔ መርቀቅ አንጻር ሳይሆን ከምእመናን አጠቃላይ ዐቅም አንጻር ዘመኑን የሚዋጅ ሥርዓት አይሠራም ማለት አይደለም:: ነገር ግን ሥርዓቱን በማስፈጸም ረገድ ሓላፊነት ያላቸው አካላት በምእመናን ዘንድ ሥርዓት እንዲሠራለት የሚፈለገውን ነገር ለሚመለከተው ለቅዱስ ሲኖዶስ በማቅረብ መፍትሔ እንዲያገኝ ማድረግ ይገባቸዋል:: ምናልባት ሥርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ ያሉበት ከባቢያዊ ሁኔታ ተጽዕኖ የፈጠረባቸው ሰዎች ካሉም እያስተማሩ ወደ ማወቅና ወደ መጽናት መምራት የሥልጣኔ ምልክት ነው::

በርግጥ የሥልጣኔ ትርጉምና አካሄድ ባልገባቸው ሰዎች ዘንድ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ማክበርና ማስከበር ፈጽሞ የማይቻል ነገር ነው መስሎ የሚታያቸው:: በቤተ ክርስቲያን ያለውን ሥርዓት መንፈስ ቅዱስ በአበው አድሮ እንዳሠራው በመዘንጋት ሥርዓቱ በተሠራበት ዘመን ከነበሩት ሰዎች አመለካከት ጋር ያቆራኙታል:: በመሆኑም ዋና ተልእኮአቸውና ትኩረታቸው የሠለጠነው ሕዝብ ምን ቢያደርግ ነው አበው በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ልሠሩት ሥርዓት ሊገዛ የሚችለው፤ የሚል ሳይሆን ሥርዓቱን እንዴት ብናደርግ ነው ለዘመናዊው ሰው የምናመቻቸው የሚል ነው:: በመሠረቱ ይህ ደግሞ ሃይማኖተኛ ከሆነ ሰው ልብ÷ ማለትም ለራሱ ሞቶ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ሕያው ከሆነ ልቡና የተገኘ አይደለም:: «በእምነት የሚደረገው ጉዞ በቀጠነው መንገድ ተጉዞ በጠበበው በር መግባት ነው» ከሚለው አምላካዊ ቃል ጋር የማይስማማ ነው:: «ይድላን÷ ይመቸን» በሚል ሁሉን ነገር ለእነርሱ በሚመች መንገድ ማስኬድ ስለ ሚፈልጉት ሰዎች ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ:- «ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንዲመጣ ይህን ዕወቅ፤ ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና... መልካም የሆነውን የማይወዱ...ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ:: የአምልኮ መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል:: ከእነዚህ ደግሞ ራቅ...::» ብሏል:: 2ጢሞ.3÷1-7::

### 3. አለማወቅ:-

ይህ በሁለት መንገድ ሊታይ ይችላል:: ምእመናን አስተማሪ ከማጣት፣ በሥራ፣በትምህርት፣በስደትና በመሳሰሉት ምክንያቶች የተነሣ ቤተ ክርስቲያን የምትፈጽመውን ሥርዓት የትመጣነት፣ ለምን እንደሚፈጸም፣የሚያስገኘውን በረከት፣ የአፈጻጸሙ ሂደት እንደምን እንደ ሆነ ሳያውቁ ይችላሉ:: በዚህም የተነሣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን በአግባቡ ላይ ፈጽሙት ከመቻላቸውም በላይ በቤተ ክርስቲያን በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ሥርዓት ሲጓደልና፣ሲፈርስ ሊጠይቁ ሊያርሙ አይችሉም::

በካህናትም በኩል ቢሆን ያለ ማወቅ ችግር ሊከሰት ይችላል:: አንድ



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ሰው መላውን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጠንቅቆ ያውቃል ማለት ይከብዳል:: የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ምን ነት÷ አስፈላጊነትና አፈጻጸም ካለማወቅ የተነሣ በአንደበታቸው ሊነቅፉ፣ በአገል ግሎታቸውም ወቅት ሊገድፉ የሚችሉ ካህናት ይኖራሉ:: ይህ ልማድ ሲቆይ ደግሞ የጸደቀና የተፈቀደ ሥርዓት ይመ ስላል:: በዚህ ወቅት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የልማዱን ከሕጉ በማፍለስ የኖላዊነት ተግባራቸውን ሊወጡ ይገ ባል::

ለአንዳንድ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን የሚደረገው ነገር እንግዳቸው ነው:: ከላይ ያለውን ነገር /ንባብ / ብቻ ስለሚመለከቱና ጥልቁንና የሬቀቀውን ሃይማኖታዊ ምሥጢር ለመረዳት ገና ዕውቀቱ ስለሌላቸው ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ይከብዳቸዋል፤ ይኸውም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ቅዱሳን ሐዋርያት ይሰብኩት የነበረው ነገረ ክርስቶስ ባልገባው ሰዓት የክርስቶስ ማደርያ÷ መገለጫ የሆኑትን ቅዱሳን ሐዋርያት እንዳሳደዳቸው ማለት ነው:: ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አለማወቁን በደማስቆ መግቢያ በር ላይ ካራቀለት በኋላ ግን ሁሉን ስለ ተረዳ፦ «ከእኛ እንደ ተቀበለው ወግ ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ አዝዛችኋለሁ» ለማለት በቃ:: አሁንም ቢሆን ባለማወቅ ወጥመድ የተያዙ ሰዎች ያመኑትን እምነት መግለጫ የሆነውን ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ከማጥላላት ይልቅ ሊያስረዷቸው ወደሚችሉ ወደ እውነተኞች የቤተ ክርስቲያን መምህራን ቀርበው መማር ይጠበቅባቸዋል::

## 4. ንዝህላልነትና ቸልተኝነት

በመንፈሳዊ ሕይወት ከሚያጋጥሙት ችግሮች መካከል ዋነኛው ንዝህላልነትና ቸልተኝነት ነው:: ንዝህላልና ቸልተኛ የሆኑ ሰዎች መሆን የሚገባው ሥርዓቱ የቱ፣ለምን፣መቼና የት መፈጸም እንዳለበት ያውቃሉ:: ይሁን እንጂ ከመሰልቸት፣ከመፍራት፣ከጥቅም ፈላጊነት...የተነሣ ዝንጉና ስልቹ ይሆናሉ:: ሊቀ ካህናት ዔሊ በአራቱ ድንኳን ያገለግሉ የነበሩ ልጆቹ የመብራቱን፣ የመሥዋዕቱን ሥርዓት ሲጥሱ እያየ በቸልተኝነት እንዳየ ከእግዚአብሔር ይልቅ ለልጆቹ እንዳደላ ይሆናሉ:: ንዝህላልነትና ቸልተኝነት የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት በሚፈጽሙና በሚያስፈጽሙ ሰዎች ዘንድ የሚታይ ችግር በመሆኑ ውጤቱ የከፋ ይሆናል:: ይህ ደግሞ ባለቤት ያቀለለውን አሞሌ ባለዕዳ አይቀበለውም እንደ ተባለው ዓይነት ሊሆን ይችላል::

በአሁኑ ጊዜ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ላይ እየተከሰተ ያለው ችግር በቅዱስ ሲኖዶስ አፋጣኝ መፍትሔ ካልተፈለገለት በስተቀር የቤተ ክርስቲያኒቷ አካልና ዋና ሀብት የሆኑ ምእመናንን ለከፋ ጉዳት ሊዳረግ ይችላል:: ሊከሰቱ ከሚችሉ ችግሮች መካከል የሚከተሉትን እንደ ምሳሌ መመልከት ይቻላል::

## ሀ. መለያየትንና ሁከትን ይፈጥራል::

በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰላማዊ አገልግሎት መስጠት÷ የተረጋጉና የሰከኑ ምእመናንን ማግኘት የሚቻለው የተሰበሰቡትን ሁሉ አንድ ሊያደርግ የሚችል እምነት÷ ትምህርትና ሥርዓት ሲኖር ነው:: አንዱ ሲዘምር ሌላኛው የሚያለቅስ፣አንዱ ቆሞ ሲያስቀድስ ሌላው የሚተኛ፣አንዷ እንደ ሥርዓቱ «ንጽሕናዋን» ጠብቃ ስትመጣ ሌላዋ ከዚህ በተቃራኒ የምትመጣ፣ አንዱ የልቡናውንና የእግሩን ጫማ አውልቆ እንደ ሥርዓቱ ሲገኝ ሌላው ምሥጢረ ሥጋዌ የሚነገርበትን ቤተ ክርስቲያን በጫማው የሚጠቀጥቀው ከሆነ መለያየትና ሁከት ይፈጠራል:: ይህ መለያየትም የሰዎች ብቻ ሳይሆን ቤተ ክርስቲያኒቷ እንደ ሮማ ካቶሊክ ከሦስትና ከአራት ቦታ እንድትከፋፈል ያደርጋታል:: የሰዎቹም ዋነኛ ዓላማ ይህ ነው::

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የቆሮንቶስን ምእመናን፦ «እግዚአብሔርስ የሰላም አምላክ ነው እንጂ የሁከት አምላክ አይደለም» ለማለት የበቃው ሥርዓተ አልበኝነት ጸንቶባቸው አንዱ በሌላ ቋንቋ ሲናገር ሌላው ትንቢት እናገራለሁ፤ ሌላው ደግሞ እዘምራለሁ፤ ሌላውም በሌላ ቋንቋ የተነገረውን እተረጉማለሁ በማለት ሲራበሹና አንዱ ሌላውን ያውክ ስለ ነበር ነው:: 1ቆሮ. 14÷33:: ሐዋርያው ይህን መሰል ሁከትና መለያየት የሚፈጠረው «የእግዚአብሔርን ማኅበር ከመናቅ» የተነሣ መሆኑን ገልጧል:: 1ቆሮ.11÷22:: በመሆኑም ይህን መሰሉን የድፍረት አካሄድና መለያየትን እንዲያስወግዱ፦ «ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን» በማለት መክሯቸዋል:: 1ቆሮ. 14÷40::

በአሁኑ ጊዜ በአንዳንድ የአሜሪካ ግዛቶች በምትገኘው ቤተ ክርስቲያን በማወቅም ይሁን ባለማወቅ መለያየትንና ሁከትን ሊፈጥሩ የሚችሉ የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ጥሰቶች እየተፈጸሙ መሆኑን ከሥፍራው የሚደርሱን መረጃዎች ያመለክታሉ:: ከእነዚህም መካከል ለእናት ቤተ ክርስቲያን ማለትም በማዕከል በመንበሩ ላለው ቅዱስ ሲኖዶስ የማይታዘዙ አጥቢያዎችን መመሥረትና በውስጣቸውም በርካታ የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አፈጻጸሞችን ማጉደል በአንድ ቀን በአንድ አካባቢ በተለያየ ሰዓት በመቀደስ ምእመናንን ለመለያየትና ለሁከት መዳረግ ይገኙበታል:: በመሠረቱ እናት አባትህን አክብር የሚለውን ቃለ እግዚአብሔር እያስተማሩና እየተማሩ የአንዲት የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን አባቶች በቅዱስ ሲኖዶስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ላወጡትና ለሚያወጡት ሥርዓት አልታዘዝም ማለት ለቤተ ክርስቲያን ጥብቅና ቆመናል፤ የሚል ምእመን ኾነ አገልጋይ ጠባይ አይደለም:: ሰዎች ተለያዩ ምክንያቶች ላይ ስማሙ ይችላሉ:: የሰዎች በራሳቸው ችግር መለያየት የአንዱ የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን ቋንቋ ለቋንቋ÷ ሥርዓት ለሥርዓት የሚለያይት ከሆነ ውጤቱ የከፋ ይሆናል::

ክቡሩን ሥርዓት ለሚገባው ምእመን እንደ ሥርዓቱ መፈጸም ግድ ነው:: ይሁን እንጂ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ቅድመ ጋብቻ ያልተገባ አኗኗር እንዲኖራቸው፣ ሥርዓተ ተክሊልን ለማይገባው ሰው መፈጸም ለጊዜው ግለሰቦችን ሊያስደስት ቢችልም ውስጡ ግን ለቤተ ክርስቲያኒቱ ሕግና ሥርዓት መጠበቅ በሚያስቡና በሌሎች መካከል መለያየትን ለመፍጠር አልያም በሥርዓት ተላላፊነታቸው ለሚጠየቁት ጥያቄ ድጋፍና አጀብ ለማብዛት ነው:: ያልተፈቀደልንንና የማይገባንን ነገር መፈጸም መብታችን አይደለም:: ዑሉደ ቆሬን፣ ናዳብና አብድዩን፣ንጉሡ ያዝያንንና ያዛን የማይገባቸውን በመፈጸማቸው ያገኛቸውን ነገር ከዚህ ላይ ማስታወስ ይገባል:: /ዘጸ. 28÷1፤1ኛሳሙ.2÷11፤22–25፤ 1ሳሙ. 6÷19፤2ዜና.26÷16–21/::

## ለ. ማንነትን ያሳጣል፦

እያንዳንዱ የእምነት ወገን ማንነቱን የሚገልጥበት የራሱ የሆነ ሥርዓት አለው:: አብያተ ክርስቲያናት ከእምነታቸው ባሻገር እምነታቸውን የሚገልጡበት፣ማንነታቸው የሚታወቅበት ሥርዓት አላቸው:: ለእኛ ለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስተያን ምእመናን የማንነታችን መገለጫ የሆኑ የቅዳሴ፣ የጾም፣ የመዝሙሩ፣የጋብቻ፣የክህነት፣የአለባበስ፣ የቅዱስ ቁርባን ሥርዓቶች አሉን:: በእነዚህ ሥርዓቶቻችን አምላካዊ በረከት ከማግኘታችን በተጨማሪ ማንነታችን ይገለጥበታል:: ቅዳሴዎቻችን፣የቅዳሴ ሰዓቶቻችን፣ መዝሙሮቻችንና የመዝሙር መሣሪያዎቻችን ከነሥርዓታቸው ኢትዮጵያዊነታችንን ብቻ ሳይሆን ቤተ ክርስቲያናችን በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረትነት ላይ የተመሠረተች መሆኗን ያሳያሉ:: ግብፃውያን፣ሮማውያን የራሳቸው መገለጫ የሆኑ የቅዳሴና የመዝሙር ሥርዓቶች እንዳላቸው ሁሉ በእኛ ቤተ ክርስቲያን ያሉ ቅዳሴያትና መዝሙራት መገለጫዎቻችን ናቸው:: «ቅዳሴው ረጅም ነው፤ ሰዓት ይፈጃል» ብሎ የማንነት መገለጫና መክበሪያ መንፈሳዊ ሀብቶቻችንን ከማጉደል ይልቅ ከቅዳሴ ውጭ ያሉትን ጊዜያት በአግባቡ መጠቀም መቻል የሥልጣኔ መሠረት ነው::

እነዚህ የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ዓይነተኛ ክፍሎች ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክቱ፦ «በኤፌሶን ላሉት ቅዱሳን» ብሎ አድራሻቸውን ገልጾ ሲያበቃ «በክርስቶስ ኢየሱስም ላሉት ምእመናን» እንዳለው /ኤፌ.1÷1/ በምድር የተለያየ ልማድና አመለካከት ባላቸው ሰዎች መካከል ብንኖርም በቅዳሴያችንና በመዝሙራችን ደግሞ በሰማያዊ አኗዋር ከመድኃኔዓለም ክርስቶስና ከቅዱሳን ጋር እንዳለን የምንረዳበት ነው:: ቅዳሴው፣መዝሙሩና ሌላው ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በመሠረቱ ሰማያዊ ነውና በዛ ተብሎ የሚቀነስ አይሆንም:: በኋላችን ያለውን እየተውን ወደፊት የምንዘረጋ፣ሀገራችንም የድል ነሺዎች ማኅበርተኞች ባሉበት ሰማያዊ ሥፍራ በመሆኑ፣ ይህም ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና ከእርሱ አብልጠን ከዚህ ዓለም የምንሻው ነገር የለንም:: /ፊልጵ.1÷23፤3÷20/::

ላቲን ለሮማ ካቶሊክ፣ኮፕት ለግብፅ ፣ሱርስት ለሶርያ አብያተ ክርስቲያናት የማንነት መገለጫ ቋንቋቸው



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

እንደ ሆነ ሁሉ ለእኛም የግእዝ ቋንቋ መገለጫችን ነው:: «ሕዝቡ የግእዝ ቋንቋን አያውቅም» በሚል ሰበብ ግእዝ ከሥርዓተ ቅዳሴው ይወገድ ማለት አንድ መገለጫን ከመጣልም በላይ በቋንቋው ከተጻፉት ሃይማኖታዊ ምሥጢራት /ትምህርት/ ሕዝቡን ቀስ በቀስ መለየት ነው:: ከዚህ ይልቅ የግእዝ ቋንቋ የሚረዳበትን ስልት መፈለግ ሥልጣኔ ነው:: በሰማርያ የነገሠው አካዝያስ ወደ አቃሮናውያን አምላክ ይገሠግሥ የነበሩትን መልእክተኞችን ተቆጥቶ ከመንገድ የመለሳቸው ኤልያስ መሆኑን ያወቀው የማንነቱ መገለጫ የሆነውን የኤልያስን አለባበስ ስለ ነገሩት ነው:: 2ነገ. 1÷1–8:: ጠቢቡ ሰሎሞንም አስቀድሞ:– «የቀድሞውን የድንበር ምልክት አታፍልስ» /ምሳ.22÷28/ ያለው አበው የእምነታቸው መገለጫና መታወቂያ የሆነውን ሥርዓተ እምነታቸውን መያዝ የሚገባ በመሆኑ ነው::

በአሁኑ ጊዜ የአብዛኞዎቹ የአፍሪካ አህጉር ባሕልና እምነት የአውሮፓውያን ጥገኛ ሆኖ የምናገኘው ፀቅኝ ገዥዎቻቸው ተንኰልና ማታለል የራሳቸውን በመጣላቸው ነው:: ይህ ደግሞ በመንፈሳዊውም ሆነ በሥጋዊው ሕይወት ላይ የሥነ ልቡና ተፅዕኖ÷ የራስን ንቆ የሌላውን መናፈቅ ያመጣል:: የአብዛኛዎቹ የአፍሪካ አህጉር በቋንቋቸው አለመማር፣በአለባበስ፣በትምህርት ሀገራዊውን ትቶ የሌላውን ሙጥኝ ማለት የቅኝ ገዥዎች ማንነትን የማሳጣት ሤራ ውጤት ነው::

እኒህና ዛሬ ልንገምታቸው የማንችላቸው ችግሮች ከመከሰታቸው በፊት እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አገ ልጋይ ቤተ ክርስቲያኒቱ የሠራቻቸውን ሥርዓቶች ዐውቆና አክብሮ ምእመናን እንዲያከብሯቸውና እንዲጠቀሙባቸው ተግቶ ማስተማር ይገባዋል::

## የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ሊሻሻል ይችላል ወይ? ከቻለስ በማን?

የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት የተሠራው የሰዎችን መንፈሳዊ ሕይወት በተሟላ ሁኔታ ጠብቆ በወንጌል ሥርዓት ምእመናንን ለመምራት ነው:: ሥርዓቱ ለምእመናን መንፈሳዊ ጥቅም ተብሎ እንደ ተሠራው ሁሉ በመንበሩ በሚገኘውና አግባብ የኾነ ሥልጣን ባለው ቅዱስ ሲኖዶስ ለምእመናን ጥቅም ተብሎ ሊሻሻል ይችላል:: ይህም ሲባል በአትኩሮት ልናስተውለው የሚገባን ቁም ነገር የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት የሚሻሻለው ስለ ምእመናን ድኅነት መሆኑን ነው::

ስለ ማንኛውም ምክንያት ቢሆን ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ሊያሻሽሉት የሚችሉት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በሲኖዶሳቸው መክረው ነው:: ይኸም በቅዱሳን ሐዋርያት ዘመን የተደረገ ነው:: በአንጾኪያ የነበሩ አሕዛብ በክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት አምነው ተጠመቁ:: ነገር ግን ከአይሁድ ወገን የነበሩ አንዳንድ ሰዎች የኦሪቱን ሥርዓት ካልፈጸማችሁ ብለው ተቃወሟቸው:: ቅዱሳን ሐዋርያት ይህንን ልዩነትና ክርክር ሰሙ:: ነገር ግን እያንዳንዳቸው በተናጠል ሆነው መልስ አልሰጧቸውም:: ይልቁንም በ50 ዓ.ም በቅዱስ ያዕቆብ ሰብሳቢነት በኢየሩሳሌም ተሰባስበው በጉዳዩ ላይ ከመከሩ በኋላ የሚበጀውን ሥርዓት ደንግገው ቅዱስ ጳውሎስንና ቅዱስ በርናባስን ወክለው በመ ላክ ልዩነቱ ጠፍቶ አንድነት የሚወርድበትን ሥርዓት ሠሩላቸው:: የሐዋ.ሥራ 15÷1-35:: ምክንያቱም ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ:– «እውነት እላችኋለሁ÷ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል» ብሏቸዋልና:: ማቴ.18÷18:: ዛሬም በሐዋርያት እግር የተተኩ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በቅዱስ ሲኖዶስ የወሰኑት÷ የደነገጉት÷ የጨመሩት ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ጽኑዕ ነው:: ጌታችን ራሱ ቅዱሳን ሐዋርያት ወንጌልን ሰብከው አሕዛብን አሳምነው እያጠመቁ ደቀ መዛሙርቱ እንዲያደርጉ ሲልካቸው:–«እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» ብሏቸ ዋል:: ማቴ.28÷20:: ይህም ሲባል ሐዋርያት በሕይወተ ሥጋ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የሚቆዩ ሆኖ ሳይሆን ለእነርሱ በሰጠው ሥልጣን መሠረት እስከ ኅልፈተ ዓለም ለሚ ነሡና በቅዱሳን ሐዋርያት ትምህርትና እምነት ጸንተው ሥልጣነ ሐዋርያትን ገንዘብ ካደረጉት ሁሉ ጋር የሚሠራ በመሆኑ ነው:: ለዚህ ነው ቅዱስ ጳውሎስ:– «ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነንና» ያለው:: 1ቆሮ.3÷9::

እያንዳንዱ ኤጲስ ቆጶስ ሥርዓትን አስመልክቶ በሀገረ ስብከቱ የተፈጠረውን ችግር ለቋሚ ሲኖዶስም ሆነ በዓመት ሁለት ጊዜ ለሚሰበሰበው ምልዓተ ጉባኤ ያቀርባል:: በፍትሐ ነገሥት:– «በቀኖናት ውስጥ በ35ኛው ትእዛዝ ከእኛ የቀረ አንዳች ነገር ቢኖር ኤጲስ ቆጶስ ያሳስብ» ማለታቸውም ይህንኑ ያስረዳል:: በ48ኛው ላይ ደግሞ «ወንድሞች ሆይ÷ ከእኛ የቀረ ምንም ቢኖር እግዚአብሔር ለተገባው ሰው ይገለጠው:: ቤተ ክርስቲያንም ጸጥታ ወዳለው ወደብ ትመራ...» ብለዋል:: ዳግመኛም ኤጲስ ቆጶሳት በዲዲስቅልያ በ4ኛው ክፍል:– «እናንተም እኮ ጌታችን በምድር ያሰራችሁት በሰማይ የታሰረ ይሁን... እንደ አምላክም በሥልጣን ፍረዱ ብሏችኋል» ይላል:: በዚህ ዐረፍተ ነገር ውስጥ «ያሳስብ» ያለውን አስተውሉ:: የሚያሳስበው ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በተገኙበት ጉባኤ አይደለ ለምን? ሊቃነ ጳጳሳቱ በጾም በጸሎት በመንፈስ ቅዱስ ታግዘው የሚወስኑት ሥርዓት ተቀባይነት ይኖረዋል:: እዚህ ላይ ማስተዋል የሚገባው ቤተ ክርስቲያን ያወገዘቻቸውና ፈራሳቸው ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን ያፈነገጡ ሰዎች የሚያወጡት መመሪያ ምእመናንን የሕይወት ባለቤት የማያደርግና ወደ እግዚአብሔር የማያቀርብ መሆኑን ነው::

## ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ለማስጠበቅ ምን ይደረግ?

ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን የመጠበቅ ሓላፊነቱ የሊቃውንቱም የምእመናንም ነው:: እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን በአንድነትና በሙሉ ልቡናው እንዲፈጽመው አስቀድሞ አንድ ወጥና ገገር የሆነ ሥርዓት ማዘጋጀት ከሊቃውንቱ ይጠበቃል:: በአሁኑ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን መንበር ያሉ ሊቃውንት «በአንድ ዓይነት ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ይመራሉ፤ ለሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አንድ ዓይነት ግንዛቤና ትኩረት አላቸው» ለማለት ፈጽሞ አይቻልም:: እንዲያውም በአንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች የሥርዓተ ቤተ ክርስቲ ያን መጣስ ይታያል:: በውስጥና በውጭ ያለውን የተለያየ አመለካከት አንድ ለማድረግ እንዲቻል በጎጥ፣ በወንዝ፣ በጉባኤ ቤት ያለውን ሐሳብ አሰባስቦ ሊቃውንቱን አወያይቶ የሥርዓቱን ምክንያት፣ የሚያስገኘውን ጥቅምና የሥርዓቱን አፈጻጸም፣ ሥርዓቱን በሚጥሱት ላይ ቤተ ክርስቲያን የምትወስደውን ርምጃ አጠቃሎ ማዘጋጀት ከአበው የሚጠበቅና ነገን ለመቅደም የሚያስችል ሥራ ነው::

ምእመናንም ሁለት ነገሮችን ማስተዋል ይጠበቅባቸዋል:: ቅዱስ ሲኖዶስ በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት የሚሠራቸውን ሥርዓቶች በአግባቡ መጠበቅ የመጀመርያው ነው:: በሌላ በኩልም በተለይ በሀገር ውጭ ባለችው ቤተ ክርስቲያን የሚገኙት ምእመናን ለአገል ግሎት የሚመጡ ሰዎችን ማንነት በቅ ድሚያ ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል:: ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት በአፍዓ የኾኑ፣ ከልቡናቸው አንቅተው የሚናገሩ፣ራሳቸ ውን ለገዛ ጥቅማቸውና ዓላማቸው በላኩ ሰዎች እንዳይታለሉ መጠንቀቅ ይገባቸዋል:: አንዲቷን ቤተ ክርስቲያን በብሔር፣ በፖለቲካ ድርጅት ስም ሊከፋፍሉ የሚሹ ሰዎች:– «እነ እገሌ የዚህ ወንዝ ተወላጆች፣ የዚህኛው ድርጅት ደጋፊዎች ናቸው» የሚሉት ድብቅ ዓላማቸውን ለማስፈጸም ነው:: ከቀደሙት ንጹሐን ሐዋርያት ያልተገኘና ዓላማቸው ያልሆነውን ትምህርት የሚዘሩ ሰዎች መቼውንም ወደ ሕይወታችን ግንድና መሠረት ሊያቀርቡን ስለማይችሉ የአንዲት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባልና ቤተሰብ የኾኑ ሁሉ ወደ ነፈሰበት ሳይነፍሱ እያንዳንዱን ነገር መመርመርና መጠንቀቅ ይገባቸዋል:: ለሁሉም የሥርዓት ባለቤት እግዚአብሔር ሥርዓተ እምነታችንን አጽንተን በቤቱ በፍቅሩ ለመኖር ያብቃን:: አሜን::



© ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰሜንና ደቡብ አሜሪካ
## *መቋቋም *መስፋፋት *ወቅታዊ ችግር

/ካለፈው የቀጠለ/

**ውድ አንባብያን፣ ባለፈው እትማችን በዚህ ርዕስ ዓለም አቀፋዊት ቤተ ክርስቲያናችን በሐዋርያዊ እግሯ ተጉዛ እንዴት በምዕራቡ ዓለም እንደ ተቋቋመችና እስከ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ዘመን ፍጻሜ እንዴት እንደ ተስፋፋች ተመልክተናል። በዚህ ዝግጅታችን ደግሞ ከ1983 ዓ.ም ወዲህ ያላትን እንቅስቃሴ በመዳሰስ የተቋቋሙትን አብያተ ክርስቲያናት በአጫጭሩ እናስተዋውቃለን።**

ባለፈው እትም እንደ ተመለከትነው የንጉሡ ነገሥቱ የአገዛዝ ዘመን በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ መንግሥት መተካቱ በሰሜን አሜሪካ የነበረውን የቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ በመጠኑ እንዲጠናከር አድርጐት ነበር። ምክንያቱም የነበረውን የቀይና ነጭ ሽብር እንቅስቃሴ በመፍራት ወደ ዚያው የተሰደዱ ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ብዙዎች ነበሩና። ከ1983 ዓ.ም ወዲህም ምንም እንኳን እንደ ቀድሞው ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን በብዛት በመሰደዳቸው ባይሆንም በአካባቢው ለቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ መጠናከር ምክንያት የሆኑ አንዳንድ ክስተቶች ተፈጥረው ነበር። እነዚህ ክስተቶች ምንም እንኳን በቀጣዩ እትም የምንዳስሳቸውን በርካታ ችግሮች ያስከተሉ ቢሆንም በአካባቢው የቤተ ክርስቲያናችን አገልግሎት እንዲስፋፋ መሠረት ሆነዋል።

ቅዱስ ሲኖዶስ በ1984 ዓ.ም አዲስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አህጉረ ስብከት ድልድል እስኪያደርግ ድረስ በውጭው ያለው የቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ በመላ "በምዕራቡ ክፍለ ዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሀገረ ስብከት" በሚል በአንድ የተጠቃለለ ነበር። ነገር ግን ቆይቶ በዓለም የተበተኑ ኢትዮጵያውያን ቁጥር እየበረከተ፥ እነርሱን ተከትሎም አብያተ ክርስቲያናት እየበዙ ሲሄዱ፥ በአንድ ሀገረ ስብከት ብቻ አገልግሎቱ ሊፈጸም ባለመቻሉ በ1984 ዓ.ም ሐምሌ ወር በተካሄደው የቅዱስ ሲኖዶስ ጠቅላላ ጉባኤ የውጭው ዓለም የቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ በአራት አህጉረ ስብከት ተከፋፍሎ እንዲመራ ተወሰነ። እነርሱም፦

ሀ. ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካና ካናዳ አንድ ሀገረ ስብከት ሆኖ መንበረ ጵጵስናው ኒውዮርክ እንዲሆን፣

ለ. የካሪቢያን ደሴቶችና ደቡብ አሜሪካ አንድ ሀገረ ስብከት ሆኖ፣ መንበረ ጵጵስናው ትሪኒዳድ እንዲሆን፣

ሐ. ምዕራብ አውሮፓ አንድ ሀገረ ስብከት ሆኖ፣ መንበረ ጵጵስና ሎንዶን እንዲሆን፣

መ. ምሥራቅ አፍሪካም እንደዚሁ አንድ ሀገረ ስብከት ሆኖ፣ መንበረ ጵጵስናው ካርቱም ሱዳን እንዲሆን።

በዚህ አዲስ የአህጉረ ስብከት ድልድል መሠረት ብፁዕ አቡነ ማትያስ በተባበሩት የአሜሪካ ሀገሮች /ዩ.ኤስ.ኤ/ እና በካናዳ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሆነው ተሾሙ። ምንም እንኳን ከአዲሱ የአህጉረ ስብከት ድልድል ጀምሮ የሊቀ ጳጳሱን ሹመት ያልተቀበሉ ሰዎች እስከ አሁን ድረስ በአህጉረ ስብከቱ ውስጥ ቢኖሩም ቤተ ክርስቲያናችን ችግሩን ሁሉ እየተቋቋመች ምእመናንን በማገልገል ላይ ትገኛለች።

ከዚህ ቀጥሎ ዝርዝራቸውን ለማግኘት የቻልነውን አብያተ ክርስቲያናት ስምና አድራሻ ከአጫጭር መግለጫዎች ጋር እናቀርባለን።

### 1. ዋሽንግተን መድኃኔ ዓለም

ይህ ቤተ ክርስቲያን በሰሜን አሜሪካ ረጅም ዕድሜ ያለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ነው። በ1971 ዓ.ም በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የተመሠረተው ይህ ቤተ ክርስቲያን በቨርጂኒያና ሜሪ ላንድ አካባቢ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መጽናኛና መሰባሰቢያ በመሆን ሰፊ አገልግሎት አበርክቷል። ቤተ ክርስቲያኑ በዚያ የሚወለዱ ሕፃናትን ከማጥመቁ፣ ተዘጋጅተው ለሚቀርቡ ትምህርቶች ምሥጢራትን ከማሳተፉ በተጨማሪ "የኢትዮጵያ ቀን" በሚል በየዓመቱ የደመራ በዓልን እያደረገ የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ባሕል ለመጀመሪያ ጊዜ በምዕራቡ ክፍለ ዓለም አስተዋውቋል። በማስተዋወቅም ላይ ይገኛል። ቤተ ክርስቲያኑ ከሌሎቹ ሁሉ ቀድሞ የተመሠረተ ቢሆንም የራሱ የሆነ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን የለውም። በዚህ የተነሣ የቤተ ክርስቲያኑ ንዋያተ ቅድሳት ሁሉ በአገልጋይ ካህናቱ ቤት ነው። ቤተ ክርስቲያኑ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካና ካናዳ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የሆኑት ብፁዕ አቡነ ማትያስ በመንበረ ጵጵስና ያሉበት ነው።

### 2.የአትላንታ ጆርጅያ ቅድስት ማርያም

ይህ ቤተ ክርስቲያን የተቋቋመውና ተባርኮ የተከፈተው መስከረም 3 ቀን 1979 ዓ.ም ሲሆን በዘመኑ በአትላንታ ጆርጂያ ብቸኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በመሆን በአካባቢው ለሚገኙት ኢትዮጵያውያን ምእመናን ሰፊ አገልግሎት አበርክቷል፤ አሁንም በማበርከት ላይ ይገኛል። ቤተ ክርስቲያኑ የራሱ የሆነ ሕንፃ የለውም።

### 3.የሲያትል ዋሽንግተን ቅዱስ ሚካኤል

የሲያትል ዋሽንግተን ቅዱስ ሚካኤል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚገኘው ኒውጀርሲ- ኒውዮርክ ሲሆን የራሱ የሆነ ሕንፃ ስለሌለው በኪራይ እየተገለገለና እያገለገለ ይገኛል። በአሁኑ ጊዜ የካህናቱና የምእመናኑ አንድነት እየጐለበተ በመሄዱ ዕድገቱና ሐዋርያዊ ይዞቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ ይገኛል።

### 4.የሳን ዲያጐ ካሊፎርኒያ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን

ይህ ቤተ ክርስቲያን በአካባቢው ምእመናን ኅብረት የተቋቋመው በኅዳር ወር 1978 ዓ.ም ነው። እንደ ሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት በካህናቱና በምእመናኑ ብርታት ጥሩ የሆነ ሐዋርያዊ እንቅስቃሴ ሲያሳይ ቆይቷል። አሁንም በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል።



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

### 5. የሳን ሆዜ ካሊፎርኒያ ደብረ ገነት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን

ከሳን ሆዜ አውራጃ ምእመናን በተጨማሪ በአካባቢው ያሉትን እንደ አክላንድና ሳን ፍራንሲስኮ በመሳሰሉት አውራጃዎች የሚገኙ ምእመናንን አጠቃሎና አስተባብሮ ያገለግል ዘንድ በ1985 ዓ.ም መጨረሻ አካባቢ የተመሠረተ ቤተ ክርስቲያን ነው:: እንደ ሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አንዳንድ ችግሮች ቢያጋጥሙትም ሁሉንም እየተቋቋመ መንፈሳዊ አገልግሎቱን ቀጥሏል:: ቤተ ክርስቲያኑ የራሱ የሆነ ሕንፃ የለውም::

### 6. የሚኒያፖሊስ ሚኒሶታ ደብረ ገነት መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን

ታኅሣሥ 13 ቀን 1984 ዓ.ም የተመሠረተው ይህ ቤተ ክርስቲያን ምንም እንኳን በተለያዩ ጊዜያት ፈተናዎች ቢያጋጥሙትም በካህናቱና በምእመናኑ ብርታት እየተቋቋመ እስከ አሁን አገልግሎቱን በማበርከት ላይ ይገኛል:: ይህ ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ወቅት "ሚኒያፖሊስ ቅድስት ማርያም" የሚል ስያሜን አግኝቷል::

### 7. የኮሎምበስ ኦሃዮ ደብረ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን

በ1987 ዓ.ም የተመሠረተው ይህ ቤተ ክርስቲያን ገና ሲቋቋም ጀምሮ በራሱ ቦታና ንብረት ላይ ነው የተመሠረተው:: ካህናቱና ምእመናኑ በርትተው በመንቀሳቀስ ሐዋርያዊ ግዴታቸውን እየተወጡ የሚገኙበት ይህ ቤተ ክርስቲያን የቦታው ስፋትና አመቺነት ወደፊት የአጥቢያው ምጣኔ ሀብት እንዲዳብር ትልቅ ካቴድራል የሚያሠራ እንደሚሆን ይነገራል::

### 8. የዴንቨር ኮሎራዶ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን

በመስከረም ወር 1984 ዓ.ም የተመሠረተው ይህ ቤተ ክርስቲያን በሌሎች አብያተ ክርስቲያናትና ምእመናን ላይ የደረሰው የመከፋፈልና የመካሰስ እንግልት ቢያጋጥመውም፤ ካህናቱና ምእመናኑ በሚያደርጉት ከፍተኛ የሆነ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ደስ በሚያሰኝ መንፈሳዊ አንድነትና የምጣኔ ሀብት ዕድገት ላይ ይገኛል:: በዚህም የተነሣ በኪራይ ይገለገሉበት የነበረውን ግሩም የሆነ ኦርቶዶክሳዊ ሥሪት /ዐቅድ/ ያለው ቤተ ክርስቲያን ገዝተው የካቲት 16 ቀን 1992 ዓ.ም በበዓለ ኪዳነ ምሕረት በርካታ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን በተሳተፉበት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ቀኖና መሠረት ከፍ ባለ ሥነ ሥርዓት ቅዳሴ ቤቱ ተከናውኖ ታቦተ ሕጉ መንበረ ክብሩን እንዲይዝ ተደርጓል:: ቤተ ክርስቲያኑ በተለያዩ ጊዜያት በድርቅ ለተጐዱ ኢትዮጵያውያን የገንዘብ ርዳታ ሲያደርግ ቆይቷል::

### 9. የአርሊንግተን ቨርጂኒያ አቡነ አረጋዊ ቤተ ክርስቲያን

በ1987 ዓ.ም የተመሠረተው ይህ ቤተ ክርስቲያን አጋጥሞ በነበረው ችግር ከአህጉረ ስብከቱ አስተዳደር ውጭ ቢቆይም በተደረገው የሰላም ስምምነት ከነሐሴ 17 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ትዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሀገረ ስብከት አስተዳደር ሥር በመሆን ሐዋርያዊ ተግባሩን በማካሄድ ላይ ይገኛል::

### 10. የኢንዲያና ፖሊስ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን

በ1991 ዓ.ም የተመሠረተው ይህ ቤተ ክርስቲያን ከአንዲት በጐ አድራጊ ኢትዮጵያዊት ሴት አንድ ሰፊ ቦታ ከነሕንፃው ተበርክቶለት አገልግሎቱን በማበርከት ላይ ይገኛል::

### 11. የሱ ፎልስ ሳውዝ ዳኮታ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን

ሰኔ 24 ቀን 1990 ዓ.ም የተመሠረተው ይህ ቤተ ክርስቲያን በዓመቱ ከሳውዝ ዳኮታ ስቴት ሕጋዊ ዕውቅና አግኝቶ አገልግሎቱን በማበርከት ላይ ይገኛል:: ቤተ ክርስቲያኑ የራሱ የሆነ ሕንፃ ስለሌለው በኪራይ ይገለገላል::

### 12. የቦስተን ማሳቹሴት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን

ይህ ቤተ ክርስቲያን ቀድሞ በቅዱስ ሚካኤል ስም ተቋቁሞ በአካባቢው ለሚገኙት ምእመናን መንፈሳዊ አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል:: ሕንፃው የኪራይ ነው::

### 13. የብሩክሊን ኒውዮርክ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን

ይህ ቤተ ክርስቲያን ከብዙ ዓመታት በፊት ራሱን «ሊቀ ጳጳስ ነኝ» ብሎ ይጠራ በነበረው የፖርቶሪኮ /Puerto Rico/ ተወላጅ በሆነው "አባ" ሚካኤል በተባለው ግለሰብ አማካይነት «ተመሥርቶ የነበረ» ሲሆን በአህጉረ ስብከቱ አስተዳደር እንደ ገና ተባርኮ በቤተ ክርስቲያናችን ሥር እንዲሆን ተደርጓል:: የአጥቢያው ምእመናን በብዛት በዚያው ተወልደው ያደጉ ጥቁር አሜሪካውያን /ምዕራባውያን/ ናቸው::

### 14. የቴኒክ ኒው ጀርሲ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን

ይህ ቤተ ክርስቲያን በ1987 ዓ.ም ሲመሠረት በጥምቀት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባላት ለሆኑት ምዕራባውያን ታስቦ የተሠራ ሲሆን ምንም እንኳን በርካታ የተደራረቡ ችግሮች ቢኖሩበትም እስከ አሁን ድረስ አገልግሎቱን በማበርከት ላይ ይገኛል::

### 15. የሎስ አንጀለስ ቅድስት ሥላሴ ወገብረ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን

ይህ ቤተ ክርስቲያን ከተቋቋመ ጀምሮ በአካባቢው የሚገኙ ምእመናንን በማገልገል ላይ ይገኛል:: ሕንፃው የኪራይ ነው::

### 16 የኒው ዮርክ ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን

ይህ ቤተ ክርስቲያን በአገልጋይ ካህናቱ ብርታት፣ በምእመናኑ ታዛዥነት በመልካም ሁናቴ አገልግሎቱን በመፈጸም ላይ ይገኛል::

### 17. የኦስተን ቴክሳስ ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን

በአካባቢው ምእመናን ጥንካሬ የተመሠረተው ይህ ቤተ ክርስቲያን የሚገለገለው በግዢ ባገኘው የራሱ በሆነ ሕንፃ ነው::

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና መሠረት በአህጉረ ስብከቱ ሥር ያሉት አብያተ ክርስቲያናት እነዚህ ናቸው:: በሚቀጥለው እትም ደግሞ ከላይ በተዘረዘሩት አብያተ ክርስቲያናት አማካይነት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የምትሰጠውን መጠነ ሰፊ አገልግሎት ሲገጥመው የቆየውንና እየገጠመው ያለውን ሳንካ ዘርዘር አድርገን እናቀርባለን::

*የአብያተ ክርስቲያናቱን ዝርዝር ከአጫጭር መግለጫዎች ጋር ያገኘነው ብፁዕ አቡነ ማትያስ በ20ኛው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ጉባኤ ላይ ተገኝተው ካቀረቡት የአህጉረ ስብከቱ ሪፖርትና በአሜሪካ ከሚኖሩ አንድ የማኅበራችን አባል ነው::*

*ይቆየን*

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን የንዋያተ ቅድሳት ማምረቻና ማከፋፈያ በአዲስ መልክ ተዋቅሮና ተደራጅቶ አገልግሎት መስጠት ጀመረ !!

**ስልክ 56-67-88**

**በኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን**



© ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

/ዲ.ደሳለኝ ቀለብ/

ባለፈው ክፍለ ትምርታችን ምክ ንያትን፣ ሁኔታን፣ቦታን የሚገልጹ፣ ውጤትን የሚያመለክቱ ተውሳከ ግሦችን በማቅረብ መልመጃ መስጠ ታችን ይታወሳል:: ለመልመጃዎቹ ምላሽ በመስጠት የተሳተፉ አንባቢያንን እያመሰገንን ስም ዝርዝራቸውንና ቀደም ሲል በተላለፉ ክፍለ ትምህር ቶች ላይ የተዘጋጁ ተጨማሪ ጥያቄ ዎችን እነሆ ብለናል:: የተለመደውን ተሳትፏችሁ እንጠብቃለን:: ለጥያ ቄዎች ምላሽ በመስጠት የተሳ ተፉ:- ሜሪ ደጉ /የተባበሩ ዐረብ ኤሚሬቶች/፣እንተ ማርያም /ቤሩት- ሊባኖስ/፣ጽጌ ለማ /ባሕር ዳር/፣ሰሎሞን በርሄ/ አዋሳ ብላቴ/፣መንግሥቱ ኃይሌ /ቡታጅራ/፣ እንተ ማርያም /ቤተ ሳይዳ ቅዱስ ገብርኤል/ ወ/ሮ ለምለም አብርሃም፣ሱራፌል ፈንታሁ፣ ተክለ ማርያም፣በላይነህ መብራቱ /አ.አ/።

## ጥያቄ

### ግብረ - ቤት /የቤት ሥራ/

ኀረየ - መረጠ

ኀርይ - ምረጥ

ኀርየ -መረጠ

ኅሪ - ምረጥ

ኅሪ /ኅረይ/፣

1. ሰላም ______ አኃውየ
   - አ. ለከሙ
   - በ.ለክን
   - ገ. ለኪ
   - ደ. ሎሙ
   - ሀ. ሎቱ
2. ሰላም ______ እንዘ ንሰግድ ንብለኪ:: እንዘ እየ ንብለኪ - እንልሻለን
   - አ. ለከ በ.ለኪ
   - ገ.ለክሙ
   - ደ.ሊተ ሀ. ሎቱ
   - ወ. ላቲ
3. አሌ ______ አ ሰብአ ሰዶም
   - አ.ሊተ በ.ለከ ገ.ለክሙ ደ. ሎሙ
   - ሀ.ሎቱ ወ. አልቦ መልስ
4. አነ ______ ሐርኩ ኀበ ደብረ ታቦር
   - አ. ለልየ
   - በ.ለሊከ
   - ገ. ለሊክሙ ደ.ለሊነ
5. ______ ሕይወት በቤተ ክርስቲያን
   - አ. ለነ በ.ሊተ ገ. ሎቱ
   - ደ. ለክሙ
   - ሀ.ኩሎሙ /ሁሉም
6. አ ማርያም ______ ድኅነ ኩሉ ዓለም ድኅነ -ዳነ
   - አ. ብከ
   - በ. ብክመ
   - ገ. ብነ
   - ደ. ብኪ
7. ወሉድ ______ ቤተ ክርስቲ ያን ሖሩ ኀበ ቤተ ትምህርት ዘሰንበት::
   - አ. ለ
   - በ.እለ
   - ገ.ዘደ.እንተ
   - ሀ.ሀ ወ ገ
8. እለ /እነ/ መኑ ውእቶሙ ___ሖሩ ኀበ መካነ ኢየሱስ ዘጎንደር
   - አ. እንተ
   - በ.ወ
   - ገ.ዘ
   - ደ.ለ
   - ሀ.አ ወ ገ
9. ደራርቱ ______ ኢትዮጵያ ሮ ጸት በመርሕበ ባርሴሎና
   - አ. ዘ
   - በ.እንተ
   - ገ.እለ
   - ደ.ወ
   - ሀ.አወበ
10. ዝንቱ መልበስ ውእቱ መልበስ ክረምት
    - አ. እለ
    - በ.ለ
    - ገ.ኀበ
    - ደ.እንተ
    - ሀ አልቦ መልስ

2. ወልጥ ኀበ ልሳነ ግእዝ

1. አባቴ ውዳሴ ማርያም አመጣልኝ:: አምጽአ /አመጣ/
2. የኔ ልጅ ቡሩክ ነው::
3. ይህች ልጅ የሰንበት ተማሪ ናት::
4. እኔና ወለተ ማርያም ወደ ግሸን ሄድን::
5. ከአምላክ የተገኘ አምላክ
6. እግዚአብሔር ኃያል ነው::
7. ይህ ቃል የግእዝ ቃል ነው
8. መድኃኔዓለም በጎልጎታ ተቀበረ::
9. እግዚአብሔር ሕይወቴን ይባርክልኝ:: /ይባርክ-ይባርክ/
10. ለአባቶቻችን አምላክ ምስጋና ይሁን::
11. መድኃኔ ዓለም ለእኛ ተሰቀለ::

ባለፉት እትሞች የቀረቡት ክፍለ ትምህርቶች ላይ በመመርኮዝ በመሳት ለሚከተሉት ቃላት ፍቻቸውን አስቀምጥ::

### የግስ ቃላት

1. ነበረ
2. አርመመ
3. ኖመ
4. ተፈሥሐ
5. ሰዓለ
6. ሖረ
7. በከየ
8. ተለወ
9. ኮነ
10. ፈተወ
11. አእመረ
12. ሰከበ
13. ገብረ
14. ከበበ
15. አተወ
16. ቦአ
17. ነቀወ
18. ገፍዐ
19. ኀልቀ
20. ፈትሐ
21. ከርመ
22. ወዐለ
23. ነጸረ
24. መሐረ
25. መሀረ
26. ደረሰ
27. ተከወሰ
28. አስሐወ
29. ተዋነየ

### ተስማሚ ቃላት

1. ከመ
2. እለ
3. ምስለ
4. ጥቀ
5. በእንተ
6. እም
7. ወ
8. ዝየ
9. ዘ
10. እለ
11. ዝንቱ
12. ዛቲ
13. ውእቱ

### ሌሎች ቃላት

1. ገብር
2. አመት
3. እድ
4. ላሕም
5. ትእይንት
6. ደወል
7. መርሶ
8. ረድእ
9. ቤተ ላሕ
10. መጥቅዕ
11. ተመሃሪ
12. መጽሔት
13. ጠያር
14. አሣዕን
15. ሣጹን
16. ክታብ

ከሚቀጥለው ዝግጅታችን ጀምሮ ደግሞ ስለ አያያዥ (Conjuction) እና እርባ ግስ (Tenses) የተመለከተ ክፍለ ትምህርቶችን ይዘን እንቀርባለን::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



© ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# መንገደኛው

## «ፎቶ ኮፒ» ሥርዓት ወይስ...

እኔ የምላችሁ÷አሁንስ «አዲስ አበባ» የሚለው ስም መቀየር አለበት:: መፈክር ነው÷ የመንገደኛው:: ለምን መሰላችሁ÷ በውስጧ የሚታየው «አዲስ አበባ» ሳይሆን የሚጠቅምም የሚጎዳም ሌላ አዳዲስ ነገር ነው:: ለካስ ሰላምታ አላቀረብኩም:: ወዳጆቼ ተቀማጮች÷ እንደምን ከርማችኋል? እኔ መንገደኛው አሁንም አለሁ÷ እንደ ተጓዝሁ:: አሁን በቅርቡ እንኳን ግሸን ደብረ ከርቤ ማርያም÷ ዝቋላ ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ፣ ቅድስት አርሴማ ደርሼ ነው የመጣሁት:: በቅርቡ ደግሞ እሄዳለሁ፤ ልቤ ሳይሆን እግሬ ወደ መራኝ:: አሁን ያቃተኝ "ወደ ራሴ መጓዝ" ነው::

ይህቺ "አዲስ አበባ" የተባለችው ከተማ የዕድገትም የልማትም÷ የውድቀትም የጥፋትም÷ የመሠልጠንም የመሰይጠ ንም÷ የመካድም የማመንም÷ የድብልቁም አዲስ መብቀያና መቀበያ ናት:: የመንገደኛው ልቤ ፍልስፍና ሳይሆን የከተማዋ የአራት ኪሎ፣ የመርካቶ.... የየዕለቱ ምሥጢር ነው:: "የአዲስ መብቀያ ናት" ስል አምጣ የምትወልደውን ሳይሆን ባልስከነ ልቡናዋ አብራ፣ ማየትን አጥቶ መኰረጅን ገንዘብ ባደረገ ዐይኖቿ "ፎቶ ኮፒ" የምታደርገውን ነው:: የፎቶ ኮፒ ዋጋ ረክሶ 0.20 ሳንቲም ገብቶ የለም ታድያ ኮፒ ብታደርግስ? ብቻ ኦሪጅናል ጠፍቶ ትምህርቱ፣ ኑሮው፣ ባሕሉ፣ ሥርዓቱ፣ ሃይማኖቱ፣ ትዳሩ.... "ፎቶ ኮፒ" እንዳይሆን መንገደኛው ልቤ መፍራት ከጀመረ ስንት ሰንበት አስቆጠረ መሰላችሁ?

አንድ አዲስ ነገር ልንገራችሁ:: ጽዋ ታውቁ የለ? የትኛው?'እንደማትሉኝ ነው:: በቅዱሳን÷ በጻድቃን÷ በሰማዕታት ስም ምእመናን ተሰባስበው የሚጠጡትን ማለቴ ነው:: አዲስ አበባ አዲስ «የጽዋ ሥርዓት»፣ አዲስ "የመዝሙር" ሥርዓት፣ አዲስ «የዐቲብ /የማማተብ/ ሥርዓት» .... አላት::

መንገደኛው የሚያውቀውን የጽዋ ሥርዓት ልንገራችሁ:: ጽዋው የአዳር ፕሮግራም አለው፤ ይታደራል:: ጸሎት፣ ትምህርት፣ መመካከር .... በአዳሩ ይካተታሉ:: ታድያ ወንዶችም ሴቶችም ናቸው በአዳሩ መርሐ ግብር የሚሳተፉት:: መንገደኛው ደንቆታል:: ታድለው!! ያር ጠፍቶላቸው ይሆናል ሳይፈተኑ እንደ መንጋ አንድ ላይ ታጉረው የሚያድሩት:: ግን እኮ እኒያ የኔታ:- "ሰው መለኮት አይደለም ልጄ ሆይ÷ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ከአንድ ቤት አትደር:: በገቢር ባትሰናከል በኅሊ ና መተዳደፍህ አይቀርምና:: ደግሞም ከፈተና መሸሽ እንጂ ራስን ለፈተና ማጋለጥ ዋጋ የማይገኝበት ሰማዕትነት ነው:: ልጄ ሆይ÷ እሳት በጭኑ ቋጥሮ የማይቃጠል ማን ነው?" ይሉኝ ነበር:: ስለ ጽዋዎቹ አልጨረስኩም:: ጠዋት ሁሉም ከ"ጸሎት ቤት" ወደ የሥራቸው ወይም ቤታቸው ይሄዳሉ:: ከሰዓት ወይስ ከቅዳሴ ውጭ ተመልሰው ይገናኛሉ:: ይበላል÷ ይጠጣል:: ከዚያም ጽዋው ይወጣል:: አዲሱ ነገር እዚህ ጋር ይከሰታል:: አይ መንገደኛው÷ ይህቺን አዲስ ሥርዓት በአዲስ አበባ ያያት ቀን፡ - "ለእግዚአብሔር ወይም ለቤተ ክርስቲያችን ምስክር መሆን" ብሎት ነበር:: ሁለት ሜትር ያህል ርዝመት ያለው:- "ሥዕለ ማርያም" /ቆማ እጆቿን የዘረጋችው ቅድስት ድንግል ማርያም ትሁን አትሁን መንገደኛው አልደረሰበትም/ ተያዘ:: በስንት መከራ "ተጋድሞ÷ ተዟዙሮ" ከቤት ወጣ:: ከበሮ ተያዘ:: "መዝሙር" ተጀመረ:: መዝጊያ የቤት በር የሚያክለው "ሥዕል" ተይዞ መዝሙር እየተዘመረ ጽዋው እስከሚገባበት ቤት ድረስ ከበሮ "እየተደለቀ" ተደረሰ:: አዲስ የጽዋ ሥርዓት!! ሰው ሁሉ በአግራሞት ያያቸዋል:: መንገደኛው ብቻ ነው በመመስጥ ዓይነት ጅልነት ሲመለከታቸው የነበረው:: ግን መንገደኛው ልቤ "መጀመሪያ ይህን ትርኢት ባየህ ጊዜ እምነትን ከመመስከር ነው ወይስ ከግብዝነት ነው ያየኸው?" ብሎኝ ነበር:: ይሁንና ሁለቱንም ላይሆን ይችላል:: አዲስ ነገር መፍጠር:: አይ ፍልስፍና!!

ሌላም አለ:: ጸሎቱ ነዋ!! አዲስ ጸሎት:: ምን ጸሎት ብቻ÷ አዲስ ቅዳሴም እንጂ:: መንገደኛው ባይማርም የተማሩት ጎረቤቱ ድሮ ይነግሩት ነበር:: ቤተ ክርስቲያን የጸሎቱን፣ የቅዳሴውን ሥርዓት.... ሰፍራ ቆጥራ አስረክባ ነበር:: አሁን ግን ሁሉም እየቅል ሆኗል:: በመጽሐፍ በተጻፈው ላይ መጨመር፣ መቀነስ÷ መለወጥ...አራቱን የሒሳብ መደቦች መለማመጃ ሆኗል::

አይ መንገደኛው ልቤ÷ "አንተ ሒሳብ አትማርና....አልኩ÷» ቀልዴን መሰላችሁ? መደበኛው ተዘንግቶ ጭማሪው ቤተ ክርስቲያንን ሊሞላት ነው:: «እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ÷ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል፣ በቅዱስ ሚካኤል፣ በቅዱስ ሩፋኤል ሰላምታ......:: ... ከጌታችን÷ ከመድኃኒታችን÷ ከአምላካችን÷ ከፈጣሪያችን..... ይቅርታንና ምሕ ረትን ለምኝልን÷ አማልጂን::» ይሄ ደግሞ አንድምታ ጸሎት መጸለይ ይባላል፤ በነ መንገደኛው መንደር:: እንዴት መሰላችሁ÷ እኛ የግእዝ መምሩ ናቸው:- መሐረ ማለት ይቅር አለ ማለት ነው ያሉኝ:: አባቶቻችንን:- ለይተን የምናውቃቸው ከሆነ ጸሎት ሲጸልዩ «መደመርና ማብዛትን ስለማያውቁ» አንዱኑ ቃል ይደጋግሙታል::

የአንድምታ ቅዳሴውንም ልንገራችሁ:: ብቻ ዲያቆናቱ የቅዳሴ ጠበል እንዳይከለክሉኝ አደራ በሉልኝ:: "ንነጽር፣ እናስተውል" እንደ ማለት ፤"የእግዚአብሔርን ጥበብ እናስተውል" ይላል ቀሳውስቱም፤ እንጂ "ደኅንነትን የምንለምንሽ ክብርን የተመላሽ ቅድስት ሆይ" የሚለውን "ድኅነተ ሥጋን ድኅነተ ነፍስን የምንለምንሽ...." እያሉ "ያስማምሩታል":: መጽሐፉስ ቢ ሆን ቢያንስ መጽሐፈ ቅዳሴው ወደ አምስት ዓይነት ደርሷል ይላሉ:: ሊቃውንቱ ዜማው፣ ዘሩ የማይገናኝ:: አንድ ምሳሌ ላቅረብላችሁ:- "በአማን ደምከ ክቡር»፤ የሚለውን "በምሳሌ ደምከ ዝንቱ" ተብሎ የተዘጋጀ የቅዳሴ መጽሐፍ አለ:: "ፎቶ ኮፒ" መሆኑ ነው:: መናፍቃኑ ሥጋ ወደሙን «አማናዊ /እውነተኛ/ ሳይሆን መታሰቢያ ምሳሌ ነው» ብለውት የለ:: ይኼም "በምሳሌ ደምከ..." ቢል ማን ሊከለክለው?

ድሮ ድሮ የትርጓሜ ትምህርት የሚሰጠው በወንበር÷ በጉባኤ ነበር:: አሁን አሁን ቅዳሴው በትርጓሜ መሆኑ ሊቅ ነት ወይስ ድንቁርና? የመንገደኛው ጥያቄ ነው:: ቤት ሲያረጅ÷ ሊፈርስ ሲዘምም በሌላ ምሰሶ ደግፈው ያቀኑታል:: ያረጀውን ምሰሶ ያፈርሱታል:: ይነቅሉብታል:: ነገ ትርጓሜው በዝቶ ንባቡን እንዳያጠፋው! ወደ አዲስ አበባና ሰዎቿ:: ፈሪሳውያን እግዚ አብሔር በሙሴ በኩል በሰጣቸው ደገኛው ሕግ ላይ ሲጨምሩ፣ ሲተረጉሙ በስተመጨረሻ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ረስተው በጭማሪው ብቻ ቀሩ:: የአዲሳባዎቹ "የመደመርና የመጨመር ተማሪዎችስ" መጨረሻቸው ምን ይሆን?

ለመንገደኛው÷ ሃይማኖተኝነት መጨመር ሳይሆን ባለው ጸንቶ መመራት መቻል ነው:: የመዝሙሩ፣ የዜማው፣ የግጥሙና የአሸባሸቡ ሥርዓት ያለ አገባብ «አድጎ÷ አድጎ» የመናፍቃን "ፎቶ ኮፒ" ለመሆን እንደ ደረሰው ሁሉ ጸሎቱም ቅዳሴውም ጉ!! ጀምሯል:: ማን ይመልሰው ይሆን? እኔ እንጃ! በቃ ከዐሥር ከሃያ ዓመት በኋላ በ"ነበር" ቅርስነት እንመላ ይሆን? መንገደኛው ሄደ:: እንጃ መመለሻውን?!!

© ማኅበረ ቅዱሳን 

# የትንቢተ ኢሳይያስ አንድምታ

**ከቀድሞ አባቶች ሲወርድ ሲወራረድ የመጣው ንባቡና ትርጓሜው በአንድምታ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡**

*አዘጋጅ፡-* ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ
*አስፋፋይ፡-* በኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን

መጽሐፉን በሁሉም የሐመር መጽሔትና ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ማከፋፈያዎች ውስጥ ያገኙታል !!
ስልክ ቁ.፡- 13-81-30/22-86-01/23-45-29

## ለሁለተኛ ዙር

## የአብነት እና የዜማ መሣሪያዎች ትምህርት ለመማር የሚሹ ከሆነ ባሉን ጥቂት ቦታዎች ቀድመው ይመዝገቡ፡፡

**የሚሰጡት የትምህርት ዓይነቶች፡-**

1ኛ/ የግእዝ ቋንቋ 2ኛ/ ንባብ (ቆጠራ) 3ኛ/ ዜማ 4ኛ/ ቅኔ
5ኛ/ በገና 6ኛ/ መሰንቆ 7ኛ/ ዋሽንት

☞ **ትምህርቱ የሚሰጥበት አድራሻ፡-**

ከደብረ ጽጌ ቅዱስ ዑራኤል ቤተ ክርስቲያን ወረድ ብሎ አዲስ አበባ ጤና ቢሮ አጠገብ የአቡነ ጎርጎርዮስ ትምህርት ማዕከል

**ስልክ ቁ.፡- 51-06-59/(09)65-95-84**

**የመረጡትን ይማሩ ዘንድ አሁኑኑ ይመዝገቡ !!**

በኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን




## አዲስ የኦሮምኛ መጽሐፍ
## ፍኖተ አሚን /የእምነት መንገድ/

በሚል ርእስ በኦሮምኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶ ለቋንቋው ተናጋሪዎችና አንባብያን ቀርቧል፡፡

ቁጥር ፩ በሥርጭት ላይ ውሏል፡፡ መጽሐፉ በውስጡ፡- ስለ ጾም ሰፋ ያለ ዝርዝር ማብራሪያ ይዟል፡

ልሳንን አስመልክቶ ፡-
ልሳን ምንድን ነው?
- የልሳን አስፈላጊነት
- ልሳንና መናፍቃን ሌሎችንም

ስለ ታቦት
- የታቦት ትርጉም፣ የታቦት ኃይል፣ የታቦት ክብር፣ በታቦት ላይ ለሚነሡ ጥያቄዎች የተሰጠ መልስና ሌሎችንም ነጥቦች አካትቷል፡፡ የመጽሐፉ ይዘትና መጠኑ አንድ ሰው ለብዙዎች በስጦታነት ሊያቀርበው በሚችለው መልኩ የተዘጋጀ ነው፡፡ ቁጥር ሁለትን ደግሞ በቅርብ ቀን ይጠብቁ፡፡

አሳታሚና አከፋፋይ፡- ማኅበረ ቅዱሳን

ዋጋ - 6.00

## DAANDII AMANTII
## ፍኖተ አሚን

Mata duree jedhun Kitaabni haaraan qophaa'ee gabaarra oleera. Kitaabni kun of keessatti kan qabate:-

- Waa'ee Soomaa, Taabotaa fi Lissaana; akkasumas Gaaffilee shakkitoonni kaasaniifis deebin kennameera. Bitaatii dubbisaa.
- Rabsaa fi Maxxansiisaan - Waldaa Qulqullootaa
- Gatiin - 6

ሁሉንም ኅትመቶች በሐመር መጽሔት እና በስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ማከፋፈያዎች ውስጥ ያገኟቸዋል!!
ሰልክ ኢ.ኢ. 22 86 01/ 23 45 29/ 13 81 30

ሜጋ ማተሚያ ድርጅት

ዋጋ ብር 3.50

© ማኅበረ ቅዱሳን

© ማኅበረ ቅዱሳን
ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፤ እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው።